ከበጎች ጕረኖ ውስጥ ወሰደው፤
71ለሕዝቡ ለያዕቆብ፣
ለርስቱም ለእስራኤል እረኛ ይሆን ዘንድ፣
የሚያጠቡ በጎችን ከመከተል አመጣው::
72እርሱም በቅን ልቡ ጠበቃቸው፤
ብልኀት በተሞላ እጁም መራቸው::

## መዝሙር 79

### ብሔራዊ ሰቆቃ

የአሳፍ መዝሙር

1አምላክ ሆይ፤ ሕዝቦች ርስትህን ወረሩ፤
የተቀደሰውን ቤተ መቅደስህን አረከሱ፤
ኢየሩሳሌምንም አፈራርሰው ባዷት::
2የባሪያዎችህን ሬሳ ለሰማይ ወፎች፣
የቅዱሳንህንም ሥጋ ለምድር አራዊት፣
ምግብ አድርገው ሰጡ::
3ደማቸውንም በኢየሩሳሌም ዙሪያ፣
እንደ ውሃ አፈሰሱ፤
የሚቀብራቸውም አልተገኘም::
4እኛም ለጎረቤቶቻችን መዘባበቻ፣
በዙሪያችንም ላሉት መሣቂያ መሣለቂያ
ሆንን::
5እግዚአብሔር ሆይ፤ ይህ እስከ መቼ ነው?
የምትቈጣውስ ለዘላለም ነውን?
ቅናትህስ እንደ እሳት ሲነድ ይኖራልን?
6በማያውቁህ ሕዝቦች ላይ፣
ስምህን በማይጠሩ፣
መንግሥታት ላይ፣
መዓትህን አፍስስ፤
7ያዕቆብን በልተውታልና፤
መኖሪያ ቦታውንም ባድማ አድርገዋል::
8የአባቶቻችንን ኀጢአት በእኛ ላይ
አትቍጠርብን፤
ምሕረትህ ፈጥና ወደ እኛ ትምጣ፤
በጭንቅ ላይ እንገኛለንና::
9አዳኛችን የሆንህ አምላክ ሆይ፤
ስለ ስምህ ክብር ብለህ እርዳን፤
ስለ ስምህ ስትል፣
ታደገን፤ ኀጢአታችንንም ይቅር በል::
10ሕዝቦች፣ "አምላካቸው የት አለ?"
ለምን ይበሉ?
የፈሰሰውን የአገልጋዮችህን ደም በቀል፣
ዐይናችን እያየ ሕዝቦች ይወቁት::

78፥71 ዘፍ37፥2፤ መዝ28፥9
78፥72 ዘፍ17፥1
79፥1 ዘፀ34፥9፤ዘሌ 20፥3፤2ነገ25፥9፤ነህ 4፥2፤ኢሳ6፥11
79፥2 ዘዳ28፥26፤ኤር 7፥33፤ራእ19፥17-18
79፥3 ኤር16፥4፤ 25፥33፤ራእ11፥9
79፥4 መዝ39፥8፤ 44፥13፤80፥6፤ሕዝ 5፥14
79፥5 ዘዳ29፥20፤ መዝ74፥1:10፤85፥5፤ 89፥46፤ሶፎ3፥8
79፥6 መዝ2፥5፤ 14፥4፤69፥24፤110፥5 ፤147፥20፤ኤር10፥25 ፤ራእ16፥1
79፥7 ኢሳ9፥12፤ ኤር10፥25
79፥8 ዘፍ9፥25፤ መዝ116፥6፤142፥6፤ ኤር44፥21
79፥9 2ዜና14፥11፤ መዝ25፥11፤31፥3፤ ኤር14፥7
79፥10 ቍ3፤መዝ 42፥3፤94፥1፤ራእ6፥10

አብሔር መንግሥት አስተዳደር አባል መሆኑን የሚያመለክት ማዕረግ ነው (የዘፀ14፥31፤ የመዝ18 ርእስ፤ የኢሳ41፥8-9፤ 42፥1 ማብ ይመ)::

78፥71 *እረኛ፤* የ23፥1 ማብ ይመ::

*78፥72፤* እስራኤል ከዳዊት ቤት በሚወጣ እረኛ እንደም ትመራና ይህንንም የእግዚአብሔር ሕዝቦች በተስፋ የሚጠባበቁት ነገር መሆኑን ነቢያት መስክረዋል (ሕዝ34፥23፤ 37፥24፤ ሚክ 5፥4 ይመ)፤ ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት ተፈጽሞአል (ማቴ2፥6፤ ዮሐ10፥11፤ ራእ7፥17 ይመ)::

*መዝ79፤* እግዚአብሔር በደሏን ይቅር እንዲላትና እንዲረዳት፣ እንዲሁም ያለ ርኅራኄ ያሳደዷትንና መከራም ያደረሱባትን እንዲበቀልላት እስራኤል ያቀረበችው ጸሎት ነው:: ይህ መዝሙር ከመዝሙር 74 መሪ ሐሳብ ጋር ተቀራራቢ ይዘት ያለው ሲሆን እንደ መዝ74 ሁሉ ይህም መዝሙር በምርኮ ዘመን የተጻፈ ነው:: በመዝሙሩ ውስጥ የተጠቀሱት አሳዛኝ ገጽታዎች፣ በእረኛና በበግ መካከል ያለውን ግንኙነት ከሚያሳዩት ሁለት መዝሙሮች ማለትም ከመዝ77 (በሙሴ አማካይነት የታየውን የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ ከሚያስታውሰው) እና ከመዝ78 (በዳዊት አማካይነት የታየውን የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ ከሚያስታውሰው) ጋር ጐን ለጐን ሊታይ የሚችል ነው፣ እግዚአብሔር ሌሎች ሕዝቦችን በመጠቀም እስራኤልን የቀጣት በኀጢአቷ ምክንያት እንደ ሆነ ተረድታለች፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ይቅር እንዲላት፣ ወደ እግዚአብሔር ጮኸች:: ግን ደግሞ በዙሪያዋ ያሉ ሕዝቦች ይህን ሁሉ መዓት ያደረሱባት ለእግዚአብሔርና ለሕዝቡ ካላቸው ጥላቻ የተነሣ እንደ ሆነ ተገንዝባለች፤ ይህም እግዚአብሔር እንዲህ ባሉ ሕዝቦች ላይ ቍጣውን እንዲያወርድባቸው መጠየቋ ትክክል መሆኑን ያሳያል (ኢሳ10፥5-11፤ 47፥6-7 ይመ)፤ የዳንኤል ጸሎት (ዳን9፥4-19) በዚህ መዝሙር ውስጥ ካለው ልመና ጋር ተመሳሳይ ይዘት አለው::

79ርእስ፤ *አሳፍ፤* የመዝ73 የርእስ ማብ ይመ::

*79፥1-4፤* የምድር ሕዝቦች በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ የፈጸሙትን ግፍ የሚገልጽ ክፍል ነው፤ እነዚህ ሕዝቦች የእግዚአብሔርን ልዩ ርስት ወረሩ፤ ቤተ መቅደሱን አረከሱ፤ ከተማውን የፍርስራሽ ክምር አደረጉ፤ ሕዝቡን በሰይፍ ዐርደው ሬሳቸውን መቀበሪያ አሳጡ (የ53፥5 ማብ ይመ)፤ ለዓለምም ሰዎች መዘባበቻና መሣለቂያ አደረጉ::

79፥1 *ርስትህን፤* ከ78፥62:71 ጋር ያነጻጽሩ:: በዚህ ቦታ ቃሉ የሚያመለክተው የእስራኤል መኖሪያ የእግዚአብሔር ርስት እንደ ሆነ ነው (የ2፥8 ማብ ይመ):: *የተቀደሰውን ቤተ መቅደስህን፤* የ78፥69 ማብ ይመ::

79፥2 *የባሪያዎችህን፤* ከምድራቸው ተነቅለው በባዕድ አገር እንዲኖሩ የተደረገው በኀጢአታቸው ምክንያት ቢሆንም፣ በምርኮ አገር ያሉት ሕዝቦች ግን ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ልዩ ኪዳን እያስታወሱ ይጸልያሉ (በዚህ ጥቅስ ላይ፣ "ቅዱሳንህ" የሚለውንና በቍ13 ላይ፣ "የመሰማሪያ በጎችህ የሆንን እኛ ሕዝቦችህ" የሚለውን ይመ):: *ቅዱሳን፤* የ4፥3 ማብ ይመ::

79፥3 *ደማቸውን በኢየሩሳሌም ዙሪያ ... አፈሰሱ፤* ከ2ነገ 21፥16 ጋር ያነጻጽሩ::

*79፥5-8፤* እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ምሕረቱን፣ እርሱን በማያውቁ ሕዝቦች ላይ ግን ቍጣውን እንዲያዘንብ የቀረበ ጸሎት ነው::

79፥5 *እስከ መቼ?* የ6፥3 ማብ ይመ (በመግቢያው ላይ "ትምህርተ መለኮት" የሚለውን ይመ):: *የምትቈጣውስ፤* በቍጥር 6 ላይ፣ "መዓት" የሚለውን ቃል እንዲሁም የ2፥5 ማብ ይመ:: *ቅናት፤* የ78፥58 ማብ ይመ:: *እንደ እሳት ሲነድ፤* ዘዳ4፥24፤ 6፥15፤ ሶፎ1፥18፤ 3፥8 ይመ::

*79፥6-7፤* ኤር10፥25 እና ማብ ይመ:: በዚህ ቦታ ምናልባት መዝሙረኛው ከኤርምያስ ላይ ሳይጠቅስ አይቀርም::

79፥6 *መዓትህን አፍስስ፤* የሕዝብህን ደም፣ "እንዳፈሰሱ" ሁሉ አንተም በእነርሱ ላይ ቍጣህን አፍስስባቸው (ቍ3) ለማለት ነው:: በምርኮ አገር ያሉ የእግዚአብሔር ሕዝቦች እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን እንዲበቀልላቸው ይማጠናሉ (የ5፥10 ማብ ይመ)::

79፥7 *በልተውታል፤* ልክ እንደ አውሬ ማለት ነው (44፥11፤ 74፥19 እና የ7፥2 ማብ ይመ):: *ያዕቆብ፤* እስራኤል ከሚለው ስም ጋር ተመሳሳይ ነው (ዘፍ32፥28 ይመ)::

79፥8 *የአባቶቻችንን ኀጢአት፤* እስራኤል በምርኮ አገር እንድትማቅቅና አበሳዋን እንድታይ የተደረገው፣ ሲጠራቀም በቆየው የሕዝቡ ኀጢአት ምክንያት ነው (2ነገ17፥7-23፤ 23፥26-27፤ 24፥3-4፤ ዳን9፥4-14 ይመ)፤ እግዚአብሔር ቍጣውን እስካዘነበባት ዕለት ድረስም ከኀጢአቷ አልተመለሰችም፤ ንስሓም አልገባችም:: በዚህ ቦታ እንደሚነበበው ግን፣ በምርኮ አገር ያሉት ሕዝቦች እግዚአብሔር በአባቶቻቸው በደል እነርሱን ተጠያቂ እንዳያደርጋቸውና የአባቶቻቸውንም ኀጢአት እየቈጠረ የቍጣውን ዘመን እንዳያስረዝምባቸው ይልቁንም አሁን በንስሓ ወደ እርሱ ተመልሰዋልና ጸሎታቸውን እንዲሰማ ልመና ያቀርባሉ:: *ምሕረት፤* በዚህ ቦታ ሰላምን በሚያመጣ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ሆኖ ተመስሎአል (የ23፥6፤ 43፥3 ማብ ይመ)::

*79፥9-11፤* እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዲረዳ፣ በደሉንም ይቅር እንዲልና የሕዝቡን ጠላት እንዲበቀል የቀረበ ጸሎት ነው::

79፥9 *ስለ ስምህ ክብር፤* የእግዚአብሔር ሕዝብ ባዶ መቅረት በእግዚአብሔር ላይ ነቀፌታን እንደሚያስከትል ሁሉ (ቍ10 ይመ)፣ የሕዝቡን ድነትን ማግኘትና መበልጸግ እግዚአብሔርን ያስከብራል (የ23፥3 ማብ ይመ):: *ይቅር በል፤* የ65፥3 ማብ ይመ::

79፥10 *አምላካቸው የት አለ?* የ3፥2 ማብ ይመ:: *በቀል፤* የክፉ ሥራቸውን ዋጋ የምትከፍል ለማለት ነው (ዘዳ 32፥35:43 ይመ)::

11 የእስረኞች ሰቈቃ በፊትህ ይድረስ፤
በክንድህም ብርታት፣
ሞት የተፈረደባቸውን አድን።

12 ጌታ ሆይ፤ ጎረቤቶቻችን በአንተ ላይ
የተዘባበቱትን መዘባበት፣
ሰባት ዕጥፍ አድርገህ አስታቅፋቸው።
13 እኛ ሕዝብህ፣ የማሰማሪያህ በጎችህ፣
ለዘላለም ምስጋና እናቀርብልሃለን፤
ከትውልድ እስከ ትውልድም፣
ውለታህን እንናገራለን።

## መዝሙር 80

### ለእስራኤል ተሐድሶ የቀረበ ጸሎት

ለመዘምራን አለቃ፤ "የኪዳን ጽጌረዳ" በሚለው ቅኝት የሚዜም፤ የአሳፍ መዝሙር

1 ዮሴፍን እንደ በግ መንጋ የምትመራ፣
የእስራኤል እረኛ ሆይ፤ ስማን፤
በኪሩቤል ላይ በዙፋን የምትቀመጥ
ሆይ፤
በብርሃንህ ተገለጥ፤
2 በኤፍሬም፣ በብንያምና በምናሴ ፊት

79፥12 ዘፍ4፥15፤ ኢሳ65፥6፤ኤር32፥18
79፥13 መዝ44፥8፤ 74፥1
80፥1 ዘፀ25፥22፤ መዝ77፥20
80፥2 ዘኍ2፥18-24 ፤መዝ35፥23፤54፥1፤ 69፥1፤71፥2፤109፥26 ፤116፥4፤119፥94
80፥3 ቍ7:19፤ዘኍ 6፥25፤መዝ71፥20፤85 ፥4፤ኤር31፥18፤ሰቆ 5፥21
80፥4 ዘዳ29፥20፤ መዝ74፥10
80፥5 ኢዮ3፥24፤ ኢሳ30፥20
80፥6 መዝ79፥4
80፥7 ቍ3
80፥8 ዘፀ15፥17፤ 23፥28-30፤ኢሱ13፥6 ፤ኢሳ5፥1-2፤ኤር2፥21 ፤ማቴ21፥33-41፤ ሐሥ7፥45

ደምቀህ ታይ።
ኀይልህን አንቀሳቅስ፤
መጥተህም አድነን።

3 አምላክ ሆይ፤ መልሰን፤
እንድንም ዘንድ፣
ፊትህን አብራልን።

4 የሰራዊት አምላክ *እግዚአብሔር* ሆይ፤
በሕዝብህ ጸሎት ላይ ቍጣህ የሚነደው፣
እስከ መቼ ድረስ ነው?
5 የእንባ እንጀራ አበላሃቸው፤
ስፍር የሞላ እንባም አጠጣሃቸው።
6 ለጎረቤቶቻችን የጠብ ምክንያት
አደረግኸን፤
ጠላቶቻችንም ተሣሣቁብን።

7 የሰራዊት አምላክ ሆይ፤ መልሰን፤
እንድንም ዘንድ፣
ፊትህን አብራልን።

8 ከግብፅ የወይን ግንድ አመጣህ፤
አሕዛብን አባርረህ እርሷን ተከልሃት።

79፥11 *የእስረኞች ... ሞት የተፈረደባቸውን፤* በምርኮ ላይ በባቢሎን ያሉ እስረኞች ናቸው (102፥20 ይመ)፤ ምንም እንኳን እስር ቤት ባይገቡም በሞት ጥላ ውስጥ ስለ ነበሩ ወደ ገዛ ምድራቸው ለመመለስ የሚናፍቁ ናቸው።

*79፥12-13፤* በመደምደሚያ ላይ የቀረበ ጸሎትና እግዚአብሔርን ለማመስገን ቃል የተገባበት ክፍል ነው።

79፥12 *በአንተ ላይ የተዘባበቱትን፤* ጠላት በእስራኤል ላይ የፈጸመው ክፉ ድርጊት በከፍተኛ ደረጃ እግዚአብሔርን አስቈጥቶአል (ቍ1:10፤ 2ነገ19፥10-12:22-23፤ ኢሳ52፥5 ይመ)። *ሰባት ዕጥፍ፤* ሙሉ በሙሉ ለማለት ነው፤ ሰባት ቍጥር የፍጹምነት ምሳሌ ነው። *ሰባት ዕጥፍ አድርገህ አስታቅፋቸው፤* የኤር32፥18 ማብ ይመ።

*79፥13፤* የ7፥17 ማብ ይመ። *የማሰማሪያህ በጎች፤* 74፥1፤ 77፥20፤ 78፥72 ይመ። *ከትውልድ እስከ ትውልድ፤* 78፥4 ይመ።

*መዝ80፤* ጠላት እንዳልነበረ ባደረጋት ጊዜ፣ እግዚአብሔር መልሶ እንዲገነባት እስራኤል ያቀረበችው ጸሎት ነው። በዚህ ቦታ እንደሚታየው፣ "ኤፍሬም፣ ብንያምና ምናሴ" (ቍ2) ሰሜናዊውን መንግሥት የወከሉ ይመስላል። በእርግጥ ለኢዮርብዓም ዐሥር ነገድ ተሰጠውና (1ነገ11፥29-36) ለሮብዓም ግን አንድ ነገድ ማለትም ይሁዳ ብቻ የተሰጠው ከሆነ (1ነገ12፥20)፣ ብንያም ሊመደብ የሚችለው ከሰሜኑ መንግሥት ጋር ነው ማለት ነው፤ ስምዖን ከይሁዳ ጋር የሚቈጠር በመሆኑ፣ ይሁዳ እንደ ሁለት ነገድ ሊታይ ይችላል (ኢሱ19፥1-9)። ሆኖም የብንያም ግማሹ ክፍል እስከ ኢየሩሳሌም ድንበር ድረስ የሚዘልቅ በመሆኑ፣ በደቡባዊው መንግሥት ሥር የሚገኝ ነው፤ ደቡባዊው መንግሥት በኢየሩሳሌም ላይ የሚደረገውን ወረራ በቍጥጥሩ ሥር ለማድረግ ብዙ ተጣጥሮአል (1ነገ12፥21)። አሦራውያን ግን ደቡባዊው መንግሥት ከቶ እንዳይገኝ አድርገው ሰባበሩት (2ነገ17፥1-6)። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በፓሌስቲና የተደረጉ ሥነ-ቍፋሮ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፣ ከአሦራውያን ሰይፍ ለማምለጥ በሸሹ ስደተኞች ምድሪቱ ተጥለቅልቃ ነበር። ይህም፣ "ኤፍሬም፣ ብንያምና ምናሴ" በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ውስጥ መገኘት እንዲችሉና ስለ ሕዝቡ መታደስ በተለይም ስለ ሦስቱ ነገዶች በሚደረገው ጸሎት ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታን ፈጥሮላቸዋል (ማብ ከታች ይመ)። በዕብራይስጡ ቅጅ ላይ እንደሚታየው ይህ ጸሎት እያንዳንዳቸው አራት መስመሮች ያሉት አምስት አንጓዎች አሉት። በቍ3 ላይ፣ "እግዚአብሔር ሆይ"፣ በቍ7 ላይ "ሁሉን ቻይ አምላክ ሆይ" በቍ19 ላይ ደግሞ፣ "ሁሉን ቻይ እግዚአብሔር አምላክ ሆይ" የሚሉት የአቤቱታ መግለጫዎች የመጀመሪያውን፣ ሁለተኛውንና የመጨረሻውን አዝማች እያሳደጉ በመምጣት ነገሩን ከመጨረሻው ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያደርሱታል።

መዝ80ርእስ *ለመዘምራን አለቃ፤* የመዝ4 የርእስ ማብ ይመ። *በቅኝት፤* የመዝ9 የርእስ ማብ ይመ። *አሳፍ፤* የመዝ73 የርእስ ማብ ይመ።

*80፥1-3፤* እግዚአብሔር በጥንት ዘመን በምድረ በዳ እንዳደረገው ሁሉ፣ ዛሬም ክንዱን እንዲያነሣና በሕዝቡ መካከል እንዲሠለጥን፣ በቀደመውም ዘመን እንዳደረገው አሁንም ክብሩንና ኀይሉን እንዲገለጥ የቀረበ አቤቱታ ነው።

*80፥1፤* በ74፥1፤ 77፥20፤ 78፥52:71-12፤ 79፥13 ላይ የተጠቀሰውን የበግና የእረኛ ግንኙነት ይመ። *ዮሴፍ፤* የ77፥15 ማብ ይመ። *በኪሩቤል ላይ በዙፋን የምትቀመጥ፤* የዘፀ25፥18 ማብ ይመ። *በብርሃንህን ተገለጥ፤* በምድረ በዳው ጕዞ ላይ እንደሆነው ሁሉ አሁንም ክብርህ ይታይ (ዘፀ24፥16-17፤ 40፥34-35 ይመ) በተለይ አሁን ግን በአዲስ የማዳን ሥራህ ይታይ ማለት ነው (102፥15-16፤ ዘፀ14፥4:17-18፤ ዘኍ14፥22፤ ኢሳ 40፥5፤ 44፥23፤ 60፥1-2 ይመ)።

80፥2 *በኤፍሬም፣ በብንያምና በምናሴ ፊት፤* ከሲና ተነሥቶ ወደ ተስፋዪቱ ምድር በሚተመው የሕዝብህ ጠላቶች ላይ እንዳወጣህ ሁሉ፣ ዛሬም በሕዝብህ ጠላቶች ላይ ውጣ፤ ሕዝብህንም አድን ማለት ነው (በዚያን ዘመን የቃል ኪዳኑ ታቦት በእነዚህ ሦስቱ ነገዶች ሰልፍ ፊት ፊት ይወጣ ነበር፤ ዘኍ 10፥21-24 እንዲሁም የመዝ68 መግቢያ ይመ)። *አንቀሳቅስ፤* የ7፥6 ማብ ይመ።

80፥3 *ፊትህን ... አብራ፤* ቍ7፥19 ይመ። ካህናት የሚያቀርቡትን ቡራኬ የሚያሳስብ ነው (ዘኍ6፥25 እና የ4፥6፤ የ13፥1 ማብ ይመ)።

*80፥4-7፤* እግዚአብሔር ሕዝቡን ክፉኛ በመቅጣቱ ሕዝቡ ያሰማው ጩኸት ነው።

80፥4 *የሰራዊት አምላክ እግዚአብሔር፤* ቍ7:14:19 እንዲሁም የ1ሳሙ1፥3 ማብ ይመ። *እስከ መቼ?* የ6፥3 ማብ ይመ። (በመጽሐፈ መዝሙር መግቢያ ላይ፣ "ትምህርተ መለኮት" የሚለውን ይመ)። *ቍጣ፤* የ2፥5 ማብ ይመ።

*80፥5፤* እግዚአብሔር፣ "መላእክትን ምግብ" እና ከዐለት ውስጥ የፈለቀውንም ውሃ እንዲጠጡ በማድረግ ፈንታ፣ አሁን እንባ እንዲበሉና እንባንም እንዲጠጡ አደረጋቸው (78፥20:25 ይመ)።

*80፥8-16፤* በዚህ ቦታ የእስራኤልን ሁኔታ ለመግለጽ የተጠቀሰው የወይን ተክል ምሳሌ፣ በነቢያት መጻሕፍትም ላይ ተደጋግሞ ተወስቶአል (ኢሳ3፥14፤ 5፥1-7፤ 27፥2፤ ኤር2፥21፤ 12፥10፤ ሕዝ17፥6-8፤ 19፥10-14፤ ሆሴ10፥1፤ 14፥7፤ ሚክ7፥1፤ እንዲሁም ዘፍ49፥22፤ ማቴ20፥1-16፤ ማር12፥1-9፤ ሉቃ20፥9-16፤ ዮሐ15፥1-5 ይመ)።

*80፥8-11፤* በአንድ ወቅት እስራኤል ለእግዚአብሔር ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ተወስዳ የተተከለችና የለመለመች የወይን ተክል ነበረች።

80፥8 *አመጣህ፤* 78፥52 ይመ። በዚህ ቦታ የዕብራይስጡ ግስ፣ "ነቀልክ" (ኢዮ19፥10) የሚል ትርጕም አለው። *አሕዛብን አባርረህ፣ እረሷን ተከልሃት፤* 44፥2 ይመ። *ተከልሃት፤* ከአንድ ቦታ ወስደህ ወደ ሌላ ቦታ ተከልሃት ለማለት ነው።

9መሬቱን መነጠርህላት፤
እርሷም ሥር ሰዳ አገሩን ሞላች።
10ተራሮች በጥላዋ ተሸፈኑ፤
ግዙፍ ዝግቦችም በቅርንጫፎቿ ተጠለሉ።
11ቅርንጫፎቿን እስከ ባሕሩ፣[ተ]
ቊጥቋጦዋንም እስከ ወንዙ[አ] ዘረጋች።

12ታዲያ ዐላፊ አግዳሚው ፍሬዋን
እንዲለቅም፣
ለምን ቅጥሯን አፈረስህ?
13ዕርያ ከዱር ወጥቶ ያበለሻሻታል፤
በሜዳ የሚንጋጋ እንስሳ ሁሉ
ይበላታል።
14የሰራዊት ጌታ አምላክ ሆይ፤ እንግዲህ
ወደ እኛ ተመለስ፤
ከሰማይ ተመልከት፤ እይም፤
ይህችን የወይን ተክል ተንከባከባት፤
15ይህች ቀኝ እጅህ የተከላት ቡቃያ፣
ለራስህ ያጸደቅሃት ተክል[ከ] ናት።

16እርሷም በእሳት ተቃጥላለች፤
የግንባርህ ተግሣጽ ያጠፋቸዋል።
17ለራስህ ባበረታኸው የሰው ልጅ ላይ፣
በቀኝ እጅህ ሰው ላይ እጅህ ትሁን።

80፥11 መዝ72፥8
80፥12 መዝ89፥40 ኢሳ5፥5፤30፥13፤ኤር 39፥8
80፥13 ኤር5፥6
80፥14 ዘዳ26፥15
80፥16 ዘዳ28፥20፤ መዝ79፥1
80፥17 ኢዮ25፥6
80፥18 መዝ85፥6፤ ኢሳ57፥15፤ሆሴ6፥2
81፥1 መዝ66፥1
81፥2 ዘፀ15፥20፤ ኢዮ21፥12፤መዝ92፥3
81፥3 ዘፀ19፥13፤ ነህ10፥33

18ከእንግዲህ አንተን ትተን ወደ ኋላ
አንመለስም፤
ሕያዋን አድርገን፤ እኛም ስምህን
እንጠራለን።

19የሰራዊት ጌታ አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፤
መልሰን፤
እንድንም ዘንድ፣
ፊትህን አብራልን።

## መዝሙር 81

### ለዳስ በዓል የሚዜም ቅኔ

*ለመዘምራን አለቃ፤ በዋሽንት የሚዜም፣ የአሳፍ መዝሙር*

1ብርታታችን ለሆነው ጌታ አምላክ በደስታ
ዘምሩ፤
ለያዕቆብ ጌታ አምላክ እልል በሉ።
2ዝማሬውን ጀምሩ፤ ከበሮውን ምቱ፤
በበገናና በመሰንቆ ጥዑም ዜማ አሰሙ።
3በሙሉ ጨረቃ፣ በክብረ በዓላችን ዕለት፣
በወሩ መግቢያ፣ ጨረቃ ስትወለድ
መለከት ንፉ፤

[ተ]11 ሜድትራኒያን ሳይሆን አይቀርም።
[አ]11 የኤፍራጥስ ወንዝ ለማለት ነው።
[ከ]15 ወንድ ልጅ የሚሉ ትርጒሞች አሉ።

80፥9 *መሬቱን መነጠርህላት፤* ኢሳ5፥2 ይመ።

80፥10 *ግዙፍ ዝግቦችም በቅርንጫፎቿ፤* ቃል በቃል ሲተረጐም "የእግዚአብሔር ዝግባ" እንደ ማለት ነው (አንዳንድ ጊዜ፣ "እግዚአብሔር" የሚለው የዕብራይስጡ ቃል፣ "ኀያል" የሚል ትርጒም አለው ለምሳሌ ያህል የ29፥1 ማብ ይመ)።

80፥11 *ባሕሩ ... ወንዙ፤* የሜድትራንያን ባሕር ወይም የኤፍራጥስን ወንዝ ማለቱ ሳይሆን አይቀርም፤ ዘፀ23፥31 እና ማብ ይመ።

*80፥12-15፤* እግዚአብሔር ከጥቅም ውጪ ለሆነው የወይኑ ተክል ክብካቤ ማድረጉን እንዲቀጥል የሚማጸን ጸሎት ነው።

80፥12 *ለምን ...?* እስራኤል እግዚአብሔር ስለ ምን እንደ ተዋት ግራ በመጋባት ያቀረበችው ጥያቄ ነው (የ6፥3 ማብ ይመ)።

80፥14 *ተንከባከባት፤* ዘፀ3፥16 ይመ። የዚህ ቃል የዕብራይስጡ ትርጒም በሩት1፥6 ላይ እንዳለው፣ "እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደጐበኘ" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ይዘት ሳይኖረው አይቀርም።

80፥15 *ተክል፤* እስራኤል ለማለት ነው (ዘፀ4፥22-23፤ ሆሴ11፥1 ይመ)። አንዳንድ ጊዜ ግን፣ "ወንድ ልጅ" የሚለው የወይን ተክል ቅርንጫፍን ያመለክታል (የዘፍ49፥22 ማብ ይመ)። በዚህም ቦታ ቃሉ የሚያመለክተው ይኸንኑ ሳይሆን አይቀርም፤ ስለዚህ ሁለቱን የአንድ አካል ክፍሎች ማለትም፣ "ሥርና ቅርንጫፍን" የወይን ምሳሌ አድርጐ አቅርቦአል (ኢዮ18፥16፤ 29፥19፤ ሕዝ17፥7፤ ሚል4፥1፤ እንዲሁም ኢሳ5፥24፤ 27፥6፤ 37፥31፤ሕዝ 17፥9፤ 31፥7፤ ሆሴ9፥16፤ አሞ2፥9፤ ሮሜ11፥16 ይመ)። *ያጸደቅሃት፤* "ያጠነከርኸው" ለማለት ነው (ቊ17 ይመ)።

*80፥16-19፤* እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ ሕይወት እንዲያድስ በመደምደሚያ ላይ የቀረበ ጸሎት ነው።

80፥16 *ተግሣጽ፤* 9፥5 እና የ76፥6 ማብ ይመ።

80፥17 *እጅህ ... ላይ ... ትሁን፤* መልካምነትህን አሳየን እንደ ማለት ነው (ዕዝ7፥6፥9፥28፤ 8፥18፥22፥31፤ ነህ2፥8፥18 ይመ)። *በቀኝ እጅህ፤* ይህ ሐረግ የሚያመለክተው ከዳዊት ወገን የሆነውንና በእግዚአብሔርም የተቀባውን፣ በእግዚአብሔር ዘንድ በክብር ቦታ የተቀመጠውንና (110፥1 ይመ) የዓለምም ተስፋ የሆነውን ሳይሆን አይቀርም (2፥7-9፤ 72፥8-11፤ 89፥21-25 ይመ)፤ ቊ15 ግን፣ "ሰውዬው" ያዕቆብ ማለትም እስራኤል መሆኑን፣ እርሱም እግዚአብሔር፣ "የተከለው" እና "ያሳደገው" በመሆኑ በእግዚአብሔር፣ "ቀኝ" የተቀመጠ መሆኑን ይናገራል።

*80፥18፤* ለእግዚአብሔር ታማኝ ለመሆንና እርሱንም ብቻ ለመከተል የተነገረ ቃል ኪዳን ነው። እንዲህ ባለው ቦታ እንዲህ ዐይነቱን ቃል ኪዳን ማግኘት የተለመደ ነው (የ7፥17 ማብ ይመ)።

*መዝ81፤* የክብረ በዓል መዝሙር ነው። ነገር ግን ክብረ በዓሉ የፋሲካ ወይም የቂጣ በዓል (ቊ5፤ ዘፀ12፥14-17 ይመ) ወይም የአይሁድ የዘመን መለወጫ በዓል (ቊ3፤ ዘሌ23፥34፤ ዘኍ29፥12 ይመ) ወይም የዳስ በዓል ስለመሆኑ ምንም አይታወቅም (ቊ3፤ ዘሌ23፥34፤ ዘኍ29፥12 ይመ)። መዝሙሩ በሦስቱም ክብረ በዓላት ላይ ሊዘመር ይችላል። ሆኖም በዘመን መለወጫ (ወር በገባ በመጀመሪያው ቀን ማለትም "በአዲስ ጨረቃ") እና በዳስ በዓል መጀመሪያ (ወር በገባ በ15ኛው ቀን ማለትም በ"ሙሉ ጨረቃ") ላይ በበለጠ ይገለገሉበታል። በበለጠ ለመረዳት ከዚህ በታች ያሉትን ማብ ይመ። መዝሙሩ የተዘመረው ከምርኮ በፊት ወይም ከምርኮ በኋላ ስለመሆኑ ምንም የሚታወቅ ነገር ባይኖርም፣ የእስራኤል ዓመታዊ ክብረ በዓላት ከፍተኛ ቦታ ያላቸው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል (በገጽ 178 ላይ "የብሉይ ኪዳን ክብረ በዓላትና ሌሎች ቅዱስ ቀናት" የሚለውን ሰንጠረዥ ይመ)። እግዚአብሔር ላደረገው የማዳን ሥራ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ በዓሉን ለማክበር፣ ሁኔታውን ለማስታወስና በድጋሚም ቃል ለመግባት (መዝ95 ይመ) ለእስራኤል ሕዝብ ጥሪ ቀርቦአል። በዚህ መዝሙር ውስጥ እንደሚታየው፣ በእግዚአብሔር ፈንታ ለእስራኤል ሕዝብ ንግግር የሚያደርግ (ትንቢታዊ በሆነ መንገድ) አንድ ሌዋዊ ነው። መዝሙሩ ከሁለት የሚከፈል ቢሆንም (ቊ1-5፥6-16) የመዝሙሩ መሪ ሐሳብ አስተዳደግ (አጐለማመስ) ግን እኩኩያዊ ሞዴልን የተከተለ ነው፤ ይኸውም ሁለት ቊጥር፣ ሦስት ቊጥር፣ ሁለት ቊጥር፣ ሦስት ቊጥር፣ ሁለት ቊጥር፣ አራት ቊጥር እያለ እያደገና እየጐለመሰ ይሄዳል። ከዚህ ላይ በቊ6-7 እና 11-12 መካከል ያለውን ንጽጽርና በቊ10 እና በቊ16 መካከል ያለውን መሪ ሐሳብ ዝምድና ማስተዋል ያስፈልጋል።

81 ርእስ *ለመዘምራን አለቃ፤* የመዝ4 ርእስ ማብ ይመ። *በ ... ፤* የመዝ6 ርእስ ማብ ይመ። *አሳፍ፤* የመዝ73 ርእስ ማብ ይመ።

*81፥1-5፤* የተቀደሰ ክብረ በዓል ያደርጉ ዘንድ የቀረበ ጥሪ ነው።

81፥1 *ያዕቆብ፤* እስራኤል ማለት ነው (ዘፍ32፥28 ይመ)።

81፥2 *ከበሮ፤* የኤር31፥4 ማብ ይመ። *በገናና በመሰንቆ፤* የ57፥8 ማብ ይመ።

81፥3 *መለከት፤* ከአውራ በግ ቀንድ የተሠራ መለከት ነው (ዘፀ19፥13 ይመ)። *በዓላችን፤* የዳስ በዓልን ሳይሆን አይቀርም፤ በብዙ ቦታ ግን፣ "በዓል" ብቻ ተብሎ ተጠቅሶአል (1ነገ8፥2፥65፤ 12፥32፤ 2ዜና5፥3፤ 7፥8፤ ነህ8፥14፥18፤ ሕዝ45፥25፤ እንዲሁም ዘዳ16፥14 ይመ)። ወር በገባ ባዐሥራ አምስተኛው ቀን የሚጀምረው ታላቁ የሰባት ቀን በዓል (ጨረቃ ሙሉ በምትሆንበት ጊዜ) በዚህ ክፍል የተጠቀሰው በዓልም በዐሥረኛው ቀን

4ይህ ለእስራኤል የተሰጠ ሥርዐት፣
የያዕቆብም ስምላክ ድንጋጌ ነውና::
5ሙሉ ለሙሉ ግብፅን ለቆ በወጣ ጊዜ፣
ይህን ለዮሴፍ ደነገገለት፤
በማላውቀውም* ቋንቋ እንዲህ ሲል
ሰማሁ:-

6"ትከሻውን ከሸክም ገላገልሁት፤
እጁንም ቅርጫት ከመያዝ አሳረፍሁ::
7በመከራህ ጊዜ ጠራኸኝ፤ እኔም ታደግሁህ፤
በነጐድጓድ መሰወሪያ ውስጥ መለስሁልህ፤
በመሪባ ውሃ ዘንድ ፈተንሁህ:: ሴላ

8"ሕዝቤ ሆይ፤ ሳስጠንቅቅህ ስማኝ፤
እስራኤል ሆይ፤ ምነው ብታደምጠኝ!
9በአንተ ዘንድ ባዕድ አምላክ አይኑር፤
ለሌላም አምላክ አትስገድ::
10ከግብፅ ምድር ያወጣሁህ፣
እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ነኝ፤
አፍህን በሰፊው ክፈተው፤ እኔም
እሞላዋለሁ::

11"ሕዝቤ ግን አላደመጠኝም፤
እስራኤልም እጅ አልሰጥ አለኝ::
12ስለዚህ በገዛ ዕቅዳቸው እንዲሄዱ፣
አሳልፌ ለደንዳናው ልባቸው ሰጠኋቸው::

13"ምነው ሕዝቤ ቢያደምጠኝ ኖሮ፣
እስራኤል በመንገዴ በሄደ ኖሮ፣
14ጠላቶቻቸውን ፈጥኜ ባንበረከክኋቸው
ነበር፤
እጄን በባላጋራዎቻቸው ላይ ባነሣሁ
ነበር::
15እግዚአብሔርን የሚጠሉ በፊቱ ይርዳሉ፤
ቅጣታቸውም እስከ ዘላለም የሚዘልቅ
ነው::
16እናንተን ግን ምርጡን ስንዴ አበላችኋለሁ፤
ከዐለቱም ማር አጠግባችኋለሁ::"

## መዝሙር 82

### ምሱናን ዳኞች

የአሳፍ መዝሙር

1እግዚአብሔር በአማልክት ጉባኤ መካከል
ተሰየመ፤

81፥4 ቍ1
81፥5 ዘፀ11፥4፤ መዝ114፥1
81፥6 ዘፀ1፥14፤ኢሳ 9፥4፤52፥2
81፥7 ዘፀ2፥23፤ 17፥7፤19፥19፤ዘዳ 33፥8
81፥8 መዝ50፥7፤ 78፥1
81፥9 ዘፀ20፥3
81፥10 ዘፀ6፥6፤ 13፥3፤29፥46፤መዝ 107፥9፤ሕዝ2፥8
81፥11 ዘፀ32፥1-6
81፥12 ሕዝ20፥25፤ ሐሥ7፥42፤ሮሜ1፥24
81፥13 ዘዳ5፥29
81፥14 መዝ47፥3፤ አሞ1፥8
81፥15 2ሳሙ22፥45
81፥16 ዘዳ32፥14
82፥1 ኢዮ21፥22፤ መዝ7፥8፤58፥11፤ኢሳ 3፥13፤66፥16፤ኢል 3፥12

*5 አንዳንዶች *የማናውቀውን ድምፅ ሰማን* ይላሉ::

የሚከበረውን የስርየት ቀን (ዘሌ 16፥29) ተከትሉ የሚመጣ ሲሆን፣ በምድረ በዳው ጒዞ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያደረገውን ጥበቃና ክብካቤ (ዘሌ23፥43 ይመ) የሚያስታውስና ለሚሰበሰ በውም መከር የምስጋና በዓል በመሆን የሚያገለግል (ዘሌ23፥39-40፤ ዘዳ16፥13-15 ይመ) እንዲሁም ከስድስት ወር በፊት በፋሲካና በቂጣ በዓል የተጀመረውንና በየዓመቱም የሚመጣውን የሃይ ማኖት በዓላት ዑደት የሚያጠቃልል ነው (ዘፀ23፥14-17፤ ዘሌ23፤ ዘዳ16፥16 ይመ):: በየሰባት ዓመቱ በዚህ በዓል ላይ የቃል ኪዳኑ ሕግ ለሕዝቡ ሁሉ ይነበባል (ዘዳ31፥9-13፤ ነህ 8፥2:15 ይመ):: የወሩም (አዲስ ጨረቃ) የመጀመሪያ ቀን መለከት በመንፋት (ዘሌ23፥24) ይከበራል:: በኋላ ግን ሰባተኛው ወር የመከር ማጠናቀቂያና የዝናብ ወራት መግቢያ (ዘር የሚዘራ በት ወቅት) በመሆኑ፣ አዲስ ዓመት ተደርጐ ተወስዶአል::

81፥4-5 *ድንጋጌ ... ደነገገለት፤* በቍ3 ማብ ላይ የተጠቀሱትን የማጣቀሻ ምንባቦች ይመ::

81፥5 *ዮሴፍ፤* የ77፥15 ማብ ይመ:: *ግብፅን ለቆ በወጣ፤* በዚህ ክፍል የተጠቀሰው በዓል የፋሲካና የቂጣ በዓል እንደ ሆነ (ዘፀ12፥14:42 ይመ) አንዳንዶች ይናገራሉ:: ክፍሉ የሚያመ ለክተው ግን ከግብፅ ጀምሮ የተደረገውን በተለይም እግዚአብሔር ሕዝቡን ነጻ ለማውጣት (ቍ6-7 ይመ) የፈጸመውን ድንቅ ሥራ ነው:: *የማላውቀውም ቋንቋ እንዲህ ሲል ሰማሁ፤* በባዕድ ምድር መጻተኞች ስለነበሩ ነው (114፥1፤ ዘዳ28፥49፤ ኢሳ19፥18፤ 33፥19፤ ኤር5፥15፤ ሕዝ3፥5-6 ይመ):: በዚህ ቦታ "ቋንቋ" ተብሎ የተተ ረጐመው፣ "ድምፅ" ሊባል ይችላል፤ ነገሩን በዚህ መልኩ ካየነው ይህ ድምፅ እግዚአብሔር በግብፃውያን ላይ ያወረደው የፍርድ "ነጐድጓድ" ነው (ቍ7 ይመ)፤ የመዝሙሩ ደራሲ ለአምልኮ ለተሰበሰበው ሕዝብ ነገሩን ያብራራውም በዚህ መልኩ ነው (ቍ 6-16)::

*81፥6-10፤* እግዚአብሔር ጩኸታቸውን ሰምቶ ታድጐአ ቸዋል፤ ስለዚህ ለእርሱ ታማኝ እንዲሆኑ ጥሪ ያቀርብላቸዋል::

81፥6 *ከሸክም ... ቅርጫት፤* በእስራኤላውያን ጫንቃ ላይ ተጭኖ የነበረውን የግብፅ የባርነት ቀንበር ያመለክታል (ዘፀ 1፥11-14 ይመ)::

81፥7 *ጠራኸኝ፤ እኔም ታደግሁህ፤* ዘፀ3፥7-10 ይመ:: *በነጐድጓድ መሰወሪያ ውስጥ መለስሁልህ፤* 106፥9፤ ዘፀ14፥21: 24፤ 15፥8:10፤ እንዲሁም የ76፥6 ማብ ይመ:: *ፈተንሁህ፤* ዘፀ 17፥1-7 ይመ::

*81፥8-10፤* እግዚአብሔር ሕዝቡ በተጨነቀ ጊዜ ጆሮውን ዘንበል አድርጐላቸዋል (ቍ6-7)፤ ስለዚህ አሁን ሕዝቡ እግዚ አብሔርን መስማት አለበት::

*81፥9-10፤* ዘፀ19፥4-5፤ 20፥2-4፤ ዘዳ4፥15-20 ይመ::

81፥10 *አፍህን በሰፊው ክፈተው፤* በሕይወት ለመኖር ለሚያስፈልጋችሁ ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር ብቻ ታመኑ ማለት ነው:: *እኔም እሞላዋለሁ፤* ቍ16 ይመ:: በምድረ በዳ ሕዝቡን እንደ መገበና እንደ ተንከባከበ ሁሉ አሁንም እንዲሁ ያደርጋል (78፥23-29፤ እንዲሁም 37፥3-4፤ ዘዳ11፥13-15፤ 28፥1-4 ይመ)::

*81፥11-16፤* የእስራኤል ሕዝብ ግን እግዚአብሔርን ሊያ ደምጥ ፈቃደኛ አልሆነም ሕዝ18፥23:32፤ 33፥11 ይመ::

*81፥11፤* 78፥10:17:32:40:56፤ ዘዳ9፥7:24፤ ኤር7፥24-26 ይመ::

*81፥12፤* የሰውን ልብ፣ "ሊገርዝ" የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው (ዘዳ30፥6 እንዲሁም 1ነገ8፥58፤ ኤር31፥33፤ ሕዝ 11፥19፤ 36፥26 ይመ):: ስለዚህ እግዚአብሔር ሕዝቡን ከኀጢአቱ የተነሣ እርግፍ አድርጐ ተወው ማለት ከሁሉ የበለጠ አስፈሪ ቅጣት ነው (78፥29፤ ኢሳ6፥9-10፤ 29፥10፤ 63፥17፤ ይመ፤ ከሮሜ1፥24:26:28 ጋር ያነጻጽሩ)::

*81፥13-16፤* በዘፀ23፥22-27፤ በዘሌ26፥3-13፤ በዘዳ7፥12-26፤ 28፥1-14 ላይ የተጠቀሰውን የቃል ኪዳን ተስፋ በረከት ይመ::

81፥13 *በመንገዴ፤* 25፥4 እና ማብ ይመ::

81፥16 *ከዐለቱም ማር፤* የዘዳ32፥13 ማብ ይመ::

*መዝ82፤* በክፉ ገዦችና ዳኞች ላይ የተላለፈ የፍርድ ቃል ነው:: የዚህ መዝሙር ጸሓፊ እንደሚገልጸው እግዚአብሔር በሰ ማያዊ ዙፋኑ ላይ ተቀምጦ በራእይ ተመልክቶአል፤ ይህም ነቢ ያት ካዩትና ከተለማመዱት ጋር የሚመሳሰል ነው (1ነገ22፥19-22፤ኢሳ6፥1-7፤ ኤር23፥18:22፤ ኢዮ15፥18 ይመ):: እግዚአብሔር ታላቅ ንጉሥ (የመዝ47 መግቢያ ይመ)፣ የምድር ሁሉ ፈራጅ (94፥2፤ ዘፍ 18፥25፤ 1ሳሙ2፥10 ይመ)፣ ፍትሕን የሚወድና (99፥4) በሕዝቦችም ላይ በጽድቅ የሚፈርድ (9፥8፤ 96፥13፤ 98፥9 ይመ) በመሆኑ፣ ለምስኪኖችና ለተገፉት ሰዎች መቆም የሚገባቸውን የሕ ዝብ አለቆች በኀላፊነት ሲጠይቃቸው ይታያል:: የጥንት ረቢያዊ ተንታኞች (ዮሐ10፥34-35 ይመ)፣ "አማልክት" (ቍ1:6) የሚለው ቃል የሚያመለክተው በእስራኤል የነበሩት በርካታ ጨካኝ ገዦችና ፈራጆችን ነው ይላሉ (1ሳሙ8፥3፤ ኢሳ1፥16-17፤ 3፥13-15፤ ኤር21፥12፤ 22፥3፤ ሕዝ34፥4:21፤ ሚክ3፥1-3፤ 7፥3 ይመ):: በአሁኑ ወቅት ግን ብዙዎች፣ "አማልክት" የሚለው ቃል የሚያ መለክተው በእስራኤል ዙሪያ የሚገኙ መንግሥታትን/ ሕዝ ቦችን ነው ይላሉ:: ሌሎች ደግሞ፣ "አማልክት" መለኮታዊ ሕል ውና ያላቸውና ነገሥታትም በአማልክት ስም አገርን እንደሚ ያስተዳድሩ ይናገራሉ (95፥3 ይመ):: ያም ሆነ ይህ ገዦችና ዳኞች፣ በሁሉ ላይ በሚፈርደውና በሚገዛው ጌታ ሥር ናቸው (መዝ58 ይመ):: ባወቃቀር ረገድ ሲታይ የጸሓፊው ቃል (ቍ1: 6) የእግዚአብሔርን ቃል ቀንብቦታል:: በመዝሙሩ መካከል ላይ የሚገኘው (ቍ5 እና የ6፥6 ማብ ይመ) ከፍርዶች ሁሉ እጅግ ታላቅ የሆነውን ፍርድ የያዘ ቃል ነው::

*82ርእስ፤* የመዝ73 ርእስ ማብ ይመ::

82፥1 *ታላቅ ጉባኤ፤* በታላቁ ፍትሕ አዳራሽ ውስጥ የሚገኝ ጉባኤ ነው (89፥5፤ 1ነገ22፥19፤ ኢዮ1፥6፤ 2፥1፤ ኢሳ6፥1-

በአማልክትም ላይ ይፈርዳል፤ እንዲህም
ይላል:-

2“ፍትሕን የምታጓድሉት እስከ መቼ ነው?
ለክፉዎች የምታደሉትስ እስከ መቼ
ነው? ሴላ
3ለዐቅመ ቢሶችና ለድኻ አደጎች
ፍረዱላቸው፤
የችግረኛውንና የምስኪኑን መብት
አስከብሩ::
4ወገን የሌለውንና ችግረኛውን ታደጉ፤
ከግፈኛውም እጅ አስጥሏቸው::

5“ዕውቀትም ማስተዋልም የላቸውም፤
በጨለማ ውስጥ ወዲያ ወዲህ
ይመላለሳሉ፤
የምድርም መሠረቶች ሁሉ ተናወጡ::

6“እኔም፤ ‘እናንተ አማልክት ናችሁ፤
ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ’ አልሁ::
7ነገር ግን እንደ ማንኛውም ሰው
ትሞታላችሁ፤
እንደ ማንኛውም ገዥ ትወድቃላችሁ::”

8እግዚአብሔር ሆይ፤ ተነሥ፤ በምድር ላይ ፍረድ፤
ሕዝቦች ሁሉ ርስትህ ናቸውና::

82፥2 ዘጸ1፥17፤መዝ 58፥1-2፤ምሳ18፥5
82፥3 ዘዳ24፥17፤ መዝ140፥12፤ኤር 5፥28፤22፥16
82፥5 መሳ5፥4፤ኢዮ 30፥26፤መዝ11፥3፤ 14፥4፤53፥2፤ኢሳ 5፥30፤8፥21-22፤9፥2፤ 59፥9፤60፥2፤ኤር13፥ 16፤23፥12፤ሰቆ3፥2
82፥6 ዮሐ10፥34
82፥7 መዝ49፥12 1ሕዝ31፥14
82፥8 መዝ2፥8፤ 12፥5፤76፥9
83፥1 መዝ28፥1፤ 35፥22፤ኢሳ42፥14፤ 57፥11፤62፥1፤64፥12
83፥2 መሳ8፥28፤ መዝ2፥1፤ኢሳ17፥12
83፥3 ዘፀ1፥10፤መዝ 17፥14፤31፥13
83፥4 አስ3፥6፤ኤር 11፥19፤33፥24
83፥5 መዝ2፥2
83፥6 ዘፍ25፥16፤ 2ዜና20፥1፤መዝ137፥ 7፤ኢሳ34፥5፤ኤር 49፥7፤አሞ1፥11
83፥7 ዘፍ14፥7፤ 19፥38፤ዘፀ15፥14፤ 17፥14፤ኢሱ13፥5፤

## መዝሙር 83
## በእስራኤል ጠላቶች ላይ የቀረበ ጸሎት

የአሳፍ መዝሙር፤ ማኅሌት

1እግዚአብሔር ሆይ፤ ዝም አትበል፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ ጸጥ አትበል፤ ጭጭ
አትበል::
2ጠላቶችህ እንዴት እንደ ተነሣሡ፣
ባላንጣዎችህም እንዴት ራሳቸውን ቀና
ቀና እንዳደረጉ ተመልከት::
3በሕዝብህ ላይ በተንኰል አሤሩ፤
በውድ ልጆችህ ላይ በአንድነት
ተመካከሩ::
4“የእስራኤል ስም ከእንግዲህ እንዳይታወስ፣
ኑና ሕዝብ እንዳይሆኑ እንደምስሳቸው”
አሉ::
5በአንድ ሐሳብ ተስማምተው ተማከሩ፤
በአንተም ላይ ተማማሉ፤
6የኤዶምና የእስማኤላውያን ድንኳኖች፣
የሞዓብና የአጋራውያን ድንኳኖች፣
7ጌባል፣[*] አሞንና አማሌቅ፣
ፍልስጥኤምም ከጢሮስ ሕዝብ ጋር
ሆነው ዶለቱ፤
8አሦርም ከእነርሱ ጋር ተባበረ፤

[*]7 *ቢብሎስ ለማለት ነው::*

4 ይመ ከ1ነገ7፥7 ጋር ያነጻጽሩ):: መዝሙረኛው በራእይ እንደሚያይ ሁሉ፣ ገዦችና ዳኞች በታላቁ ንጉሥ ፊት ቀርበው በአስተዳደራቸው ወቅት ስለ ሰጡት ፍርድና ፍትሕ መልስ ሲ ሰጡ ተመልክቶአል:: *አማልክት፤* ቍ6 ይመ:: በብሉይ ኪዳን አገላለጽና በጥንት ቅርብ ምሥራቃውያን አስተሳሰብ መሠረት ገዦችና ዳኞች የሰማዩ ንጉሥ እንደራሴዎች/ ተወካዮች በመሆ ናቸው፣ “አማልክት” የሚል የክብር ስም ይሰጣቸው (የ45፥6 ማብ ይመ) ወይም፣ “የእግዚአብሔር ልጅ” ተብለው ይጠሩ ነበር (2፥7 እና ማብ ይመ)::

*82፥3-4፤* በብሉይ ኪዳን የገዦችና የዳኞች የመጀመሪያ ተግባር ደካሞችንና ድኾችን ከጨካኞችና ከጨቋኞች እጅ መጠ በቅ ነው (72፥2:4:12-14፤ ምሳ31፥8-9፤ ኢሳ11፥4፤ ኤር23፥3:16 ይመ)::

82፥5 *ምንም አያውቁም፤* የግጥሙ ማእከል ነው (የ6፥6 ማብ ይመ):: የእግዚአብሔርን ጥበብ ሊጋሩ ሲገባ (1ነገ3፥9፤ ምሳ8፥14-16፤ ኢሳ11፥2 ይመ) እነርሱ ግን የእግዚአብሔር ቃል የሚያስተምረውን ምግባራዊ ሥርዐት አቃለሉ፤ የእግዚአብሔርም አገዛዝ ከሕዝቡ የሚጠብቀውን አኗኗር አጣጣሉ (ኢሳ44፥19 ይመ):: ... *መሠረቶች ሁሉ ተናወጡ፤* እንዲህ ያሉ ሰዎች የሥል ጣን ቀንበር ሲጨብጡ የዚህ ዓለም ሥርዐት እንኰትኵት ብሎ ይወድቃል (11፥3፤ 75፥3 እና ማብ ይመ)::

82፥6 *እኔም ... አልሁ፤* ገዦች ወይም ዳኞች በእግዚ አብሔር የተሾሙ ናቸው (2፥7፤ ኢሳ44፥28)፤ ስለዚህ እነርሱ ይህንን እውነታ ተቀበሉትም አልተቀበሉትም እነርሱ ግን የእግዚ አብሔር እንደራሴዎች ወይም ወኪሎች ናቸው (ዘፀ9፥16፤ ኤር 27፥6፤ ዳን2፥21፤ 4፥17:32፤ 5፥18፤ ዮሐ19፥11፤ ሮሜ13፥1 ይመ):: *አማልክት፤* የቍ1 ማብ ይመ:: *የ... ልጆች፤* የቍ1 ማብ ይመ:: *ልዑል፤* የዘፍ14፥19 ማብ ይመ::

*82፥7፤* እነዚህ ዐመፀኛ፣ “አማልክት” ሥልጣናቸው ምንም ያህል ከፍ ቢል እነርሱም እንደ ማንኛውም ሰው ይፈረድባቸ ዋል:: *ትወድቃላችሁ፤* የ13፥4 ማብ ይመ::

*82፥8፤* መዝሙረኛው ወደፊት ሊሆን ያለውን በመረዳት እግዚአብሔር ፈጥኖ ፍርዱን እንዲሰጥና ፍጹም የሆነውም የእ ግዚአብሔር አስተዳደር በአስቸኳይ እንዲመጣ ይጸልያል:: *ተነሥ፤* የ3፥7 ማብ ይመ:: *ርስትህ፤* ግዛት ለማለት ነው (የ79፥1 ማብ ይመ)::

*መዝ 83፤* መላው ዓለም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማ ጥፋት በመነሣቱ፣ እግዚአብሔር ጠላቶቹን እንዲሰባብር እስራኤል ያቀረበችው ጸሎት ነው:: መጽሐፈ ነገሥትም ሆነ ዜና መዋዕል መንግሥታት በእስራኤል ላይ ስለማሤራቸውና በአንድ ሐሳብ ተስማምተው ስለ መዶለታቸው ምንም የሚናገሩት ነገር የለም:: ከተጠቀሱት መንግሥታት ውስጥ ምናልባት ጥቂቶቹ በእስራኤል ላይ ሳይዘምቱና የተቀሩት የእስራኤል ታሪካዊ ጠላቶች ደግሞ ዘመቻቸውን በተለያየ መንገድ ሳይደግፉ አይቀሩም:: ነገሩ እን ዲህ ከሆነ መዝሙሩ የተጻፈው በ2ዜና 20 ላይ እንደ ተጠቀሰው ሞአብ፣ አሞን፣ ኤዶምና ተባባሪዎቻቸው ይሁዳን በወረሩበት ወቅት ነው:: የሆነ ሆኖ መዝሙሩ ከሰሎሞን ዘመነ መንግሥት በኋላና ምናሔም በአሦራውያን እርዳታ ሥልጣኑን እንደ ገና ከማ ግኘቱ በፊት (2ነገ15፥19 ይመ) የተጻፈ ሳይሆን አይቀርም:: የመዝሙሩ ሁለት ታላላቅ ክፍሎች (ቍ1-8:9-18) እያንዳንዳቸው ሁለት ባለ አራት ቍጥር አንጓ ያላቸው ሲሆን፣ የመዝሙሩ ሁለ ተኛው ክፍል ግን ጸሎቱን ከመጨረሻው ከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚያደርስ ባለ ሁለት ቍጥር አንጓ አለው::

83 *ርእስ፤ ማኅሌት፤* የመዝ30 ርእስ ማብ ይመ:: *አሳፍ፤* የመዝ73 ርእስ ማብ ይመ::

*83፥1-4፤* እግዚአብሔር እስራኤልን ፈጽሞ ሊያጠፋት ካለው አደጋ እንዲጠብቃት የቀረበ ልመና ነው::

83፥1 *ዝም አትበል፤* ችላ አትበል፤ አትተወን (35፥22፤ 109፥1 ይመ) ለማለት ነው::

83፥4 *አሉ፤* የ3፥2 ማብ ይመ:: *እንደምስሳቸው፤* የእስራ ኤል ሕልውና እስከ ሁኔታ ላይ እንደ ነበረ ያመለክታል (ቍ12 ይመ)::

*83፥5-8፤* እስራኤልን ከምድረ ገጽ ለማጥፋት በተለያየ አቅጣጫ የተሰለፉ ጠላቶች የተነሡ መሆናቸውን የሚያሳይ ክፍል ነው::

83፥6 *አጋራውያን፤* የአጋር ዘሮች የሆኑ እስማኤላውያንን ወይም በአሦራውያን መዝገብ ላይ አራማውያን በመባል የተጠ ቀሱትን ቡድኖች ሳይሆን አይቀርም (1ዜና5፥10: 18-22፤ 27፥31 ይመ)::

83፥7 *ጌባል፤* 1ነገ5፥18፤ ሕዝ27፥9 ይመ:: ቢብሎስ ተብሎ ይጠራ የነበረ የታወቀ የፍንቃውያን ከተማ ነው::

83፥8 *አሦር፤* ከሞአብና ከአሞን (የሎጥ ዘሮች ናቸው፤ የዘፍ19፥36-38 ማብ ይመ) ጋር አባሪ ተባባሪ ተደርጉ ቢጠቀ ስም፣ በራሱ ክልል እንጂ ወደ እስራኤል ዘልቆ በመምጣት የእስ ራኤል ዋና ጠላት ሆኖ ገና አልቀረበም ነበር::

*83፥9-12፤* እግዚአብሔር በቀደመው የመሳፍንት ዘመን እንዳደረገው ሁሉ ዛሬም ጠላቶቹን እንዲደመስስ የቀረበ ልመና ነው:: የእግዚአብሔር የጽድቅና የሰላም መንግሥት እንዲመጣና እንዲሰፍን ከተፈለገ የእግዚአብሔርን መንግሥት ከምድረ ገጽ ለማ ጥፋት ሸር ጉድ የሚሉና የዓለምን ዕድል ፈንታ እንዳሻቸው ለመዘወር ደፋ ቀና የሚሉ ሁሉ መደምሰስ አለባቸው (የ5፥10

የሎጥ ልጆችም ረዳት ሆኑ። ሴላ
9በምድያም ላይ እንዳደረግኸው አድርግባቸው፤
በቂሶንም ወንዝ በሲሣራና በኢያቢስ
ላይ ያደረስኸው ይድረስባቸው።
10እነርሱም በዐይንዶር ጠፉ፤
እንደ ምድርም ጕድፍ ሆኑ።
11መኳንንታቸውን እንደ ሔሬብና እንደ
ዜብ፣
መሳፍንታቸውንም ሁሉ እንደ ዛብሄልና
እንደ ስልማና አድርጋቸው፤
12እነዚህም፣ “የእግዚአብሔርን የግጦሽ ቦታ፣
ወስደን የግላችን እናድርግ” የሚሉ
ናቸው።
13አምላኬ ሆይ፤ በዐውሎ ነፋስ እንደሚነዳ
ትቢያ፣
በነፋስም ፊት እንዳለ ገለባ አድርጋቸው።
14እሳት ደንን እንደሚያጋይ፣
ነበልባልም ተራራን እንደሚያቃጥል፣
15እንዲሁ በሞገድህ አሳዳቸው፤
በማዕበልህም አስደንግጣቸው።
16እግዚአብሔር ሆይ፤ ስምህን ይሹ ዘንድ፣
ፊታቸውን በዕፍረት ሙላው፤
17ለዘላለም ይፈሩ፤ ይታወኩም፤
በውርደትም ይጥፉ።

ኢሳ23፥3፤ሕዝ27፥3
83፥8 ዘፍ10፥11፤ ዘዳ2፥9
83፥9 ዘፍ25፥2፤ ኢሱ11፥1፤መሳ4፥2፡ 23-24፤7፥1-23
83፥10 1ሳሙ28፥7 ፤2ነገ9፥37፤ኢሳ5፥25፤ ኤር8፥2፤9፥22፤16፥4፤ 25፥33፤ሶፎ1፥17
83፥11 መሳ7፥25፤ 8፥5
83፥12 2ዜና20፥11 ፤ሕዝ35፥10
83፥13 ኢዮ13፥25
83፥14 ዘዳ32፥22 ፤ኢሳ9፥18
83፥15 ኢዮ9፥17፤ መዝ50፥3
83፥16 መዝ34፥5፤ 109፥29፤132፥18
83፥17 2ነገ19፥26፤ መዝ35፥4
83፥18 ኢዮ34፥29፤ መዝ7፥8፤18፥13፤ 68፥4
84፥1 ዘዳ33፥27፤ መዝ27፥4፤43፥3፤ 90፥1፤132፥5
84፥2 ኢሱ3፥10፤ ኢዮ19፥27
84፥3 መዝ2፥6፤ 5፥2፤43፥4፤44፥11
84፥5 መዝ81፥1፤

18ስምህ እግዚአብሔር የሆነው አንተ ብቻ፣
በምድር ሁሉ ላይ ልዑል እንደ ሆንህ
ይወቁ።

## መዝሙር 84

### ወደ መቅደሱ ጕዞ መዝሙር

ለመዘምራን አለቃ፤ በዋሽንት የሚዜም የቆሬ ልጆች መዝሙር

1የሰራዊት አምላክ ሆይ፤
ማደሪያህ ምንኛ የተወደደ ነው!
2ነፍሴ የእግዚአብሔርን አደባባዮች
ትናፍቃለች፤
እጅግም ትጓጓለታለች፤
ልቤና ሥጋዬም፣
ለሕያው አምላክ እልል በሉ።
3ንጉሤና አምላኬ የሰራዊት አምላክ ሆይ፤
መሠዊያህ ባለበት ስፍራ፣
ድንቢጥ እንኳ መኖሪያ ቤት፣
ዋኖስም ጫጩቶቿን የምታኖርበት
ጐጆ አገኘች።
4በቤትህ የሚኖሩ የተባረኩ ናቸው፤
እነርሱም ለዘላለም ያመሰግኑሃል። ሴላ
5አንተን ብርታታቸው ያደረጉ፣
በልባቸው የጽዮንን መንገድ የሚያስቡ
ቡሩካን ናቸው።

ማብ ይመ)።

83፥9 *በምድያም ላይ እንዳደረግኸው፤* ጌዴዎን ድል በነሣ ጊዜ (መሳ7 ይመ) ለማለት ነው። *በሲሣራና በኢያቢስ ላይ ያደረስኸውን፤* የከነዓናውያንን ጥምር ሤራ ባርቅ ባሸነፈ ጊዜ ለማለት ነው (መሳ4 ይመ)።

83፥10 *በዓይንዶር፤* ኢሱ17፥11 እና ማብ ይመ። ዋናው ጦርነት የተካሄደበትና በሰሜን ምሥራቅ የሚገኝ ሥፍራ ሲሆን ከጦር ሜዳ የሚሸሹ ወታደሮች የሚገደሉበት ቦታ ነው።

83፥11 *ሔሬብና ... ዜብ ... ዛብሄልና ... ስልማና፤* በጌዴዎን የተገደሉ የሜዶናውያን ሰራዊት መሪዎች ናቸው።

*83፥12፤* ቊ4 ይመ።

*83፥13-16፤* በአዲስ መልክ የቀረበ ልመና ሲሆን የእግዚአብሔርን አስፈሪ ኀይልና ከጦር ሜዳ የሸሹ ወታደሮችን ሁኔታ ምስላዊ በሆነ መንገድ የሚገልጽ ነው።

83፥15፤ እንደ ነጐድጓድ አስፈሪ የሆነ ሰማያዊ ተዋጊ ጠላቶቹን ዶግ ዐመድ ማድረጉን የሚገልጽ ምስላዊ አቀራረብ ነው (18፥7-15፤ 68፥33፤ 77፥17-18፤ ዘፀ15፥7-10፤ ኢሱ10፥11፤ መሳ5፥4፡20-21፤ 1ሳሙ2፥10፤ 7፥10፤ ኢሳ29፥5-6፤ 33፥3 ይመ)። እግዚአብሔር ሞገድንና ደመናት ሠረገላዎቹ ስለማድረጉ 68፥4 እና ማብ ይመ።

83፥16 *ስምህን፤* የ5፥11 ማብ ይመ። *ይሹ፤* የቊ18 ማብ ይመ።

*83፥17-18፤* ጸሎቱ የተጠቃለለበትና የተደመደመበት ቦታ ነው።

*83፥18፤* የእግዚአብሔር ጦርነት የመጨረሻ ግብ፣ የእስራኤልን ዋስትና ማረጋገጥና የእስራኤልንም (የራሱንም) ጠላቶች መደምሰስ ብቻ ሳይሆን፣ መላው ዓለም እውነተኛ አምላክና ገዥ እርሱ ብቻ መሆኑን እንዲያውቅና ሕዝቡ እርሱን እንደሚሻ ሁሉ መላውም ዓለም እርሱን እንዲሻው ለማድረግም ጭምር ነው (ቊ16፤ 40፥9፤ 47፥9፤58፥11፤59፥13 እና ማብ ይመ)። *ልዑል፤* የዘፍ14፥19 ማብ ይመ።

*መዝ84፤* በእግዚአብሔር ቤት ለመሆን እጅግ ከመናፈቅ የተነሣ የቀረበ በድምፀቱና በይዘቱ ከመዝ42 ጋር የሚቀራረብና ተመሳሳይ ሁኔታንም የሚያንጸባርቅ መዝሙር ነው። ነገሩ እንዲህ ከሆነ የመዝሙሩ ጸሐፊ (ምናልባት በቤተ መቅደስ ውስጥ የሚያገለግል ሌዋዊ ሳይሆን አይቀርም) በእግዚአብሔር ቤት እንዳይገኝ በመከልከሉ (ምናልባት ሰናክሬም ይሁዳን የፍርስራሽ ክምር ባደረገበት ወቅት ሊሆን ይችላል፤ 2ነገ18፥13-16 ይመ) ከዚህ ቀደም በእግዚአብሔር ቤት በመገኘቱ ያገኝ የነበረው በረከት ስለናፈቀው ጩኸቱን ከፍ አድርጐ ያሰማል። በመዝሙሩ ውስጥ ስለ እግዚአብሔርና ስለ ቤተ መቅደሱ እንዲሁም በእግዚአብሔር ቤት ለመገኘት ዕድል ፈንታ ስላገኙ ሰዎች፣ የተጠቀሰ ነገር በመኖሩ የመዝሙሩም ዐቢይ ሐሳብ እነዚሁ ነገሮች ናቸው (ቊ4-5፡12 ይመ)። መዝሙሩ ሦስት ዋና ዋና ክፍሎችና (ቊ1-4፡5-7፡8-11) መደምደሚያ አለው። በዕብራይስጡ ቅጅ ላይ ራሱን የቻለው ባለ ስድስት መስመር ክፍል ቀድሞ ሲመጣ ወደ ጽዮን የሚጓዙ መንገደኞች የተባረኩ መሆናቸውን የሚገልጸው ባለ ሦስት መስመር ማብራሪያ ደግሞ ተከትሎ ይመጣል። እነዚህ ባለ ስድስት መስመር ክፍሎች እያንዳንዳቸው፣ “እግዚአብሔር” የሚለውን ስም ሦስት ጊዜ የያዙ ሲሆን ሰባተኛው የእግዚአብሔር ስም ደግሞ (ሙሉነትን ወይም ፍጹምነትን ያመለክታል) በመደምደሚያው ላይ ተጠቅሷል።

84 *ርእስ፤ ለመዘምራን አለቃ፤* የመዝ4 ርእስ ማብ ይመ። *የቆሬ ልጆች፤* የመዝ42 ርእስ ማብ ይመ።

*84፥1-4፤* በእግዚአብሔር ቤት ለመገኘት ከፍተኛ ጉጉት ያለው መሆኑን የገለጠበት ቦታ ነው።

84፥1 *የተወደደ፤* በዕብራይስጥ የተለመደ አገላለጽ ሲሆን፣ “የተወደደ” ወይም “ተወዳጅ” ተብሎ ሊተረጐም ይችላል። ሁሉን ቻይ እግዚአብሔር፤ ቊ3፡8፡12 እንዲሁም የ1ሳሙ1፥3 ማብ ይመ።

84፥2 *ነፍሴ፤* እኔ (የ6፥3 ማብ ይመ) ማለት ነው። *አደባባዮች፤* የቤተ መቅደሱ አደባባዮች (ቊ10፤ 2ነገ21፥5፤ 23፥11-12 ይመ) ማለት ነው። *ልቤና ሥጋዬ፤* ሁለንተናዬ (73፥26 ይመ) ማለት ነው። *ልቤ፤* የ4፥7 ማብ ይመ። *ለሕያው አምላክ፤* ዘዳ 5፥26 ይመ።

*84፥3፤* መዝሙረኛው ድንቢጦች እንኳ ወደ ቤተ መቅደሱና ወደ መሠዊያው ውስጥ መግባት ስለቻሉ በእነርሱ ቀንቶ አል፤ እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት በምታደርግበት ቦታ ለጫጩቶቻቸው ጐጆ ለመሥራት እንኳን ችለዋል።

84፥4-5፡12 *የተባረኩ፤* የ1፥1 ማብ ይመ።

84፥4 *በቤትህ የሚኖሩ፤* የ15፥1 ማብ ይመ።

*84፥5-7፤* መዝሙረኛው ወደ ጽዮን በሚጓዙ መንገደኞችም ቀንቶአል።

84፥5 *አንተን ብርታታቸው ያደረጉ፤* እግዚአብሔር የሕይወታቸው ታዳጊና ጠባቂ መሆኑን የተረዱ ማለት ነው። *ልባቸው የጽዮንን መንገድ የሚያስቡ፤* ቃል በቃል ሲተረጐም “በልባቸው አውራ መንገድ ያለ” ማለት ነው፤ እስራኤላውያን ሃይማኖታዊ በዓላትን ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም የሚጓዙት በዚህ አውራ መንገድ ነው (ቊ7 ይመ)። *ልባቸው፤* የ4፥7 ማብ ይመ።

6 በልቅሶ ሸለቆ በሚያልፉበት ጊዜ፣
የምንጭ መፍለቂያ ቦታ ያደርጉታል፤
የበልጉም ዝናብ ያረሰርሰዋል::°
7 ከኀይል ወደ ኀይል ይሸጋገራሉ፤
እያንዳንዱም በጽዮን ባለው ስሙ ባክ ፊት
ይቀርባል::
8 የሰራዊት ስሙ ባክ ሆይ፤ ጸሎቴን ስማ፤
የያዕቆብ ስሙ ባክ ሆይ አድምጠኝ::
ሴላ
9 ስሙ ባክ ሆይ፤ ጋሻችንን" እይልን፤
የቀባኸውንም ተመልከት::
10 በሌላ ስፍራ ሺህ ቀን ከመኖር፣
በአደባባይህ አንዲት ቀን መዋል
ይሻላል፤
በክፉዎች ድንኳን ከመቀመጥ ይልቅ፣
በስሙ ባኬ ቤት ደጅ መቆም እመርጣለሁ::
11 እግዚአብሔር ስሙ ባክ ፀሓይና ጋሻ ነውና፤
እግዚአብሔር ሞገስንና ክብርን ይሰጣል፤
እግዚአብሔር በቅንነት የሚሄዱትን፣
መልካም ነገር አይነፍጋቸውም::
12 የሰራዊት ስሙ ባክ ሆይ፤
በአንተ የታመነ ሰው ቡሩክ ነው::

ኤር31፥6
84፥6 ኢዮ38፥26፤ ኢል2፥23
84፥7 ዘዳ16፥16፤ 1ነገ8፥1፤ኢዮ17፥9
84፥8 መዝ4፥1
84፥9 1ሳሙ16፥6፤ መዝ2፥2፤18፥50፤ 59፥11፤132፥17
84፥10 1ዜና23፥5
84፥11 ዘፍ15፥1፤ መዝ34፥10፤ኢሳ 60፥19፤ኤር43፥13፤ ራእ21፥23
84፥12 መዝ2፥12
85፥1 ዘዳ30፥3፤ መዝ14፥7
85፥2 ዘፀ32፥30፤ ዘኍ14፥19፤መዝ 78፥38
85፥3 ዘፀ32፥12፤ዘዳ 13፥17፤መዝ78፥38፤ 106፥23፤ዳን9፥16፤ ዮና3፥9
85፥4 መዝ65፥5፤ 71፥20
85፥5 መዝ50፥21
85፥6 መዝ80፥18፤ ፊል3፥1
85፥7 መዝ6፥4፤

## መዝሙር 85
### ለሰላም የቀረበ ጸሎት

ለመዘምራን አለቃ፤ የቆሬ ልጆች፤ መዝሙር

1 እግዚአብሔር ሆይ፤ ለምድርህ በጎ
ውለሃል፤
የያዕቆብንም ምርኮ መለስህ::
2 የሕዝብህን በደል ይቅር አልህ፤
ኀጢአታቸውንም ሁሉ ሸፈንህ::
3 መዓትህን ሁሉ አራቅህ፤
ከብርቱ ቍጣህም ተመለስህ::
4 መድኀኒታችን የሆንህ ስሙ ባክ ሆይ፤
መልሰን፤
በእኛ ላይ የተቃጣውን ቍጣህን
መልሰው::
5 የምትቈጣን ለዘላለም ነውን?
ቍጣህስ ከትውልድ እስከ ትውልድ
ይቀጥላልን?
6 ሕዝብህ በአንተ ሐሤት ያደርግ ዘንድ፣
መልሰህ ሕያዋን አታደርገንምን?
7 እግዚአብሔር ሆይ፤ ምሕረትህን አሳየን፤
ማዳንህን ለግሰን::

°6 ወይም ይባርከዋል "9 ወይም ልዑል

84፥6 *በሚያልፉበት ጊዜ፤* ወደ ቤተ መቅደስ በሚሄዱበት ወቅት ማለት ነው:: *በልቅሶ ሸለቆ፤* "ማልቀስ" ወይም "የበለሳን ዛፍ" ማለት ነው፤ ቦታው የት እንደ ሆነ አይታወቅም፤ ምናልባት ዘይቤያዊ አነጋገር ሊሆንም ይችላል (23፥4 ይመ):: *የምንጭ መፍለቂያ፤* የሃይማኖት መንገደኞች ስለ ምንጩ ያላቸው ግምት አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ወደ መልካም ሁኔታ ይለውጥላቸዋል:: *የበልጉም ዝናብ፤* ቀጥሎ የሚመጣውን ዝናብ የሚያበስር ለስላሳ ካፊያ ነው (ኢል2፥23 ይመ):: *ሸለቆ፤* የዚህ የዕብራይስጥ ቃል ፍቺ የሚያመለክተው "በረከት" ወይም "ኩሬ" ስለመሆኑ እርግጠኛ መሆን ባይችልም ቃሉ ግን ሁለቱንም ሳያመለክት አይቀርም:: እግዚአብሔር ልባቸውን ወደ ጽዮን ለመለሱ መንገደኞች ከሚሰጠው በረከት የተነሣ የልቅሶ ሸለቆ የነበሩ ወደ ምስጋና ስፍራ ይለወጣሉ (2ዜና20፥26 ይመ):: የሲናን ምድረ በዳ አቋርጠው ወደ ተስፋዪቱ ምድር ወደ ከነዓን (78፥15-16፤ 105፥41፤ 114፥8 ይመ) እንደ ተጓዙት እንደ ቀድሞ አባቶቻቸውና ከእነርሱም በኋላ ከባቢሎን ምርኮ ነጻ ወጥተው ወደ ጽዮን እንደ ተመለሱት ልጆቻቸው (ኢሳ41፥17-20፤ 43፥19-20፤ 49፥10 ይመ) ሁሉ፣ ዛሬም የእግዚአብሔር ቅዱሳን ወደ ተስፋዪቱ አገራቸው ወደ ጽዮን በሚጓዙበት ጊዜ፣ የእግዚአብሔርን ቸርነትና የተትረፈረፈ በረከት አዲስ በሆነ መንገድ ይለማመዳሉ::

84፥7 *ከኀይል ወደ ኀይል፤* ድካምና መከራ የበዛበት ጕዞ ቢሆንም (ኢሳ40፥31 ይመ)፣ እግዚአብሔር ግን ብርታታቸው ይሆናል:: *ጽዮን፤* 9፥11 እና ማብ ይመ::

*84፥8-11፤* ስለ ንጉሥ የተደረገ ጸሎት ነው፤ መዝሙረኛው ከዚህ ቀደም በቤተ መቅደሱ ውስጥ ወደ ነበረው አገልግሎት ለመመለስ ታላቅ ናፍቆት እንዳለው የሚገነዘበው እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም ያለውን ንጉሥ ሲባርክ ብቻ እንደ ሆነ የሚገልጽ ክፍል ነው::

84፥8 *የሰራዊት አምላክ ሆይ ... የያዕቆብ አምላክ፤* ሁሉን ቻይ የሆንክ የያዕቆብ አምላክ ሆይ ለማለት ነው (59፥5 እና የ3፥7 ማብ ይመ):: *ያዕቆብ፤* እስራኤል ማለት ነው (ዘፍ32፥28 ይመ)::

84፥9 *ጋሻችን፤* አንዳንድ ቅጆች፣ "ልዑል እግዚአብሔር" ይላሉ:: በዚህ ክፍል ግን ቃሉ በኢየሩሳሌም ያለውን ንጉሥ ያመለክታል (የ3፥3 ማብ ይመ):: *የቀባኸውን፤* በምድር ላይ የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚገዛ የእግዚአብሔር (ከዳዊት ዘር የሆነ) እንደራሴ ማለት ነው፤ የ2፥2 ማብ ይመ::

84፥10 *ደጅ መቆም፤* ምናልባት መዝሙረኛው በቤተ መቅደስ ውስጥ ያለው መደበኛ አገልግሎት ይህ ሳይሆን አይቀርም (የመዝሙረኛውን ዝቅተኛ/የአገልግሎት ቦታ ያሳያል፤ 2ነገ22፥4 ይመ):: *በክፉዎች ድንኳን ከመቀመጥ፤* የጽዮንን አምላክ የሚያከብሩ ሰዎች የሚኖሩትን ኑሮ ያልተካፈለ ለማለት ነው::

84፥11 *ፀሓይ፤* ታላቁ የሕይወት ብርሃን ምንጭ ነው (የ27፥1 ማብ ይመ):: *ጋሻ፤* የ3፥3 ማብ ይመ:: *በቅንነት የሚሄዱትን፤* 15፥2 እና የዘፍ17፥1 ማብ ይመ::

*84፥12፤* የመዝሙሩ ማጠቃለያ ነው (40፥4 ይመ)::

*መዝ85፤* በክፉና በአስጨናቂ ጊዜ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ምሕረት ማድረጉን እንዳይተው በኅብረት የቀረበ ጸሎት ነው:: ብዙዎች እንደሚናገሩት ከሆነ ከቍ1-3 ያለው ክፍል የሚያመለክተው፣ ከምርኮ ስለ መመለስ ሲሆን በክፍሉ ውስጥ የተጠቀሰውን መከራ ያዩ ሰዎች እንዳሉ ነህምያና ሚልክያስ ጠቅሰዋል:: በቍ12 ላይ እንደ ተመለከተው ድርቅ ምድሪቱን ፍጹም ያራቈተ ሲሆን፣ ይህም በሐጌ ዘመን እግዚአብሔር ሕዝቡን የቀጣበት ድርቅ ሳይሆን አይቀርም (ሐጌ1፥5-11 ይመ):: ክርስቲያኖች ይህንን መዝሙር በገና ወራት ለቅዳሴ አገልግሎት ይጠቀሙበታል:: መዝሙሩ እያንዳንዳቸው ሰባት መስመሮች (በዕብራይስጡ ቅጅ ላይ ማለት ነው) ባሉት በሁለት ክፍል ይከፈላል፤ (1) ስለ ጸሎት (ቍ1-7) እና (2) ስለ ማረጋገጫ ቃል (ቍ8-13) ነው:: እያንዳንዱ ክፍል ባለ ሦስት መስመር አንጓ የያዘና ከዚህም አንጓ ተከትሎ የሚመጣ ሌላ ባለ አራት መስመር አንጓ ያለ ሲሆን ተከትሎ የሚመጣው ሁለተኛው አንጓ ለመጀመሪያው አንጓ መልስ የሚሰጥ ነው:: ይኸውም ቍ1-3 ምሕረት እንደ ተሰጠ የሚናገር ሲሆን፣ ቍ8-9 ምሕረት በቅርብ ጊዜ ውስጥ እንደሚመጣ ይናገራል:: ቍ4-7 ጸሎት የሚያቀርብ ሲሆን ቍ10-13 ጸሎቱ የሚሰማ መሆኑን ይገልጻል:: አራቱም አንጓዎች የእግዚአብሔርን ስም ይጠቅሳሉ::

85 *ርእስ ለመዘምራን አለቃ፤* የመዝሙር 4 ርእስ ማብ ይመ:: *የቆሬ ልጆች፤* የመዝ42 ርእስ ማብ ይመ::

*85፥1-7፤* የእግዚአብሔር ምሕረት እንዲታደስ የቀረበ ጸሎት ነው::

*85፥1-3፤* እስራኤል ከዚህ ቀደም እግዚአብሔር ያደረገላትን ምሕረትና ይቅርታ በማስታወስ ጸሎቷን ትጀምራለች (ይህም ከምርኮ ስለ መመለሳቸው የሚያወሳ ሊሆን ይችላል)::

85፥1 *የያዕቆብንም ምርኮ መለስህ፤* "ያዕቆብን ከምርኮ መለስህ" እንደ ማለት ነው (ኤር29፥14 ይመ):: *ያዕቆብ፤* እስራኤል ማለት ነው (ዘፍ32፥28 ይመ)::

85፥3 *መዓት ... ቍጣ፤* ቍ5 እና የ2፥5 ማብ ይመ::

85፥4-7 ጸሎቱና በሕዝቡም ላይ የደረሰው መከራ የሚያመለክተው፣ እግዚአብሔር ደስ ያልተሰኘ መሆኑን ነው:: በጸሎቱ ውስጥ ሕዝቡ ንስሓ ስለ መግባቱ የሚያመለክት ምንም ነገር የለም፤ ይሁን እንጂ ከቍ3 ላይ መገንዘብ እንደሚቻለው (ምናልባትም ከቍ8 ላይ) ሕዝቡ ንስሓ ሳይገባ አልቀረም::

85፥7 *ምሕረት፤* ቍ10 እና የ6፥4 ማብ ይመ::

*85፥8-13፤* እግዚአብሔር ለጸሎታቸው መልስ እንደሚሰጥ ማስተማመኛ የሰጠው በአንድ ካህን ወይም ሌዋዊ ምናልባትም

8 እግዚአብሔር አምላክ የሚናገረውን
እሰማለሁ፤
ለሕዝቡ፣ ለቅዱሳኑ ሰላምን ይናገራልና፤
ዳሩ ግን ወደ ከንቱ ምግባራቸው
አይመለሱ።
9 ክብሩ በምድራችን ይኖር ዘንድ፣
ማዳኑ ለሚፈሩት በእርግጥ ቅርብ ነው።
10 ምሕረትና ታማኝነት ተገናኙ፤
ጽድቅና ሰላም ተቃቀፉ።
11 ታማኝነት ከምድር በቀለች፤
ጽድቅም ከሰማይ ተመለከተች።
12 እግዚአብሔር በጎ ነገር ይለግሳል፤
ምድራችንም ፍሬዋን ትሰጣለች።
13 ጽድቅ በፊቱ ይሄዳል፤
ለአረማመዱም መንገድ ያዘጋጃል።

## መዝሙር 86

### የመከራ ጊዜ ጸሎት

የዳዊት ጸሎት

1 እግዚአብሔር ሆይ፤ ጆሮህን ወደ እኔ
ጣል፤ ስማኝም፤
እኔ ድኻና ችግረኛ ነኝና።
2 ለአንተ የተለየሁ ሰው ነኝና ነፍሴን
ጠብቃት፤
አንተ አምላኬ ሆይ፤
በአንተ የታመነብህን ባሪያህን አድን።
3 ጌታ ሆይ፤ ማረኝ፤
ቀኑን ሙሉ ወደ አንተ እጮኻለሁና።
4 የባሪያህን ነፍስ ደስ አሰኛት፤
ጌታ ሆይ፤ ነፍሴን ወደ አንተ አነሣለሁና።
5 ጌታ ሆይ፤ አንተ ቸርና ይቅር ባይ ነህ፤
ለሚጠሩህ ሁሉ ምሕረትህ ወሰን
የለውም።
6 እግዚአብሔር ሆይ፤ ጸሎቴን አድምጥ፤
የልመናዬን ጩኸት ስማ።
7 አንተ ስለምትመልስልኝ፣
በመከራዬ ቀን ወደ አንተ እጣራለሁ።
8 ጌታ ሆይ፤ ከአማልክት መካከል እንደ
አንተ ያለ የለም፤
ከአንተም ሥራ ጋር የሚወዳደር
ሥራ የለም።

27፥1
85፥8 ዘሌ26፥6፤ ምሳ26፥11፤27፥22፤ ኢሳ60፥17፤ዮሐ 14፥27፤2ተሰ3፥16
85፥9 ዘፀ29፥43፤ መዝ27፥1፤ኢሳ43፥3፤ 45፥8፤46፥13፤51፥5፤ 56፥1፤60፥19፤62፥11 ፤ሐጌ2፥9፤ዘካ2፥5
85፥10 መዝ72፥2-3፤89፥14፤115፥1፤ምሳ 3፥3፤ኢሳ32፥17
85፥11 ኢሳ45፥8
85፥12 ዘሌ26፥4፤ መዝ67፥6፤84፥11፤ዘካ 8፥12፤ያዕ1፥17
86፥1 መዝ17፥6
86፥2 መዝ25፥2፤ 31፥14
86፥3 መዝ4፥1፤ 9፥13፤57፥1፤88፥9
86፥4 መዝ46፥5፤ 143፥8
86፥5 ዘፀ34፥6፤ነህ 9፥17፤መዝ103፥8፤14 5፥8፤ኢል2፥13፤ ዮና4፥2
86፥6 መዝ5፥2፤ 17፥1
86፥7 ኢዮ22፥27፤መዝ3፥4፤4፥3፤27፥5፤50፥15፤80፥18፤ 91፥15፤94፥13፤ኢሳ30፥19፤58፥9፤65፥24፤ዕን3፥16፤ዘካ13፥19
86፥8 ዘፀ8፥10፤ኢዮ21፥22፤መዝ18፥31

ከቆሬ ልጆች በአንዱ በኩል (የ12፥5-6 ማብ እንዲሁም 2ዜና 20፥14 ይመ)።

*85፥8-9፤* እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደ ገና እንደሚባርክ የተሰጠ ማረጋገጫ ነው።

85፥8 *እሰማለሁ፤* የመዝሙሩ ተናጋሪ እግዚአብሔር የሚሰጠው ቃል እንዳለ ይጠብቃል። *ሰላምን ይናገራል፤* ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣው ቃል ካህናት የሚሰጡትን የቡራኬ ቃል መልክ ሳይዝ አልቀረም (ዘኍ6፥22-26 ይመ)። *ቅዱሳኑ፤* የ4፥3 ማብ ይመ። *ወደ ከንቱ ምግባራቸው አይመለሱም፤* እግዚአብሔር በሕዝቡ ደስ አለመሰኘቱን በድጋሚ የሚያመለክት ነው። ይህንን ሐረግ፣ "በስንፍና የሚመላለሱ" ብሎ መተርጐም ይቻላል። *ከንቱ፤* የሥነ ምግባር ጕድለትን ያሳያል።

85፥9 *ክብሩ፤* የእግዚአብሔር የማዳን ሥራ በተገለጠባቸው ስፍራዎች ሁሉ ክብሩም ይገለጣል (57፥5:11፤ 72፥18-19፤ ዘፀ 14፥4: 17-18፤ ዘኍ14፥22፤ ኢሳ40፥5፤ 44፥23፤ 66፥19፤ ሕዝ 39፥21 ይመ)።

*85፥10-13፤* እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለው ምሕረት በቃል ኪዳኑ ላይ የተመሠረተ ሲሆን፣ እግዚአብሔር ታማኝና ጻድቅ መሆኑ ቃል ኪዳኑን የሚጠብቅ አምላክ ነው፤ ይህም ለሕዝቡ ደኅንነት ዋስትና ነው።

85፥10 *ምሕረትና ታማኝነት... ጽድቅና ሰላም፤* በዚህ ቦታ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለው በጎ አመለካከት በሰውኛ አገላለጽ ቀርቦአል (የ23፥6 ማብ ይመ)፤ የእነዚህ ነገሮች መገናኘትና መተቃቀፍ በዚህ መልክ መገለጹ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኙት ምስላዊ አገላለጾች ሁሉ ይልቅ፣ እግዚአብሔር ለቃል ኪዳን ሕዝቡ ያደረገውን በጎነት እጅግ ውብ በሆነ ምስላዊ አገላለጽ የሚያሳዩ ናቸው። *ጽድቅ፤* ቍ11:13 እንዲሁም የ4፥1 ማብ ይመ። *ሰላም፤* የዘኍ6፥26 ማብ ይመ።

85፥11 *ታማኝነት ... በቀለች፤* ለሰው ልጅ በረከት የሚሆን አዲስ ተክል ከምድር እንደሚበቅል ሁሉ ማለት ነው። *ጽድቅም ከሰማይ ተመለከተች፤* በጎነት ከሰማይ አበራ ለማለት ነው። የእስራኤል ጽዋ ሞልቶ እስኪፈስ ድረስ የእግዚአብሔር የኪዳኑ በረከት ከሰማይና ከምድር ተትረፍርፎ ይፈልቃል።

85፥12 *በጎ ነገር፤* 31፥19 እና ማብ ይመ።

85፥13 *ጽድቅ በፊቱ ይሄዳል፤* መዝሙረኛው ጽድቅን አሁንም የሚገልጸው በሰውኛ ዘይቤ ነው። ጽድቅ እንደ አንድ መሪ በመሆን፣ በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ቀድማ እየሄደች የእግዚአብሔርን መንገድና ፈቃድ ታስታውቃለች፤ ጽድቅ እግዚአብሔር ለቃል ኪዳን ሕዝቡ ያለውን ፍጹም ታማኝነት የሚገልጥበት ነው (የ4፥1 ማብ ይመ)።

*መዝ86፤* እግዚአብሔርን የማይፈሩ እብሪተኞች፣ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ጥቃት ባደረሱ ጊዜ የቀረበ ጸሎት ነው። ጸሓፊው ዳዊት ይሁን ወይም አይሁን ምንም የሚታወቅ ነገር ባይኖርም፣ መዝሙረኛው ራሱን የእግዚአብሔር፣ "አገልጋይ" አድርጐ ማቅረቡ (ቍ2) በንጉሣዊያን ቤተ ሰብ መካከል ያለውን ስፍራና ከእግዚአብሔርም ጋር ያለውን ልዩ ግንኙነት ይጠቁማል (2ሳሙ7፥5:8 እና የመዝ18 ርእስ ማብ ይመ)። እንግዲህ ጠላቶቹ በራሱ መንግሥት ውስጥ ያሉና በእግዚአብሔር የተቀባ መሆኑን የማይቀበሉ ወይም በዓለም ላይ ያለውን ተቀባይነት መና ለማስቀረት ሌት ተቀን የሚሯሯጡ የውጭ መንግሥታት ሊሆኑ ይችላሉ። መዝሙሩ ከአምስት አንጓዎች የተዋቀረ ሲሆን እኩኩያዊ የሆነ የቍጥር አቀማመጥ አለው (አራት አንጓ፣ሦስት አንጓ፣ ሦስት አንጓ፣ ሦስት አንጓ፣ አራት አንጓ)። የመዝሙሩ ጸሓፊ የጌታ አገልጋይ መሆኑን በመጀመሪያውና በመጨረሻው አንጓ ላይ ያስታወቀ ሲሆን፣ አንጓዎቹ የእግዚአብሔርን ምሕረትና አዳኝነት የሚጠይቅ ልመናም ይዘዋል። መካከለኛው አንጓ (ቍ8-10) እግዚአብሔርን ተወዳዳሪ እንደሌለው፣ ብቸኛ አምላክ እንደ ሆነና የዓለምም ሕዝቦች አንድ ቀን በፊቱ ወድቀው እንደሚያመልኩት አድርጎ ያቀርባል፤ ቍ9 የመዝሙሩ ማእከላዊ (መካከለኛ) ነው (የ6፥6 ማብ ይመ)።

86 *ርእስ ጸሎት፤* የመዝ17 ርእስ ማብ ይመ፤ እንዲሁም የ72፥20 ማብ ይመ። *የዳዊት፤* በሦስተኛው የመዝሙር መጽሐፍ ውስጥ (መዝ73-89) በዳዊት ስም የተጠቀሰው ይህ መዝሙር ብቻ ነው። መዝሙሩ ከቆሬ ልጆች መዝሙር ጋር የተመደበበት ምክንያት ምናልባት የመዝሙሩን ቅደም ተከተል ሥርዐት ያስያዙት ሰዎች በቍ9 እና በመዝ 87፥4 መካከል የመሪ ሐሳብ ትስስር እንዳለ ስለ ተገነዘቡ ሊሆን ይችላል።

*86፥1-4፤* እግዚአብሔር የአገልጋዩን ሕይወት እንዲጠብቅና ምሕረትም እንዲያደርግለት የቀረበ የመግቢያ ጸሎት ነው።

86፥1 *ድኻና ችግረኛ፤* 35፥10 እንዲሁም 34፥6 እና ማብ ይመ።

86፥2 *የታመነብህን፤* ይህ ቃል፣ "ሃሲድ" ከሚለው የዕብራይስጥ ቃል የተተረጐመ ነው (የ4፥3 ማብ ይመ)። *አንተ አምላኬ ሆይ፤* እግዚአብሔር ዳዊትን አገልጋዩ አድርጐ መረጠው እንጂ፣ ዳዊት እግዚአብሔርን አልመረጠውም (1ሳሙ13፥14፤ 15፥28፤ 16፥12፤ 2ሳሙ7፥8 ይመ)። ዳዊት በእግዚአብሔር ላይ ያለው እምነትና ለእግዚአብሔርም ቃል ያለው ታዛዥነት ሆነ ተብሎ ጐን ለጐን ቀርበዋል። *ባሪያህን፤* ቍ4:16 እንዲሁም መግቢያውን ይመ።

86፥4 *ነፍሴን፤* የ6፥3 ማብ ይመ።

*86፥5-7፤* ዳዊት፣ እግዚአብሔር ከምሕረቱና ከፍቅሩ የተነሣ ለጸሎቱ መልስ እንደሚሰጠው ስለ ተረዳ መከራ በደረሰበት ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ልመናውን አቀረበ።

86፥5 *ምሕረትህ፤* ቍ13:15 እንዲሁም የ6፥4 ማብ ይመ።

*86፥8-10፤* ዳዊት ልመናውን ያቀረበው ብቸኛና እውነተኛ ወደ ሆነ አምላክ ነው። በታላቅ ልዕልና እርሱ ያደረጋቸውን ያደረገ፣ "ከአማልክት" መካከል ማንም የለም (115፥3-7፤ 135፥13-17 ይመ)፤ ዳዊት ወደዚህ አምላክ የሚጮኸውና ሕዝቦችም ሁሉ

9ጌታ ሆይ፤ አንተ የሠራሃቸው ሕዝቦች
ሁሉ፣
መጥተው በፊትህ ይሰግዳሉ፤
ለስምህም ክብር ይሰጣሉ፤
10አንተ ታላቅ ነህና፤ ታምራትም ትሠራለህ፤
አንተ ብቻህን አምላክ ነህ።

11እግዚአብሔር ሆይ፤ መንገድህን
አስተምረኝ፤
በእውነትህም እሄዳለሁ፤
ስምህን እፈራ ዘንድ፣
ያልተከፋፈለ ልብ ስጠኝ።
12ጌታ አምላኬ ሆይ፤ በፍጹም ልቤ
አመሰግንሃለሁ፤
ስምህንም ለዘላለም አከብራለሁ፤
13ለእኔ ያሳየሃት ምሕረት ታላቅ ናትና፤
ነፍሴንም ከሲኦል[ሀ] ጥልቀት አውጥተሃል።

14አምላክ ሆይ፤ እብሪተኞች ተነሥተውብኛል፤
የዐመፀኞችም ጉባኤ ነፍሴን ይሿታል፤
አንተንም ከምንም አልቈጠሩም።
15ጌታ ሆይ፤ አንተ ግን መሐሪና ርኅሩኅ
አምላክ ነህ፤
ለቍጣ የዘገየህ፣ ምሕረትህና ታማኝነትህ
የበዛ።
16ወደ እኔ ተመልከት፤ ማረኝም፤
ለባሪያህ ኀይልህን ስጥ፤
የሴት ባሪያህንም[ለ] ልጅ አድን።
17የሚጠሉኝ አይተው ያፍሩ ዘንድ፣
የበጎነትህን ምልክት አሳየኝ፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ
ረድተኸኛልና፤ አጽናንተኸኛልም።

86፥9 መዝ65፥2፤ 66፥4፤ኢሳ19፥21፤ 27፥13፤43፥7፤44፥23 ፤49፥7፤ዘካ8፥20-22፤ 14፥16፤ራእ15፥4
86፥10 ዘፀ3፥20፤ዘዳ 6፥4፤2ሳሙ7፥22፤ መዝ48፥1፤71፥17፤72 ፥18፤ኢሳ43፥10፤ማር 12፥29፤1ቆሮ8፥4
86፥11ዘፀ33፥13፤ዘዳ 6፥24፤1ሳሙ12፥23፤ መዝ25፥5፤26፥3፤ኤር 24፥7፤32፥39፤ሕዝ 11፥19፤1ቆሮ7፥35
86፥12 መዝ9፥1
86፥13 መዝ16፥10 ፤34፥4፤49፥15፤56፥1 3፤116፥8
86፥14 መዝ54፥3
86፥15 ቍ5፤ዘፀ 34፥6፤ዘኍ14፥18፤ነህ 9፥17፤መዝ51፥1፤103 ፥8፤111፥4፤116፥5፤ 145፥8፤ኢዩ2፥13
86፥16 መዝ6፥4፤ 9፥13፤18፥1፤116፥16
86፥17 ዘፀ3፥12፤ ማቴ24፥3፤ዮሐ2፥11
87፥1 መዝ48፥1
87፥2 መዝ2፥6
87፥3 መዝ46፥4
87፥4 2ሳሙ8፥11 ኢዮ9፥13፤መዝ45፥12

## መዝሙር 87

### ጽዮን የሕዝቦች እናት

የቆሬ ልጆች መዝሙር፤ ማሕሌት

1መሠረቱን በተቀደሱ ተራሮች አቆመ፤
2እግዚአብሔር ከያዕቆብ ማደሪያዎች
ሁሉ ይልቅ፣
የጽዮንን ደጆች ይወዳል።
3የእግዚአብሔር ከተማ ሆይ፤
ስለ አንቺ ክቡር የሆነ ነገር እንዲህ
ተብሎ ይነገራል፤ ሴላ
4"ከሚያውቁኝ መካከል፣
ረዓብንና[ሐ] ባቢሎንን እጠቅሳለሁ፤
እነሆ፤ ፍልስጥኤምና ጢሮስ ከኢትዮጵያ
ጋር፣
'ይህ[መ] ሰው በዚያ ነው የተወለደው'

[ሀ]13 አንዳንዶች *መቃብር* ይላሉ።
[ለ]16 *ታማኝ ወንድ ልጅህን* የሚሉ አሉ።
[ሐ]4 የግብፅ ቅኔያዊ ስያሜ ነው።
[መ]4 *ወይም ረዓብ ባቢሎን፣ ፍልስጥኤምና ኢትዮጵያ* ለማለት ነው።

አንድ ቀን በፊቱ ወድቀው የሚያመልኩት ለዚህ ነው።

86፥9 *ሕዝቦች ሁሉ፤* የ46፥10 ማብ ይመ። የመዝሙሩ ማእከላዊ ቍጥር ሲሆን (የ6፥6 ማብ ይመ)፣ በመዝሙሩ ውስጥ እግዚአብሔር ልዑልና የዓለማትም ገዥ እንደ ሆነ የተነገረው በዚህ ቦታ ነው። *ክብር ይሰጣሉ፤* ዳዊት ክብር ለመስጠት ቃል እንደ ገባ ሁሉ እነርሱም እንዲሁ ያደርጋሉ (ቍ12)። *ስምህ፤* ቍ11-12 እንዲሁም የ5፥11 ማብ ይመ።

86፥10 *ታምራትም ትሠራለህ፤* የ9፥1 ማብ ይመ።

*86፥11-13፤* እግዚአብሔርን ለመምሰልና እርሱንም ለማመስገን የተገባ ቃል ነው።

86፥11 *አስተምረኝ ... ስጠኝ፤* እግዚአብሔር ዳዊትን ከጠላቶቹ ቢያድነው፣ ነገር ግን ለገዛ መንገዱ አሳልፎ ቢሰጠው ምን ዋጋ አለው? ዳዊት በእግዚአብሔር ላይ ያለው እምነት ፍጹም ነው፤ ደግሞም ለእግዚአብሔር ያለው ታማኝነት ብርቱ ነው፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ከውጭ ጠላቶቹ ብቻ ሳይሆን በውስጡ ካለው ከንቱነት እንዲታደገው ይጸልያል (25፥5፤51፥7:10 ይመ)። የእግዚአብሔርን በጎነትና እርዳታ ለማግኘት ተስፋ የሚያደርግ በእግዚአብሔር የሚታመን ሰው ነው፤ ለእግዚአብሔር የገባውን ቃል በእርግጥ የሚፈጽም እንዲህ ያለ ሰው ነው (ቍ12)። *ያልተከፋፈለ ልብ፤* ሕዝ11፥19 እንዲሁም 1ዜና12፥33፤ 1ቆሮ7፥35 ይመ። *ልብ፤* የ4፥7 ማብ ይመ።

*86፥12፤* እግዚአብሔርን ለማመስገን የተገባ ቃል ነው (የ7፥17 ማብ ይመ)።

*86፥13፤* ዳዊት ለጸለየው ጸሎት መልስ አገኘ (የ3፥8 ማብ ይመ)። *ጥልቀት፤* የ30፥1 ማብ ይመ።

*86፥14-17፤* ማጠቃለያ ነው፤ ጸሎቱም ታድሶአል።

86፥14 *እብሪተኞች፤* የዕብራይስጡ ቃል ርኅራኄ የለሽነትን ያመለክታል። *አንተንም ከምንም አልቈጠሩም፤* ከእብሪተኝነታቸው የተነሣ ሰማያዊውን ጠረኛና የዳዊትን ተሟጋች ያቃልላሉ (የ10፥11 ማብ እንዲሁም ኤር20፥11 ይመ)።

*86፥15፤* ቍ5 ላይ ያለውን አሳብ መልሶ ያስተጋባል፤ ግን ደግሞ ከዘፀ 34፥6 ጋር ይመሳሰላል (የዘፀ 34፥6-7 ማብ ይመ)።

86፥16 *ኀይልን ስጥ፤* ክንድህን ስለ እኔ ዘረጋ ለማለት ነው። *የሴት ባሪያህንም ልጅ፤* ታማኝ አገልጋይህን አድን ማለት ነው፤ 116፥16 ይመ። አገልጋይህን ወይም ታማኝ ልጅህ ማለት ሊሆን ይችላል።

86፥17 *በጎነት፤* ብቃል ኪዳን ላይ የተዘረዘረውን በጎነት ማለት ነው (27፥13 እና ማብ ይመ)። *አይተው፤* አንተ በአጠገቤ እንደ ቆምክና የእኔም ረዳት እንደ ሆንክ ጠላቶቼ ይመልከቱ ማለት ነው (31፥19 እና ማብ ይመ)።

*መዝ87፤* ጽዮን "የእግዚአብሔር ከተማ" በመሆኗ ለእርሷ ክብር የተዘጋጀ የምስጋና መዝሙር ነው (ቍ3)፤ ይህች ከተማ በእግዚአብሔር የተወደደችና የመንግሥቱም መናገሻ ከተማ ናት (የ46፤ የ48፤ የ76 መግቢያን ይመ)። በጥንት የአይሁዶችና የክርስቲያን ምሁራን አስተያየት መሠረት ይህ መዝሙር በመዝሙር መጽሐፍ ውስጥ ካሉት መዝሙሮች ሁሉ የተለየ ባሕርይ አለው (ግን 47፥9 ይመ)፤ ምክንያቱም አንድ ቀን የዓለም ሕዝቦች የእስራኤል ሕዝብ ወዳጅ ሆነው በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ በጽዮን እንደሚሰበሰቡ አስቀድሞ ይናገራል፤ ይህም የሚሆነው በነቢያት መጽሐፍ ላይ በተጻፈው መሠረት ነው (ኢሳ 2፥2-4፤ 19፥19-25፤ 25፥6፤ 45፥14:22-24፤ 56፥6-8፤ 60፥3፤ 66፥23፤ ዳን7፥14፤ ሚክ4፥1-3፤ ዘካ8፥23፤ 14፥16 ይመ)፤ አንዳንዶች ይህ ትንቢት በኢሳይያስና በሚክያስ ዘመን እንደ ተፈጸመ አድርገው ሲናገሩ፣ ሌሎች ደግሞ ከባቢሎን ምርኮ በኋላ መፈጸሙን ይናገራሉ። ይህ መዝሙር በዚህ መልክ የተተረጐመ ከሆነ ስለ ጽዮን ከተዘመሩት ሌሎች መዝሙሮች ጋር በከፍተኛ ደረጃ የሚነጻጸር ነው (መዝ 46፤48፤76፤125፤ 129፤137 ይመ)። የመዝሙሩ ዋና ሐሳብ ቍ4 ላይ ይገኛል። የዚህ መዝሙር ታሪካዊ ትርጓሜ የዕብራይስጡን የሰዋስው አገነባብ በሚገባ ጠብቆ ካለማቆየት የመነጨ ሊሆን ይችላል። መዝሙሩ በዚህ መልክ ከታየ፣ የመዝሙሩ መሪ ሐሳብ እግዚአብሔር ለጽዮን ያለውን ልዩ ፍቅር ከሚያወድሱ ከሌሎች መዝሙሮች ጋር የሚዛመድ ነው፤ ጽዮን ለታሪካዊ ጠላቶቿ ንክሻ አልፋ የተሰጠችበት ጊዜ ነበር (ቍ4 ማብ ይመ)።

87 *ርእስ የቆሬ ልጆች፤* የመዝ 42 ርእስ ማብ ይመ። *መዝሙር፤* የመዝ30 ርእስ ማብ ይመ።

87፥1 *መሠረቱን፤* የጽዮንን መሠረት ያቆመና (ኢሳ14፥32 ይመ) ቤት መቅደሱንም የሥልጣኑ መንበር ያደረገ ራሱ እግዚአብሔር ነው። *ተራሮች፤* በዕብራይስጡ ቅጅ ይህ ቃል በብዙ ቍጥር የተጠቀሰ ሲሆን የእግዚአብሔር ዙፋን የተቀመጠበት ተራራ የተቀደሰና የተከበረ መሆኑን ያስገነዝባል (48፥2 እና ማብ ይመ)።

87፥2 *ከ... ይልቅ ... ይወዳል፤* እግዚአብሔር የመሠረታትና ሕዝቡንም ይገዛ ዘንድ ዙፋኑን የተከለባት ጽዮን፣ በእስራኤል ከሚገኙ ከተሞች ሁሉ ይልቅ የተወደደች ናት (9፥11፤ 78፥68፤ 132፥12-14 ይመ)። *ያዕቆብ፤* እስራኤል ማለት ነው (ዘፍ32፥28 ይመ)።

87፥4 *እጠቅሳለሁ ... ይህ ሰው በዚያ ነው የተወለደው፤* እግዚአብሔር የንጉሣዊ ከተማው ተወላጅና ዜጎች አድርጎ በንጉሣዊ መዝገቡ ላይ ይመዘግባቸዋል (የ9፥5፤ 51፥1፤ 69፥28

ይላሉ።"

5በእርግጥም ስለ ጽዮን፣
"ይህም ያም ሰው በእርሷ ውስጥ
ተወለዱ፤
ልዑልም ራሱ ያጸናታል" ይባላል።
6እግዚአብሔር ሕዝቡን ሲመዘግብ፣
"ይህ ሰው የተወለደው በዚያ ነው" ብሎ
ይጽፋል። ሴላ
7የሚያዜሙም መሣሪያ የሚጫወቱም፣
"ምንጬ ሁሉ በአንቺ ውስጥ ይገኛል"
ይላሉ።

## መዝሙር 88

ሰቆቃ

*ማኅሌት፤ የቆሬ ልጆች መዝሙር፤ ለመዘምራን አለቃ፤ በማኸላት የሚዘመር፤ የይዝራኤላዊው የኤማን ትምህርት*

1አዳኜ የሆንህ ስምላክ እግዚአብሔር ሆይ፤
በቀንና በሌሊት በፊትህ አጮኻለሁ።
2ጸሎቴ በፊትህ ትድረስ፤
ጆሮህንም ወደ ጩኸቴ አዘንብል፤
3ነፍሴ በመከራ ተሞልታለችና፤
ሕይወቴም ወደ ሲኦል[1] ተቃርባለች።

4ወደ ጉድጓድ ከሚወርዱት ጋር
ተቈጠርሁ፤
ዐቅምም አጣሁ።
5በሙታን መካከል እንደ ተጣሉ፣
ተገድለው በመቃብር ውስጥ እንደ
ተጋደሙ፣
አንተ ከእንግዲህ እንደማታስባቸው፣
ከእጅህም ወጥተው እንደ ተወገዱ
ሆንሁ።
6በዐዘቅት ጥልቀት ውስጥ ጣልኸኝ፤
በጨለማ ጉድጓድ ውስጥ ከተትኸኝ።
7የቍጣህ ክብደት በላዬ ዐርፎአል፤
በማዕበልህም ሁሉ አጥለቅልቀኸኛል። ሴላ
8የሚቀርቡኝ ባልንጀሮቼን ከእኔ አራቅህ፤
እንዲጸየፉኝም አደረግህ፤
ተከብቤአለሁ፤ ማምለጥም አልችል፤
9ዐይኖቼም በሐዘን ፈዘዙ።
እግዚአብሔር ሆይ፤ ዘወትር ወደ አንተ
እጣራለሁ፤
እጆቼንም ወደ አንተ ዘረጋሁ።

[1]3 *መቃብር የሚሉ አሉ።*

183፥7፤ኢሳ19፥25፤ ኢል3፥4
87፥6 ዘፀ32፥32፤ መዝ69፥28፤ኢሳ 4፥3፤ሚል3፥16
87፥7 መዝ36፥9፤ 149፥3
88፥1 መዝ3፥4፤22፥2 ፤51፥14፤ሉቃ18፥7
88፥3 ኢዮ33፥22፤ መዝ6፥3፤25፥17
88፥4 መዝ18፥1፤ 31፥12
88፥5 መዝ31፥22
88፥6 መዝ30፥1፤ 69፥15፤ሰቆ3፥55፤ዮና 2፥3
88፥7 መዝ7፥11፤ 42፥7
88፥8 ኢዮ3፥23፤ 19፥13፤መዝ31፥11፤ ኤር32፥2፤33፥1
88፥9 ኢዮ11፥13፤ መዝ5፥2፤38፥10፤ 143፥6

ማብ ይመ)፤ እነርሱም የዜግነት መብት ስላላቸው የበረከቱ ተካፋዮችና ቀስትናም ያላቸው ሰዎች ይሆናሉ። *ረዓብ፤* በሌላ ስፍራ ከጥልቁ የሚወጣውን አውሬ ያመለክታል (89፥10 እና የ32፥6፤ የኢዮ9፥13 ማብ ይመ)። በዚህ ቦታ ግን በኢሳ 30፥7 ላይ እንደ ተጠቀሰው ሁሉ ግብፅን ያመለክታል (ማብ ይመ)። በዚህ ክፍል የተዘረዘሩት መንግሥታት የአሕዛብ መንግሥታትን ሁሉ ይወክላሉ። በተለምዶ እንደሚተረጐመው ከሆነ መዝሙሩ ለረጅም ጊዜ የእግዚአብሔር ጠላቶች የነበሩ ሕዝቦች ተለውጠው የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጐች እንደሚሆኑ ይተነብያል (ኢሳ 19፥21 ይመ)። በዚህ ቦታ ግን እግዚአብሔር እርሱን የቃል ኪዳን አምላካቸው አድርገው የተቀበሉትን ሁሉ በጥንቃቄ እንደሚመዘግባቸውና (ሆሴ6፥3) በንጉሣዊ ከተማውም ውስጥ እንደ ዜጐች አድርጐ እንደሚጠብቃቸው የሚናገር ይመስላል (ቍ5 ይመ)። ሕዝቡን ሁሉ በጥንቃቄ መመዝገቡን በመግለጽም በሕዝቡ ላይ አደጋ የሚያደርስ ማናቸውም መንግሥት በኀላፊነት የሚጠየቅ መሆኑ (ኢሳ14፥28-32) ያስጠነቅቃል (105፥15 ይመ)።

87፥5 *ይህም ያም፤* በተበተኑበት አገር ሁሉ ቢሆኑም ለማለት ነው። *ልዑል፤* የዘፍ14፥19 ማብ ይመ።

87፥7 *ምንጩ ሁሉ፤* ደስ የሚያሰኛቸው ሁሉ በእግዚአብሔር ከተማ ይገኛሉ፤ ሐረጉ፣ "የደስታን ወንዝ" ከሚለው ጋር ሳይመሳሰል አይቀርም (36፥8)፤ ይህ ወንዝ፣ "የእግዚአብሔርን ከተማ ደስ" የሚያሰኝ ነው (46፥4)፤ የጥቅሶቹን ማብ ይመ። "ምንጮቼ" የሚለው ቃል የአንድን ነገር መገኛ የሚያመለክት ተምሳሌታዊ አነጋገር ነው፤ አባባሉም እኛ ሁላችን ከአንተ ተወልደናል እንደ ማለት ነው።

*መዝ88፤* ከጥልቁ የተሰማ ጩኸት ሲሆን ሕይወቱ በሙሉ ተሟጦ እንዳለቀ፣ የሲኦልን ዕጣ ለመቀበል እንደ ተቃረበና በሞትም አፋፍ ላይ እንዳለ የሆነ ሰው ያቀረበው ጸሎት ነው። ዘመኑን በሙሉ በታላቅ መከራ ውስጥ ያሳለፈ በመሆኑ እርሱ የሚያውቀው የእግዚአብሔርን የጀርባ እጅ (የእግዚአብሔርን "ቍጣ" ቍ7) ብቻ ነው፤ በዚህም ምክንያት እጅግ ቅርቤ ናቸው የሚላቸው ወዳጆቹ እንኳን፣ ተላላፊ የቆዳ በሽታ አለብህ በማለት ጥለውት ሸሹ (ቍ8 ይመ)። ከመዝሙረኛው ከናፍርት ላይ የተስፋ ጭላንጭል ከቶ አይታይም (በብዙ የመዝሙረኛው ጸሎት ላይ ተመሳሳይ ነገር ይታያል)፤ ምክንያቱም በመጨረሻ ላይ የተናገረው ቃል "ጨለማ ብቻ ጓደኛዬ" ነው በማለት ነው። ይሁን እንጂ ጸሎቱ፣ "የምታድነኝ አምላክ እግዚአብሔር ሆይ" በማለት ይጀምራል። የእግዚአብሔር ሰዎች አንዳንድ ጊዜ በማያልቅ መከራ ውስጥ ቢያልፉም (73፥14 ይመ) በእግዚአብሔር አዳኝነት ላይ ተስፋቸውን ምን ጊዜም እንደሚጥሉ መዝሙረኛው ያስታውሳል። ከዕብራይስጡ አወቃቀር አኳያ ሲታይ በባለ ሦስት አራት መስመር አንጓዎች (ቍ3-5፡6-9፡9-12) በባለ ሁለት ሦስት ጸሎቶች ተቀንብበዋል፤ በዚህ ላይ መዝሙረኛው የሕይወት ዘመኑን ሁሉ በመከራና በሥቃይ ውስጥ ያሳለፈ መሆኑን በምሬት የገለጸበት ባለ አራት መስመር አንጓ በተጨማሪ ቀርቦአል።

88 *ርእስ፤* መዝሙሩ ሁለት የተለያዩ ወጐችን (ባሕሎችን) የሚወክል በመሆኑ ጥንድ ርእስ ሊሰጠው ይችላል። *መዝሙር፤* የመዝ30 ርእስ ማብ ይመ። *የቆሬ ልጆች፤* የመዝ42 ርእስ ማብ ይመ። *ለመዘምራን አለቃ፤* የመዝ4 ርእስ ማብ ይመ። *ትምህርት፤* የመዝ32 ርእስ ማብ ይመ። *ኤርማን፤* የመዝ39 ርእስ ማብ ይመ። *ይዝራኤላዊው፤* ከይሁዳ ልጆች አንዱ የሆነውን ዛራን ያመለክታል። ከዛራ ልጆች መካከል (1ዜና2፥6 ይመ) ሁለቱ ኤማንና ኤታን (መዝ89 ርእስ ይመ) ይባላሉ። ነገሩ እንዲህ ከሆነ የርእሱ ችግር በዚህ ሥፍራ የተጠቀሱትን የይሁዳ ልጆችና የቆሬ ልጆች የመዘምራን መሪዎች የነበሩትን ኤማንና ኤታንን (የመዝ 39 ርእስ ማብ ይመ) ባለ መለየት ላይ የተመሠረተ ነው።

*88፥1-2፤* አዳኝ ለሆነ አምላክ በመግቢያ ላይ የቀረበ አቤቱታ ነው።

*88፥3-5፤* በሞትና በሕይወት መካከል ያለ ሰው የተናገረው ነገር ነው። መዝሙረኛው ለሞት ተቃርቦ እንደ ነበር ወይም ተመሳሳይ መከራ ደርሶበት እንደ ነበር ምንም ማወቅ አይቻልም።

88፥3 *ነፍሴ፤* የ6፥3 ማብ ይመ።

88፥4 *ጉድጓድ፤* የ30፥1 ማብ ይመ።

88፥5 *ከእንግዲህ እንደማታስባቸው፤* ከዚህ ሕይወት አንጻር ስንመለከተው ሞት ሰውን ከእግዚአብሔር ክብካቤ ይለያል፤ ሰው ከሞተ በኋላ የእግዚአብሔርን ማዳን ሊያይና እግዚአብሔርም ሊያስታውሰው አይችልም (25፥7፤ 74፥2፤ 106፥4 ይመ)፤ ጸሓፊው ጨለማ በሆነ ሁኔታ ውስጥ መውደቁን በግልጽ አስቀምጦታል (የ6፥5 ማብ ይመ)።

*88፥6-9፤* ጸሓፊው አምላክ ሆይ ይህን ሁሉ ያደረስክብኝ አንተ ነህ ይላል። መዝሙረኛው የእግዚአብሔር እጅ በሁኔታው ውስጥ እንዳለ እንጂ (ሩት1፥20-21፤ አሞ3፥6 ይመ) ምክንያቱን አያውቅም (ቍ14 ይመ)። አዳኙና አምላኩ የቍጣና የመዓት ፊት ስላሳየው ሐዘኑ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ተባብሶአል፤ ነገር ግን ጨለማና ምስጢር የሆነበትን ነገር ግልጽ ለማድረግ ጥረት ሲያደርግ አይታይም፤ ሆኖም ሊያደርግ የሚችለው ችግሩን አዳኙና አምላኩ ወደ ሆነው ጌታ ማቅረብ ብቻ በመሆኑ አቤቱታውን ወደዚሁ ጌታ ያቀርባል።

88፥6 *በዐዘቅት ጥልቀት ... በጨለማ ጉድጓድ፤* የ30፥1 ማብ ይመ።

88፥7 *ቍጣህ፤* ቍ16 እንዲሁም የ2፥5 ማብ ይመ። *በማዕበልህም ሁሉ፤* የ32፥6 ማብ ይመ።

88፥8 *የሚቀርቡኝ ባልንጀሮቼ፤* ቍ18 እና የ31፥11-12 ማብ ይመ።

88፥9 *ዐይኖቼም ... ፈዘዙ፤* የ6፥7 ማብ ይመ።

*88፥9-12፤* መዝሙረኛው ወደ፣ "ተረሳች ምድር" (የቍ5

[10]ድንቅ ሥራህን ለሙታን ታሳያለህን?
የሙታንስ መናፍስት ተነሥተው
ያመሰግኑሃልን?
ሴላ
[11]ምሕረትህ በመቃብር ውስጥ፣
ታማኝነትህስ እንጦርጦስ[m]
ይነገራልን?
[12]ድንቅ ሥራህ በጨለማ ስፍራ፣
ጽድቅህስ በመረሳት ምድር
ትታወቃለችን?
[13]እግዚአብሔር ሆይ፤ እኔ ግን ትረዳኝ
ዘንድ ወደ አንተ እጮኻለሁ፤
በጧትም ጸሎቴን በፊትህ አደርሳለሁ::
[14]እግዚአብሔር ሆይ፤ ለምን ታርቀኛለህ?
ፊትህንስ ከእኔ ለምን ትሰውራለህ?
[15]እኔ ከልጅነቴ ጀምሮ ችግረኛና ለሞት
የተቃረብሁ ነበርሁ፤
መዓትህ አሠቃየኝ፤ ግራም ተጋባሁ::
[16]ቍጣህ በላዬ ላይ ተከነበለ፤
መዓትህም አጠፋኝ::
[17]ቀኑን ሙሉ እንደ ጐርፍ ከበቡኝ፤
በአንድነትም ዙሪያዬን አጥረው
ያዙኝ::
[18]ወዳጄንና ባልንጀራዬን ከእኔ አራቅህ፤
ጓደኛዬ ጨለማ ብቻ ሆኖ ቀረ::

88፥10 መዝ6፥5
88፥11 መዝ30፥9
88፥13 መዝ5፥3፤ 30፥2፤55፥17፤ 119፥147
88፥14 መዝ13፥1፤ 43፥2
88፥15 ኢዮ6፥4፤ 18፥11፤መዝ9፥12፤12 9፥1፤ኤር22፥21፤ሕዝ 16፥22፤ሆሴ2፥15፤ 2ቆሮ4፥8
88፥16 ኢዮ6፥4፤ መዝ7፥11
88፥17 መዝ124፥4
88፥18 ቍ8፤መዝ 38፥11
89፥1 መዝ36፥5፤ 40፥10፤59፥16
89፥2 መዝ36፥5
89፥4 2ሳሙ7፥12-16፤1ነገ8፥16፤መዝ13 2፥11-12፤ኢሳ9፥7፤ ሕዝ37፥24-25፤ ማቴ1፥1፤ሉቃ1፥33
89፥5 መዝ1፥5፤ 19፥1
89፥6 ዘፍ1፥26፤ዘፀ 9፥14፤መዝ18፥31፤11 3፥5

## መዝሙር 89
## መዝሙርና ለእግዚአብሔር ታማኝነት የቀረበ ጸሎት

የይዝራኤላዊው የኤታን ትምህርት

[1]ስለ እግዚአብሔር ምሕረት ለዘለዓለም
እዘምራለሁ፤
በአፌም ታማኝነትህን ከትውልድ እስከ
ትውልድ እገልጻለሁ::
[2]ምሕረትህን ለዘላለም እንደምትመሠርት፣
ታማኝነትህንም በሰማይ እንደምታጸና
እናገራለሁና::
[3]አንተም እንዲህ ብለሃል፤ "ከመረጥሁት
ጋር ኪዳን ገብቻለሁ፤
ለባሪያዬ ለዳዊት ምያለሁ፤
[4]'ዘርህን ለዘላለም እተክላለሁ፤
ዙፋንህንም ከትውልድ እስከ ትውልድ
አጸናለሁ::' "
ሴላ
[5]እግዚአብሔር ሆይ፤ ሰማያት ድንቅ
ሥራህን፣
ታማኝነትህንም በቅዱሳን ጉባኤ
መካከል ያወድሳሉ፤
[6]በላይ በሰማያት ከእግዚአብሔር ጋር
ማን ሊስተካከል ይችላል?
ከሰማያውያን ፍጥረታትስ መካከል

[m]11 በዕብራይስጥ አባዶን ማለት ነው፤ የመውደሚያ ስፍራ ነው::

ማብ ይመ) ሰጥሞ ከመቅረቱ በፊት እግዚአብሔር እንዲታደገው አቤቱታውን ያቀርባል::

88፥10:12 *ድንቅ ሥራህን፤* እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚያ ደርገውን የማዳን ሥራ ያመለክታል (የ9፥1 ማብ ይመ)::

88፥10 *ተነሥተው፤* በሙታን ዓለም ያሉ ማለት ነው (ትንሣኤን የሚያገኙትን አያመለክትም)፤ ኢሳ14፥9 ይመ::

88፥11 *ምሕረትህ ... ታማኝነትህ፤* ፍቅርህና ታማኝነትህ ለማ ለት ነው (የ36፥5 እና የ3፥7 ማብ ይመ):: *ምሕረትህ፤* የ6፥4 ማብ ይመ::

88፥12 *ድንቅ ሥራህ፤* የ71፥24 ማብ ይመ::

*88፥13-14፤* የመዝጊያ ጸሎት ነው::

88፥14 *ለምን፤* የ6፥3 ማብ ይመ (በመዝሙሩ መግቢያ ላይ "ትምህርተ መለከት" የሚለውን ይመ):: *ፊትህንስ ... ትሰውራለህ፤* የ13፥1 ማብ ይመ::

*88፥15-18፤* ለመዝሙረኛው መከራ እንግዳ ነገር አይደ ለም፤ ሕይወቱን በሙሉ ከእግዚአብሔር ዘንድ መከራን ሲቀበል ኖሮአል::

*መዝ89፤* የዳዊት ሥርወ መንግሥት በመውደቁ የተለቀሰ ለቅሶና ወደ ቀድሞውም እንዲመለስ የተጸለየ ጸሎት ነው:: ይህ አሳዛኝ ታሪክ (በቍ38 ላይ በከፊል ተጠቅሶአል) መራራ በመሆኑ ፍጹም የማይሸከሙት ነው፤ ታማኝና ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ እርሱ የቀባውን ሰው ወግድ ብሎ ተወው፤ የሕዝቦችም መዘባበቻ አደረገው፤ በዚህም ከዳዊት ጋር ያደረገውን ቃል ኪዳን ያፈረሰ ይመስላል፤ ስለዚህ መዝሙረኛው የዋይታ ሰውና የጠላቶቹም መፈንጫ ሆነ (ቍ38-45):: ድርጊቱ የተፈጸመው ከክርስቶስ ልደት በፊት በ597 (2ነገ24፥8-17 ይመ) ላይ ሲሆን፣ ወቅቱም የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር ኢየሩሳሌምን አጥፍቶ ንጉሥ ዮአኪ ንን ወደ ምርኮ በወሰደ ጊዜ ሳይሆን አይቀርም:: እንደ መዝ44 ሁሉ (የዚህን መዝሙር መግቢያ ይመ) ለዚህም መዝሙር ጸሎት መሠረትና መደምደሚያ ሊጥል ይችላል:: ከቍ1-4 የመዝሙሩ መግቢያ ሲሆን ቍ1-2 የእግዚአብሔርን ፍቅርና ታማኝነት ምልክት ሲገልጽ ቍ3-4 ደግሞ እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር ያደረገውን ቃል ኪዳን ይናገራል:: እነዚህ ሁለት ዐቢይ ሐሳቦች በሚያስደንቅ ሁኔታ በቅደም ተከተል ተብራርተው ተቀምጠዋል፤ ይኸውም ከቍ5-18 ስለ እግዚአብሔር ፍቅርና ታማኝነት የሚና ገር ሲሆን፣ ከቍ19-37 ደግሞ እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር ስለ ገባው ቃል ኪዳን ይናገራል:: በዚህ መኻል ግን ደስታ ወደ ሐዘን ድንገት ሲለወጥ ይታያል፤ ከዚያም መዝሙረኛው እግዚአብሔር የተቀባውን ባሪያውን እንዴት አሽቀንጥሮ እንደጣለው በዝርዝር ይናገራል (ቍ38-45):: መዝሙረኛው ትዕግሥት ባጣ እና በተጣ ደፈ ሁኔታ ወደ እግዚአብሔር በመምጣት እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር የገባውን ኪዳን አንድ ጊዜ እንዲያስብ ይጸልያል (ቍ46-51):: ቍ52 የዚህ መዝሙር መደምደሚያ ሳይሆን የሦስተኛው መጽሐፍ መደምደሚያ ነው::

89 *ርእስ፤ ትምህርት፤* የመዝ32 ርእስ ማብ ይመ:: *ኤታን፤ ኤዶታም፤* (የመዝ39 ርእስ ማብ ይመ) ለማለት ነው:: የሕዝቡ አፈ ቀላጤ በመሆን ይህን መራራ ጸሎት ያደረሰው አንድ ሌዋዊ ስለ መሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም (ምናልባትም የኤዶታም ዘር ሊሆን ይችላል):: *ይዝራኤላዊው፤* የ88 ርእስ ማብ ይመ::

*89፥1-2፤* የእግዚአብሔር ፍቅርና ታማኝነት የተወደሰበት ክፍል ነው::

89፥1 *ምሕረት ... ታማኝነትህን፤* ቍ2:33:49 ይመ፤ ይህም ፍቅርና ታማኝነት ለማለት ነው (ቍ14 ይመ)፤ የ36፥5 ማብ ይመ:: *ታማኝነትህን፤* ቍ2:14:24:28:33:49 ይመ፤ እንዲ ሁም የ6፥4 ማብ ይመ:: እግዚአብሔር ፍቅሩንና ታማኝነቱን ከዳዊት ቤት ላይ በማንሣቱ የዳዊትን ቤት ቸል አለ (ቍ38-45 ይመ):: ጸሐፊው እነዚህን ቃላት ሰባት ጊዜ ደጋግሞአቸዋል (በቍ14 ላይ ግን የዕብራይስጡ ቅጅ፣ "ታማኝነት" ከሚለው ጋር የሚቀራረብ ሌላ ቃል ይጠቀማል)::

89፥2 *በሰማይ፤* የእግዚአብሔር ፍቅርና ታማኝነት በብ ርቱዎችና በታላላቆች ጉባኤም ውስጥ የጸና ነው (ቍ 5-8 ይመ)::

*89፥3-4፤* እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር ያደረገው ቃል ኪዳን የተወደሰበት ቦታ ነው (2ሳሙ7፥8-10 ይመ)::

89፥3 *ለባሪያዬ፤* ቍ20:39:50 ይመ:: በዚህ ቦታ የማዕረግ ስም ነው (የ78፥70 ማብ ይመ)::

*89፥5-8፤* የእግዚአብሔር ታማኝነትና የሚያስፈራው ኀይሉ በሰማይ ካሉት ኀይላት ሁሉ ልዩ ያደርገዋል፤ የሰማይ አካላትም እርሱን የሚተካከል እንደ ሌለ ተረድተው በምስጋና ያከብሩታል::

89፥5 *ሰማያት፤* ሕያዋን የሆኑ የሰማይ ፍጥረታትን ሁሉ ያጠቃልላል:: *ድንቅ ሥራህን፤* የእግዚአብሔርን የመፍጠርና የመ ቤዠት ሥራ ያመለክታል (የ9፥1 ማብ ይመ):: *በቅዱሳን ጉባኤ፤* በሰማይ ያለ የቅዱሳን መለኮታዊ ጉባኤን ያሳያል (ቍ7 እንዲ ሁም የ82፥1 ማብ ይመ)::

89፥6 *ከሰማያውያን ፍጥረታትስ፤* ቃል በቃል ሲተረጐም "የእግዚአብሔር ልጆች" ማለት ነው (29፥1 እና ማብ ይመ)::

ማን *እግዚአብሔርን* ይመስለዋል?
7እግዚአብሔር በቅዱሳን ጉባኤ መካከል በጣም
የሚፈራ፣
በዙሪያውም ካሉት ሁሉ በላይ እጅግ
የሚከበር ነው::
8የሰራዊት አምላክ *እግዚአብሔር* ሆይ፤
እንደ አንተ ያለ ማን ነው?
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ አንተ ኀያል ነህ፤
ታማኝነትህም ከብቦሃል::
9የባሕርን ቍጣ ትቈጣጠራለህ፤
ሞገዱም ሲነሣ ጸጥ ታደርገዋለህ::
10አንተ ረዓብን የተሰየፈ ያህል
አደቀቅሸው፤
በብርቱ ክንድህም ጠላቶችህን
በተንሃቸው::
11ሰማያት የአንተ ናቸው፤ ምድርም የአንተ
ናት፤
ዓለምንና በውስጧ ያለውን ሁሉ አንተ
መሠረትህ::
12ሰሜንንና ደቡብን የፈጠርህ አንተ ነህ፤
ታቦርና አርሞንዔም በስምህ ሐሤት
ያደርጋሉ::
13አንተ ክንደ ብርቱ ነህ፤
እጅህ ኀያል ናት፤ ቀኝ እጅህም ከፍ ከፍ
ያለች ናት::
14ጽድቅና ፍትሕ የዙፋንህ መሠረቶች
ናቸው፤
ምሕረትና ታማኝነት በፊትህ ይሄዳሉ::
15*እግዚአብሔር* ሆይ፤ እልልታን
የሚያውቅ፣
በፊትህም ብርሃን የሚሄድ ሕዝብ ምስጉን
ነው::
16ቀኑን ሙሉ በስምህ ደስ ይላቸዋል፤
በጽድቅህም ሐሤት ያደርጋሉ፤

89፥7 ኢዮ5፥1፤መዝ 47፥2፤111፥1
89፥8 መዝ71፥19፤ ኢሳ6፥3
89፥9 መዝ65፥7
89፥10 ኢዮ9፥13፤ መዝ59፥11፤68፥1፤ 92፥9
89፥11 ዘፍ1፥1፤ዘዳ 10፥14፤1ዜና29፥11፤ መዝ24፥1፤115፥16
89፥12 ዘዳ3፥8፤ 4፥48፤ኢሱ19፥22፤ መዝ98፥8
89፥13 ኢሱ4፥24
89፥14 መዝ85፥10-11፤97፥2
89፥15 መዝ1፥1፤ 44፥3
89፥16 መዝ30፥4፤ 105፥3
89፥17 ቍ24፤መዝ 18፥1፤75፥10፤92፥10 ፤112፥9፤148፥14
89፥18 መዝ18፥2፤ 47፥9፤ኢሳ16፥5፤ 33፥17:22
89፥20 ዘፀ29፥7፤ 1ሳሙ2፥35፤2ሳሙ22 ፥51፤1ነገ1፥39፤መዝ 78፥70፤ሐሥ13፥22
89፥21 ቍ13፤መዝ 18፥35
89፥22 መሳ3፥15፤ 2ሳሙ7፥10
89፥23 2ሳሙ7፥9፤ መዝ18፥40
89፥24 2ሳሙ7፥15
89፥25 መዝ72፥8
89፥26 2ሳሙ7፥14 ፤22፥47፤መዝ62፥2፤ ኤር3፥4፤ዕብ1፥5
89፥27 ዘኍ24፥7፤ መዝ2፥6፤ቈላ1፥18፤ ራእ1፥5፤19፥16
89፥28 ቍ33-34፤ ኢሳ55፥3

17አንተ የብርታታቸው ክብር ነህና፤
በሞገስህም ቀንዳችንን[ሀ] ከፍ ከፍ
አደረግህ::
18ጋሻችን[ለ] *የእግዚአብሔር* ነውና፤
ንጉሣችንም የራሱ የእስራኤል ቅዱስ
ነው::
19በዚያን ጊዜ በራእይ ተናገርህ፤
ታማኝ ሕዝብህንም እንዲህ አልህ፤
"ኀያሉን ሰው ሥልጣን አጐናጸፍሁት፤
ከሕዝብ መካከል የተመረጠውንም ከፍ
ከፍ አደረግሁት::
20ባሪያዬን ዳዊትን አገኘሁት፤
በተቀደሰው ዘይቴም ቀባሁት::
21እጄ ይደግፈዋል፤
ክንዴም ያበረታዋል::
22በጠላት አይበለጥም፤
ክፉ ሰውም አይበግረውም::
23ባላንጣዎቹን በፊቱ አደቅቃቸዋለሁ፤
ጠላቶቹንም እቀጠቅጣለሁ::
24ታማኝነቴና ምሕረቴ ከእርሱ ጋር
ይሆናል፤
በስሜም ቀንዱ ከፍ ከፍ ይላል::
25እጁን በባሕር ላይ፣
ቀኝ እጁንም በወንዞች ላይ አኖራለሁ::
26እርሱም፣ 'አንተ አባቴ ነህ፤
አምላኬና መዳኛ ዐለቴም ነህ' ብሎ
ይጠራኛል::
27እኔም ደግሞ በኵሬ አደርገዋለሁ፤
ከምድር ነገሥታትም በላይ ከፍ ይላል::
28ምሕረቴንም ለዘላለም ለእርሱ
እጠብቃለሁ፤
ከእርሱ ጋር የገባሁት ኪዳንም ጸንቶ
ይኖራል::

[ሀ] 17 የጥንካሬ ምልክት ነው::
[ለ] 18 ወይም ልዑል ማለት ነው::

89፥8 *የሰራዊት አምላክ፤* የ1ሳሙ1፥3 ማብ ይመ::

*89፥9-13፤* እግዚአብሔር ኀያል ፈጣሪ እንደሆነ የሚያመለክት ክፍል ሲሆን፣ ፍጥረታትም በእግዚአብሔር ሐሴት የሚያደርጉ መሆኑም ተገልጾአል::

*89፥9-10፤* ከጥንት ቅርብ ምሥራቃውያን የሥነ ፍጥረት አፈ ታሪክ ላይ በውሰት የተወሰደ ቅኔ ነው፤ በዚህ ቦታ እግዚአብሔር ለፍጥረታት የሰጠው ሥርዐት ጸንቶ እንዲቀጥል የጥንቱን ዐመፀኛ ውሃ በብርቱ ክንዱ ልክ ስላስገባ ለታላቅነቱ የቀረበ ምስጋና ነው (ዘፍ1፥6-10፤ የ65፥6-7፤ 74፥13-14 ማብ ይመ)::

89፥10 *ረዓብ፤* በጥንት አፈ ታሪክ ውስጥ የታወቀ የባሕር ውስጥ አውሬ ወይም ዘንዶ ሲሆን (የ32፥6፤ 87፥4 ማብ ይመ)፣ ምናልባት የሌዋታን ሌላው ስሙ ነው (74፥14፤ 104፥26 ይመ):: የዚህ ቍጥር የመጨረሻው ክፍል በሉቃ 1፥51 ላይ ሳይጠቀስ አይቀርም::

89፥12 *ሰሜንና ደቡብ፤* ሁለት ተራሮችን ያመለክታል፤ በዚህ ቦታ ከታቦርና ከአርሞኒዔም ተራሮች ጋር ይጓደናሉ፤ የመጀመሪያው "ሰሜን ተራራ" (ዘጬን 48፥2 እና ማብ ይመ)፣ ሁለተኛው ደግሞ አመና ተራራ (ማሕ4፥8 ይመ) ይባላሉ:: *ታቦር፤* የመሳ4፥6 ማብ ይመ:: *አርሞንዔም፤* የዘዳ3፥8 ማብ ይመ:: *በስምህ ሐሴት ያደርጋሉ፤* የ65፥13 ማብ ይመ:: *ስም፤* ቍ16:24 እና የ5፥11 ማብ ይመ::

*89፥14-18፤* እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል በጽድቅና በታማኝነት ይገዛል፤ ሕዝቡም በዚህ አገዛዙ ሐሴት ያደርጋል::

*89፥14፤* ጽድቅና ፍትሕ የእግዚአብሔር ዙፋን የመሠረት ድንጋዮች ናቸው፤ ፍቅርና ታማኝነት ደግሞ በሰውኛ አገላለጽ የቀረቡ ሲሆን የእግዚአብሔርን ሕያው ሥራና በሕዝቡም መካከል የሚያደርገውን ተሳትፎ የሚገልጹ ናቸው (የ23፥6 ማብ ይመ):: *ታማኝነት፤* ቍ16 እንዲሁም የ4፥1 ማብ ይመ::

89፥17 *ቀንዳችንን፤* ንጉሣችንን ለማለት ነው፤ ቍ18 ይመ::

89፥18 *የእስራኤል ቅዱስ፤* የኢሳ1፥4 ማብ ይመ::

*89፥19-29፤* በሕዝቡ ላይ የእግዚአብሔር እንደራሴ ይሆን ዘንድ፣ እግዚአብሔር ዳዊትን መምረጡን፣ ከእርሱም ጋር የዘላለም ቃል ኪዳን ማድረጉን የሚናገር ክፍል ነው:: የክፍሉ ሐሳብ በሁለት ቤት እያደገ የሚሄድ ነው፤ (1) መግቢያ (ቍ19) (2) ዳዊትን አገልጋዬ አድርጌ ቀብቼዋለሁ፤ ደግሞም እስከ መጨረሻ እጠብቀዋለሁ (ቍ20-21)፤ (3) ጠላቶቹን ሁሉ እሰባብራለሁ (ቍ22-23)፤ (4) መንግሥቱን አሰፋለሁ (ቍ24-25)፤ (5) ከነገሥታት ሁሉ በላይ አደርገዋለሁ (ቍ26-27)፤ (6) መንግሥቱም ለዘላለም ጸንቶ እንዲኖር አደርጋለሁ (ቍ28-29)፤ ይህ ቃል ኪዳን በኢየሱስ ክርስቶስ የዘላለም መንግሥት ተፈጽሞአል (ዮሐ12፥34 ይመ)::

89፥19 *ራእይ፤* ሳሙኤል (1ሳሙ16፥12 ይመ) እና/ወይም ናታን (2ሳሙ7፥4-16 ይመ) ያየውን ራእይ የሚያመለክት ነው:: *ታማኝ ሕዝብህንም፤* የ4፥3 ማብ ይመ::

89፥25 *ባሕር ... ወንዞች፤* የዳዊት ግዛት ከሜድትራኒያን ባሕር እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ይደርሳል (78፥8፤ 80፥11፤ እንዲሁም የ23፥31 ማብ ይመ):: ዳዊት የንጉሥ ልጅ (ቍ26 ይመ) እና እንደራሴ በመሆኑ የዳዊት አገዛዝ የእግዚአብሔር አገዛዝ ነጸብራቅ መሆኑን የሚገልጽ ምስላዊ አገላለጽ ጸሐፊው ይጠቀማል (ቍ9-10 እና ማብ ይመ፤ ቍ23 ከቍ10 ጋር ያነጻጽሩ)::

89፥27 *በኵሬ፤* በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ለንጉሥ ልጅ የሚሰጥ ከፍተኛ የክብር ስፍራ ነው (2፥7-12፤ 45፥6-9፤ 72፥8-11፤ 110 ይመ)፤ በመሆኑም በምድር ላይ ካሉት ነገሥታት ሁሉ የላቀና የተከበረ ነው (ራእ1፥5 ይመ)::

29 የዘር ሐረጉን ለዘላለም፣
ዙፋኑንም በሰማያት ዕድሜ ልክ አጸናለሁ።
30 "ልጆቹ ሕጌን ቢተዉ፣
ደንቤን ባይጠብቁ፣
31 ሥርዐቴን ቢጥሱ፣
ትእዛዜንም ባያከብሩ፣
32 ኀጢአታቸውን በበትር፣
በደላቸውን በጅራፍ እቀጣለሁ።
33 ምሕረቴን ግን ከእርሱ አላርቅም፤
ታማኝነቴንም አላጓድልበትም።
34 ኪዳኔን አላፈርስም፤
ከአፌ የወጣውንም አላጥፍም።
35 በአንድ ጊዜ በቅድስናዬ ምያለሁና፣
ዳዊትን አልዋሸውም።
36 የዘር ሐረጉ ለዘላለም፣
ዙፋኑም በፊቴ እንደ ፀሓይ ጸንቶ
ይኖራል፤
37 በሰማይ ታማኝ ምስክር ሆና
እንደምትኖረው፣
እንደ ጨረቃ እርሱ ለዘላለም
ይመሠረታል።" ሴላ

38 አሁን ግን ናቅኸው፤ ጣልኸውም፤
የቀባኸውንም እጅግ ተቈጣኸው።
39 ከባሪያህ ጋር የገባኸውን ኪዳን አፈረስህ፤
የክብር ዘውዱን ትቢያ ላይ ጥለህ
አቃለልኸው።
40 ቅጥሩን ሁሉ አፈራረስህ፤
ምሽጉንም ደመሰስህ።
41 ዐላፊ አግዳሚው ሁሉ ዘረፈው፤
ለጎረቤቶቹ መዘባበቻ ሆነ።
42 የጠላቶቹን ቀኝ እጅ ከፍ ከፍ አደረግህ፤
ባላንጣዎቹም ሁሉ ደስ አላቸው።
43 የሰይፉን ስለት አጠፍህ፤
በጦርነትም ጊዜ አልረዳኸውም።
44 ግርማዊነቱን አጠፋህበት፤
ዙፋኑንም ከዐፈር ደባለቅኸው።
45 የወጣትነት ዘመኑን አሳጠርኸው፤
ዕፍረትንም አከናነብኸው። ሴላ
46 እግዚአብሔር ሆይ፤ ይህ እስከ መቼ
ይሆናል? ራስህንስ ለዘላለም
ትሰውራለህን?
ቍጣህስ እንደ እሳት የሚነደው እስከ
መቼ ነው?
47 ዘመኔ ምን ያህል አጭር እንደ ሆነች
አስብ፤
የሰውን ልጆች እንዲያው ለከንቱ
ፈጠርሃቸው!
48 ሞትን ሳያይ ሕያው ሆኖ የሚቀር
ሰው አለን?
ራሱን ከሲኦል እጅ ማዳን የሚችል
ማን ነው? ሴላ።
49 ጌታ ሆይ፤ ለዳዊት በታማኝነትህ
የማልህለት፣
የቀድሞው ምሕረትህ የት አለ?
50 ጌታ ሆይ፤ ባሪያህ* እንዴት እንደ
ተፌዘበት፣
የብዙ ሰዎችንም ነቀፋ እንደ ታቀፍሁ
አስብ።
51 እግዚአብሔር ሆይ፤ ጠላቶችህ
የተሣለቁበትን፣
የቀባኸውን ሰው እርምጃ የነቀፉበትን
ሁኔታ አስብ።

52 እግዚአብሔር ለዘላለም ይባረክ፤
አሜን፤ አሜን።

## አራተኛ መጽሐፍ
## ከመዝሙር 90-106

## መዝሙር 90

### የሰው ልጅ ሕይወት

የእግዚአብሔር ሰው የሙሴ ጸሎት

1 እግዚአብሔር ሆይ፤
አንተ ከትውልድ እስከ ትውልድ
መጠጊያችን ሆንህልን።

89፥29 ቍ4:36
89፥32 2ሳሙ7፥14
89፥33 2ሳሙ7፥15
89፥34 ዘኍ23፥19
89፥36 ቍ4
89፥37 ኤር33፥20-21
89፥38 1ዜና28፥9፤ መዝ44፥9፤78፥59
89፥39 ሰቆ5፥16
89፥40 መዝ80፥12፤ኢሳ22፥5፤ሰቆ2፥2
89፥41 መሳ2፥14፤ መዝ44፥13
89፥42 መዝ13፥2፤ 80፥6
89፥43 መዝ44፥10
89፥45 መዝ39፥5፤ 44፥15፤109፥29
89፥46 መዝ79፥5
89፥47 ዘፍ47፥9፤ ኢዮ7፥7፤መዝ39፥5፤ 1ጴጥ1፥24
89፥48 ዘፍ5፥24፤ መዝ22፥29
89፥50 መዝ69፥19
89፥51 መዝ74፥10
89፥52 መዝ41፥13 ፤72፥19
90፥1 ዘዳ33፥27፤ ኤፌ2፥22፤ራእ21፥3

*50 ባሮችህ የሚሉ አሉ።

89፥29 *በሰማያት ዕድሜ ልክ፤* ቍ36-37 ይመ።

*89፥30-37፤* እግዚአብሔር ከዳዊትና ከሥርወ መንግሥቱ ጋር የገባው ቃል ኪዳን (በገጽ 18 ላይ "ብብሉይ ኪዳን የተደረጉ/ የተገቡ ዋና ዋና ኪዳኖች" የሚለውን ይመ) ዘላለማዊና በሁኔታዎችም ላይ ያልተመሠረተ ነው (ቍ28 ይመ)፤ ነገር ግን ከዘሮቹ አንዱ ለእግዚአብሔር ታማኝ ሳይሆን ቢቀር በግሉ ይቀጣል።

*89፥38-45፤* እግዚአብሔር የዳዊትን ልጅ ለጊዜው እንደ ናቀውና የገባውንም ቃል ኪዳን ችል ያለ መሆኑን የሚገልጽ ክፍል ነው (ቍ19-29 ይመ)።

*89፥46-51፤* እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር የገባውን ቃል ኪዳን በታማኝነት እንዲጠብቅ የቀረበ አቤቱታና ጸሎት ነው፤ መዝሙረኛው ዙሪያ ሁሉ ጨለማ በሆነበት ሰዓት ብቸኛው ተስፋ ይህ ነውና።

89፥46 *እስከ መቼ ...?* የ6፥3 ማብ እንዲሁም በመዝሙሩ መግቢያ ላይ፣ "ትምህርተ መለኮት" የሚለውን ይመ። *ቍጣ፤* የ2፥5 ማብ ይመ።

89፥50 *አስብ፤* ቍ47 ይመ።

*89፥52፤* የሦስተኛው መጽሐፍ አርታኢዎች፣ የመጽሐፉን ሐሳብ ያጠቃለሉበት አጭር የቡራኬ ቃል ነው (የ41፥13 ማብ ይመ)።

*መዝ90፤* በእግዚአብሔር የቍጣ በትርና የሞት ፍርድ ሥር የጕስቍልናን ኑሮ ለሚገፉ ባሪያዎቹ እግዚአብሔር እንዲራራላቸው፣ ፍቅሩን እንዲገልጽላቸው፣ የድካማቸውን ፍሬ እንዲባርክላቸውና በደስታም እንዲሞላቸው ዘላለማዊ ለሆነው አምላክ የቀረበ ጸሎት ነው። ከዚህ መዝሙር በስተቀር ቅዱስና ዘላለማዊ በሆነው አምላክ ፊት ሰው ምን ያህል ደካማና ምስኪን እንደሆነ ልዩ በሆነ መንገድ የሚገልጽ አንድም መዝሙር የለም። ይሁንና ረዳት የለሽና ተስፋ ቢስ እንደሆኑ ሰዎች አልቀረቡም፤ እውነተኛ የሆነ ሰው በደል በእርሱ ዘንድ እንዳለ ያውቃል፤ እምነት ያለው ሰው ደግሞ የእግዚአብሔርን፣ "ጽኑ ፍቅር" (ቍ14) የሚያውቅና በእምነትም አቤቱታውን ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርብ ነው። የእስራኤል ሕዝብ ወደ ተስፋዪቱ ምድር ለመግባት፣ "አስፈሪ በሆነ በዚያ ሰፊ በረሓ" (ዘዳ8፥15) ለ40 ዓመታት ያህል ሲንከራተቱ እንዲህ ያለ ጸሎት ማቅረባቸው የሚያስደንቅ አይደለም (ዘኍ14፥26-35 ይመ)። በእግዚአብሔር ቍጣ ሥር ያለውን የሰው ሁኔታ የሚገልጹ ሁለት አንጓዎች (ቍ3-6፡7-10) በሁለት ቤት በተቀናጁ ቍጥሮች የተቀነበቡ ሲሆን (ቍ1-2፡11-12)፣ በቅንብቡ ውስጥ ባሉት ሁለት አንጓዎች መካከል የአሳብ ልዩነት እንዳለ በንጽጽር ቀርቦአል፤ ይኸውም፡- (1) በዘመናት ሁሉ፣ "መኖሪያችን" የሆነው እግዚአብሔር (ቍ1)፣ የቍጣውን ብርታት አሳይቶናል (ቍ7)። (2) እግዚአብሔር የዘላለም አምላክ ነው (ቍ2)፤ የእኛ ዕድሜ ግን አጭር ነው (ቍ12)። ይህም የመዝሙሩ መደምደሚያ ወደ ሆነው ጸሎት ይወስዳል (ቍ13-17)።

90 *ርእስ፤ ጸሎት፤* የመዝ17 ርእስ ማብ ይመ። *የእግዚአብሔር ሰው፤* በብሉይ ኪዳን ሙሴን ጨምሮ (ኢሱ14፥6) ነቢያትን ለመግለጽ የሚያገለግል ሐረግ ነው (የ1ሳሙ2፥27 ማብ ይመ)።

90፥1 *መጠጊያችን፤* 91፥9 ይመ። የዕብራይስጡ ቃል፣ "መሸሸጊያ" (71፥3) የሚል ትርጕም አለው።

[2]ገና ተራሮች ሳይወለዱ፣
ምድርንና ዓለምን ከመፍጠርህ በፊት፣
አንተ ከዘላለም እስከ ዘላለም ስምባክ ነህ።
[3]ሰዎችን ወደ ዐፈር ትመልሳለህ፤
"የሰው ልጆች ሆይ፤ ወደ ቦታችሁ
ተመለሱ" ትላለህ፤
[4]ሺህ ዓመት በፊትህ፣
እንዳለፈችው እንደ ትናንት ቀን፣
እንደ ሌሊትም እርቦ ነውና።
[5]እንደ ጐርፍ ጠርገህ ስትወስዳቸው፣
እንደ ሕልም ይበናሉ፤
እንደ ማለዳ ሣር ታድሰው ይበቅላሉ፤
[6]ሣሩም ንጋት ላይ አቈጥቍጦ
ይለመልማል፤
ምሽት ላይ ጠውልጎ ይደርቃል።
[7]በቍጣህ አልቀናልና፤
በመዓትህም ደንግጠናል።
[8]በደላችንን በፊትህ፣
የተሰወረ ኀጢአታችንንም በገጽህ
ብርሃን ፊት አኖርህ።
[9]ዘመናችን ሁሉ በቍጣህ ዐልፎአልና፤
ዕድሜአችንንም በመቃተት እንጨርሳለን።
[10]የዕድሜአችን ዘመን ሰባ ዓመት፣
ቢበዛም ሰማንያ ነው፤
ከዚያ በላይ ከሆነም ድካምና መከራ
ብቻ ነው፤
ቶሎ ያልፋልና፤ እኛም ወዲያው
እንነጒዳለን።
[11]የቍጣህን ኀይል ማን ያውቃል?
መዓትህም የመፈራትህን ያህል
ታላቅ ነው።
[12]ጥበብን የተሞላ ልብ ይኖረን ዘንድ፣
ዕድሜያችንን መቍጠር አስተምረን።
[13]እግዚአብሔር ሆይ፤ ተመለስ፤ ይህ
እስከ መቼ ይሆናል?
ለአገልጋዮችህም ራራላቸው።
[14]በዘመናችን ሁሉ ደስ እንዲለን፣
ሐሤትም እንድናደርግ፣
ምሕረትህን በማለዳ አጥግበን።
[15]መከራ ባሳየኸን ዘመን መጠን፣
ክፉም ባየንባቸው ዓመታት ልክ
ደስ አሰኘን።
[16]ሥራህ ለአገልጋዮችህ፣
ክብርህም ለልጆቻቸው ይገለጥ።
[17]የጌታ የአምላካችን ሞገስ[a] በላያችን ይሁን፤
የእጆቻችንን ሥራ ፍሬያማ አድርግልን፤
አዎን፣ ፍሬያማ አድርግልን።

## መዝሙር 91

### የእግዚአብሔር ጥበቃ

[1]በልዑል መጠጊያ የሚኖር፣
ሁሉን በሚችል አምላክ[b] ጥላ ሥር
ያድራል።

90፥2 ዘፍ21፥33፤ ኢዮ10፥5፤15፥7፤ መዝ102፥24-27፤ምሳ 8፥23-26፤ኢሳ9፥6፤ 57፥15
90፥3 ዘፍ2፥7፤ኢዮ 7፥21፤34፥15፤ 1ቆሮ15፥47
90፥4 ኢዮ10፥5፤ 2ጴጥ3፥8
90፥5 ዘፍ19፥15
90፥6 ኢሳ40፥6-8፤ ማቴ6፥30፤ያዕ1፥10
90፥8 መዝ19፥12፤ 2ቆሮ4፥2፤ኤፌ5፥12፤ ዕብ4፥13
90፥9 መዝ78፥33
90፥10 2ሳሙ19፥35 ፤ኢዮ5፥7፤20፥8፤ 34፥15፤ኢሳ23፥15፡ 17፤ኤር25፥11
90፥11 መዝ7፥11፤ 76፥7
90፥12 ዘዳ32፥29፤ መዝ39፥4፤139፥16፤ ምሳ16፥9፤20፥24
90፥13 ዘዳ32፥36፤ መዝ6፥3
90፥14 መዝ5፥11፤ 31፥7፤77፥8፤103፥5፤ 107፥9፤143፥8፤ 145፥16፡19
90፥16 መዝ44፥1 ፤ዕን3፥2
90፥17 ኢሳ26፥12
91፥1 ዘዐ33፥22፤ መዝ63፥7፤ኢሳ49፥ 2፤ሰቆ4፥20

[a]17 *ውበት* ለማለት ነው።
[b]1 በዕብራይስጥ *ሻዳይ* ማለት ነው።

*90፥3-6፤* ሰው "ዐፈር ... ወደ ዐፈር" (ዘፍ3፥19) በተባለው የእግዚአብሔር የሞት ፍርድ ሥር ይኖራል (ዘፍ3፥19)።

*90፥4-5፤* በእግዚአብሔር ዘንድ አንድ ሺህ ዓመት በእን ቅልፍ ላይ ወዲያው እንዳለፈ እንደ ሌሊት ሰዓት ነው፤ እግዚአ ብሔር የሰውን ሕይወት፣ ሲነጋ በቅሎ ሊመሽሽ ሲል በከነዓናው ያን ሐሩር ፀሓይ ደርቆ እንዲረግፍ ያደርገዋል።

90፥4 *እንደ ሌሊትም እርቦ፤* የመሳ7፥19 ማብ ይመ።

*90፥7-10፤* እግዚአብሔር የሰውን የተሰወረ ኀጢአት እንዲ ታይና ጻድቅ ቍጣውንም እንዲገነዘቡ ያደርጋል፤ የሰዎች አጭሯ ዕድሜ ግን በመከራ የተሞላች ናት።

90፥7 *ቍጣህ ... በመዓትህ፤* ቍ9፡11 ይመ እንዲሁም የ2፥5 ማብ ይመ።

90፥8 *በገጽህ ብርሃን፤* በልብ ውስጥ የተሸሸገውንና የተደበቀውንም ምስጢር ወደ ብርሃን የሚያወጣውን የእግዚ አብሔርን ቅዱስ ብርሃን የሚያመለክት ነው።

90፥10 *ሰማንያ፤* በዕብራይስጥ የግጥም አጻጻፍ 70 ከተጻፈ በኋላ በሁለተኛው መስመር ላይ 80 ይጻፋል (የአሞ1፥3 ማብ ይመ)። *ቢበዛ፤* ቃል በቃል ሲተረጐም፣ "ትዕቢታቸው" ማለትም ሰዎች በዘመናቸው የሚመኩበት ነገር ማለት ነው፤ የዚህ ቃል መሠረታዊ ሐሳብ ጤንነታቸው፣ ደስታቸው፣ ሀብታቸው፣ ክብራ ቸው ሁሉ በመከራና በሐዘን የተዋጠ ይሆናል እንደ ማለት ነው። *መከራ፤* ወይም፣ "ባዶነት" ማለት ነው።

90፥11-12 *ማን ያውቃል? ... አስተምረን፤* የእግዚአብሔ ርን ቍጣ መለካት የቻለ ማንም ሰው የለም። ነገር ግን እያንዳንዱ ሰው ዘመኑ አጭር መሆኑን መገንዘብ አለበት፤ አለበ ለዚያ ግን ኀሊና ያጣ ወይም እግዚአብሔር የሰጠውን ኀላፊነት የዘነጋ ይሆናል (መዝ49፤ 73፥4-12 ይመ)።

90፥11 *የመፈራትህን ያህል፤* የዘፍ20፥11 ማብ ይመ።

90፥12 *ይኖረን ዘንድ፤* "መከር" እንዲኖረን ለማለት ነው። *ልብ፤* የ4፥7 ማብ ይመ።

*90፥13-17፤* እግዚአብሔር ለሕዝቡ እንዲራራ የቀረበ ጸሎት ነው፤ ከእርሱ ዘንድ ደስታና እልልታ ይገኛልና።

90፥13 *ተመለስ፤* ቃል በቃል ሲተረጐም፣ "ፊትህን አት መልስብን" ማለት ነው (ከቍ3 ጋር ያነጻጽሩ)። *እስከ መቼ፤* የ6፥3 ማብ ይመ።

90፥14 *በማለዳ፤* ከቍጣህ ጨለማ እንድናርፍ የፍቅርህ ማለዳ ይሁንልን ማለት ነው። ምናልባት ሙሴ (ርእስ ይመ) በተስፋዪቱ ምድር ስለ ተሰጠው ዕረፍት የጸለየው ጸሎት ሳይሆን አይቀርም (ዘዐ33፥14፤ ዘዳ12፥9 ይመ)። የጸሎቱን መልስ የሚያ ገኘው በትንሣኤ ወቅት ነው (ሮሜ5፥2-5፤ 8፥18፤ 2ቆሮ4፥16-18 ይመ)። *ምሕረትህን፤* የ6፥4 ማብ ይመ።

90፥16 *ሥራህ ... ክብርህም፤* ክቡር ሥራህን ማለት ነው (111፥3 እንዲሁም የ3፥7 ማብ ይመ)። ይህንን ሥራ አስመልክቶ የተሟላ መግለጫ ለማግኘት መዝ111 ይመ። *ለልጆቻቸው፤* ባለፈው ዘመን የነበረውን ትውልድ ማለት ነው (ቍ1)።

90፥17 *ሞገስ፤* ውበት ለማለት ነው፤ 27፥4 እና ማብ ይመ። *ፍሬያማ አድርግልን፤* ዋስትናችንና ተስፋችን አንተ ብቻ ነህ (ቍ1 ይመ)፤ ከንቱዎችና ጠፊዎች ብንሆንም ድካማችንን ፍሬያማ አድርግልን፣ ባርከልንም ማለት ነው።

*መዝ91፤* በእግዚአብሔር የሚታመኑ ሁሉ ጽኑ ዋስትና እንዳላቸው የሚያረጋግጥ ምስክርነት ነው። ይህ መዝሙር እግዚ አብሔርን ለማምለክ የመጡ ሰዎችን ለማበረታታት በቤተ መቅደስ ውስጥ በሚያገለግሉ ካህናት ወይም ሌዋውያን የተጻፈ ሳይሆን አይቀርም። ከቍ3-13 ያለው ሐሳብ "እግዚአብሔርን ማደሪያቸው" ወይም "መጠጊያቸው" (ቍ9፤ 90፥1 ይመ) ላደረጉ ሁሉ የሚውል በመሆኑ ዲያቢሎስ በቍ 11-12 ላይ ያለውን ሐሳብ ለኢየሱስ ተጠቅሞበታል (ማቴ 4፥6፤ ሉቃ 4፥10-11 ይመ)። ባወቃቀር ረገድ መዝሙሩ እያንዳንዳቸው ስምንት ቍጥር ባላቸው ሁለት ክፍሎች የተከፈለ ሲሆን የሁለተኛው ክፍል መግቢያ (ቍ9-11) የቍ1-2 ሐሳብን እንደ ገና መልሶ ያስተ ጋባል። ምንም እንኳን አንድ ሺህ የሚያህሉ ሰዎች ቢወድቁም (ቍ 7) በመጀመሪያው ክፍል አጋማሽ ላይ (ቍ 5-6) የእግዚ አብሔር ሰዎች ከአራት መጥፎ ጠላቶች እንደሚጠበቁ ዋስትና ተሰጥቶአቸዋል፤ በሁለተኛው ክፍል ደግሞ በአራት አስፈሪ አው ሬዎች ላይ በድል እንዲራመዱ ተገልጾአል (ቍ 13)። ቍ 14-16 የዋስትናውን ደረጃ ከመጨረሻው ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያደርሰዋል።

91፥1 *ልዑል፤* ቍ9 እንዲሁም የዘፍ14፥19 ማብ ይመ። *መጠጊያ፤* የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ለማለት ነው (27፥5፤ 31፥20፤ 23፥6፤ 27፥4 ይመ)፤ በዚያም የእግዚአብሔር ሰዎች ከእግዚ አብሔር ክንፎች በታች ከለላን ያገኛሉ (ቍ4፤ 61፥4 ይመ)። *ጥላ፤* የ17፥8 ማብ ይመ። *ሁሉን በሚችል አምላክ፤* በዕብራይስጥ

2 እግዚአብሔርን፣ “መጠጊያዬ፣ ምሽጌ፣
የምታመንብህ አምላኬ” እለዋለሁ።[T]
3 እርሱ ከአዳኝ ወጥመድ፣
ከአሰቃቂ ቸነፈር ያድንሃልና።
4 በላባዎቹ ይጋርድሃል፤
በክንፎቹ ሥር መሸሸጊያ ታገኛለህ፤
ታማኝነቱ ጋሻና መከታ ይሆንሃል።
5 የሌሊትን አስደንጋጭነት፣
በቀን የሚወረወረውንም ፍላጻ
አትፈራም፤
6 በጨለማ የሚያደባ ቸነፈር፣
በቀትር ረፍራፊውም አያሠጋህም።
7 በአጠገብህ ሺህ፣
በቀኝህም እሥር ሺህ ይወድቃል፤
ወደ አንተ ግን አይቀርብም።
8 በዐይንህ ብቻ ትመለከታለህ፤
የክፉዎችንም መቀጣት ታያለህ።

9 እግዚአብሔርን መሸሸጊያ፣
ልዑልንም መጠጊያህ አድርገሃልና፤
10 ክፉ ነገር አያገኝህም፤
መቅሠፍትም ወደ ድንኳንህ አይገባም፤
11 በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ፣
መላእክቱን ስለ አንተ ያዛቸዋልና።
12 እግርህ ከድንጋይ ጋር እንዳይጋጭ፣
በእጆቻቸው ወደ ላይ ያነሡሃል።
13 በአንበሳና በእፉኝት ላይ ትጫማለህ፤
ደቦሉን አንበሳና ዘንዶውን ትረግጣለህ።
14 “ወዶኛልና እታደገዋለሁ፤
ስሜን አውቆአልና እከልለዋለሁ።
15 ይጠራኛል፤ እመልስለታለሁ፤
በመከራው ጊዜ ከእርሱ ጋር እሆናለሁ፤
አድነዋለሁ፤ አከብረዋለሁ።
16 ረጅም ዕድሜን አጠግበዋለሁ፤
ማዳኔንም አሳየዋለሁ።”

91፥2 ቍ9፥2ሳሙ 22፥2፡3፤መዝ9፥9
91፥3 1ነገ8፥37፤ መዝ124፥7፤ምሳ6፥5
91፥4 ዘዳ32፥10፤ ሩት2፥12፤መዝ17፥8 ፤35፥2፤ኢሳ27፥3፤ 31፥5፤ዘካ12፥8
91፥5 ኢዮ5፥21
91፥8 መዝ37፥34፤ 58፥10
91፥10 ምሳ12፥21
91፥11 ዘፍ32፥1፤ መዝ34፥7፤ዕብ1፥14
91፥12 ማቴ4፥6፤ ሉቃ4፥10-11
91፥13 ዳን6፥22፤ ሉቃ10፥19

91፥15 1ሳሙ2፥30 ፤ዮሐ12፥26
91፥16 ዘዳ6፥2፤ መዝ21፥4፤50፥23
92፥1 መዝ9፥2፤ 27፥6፤135፥3፤147፥1
92፥2 መዝ55፥17
92፥3 1ሳሙ10፥5፤ ነህ12፥27፤መዝ33፥2፤ 71፥22፤81፥2
92፥4 መዝ5፥11፤ 8፥6፤27፥6፤111፥7፤ 143፥5
92፥5 ኢዮ36፥24፤ መዝ40፥5፤139፥17፤ ኢሳ28፥29፤31፥2፤ ሮሜ11፥33፤ራእ15፥3

## መዝሙር 92

### ጻድቅ ሰው ሲደሰት

በሰንበት ቀን የሚዘመር መዝሙር፤ ማኅሌት

1 እግዚአብሔርን ማመስገን መልካም ነው፤
ልዑል ሆይ፤ ለስምህ መዘመር
ጥሩ ነው፤
2 ምሕረትህን በማለዳ፣
ታማኝነትህንም በሌሊት ማወጅ
መልካም ነው፤
3 ዐሥር አውታር ባለው በገና፣
በመሰንቆም ቅኝት ታጅቦ ማወጅ
ጥሩ ነው።
4 እግዚአብሔር ሆይ፤ በሥራህ
ስለተደሰትሁ፣
ስለ እጅህ ሥራ በደስታ እዘምራለሁ።
5 እግዚአብሔር ሆይ፤ ሥራህ እንዴት
ታላቅ ነው!

[T]2 አንዳንድ ትርጕሞች ይላል ይላሉ።

ኤልሻዳይ ማለት ነው፤ ዘፍ17፥1 ይመ።

91፥3 *ከአዳኝ ወጥመድ፤* ከጠላት የሚወረወረውን ፍላጻ የሚያመለክት ተምሳሌት ነው። *ቸነፈር፤* እነዚህ ሁለት መቅሠፍቶች በቍ5-6 ላይ ተብራርተዋል።

91፥4 *በላባዎቹ፤* የ17፥8 ማብ ይመ።

91፥5 *አስደንጋጭነት፤* በ64፥1 ላይ እንደ ተጠቀሰው ቃሉ (“አስጨናቂ”) የሚያመለክተው ጠላት የሚያደርሰውን አደጋ ነው፤ ስለዚህ፣ “ፍላጻ” ከሚለው ቃል ጋር ተጣምሮ ቀርቦአል። ጠላት የሚያደርሰውን አደጋ የሚያመለክቱት እነዚህ ሁለት ቃላት “ቸነፈር” እና፣ “መቅሠፍት” ከሚሉት ቃላት ጋር (ቍ6) ጐን ለጐን የቀረቡ ሲሆን የበሽታና የሞት ምሳሌ ናቸው። *ሌሊት ... ቀን፤* በየትኛውም ጊዜ ማለትም በቀንም ሆነ በሌሊት፣ አደጋው ቢመጣ ምንም ነገር አይነካህም ማለት ነው፤ አደጋው የሚመጣበት ጊዜ ግን በውል አልተጠቀሰም።

91፥7 *ዐሥር ሺህ፤* በዕብራይስጡ የግጥም አጻጻፍ መሠረት አንድ ሺህ እና ዐሥር ሺህ በተጓዳኝ ስንኝ ተዋቅረው ቀርበዋል (የ90፥10፤ የአሞ1፥3 ማብ ይመ)፤ ከ1ሳሙ18፥17 ጋር ያነጻጽሩ።

91፥9 *መጠጊያ፤* 90፥1 እና ማብ ይመ።

*91፥11-12፤* በማቴ4፥6 እና በሉቃ4፥10-11 ላይ በሰይጣን ተጠቅሶአል።

91፥11 *መላእክቱን፤* የ34፥7 ማብ ይመ።

91፥12 *እግርህ ከድንጋይ፤* ድንጋያማ በሆነው በከነዓን መንገድ ማለት ነው (ምሳ3፥23 ይመ)።

91፥13 *በአንበሳና በእፉኝት ... ደቦሉን አንበሳና ዘንዶውን፤* አንበሳውንና መርዘኛውን እባብ አስመልክቶ የቀረበው ሐሳብ በቍ5-6 ላይ ከተጠቀሰው ሐሳብ ጋር የሚነጻጸር ሲሆን ዝርዝሩን የተሟላ ያደርገዋል (አሞ5፥19 ይመ)።

*91፥14-16፤* ደራሲው ትንቢታዊ በሆነ ንግግር (መግቢያውን ይመ) እግዚአብሔርን ለሚወዱና በእርሱም ለሚታመኑ ሁሉ የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል የማይሻር መሆኑን ያረጋግጣል።

91፥14 *እታደገዋለሁ፤* ቃል በቃል ሲተረጐም፣ “ከፍተኛ ወደ ሆነና ዋስትናም ወዳለው እወስደዋለሁ” ማለት ነው። *ስሜን፤* የ5፥11 ማብ ይመ።

*መዝ92፤* በጽድቅ የተሞላውን የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚያወድስ የምስጋና መዝሙር ነው። ስለ ጻድቃን መለምለም ምስክርነት የሚሰጠው ሐረግ ማለትም፣ “በእግዚአብሔር ቤት ተተክለው” (ቍ13) የሚለው ከመዝ91 ጋር የሚያስተሳስረው ሲሆን፣ በእግዚአብሔር ጻድቅ አገዛዝ፣ ምን ያህል ደስተኛ እንደሆን የሚገልጸው ክፍል ደግሞ ከዚህ መዝሙር ተከትለው ከሚመጡት ጋር ያያይዘዋል (መዝ93-100፤ በተለይ ደግሞ መዝ94 ይመ)። በእርግጥ የእግዚአብሔር አገዛዝ “ፍቅርና ታማኝነት” የሰፈነበት በመሆኑ (ቍ2፤ 100፥5 ይመ) ይህ ባሕርይ ለመዝሙሩ አርታኢዎች እንደ መቀንበቢያ ሳያገለግላቸው አልቀረም። የዚህ መዝሙር ደራሲ ንጉሥ ሳይሆን አይቀርም (ቍ10-11 ይመ)። በመግቢያው ላይ ለእግዚአብሔር ምስጋና የቀረበ ሲሆን (ቍ1-3) በቍ4-5 ላይ ደግሞ ምስጋና ለማቅረብ ምክንያት የሆኑት ነገሮች ተጠቅሰዋል፤ ምስጋና ለማቅረብ ምክንያት የሆኑት ነገሮች በቍ10-11 ላይ ተደግመዋል። ቍ6-9 የክፉዎች ዕድል ፈንታ ምን እንደ ሆነ የሚያብራሩ ሲሆን ቍ12-15 ደግሞ ስለ ጻድቃን የተነገረውን በረከት ያብራራሉ። በቍ7 እና በቍ13 መካከል መሠረታዊ ትስስር እንዳለ ልብ ማለት ያሻል። ከዚህ በላይ የተደረገውን ትንተና ከተከትልን ቍ8 የቍ7 ማጠቃለያ መሆን አለበት።

92 *ርእስ መዝሙር፤* የመዝሙር 30 ርእስ ማብ ይመ። *በሰንበት ቀን፤* ይህ መዝሙር ከምርኮ በኋላ በነበረው የቤተ መቅደስ ቅዳሴ ላይ በዕለተ ሰንበት በነግህ መሥዋዕት ላይ ይዘመር ነበር (በቀሩት የሳምንቱ ቀናት በመጀመሪያው ቀን መዝ24፤ በሁለተኛው ቀን መዝ48፤ በሦስተኛው ቀን መዝ82፤ በአራተኛው ቀን መዝ94፤ በአምስተኛው ቀን መዝ81፤ በስድስተኛው ቀን መዝ93 ይዘመሩ ነበር)።

*92፥1-3፤* የዝማሬው መግቢያ ነው።

92፥1 *እግዚአብሔር ... ልዑል፤* ልዑል እግዚአብሔር ለማለት ነው (7፥17 እንዲሁም የ3፥7 ማብ ይመ)። *ለስምህ፤* የ5፥11 ማብ ይመ። *ልዑል፤* የዘፍ14፥19 ማብ ይመ።

92፥2 *ምሕረትህን ...ታማኝነትህን፤* ፍቅርና ታማኝነት ለማለት ነው (የ36፥5 እና የ3፥7 ማብ ይመ። *ምሕረትህን በማለዳ ... በሌሊት፤* ያለ ምንም ማቋረጥ ማለት ነው።

92፥3 *በገና ...መሰንቆ፤* የ57፥8 ማብ ይመ። *መሰንቆ፤* የዘፍ31፥27 ማብ ይመ።

*92፥4-5፤* በእግዚአብሔር የማዳን ሥራ ላይ የተመሠረተ ደስታ ነው (ቍ10-11 ይመ)።

92፥5 *ታላቅ፤* ስውር ሚስጢር ያለው ማለት ነው። ሐሳ

ሐሳብህስ ምን ያህል ጥልቅ ነው!
6ደነዝ ሰው ይህን አያውቅም፤
ነኁላላም አያስተውለውም።
7ክፉዎች እንደ ሣር ቢበቅሉ፣
ክፉ አድራጊዎች ቢለመልሙ፣
ለዘላለሙ ይጠፋሉ፤
8እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ግን
ለዘላለም ልዑል ነህ።
9ጠላቶችህ እግዚአብሔር ሆይ፤
ጠላቶችህ ይጠፋሉና፤
ክፉ አድራጊዎችም ሁሉ ይበተናሉ።
10የእኔን ቀንድ ግን እንደ አውራሪስ
ቀንድ[ሀ] ከፍ ከፍ አደረግኸው፤
በለጋ ዘይትም አረሰረሰኸኝ።
11ዐይኖቼ የባላንጦቼን ውድቀት አዩ፤
ጆሮዎቼም የክፉ ጠላቶቼን ድቀት ሰሙ።
12ጻድቃን እንደ ዘንባባ ይንሰራፋሉ፤
እንደ ሊባኖስ ዝግባም ይንዠረገጋሉ።
13በእግዚአብሔር ቤት ተተክለዋል፤
በአምላካችንም አደባባይ ይንሰራፋሉ።
14ባረጁ ጊዜ እንኳ ያፈራሉ፤
እንደ ለመለሙና እንደ ጠነከሩም
ይኖራሉ።
15"እግዚአብሔር ትክክለኛ ነው፤
እርሱ ዐለቴ ነው፤ በእርሱ ዘንድ እንከን
የለም" ይላሉ።

## መዝሙር 93

### የእግዚአብሔር ግርማ

1እግዚአብሔር ነገሠ፤ ግርማንም ተጐናጸፈ፤
እግዚአብሔር፣ ግርማን ለበሰ፤
ብርታትንም ታጠቀ፤
ዓለም እንዳትናወጥ ጸንታለች፤
ማንም አይነቀንቃትም።
2ዙፋንህ ከጥንት ጀምሮ የጸና ነው፤
አንተም ከዘላለም እስከ ዘላለም አለህ።
3እግዚአብሔር ሆይ፤ ወንዞች ከፍ አደረጉ፤
ወንዞች ድምፃቸውን ከፍ አደረጉ፤
ወንዞች የሚያስገመግም ማዕበላቸውን
ከፍ አደረጉ።
4ከብዙ ውሆች ድምፅ ይልቅ፣
ከባሕርም ሞገድ ይልቅ፣
ከፍ ብሎ ያለው እግዚአብሔር ኀያል
ነው።
5ሥርዐትህ የጸና ነው፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ እስከ ዘላለሙ፣
ቤትህ በቅድስና ይዋባል።

[ሀ]10 ጥንካሬን የሚያመለክት ነው።

92፥6 መዝ73፥22
92፥7 መዝ37፥2
92፥9 መዝ45፥5፤ 68፥1፤89፥10
92፥10 መዝ23፥5፤ 29፥6፤89፥17
92፥11 መዝ54፥7፤ 91፥8
92፥12 መዝ1፥3፤ 52፥8፤72፥7፤ኤር 17፥8፤ሆሴ14፥6
92፥13 መዝ135፥2
92፥14 መዝ1፥3፤ ዮሐ15፥2
92፥15 ኢዮ34፥10
93፥1 1ዜና16፥30፡ 31፤ኢዮ40፥10፤መዝ 21፥5፤24፥2፤65፥6፥7 8፥69፤96፥10፤97፥11 119፥90
93፥2 ዘፍ21፥33፤ 2ሳሙ7፥16
93፥3 ኢዮ9፥8፤መዝ 46፥3፤96፥11፤98፥7፤ 107፥25፡29፤ኢሳ5፥30 ፤17፥12-13፤51፥15፤ ኤር6፥23፤31፥35፤ ዕን3፥10
93፥4 ነሀ9፥32፤ኢዮ 9፥4፤መዝ18፥4፤65፥7 ፤ኤር6፥23፤ዮና1፥15
93፥5 መዝ5፥7፤ 23፥6፤29፥2፤96፥9

*ብህ፣* በተግባር የተገለጠ ሥራህ ማለት ነው።

*92፥6-9፣* የክፉዎችን የመጨረሻ ጥፋት የሚገልጽ ነው (ከቍ12-15 ጋር ያነጻጽሩ)።

92፥6 *ደነዝ ... ነኁላላም፣* 14፥1 እንዲሁም 49፥10፤ 94፥8-11 ይመ። እንዲህ ያሉ ሰዎች እግዚአብሔር በጽድቅ እንደሚገዛ አያስተውሉም፤ እነርሱ የሚያዩት ኀጢአተኞች መበልጸጋቸውን እንጂ፣ እግዚአብሔር በኀጢአተኞች ላይ የቀጠረውን ፍርድ አያውቁም። የመዝሙሩ ደራሲ ግን እግዚአብሔር "ባላጋሮቹን" እንዳጠፋለት (ቍ11) ይናገራል።

*92፥7፣* በመዝ73 ላይ ተስፋፍቶ የተነገረውን ሐሳብ በአጭሩ የሚያቀርብ ክፍል ነው (የ90፥4-5 ማብ ይመ)።

92፥8 *ለዘላለም ልዑል ነህ፣* የእግዚአብሔር ለዘላለም ከፍ ከፍ ብሎ መኖር የጠላቶቹን መደምሰስ እርግጠኛና እውን ያደርገዋል።

92፥9 *ጠላቶችህ፣* በዚህ ቦታ ክፉ አድራጊዎችን የሚያመለክት ሲሆን በቍ7 ላይ ተጠቅሶአል።

*92፥10-11፣* መዝሙረኛው እግዚአብሔር ስላደረገለት ቸርነት ደስ ተሰኝቶአል (ቍ4-5 ይመ)፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ድል አድራጊ እንዲሆን አድርጎታል (89፥24 ይመ)። ደግሞም በጠላቶቹ ሁሉ ላይ ከፍ ከፍ እንዲል፣ "በደስታ ዘይት" ቀብቶታል (45፥7 እንዲሁም 23፥5 ይመ)።

*92፥12-15፣* የጻድቃን መለምለም እርግጠኛና ዋስትናም ያለው መሆኑን የሚናገር ክፍል ነው (ከቍ6-9 ጋር ያነጻጽሩ)።

92፥13 *በእግዚአብሔር ቤት ተተክለው፣* ክፉዎች "እንደ ሣር ቱግ ብለው ቢበቅሉ" እንኳ (ቍ7)፣ መጨረሻቸው የታወቀ ነው። ጻድቃን ግን በማይናወጥ ቦታ ተተክለዋል (መዝ91 ይመ)፤ በእርጅናቸው ዘመን እንኳ እንደ ወጣት ናቸው፤ በእግዚአብሔርም ትክክለኛ ፍርድ ደስ ይሰኛሉ (ቍ15 ይመ)። *አደባባይ፣* የቤተ መቅደሱን አደባባይ ለማለት ነው (84፥2፡10፤ 2ነገ21፥5፤ 23፥11-12 ይመ)።

*መዝ93፣* ዘላለማዊ፣ በሁሉ ላይ ከፍ ከፍ ያለውንና የማይሻረውን የእግዚአብሔርን አገዛዝ የሚያወድስ ዝማሬ ሲሆን ከመዝ 47 እና 94-100 ጋር አንድ መሪ ሐሳብ ይጋራል። መዝሙሮቹ የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር ላይ እንደምትሰፍን ያላቸውን እምነትና ተስፋ ልዩ በሆነ መንገድ ይገልጻሉ። እነዚህ መዝሙሮች ከፍተኛ በሆነ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓል ላይ እግዚአብሔር ንጉሥ፣ የዓለም ሁሉ ጌታ እንዲሁም የሕዝቦች በተለይም የእስራኤል አምላክ እንደሆነ በሚታወጅበት ዓመታዊ ክብረ በዓል ላይ የሚዘምሩ ናቸው (የመዝ47 መግቢያን ይመ)። የእግዚአብሔር ንጉሥነት አጽናኦት የተሰጠው ሲሆን፣ "ከአማልክት ሁሉ በላይ በሆነ ታላቅ ንጉሥ" (95፥3) እንደ ሆነም በስሱ ተነግሮአል። መዝ93-100 በቤተ መቅደስ አለቆች የተደረሱ ሳይሆኑና የሚዘመሩትም በእርሱ ሳይሆን አይቀርም። መዝሙሮቹ የተጻፉት ምናልባት ከምርኮ በፊት ሊሆን ይችላል። ባወቃቀር ረገድ ሲታይ መዝሙሩ ሁለት አጭር አንጓዎች (ቍ1-2፡3-4) እና መደምደሚያ አለው (ቍ5)።

*93፥1-2፣* የፍጥረታት ሥርዐት በዘመናት ሁሉ ጸንቶ የኖረውና የሚኖረው እግዚአብሔር የፍጥረታት ንጉሥ በመሆኑ ነው፤ የእግዚአብሔር አገዛዝ ዘላለማዊ ነው (ዘፍ1፥1 ይመ)። ምንም እንኳን እስራኤል በሕዝብ ደረጃ የተቋቋመችው ከፍጥረት በኋላ ቢሆንም፣ አምላኳ እግዚአብሔር ግን ዓለም ሳይፈጠር ጀምሮ ንጉሥ ነው።

93፥1 *እግዚአብሔር ነገሠ፣* በእስራኤል የእምነት አንቀጽ ላይ የመጀመሪያው ድንጋጌና የመጨረሻው ትልቁ እውነት ነው (96፥10፤ 97፥1፤ 99፥1 እንዲሁም ዘካ14፥9 እና ማብ ይመ)።

*93፥3-4፣* እግዚአብሔር ዓለምን ከመሠረተ ጀምሮ የእርሱን መንግሥት ለማፈራረስ ከሚያሤሩ ኀይላት በላይ እጅግ ብርቱ መሆኑን አሳይቶአል።

93፥3 *ወንዞች፣* ይህ ቃል የሚያመለክተው የጥንቱን ዐመፀኛ ውሃ ሲሆን፣ እግዚአብሔር ይህንን ዐመፀኛ ውሃ በብርቱ ቃሉ ገርቶና ፈር አስይዞ ስፍራ ሰጥቶታል (33፥7፤ 104፥7-9፤ ዘፍ1፥6-10፤ ኢዮ38፥8-11 ይመ)። በሌላ በኩል ደግሞ ቃሉ የጌታን መንግሥት መምጣት የሚቃወሙትንም ያመለክታል (65፥6-7፤ 74፥13-14 እና ማብ ይመ)።

*93፥4፣* ከዐመፀኛው ወይም ከውጥንቅጡ (ቅጥ ካጣው፣ ከሥርዐት አልባው) ውሃ እያስገመገመ የሚወጣው ነጐድጓድ ድምፅ ሁሉን ነገር ሥርዐት ከሚያሲዘው የእግዚአብሔር ነጐድጓድ ቃል ጋር ከቶ አይወዳደርም (104፥7 ይመ)።

93፥5 *ሥርዐትህ፣* ከቶ የማይሻረው የእግዚአብሔር አገዛዝ ለዓለም ሰላም ሲሰጥ ለሕዝቡ ደግሞ አስተማማኝና የማይናወጥ የሕይወት መመሪያ ሰጥቶአል (19፥7 ይመ)፤ ሕዝቡ ይህንን መመሪያ ሊያከብሩት ይገባል (95፥8-11 ይመ)። *ቤትህ፣* በምድር ያለውን ቤተ መቅደሱን ወይም በሰማይ ያለውን መኖሪያውን ነው።

*መዝ94፣* "የምድር ሁሉ ፈራጅ" (ቍ2) የሆነው እግዚአብሔር፣ በሥልጣን ወንበር ላይ የተቀመጡ ትዕቢተኞችና ክፉዎች በድኾችና በደካሞች ላይ የሚያደርሱትን በደል ተመልክቶ እንዲበቀል የቀረበ ልመና ነው። መዝሙሩ ከመዝ92 ጋር ተያያዥነት ያለው ቢሆንም፣ መዝሙሩ የሚናገረው ግን በእስራኤል የሚኖሩ ምስኪኖች ስለደረሰባቸው በደል (ስለ ንጉሥ

## መዝሙር 94
### የእግዚአብሔር ፍትሕ

1የበቀል ስምባክ፣ አንተ *እግዚአብሔር* ሆይ፤
የበቀል ስምባክ ሆይ፤ ደምቀህ ተገለጥ።
2አንተ የምድር ዳኛ ሆይ፤ ተነሥ፤
ለትዕቢተኞች የእጃቸውን ስጣቸው።
3ክፉዎች እስከ መቼ *እግዚአብሔር* ሆይ፤
ክፉዎች እስከ መቼ ይፈነጫሉ?
4የእብሪት ቃላት ያዥጐደጕዳሉ፤
ክፉ አድራጊዎች ሁሉ ጕራ ይነዛሉ።

5*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ሕዝብህን አደቀቁ፤
ርስትህንም አስጨነቁ።
6መበለቲቱንና መጻተኛውን ገደሉ፤
የድኻ አደጉንም ነፍስ አጠፉ።
7እነርሱም "*እግዚአብሔር* አያይም፤
የያዕቆብም ስምባክ አያስተውልም" አሉ።

8እናንት በሕዝቡ መካከል ያላችሁ ደነዞች፤
ልብ በሉ፤
እናንት ቂሎች፤ ጥበበኞች የምትሆኑት
መቼ ነው?
9ጆሮን የተከለው እርሱ አይሰማምን?
ዐይንንስ የሠራ እርሱ አያይምን?
10ሕዝቦችን በተግሣጽ ወደ መንገድ
የሚመልስ፣
ዕውቀትንስ ለሰው ልጆች የሚያስተምር
አይቀጣምን?
11*እግዚአብሔር* የሰው ሐሳብ መና፣
ከንቱም እንደ ሆነ ያውቃል።

12*እግዚአብሔር* ሆይ፤ አንተ
የምትገሥጸው፣
ከሕግህም የምታስተምረው ሰው ምስጉን
ነው።
13ለኀጢአተኞች ጕድጓድ እስኪማስላቸው
ድረስ፣
እርሱን ከመከራ ታሳርፈዋለህ።
14*እግዚአብሔር* ሕዝቡን አይጥልምና፤
ርስቱንም አይተውም።
15ፍርድ ተመልሶ በጽድቅ አሠራር ላይ
ይመሠረታል፤
ልባቸውም ቀና የሆነ ሁሉ ይከተሉታል።
16ክፉዎችን የሚቋቋምልኝ ማን ነው?
ከክፉ አድራጊዎችስ ጋር የሚሟገትልኝ
ማን ነው?
17*እግዚአብሔር* ረዳቴ ባይሆን ኖሮ፣
ነፍሴ ወደ ዝምታው ዓለም ፈጥና
በወረደች ነበር።
18እኔ፣ "እግሬ አዳለጠኝ" ባልሁ ጊዜ፣
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ምሕረትህ ደገፈ
ያዘኝ።
19የውስጤ ጭንቀት በበዛ መጠን፣
ማጽናናትህ ነፍሴን ደስ አሰኘት።

20ዐመፃን ሕጋዊ የሚያደርግ፣
የጥፋት ዙፋን ከአንተ ጋር ሊያብር
ይችላልን?
21በጻድቁ ላይ ተሰልፈው ይወጣሉ፤
በንጹሑም ላይ ሞት ይፈርዳሉ።
22ለእኔ ግን *እግዚአብሔር* ምሽግ፣
ስምባኪም መጠጊያ ዐለት ሆኖኛል።
23በደላቸውን ወደ ራሳቸው ይመልሳል፤

94፥1 ዘፍ4፥24፤ዘዳ 33፥2፤መዝ80፥1፤ ሮሜ12፥19
94፥2 ዘፍ18፥25፤ ዘኍ10፥35፤መዝ 31፥23፤ዕብ12፥23፤ ያዕ5፥9
94፥3 መዝ13፥2
94፥4 መዝ52፥1፤ ኤር43፥2
94፥5 መዝ28፥9፤ 44፥2፤74፥8፤ኢሳ 3፥15፤ኤር8፥21
94፥6 ዘዳ10፥18፤ 24፥19፤ኢሳ1፥17
94፥7 ዘፍ24፥12፤ ኢዮ22፥14
94፥8 ዘዳ32፥6፤ መዝ73፥22
94፥9 ዘፀ4፥11፤ ምሳ20፥12
94፥10 ዘፀ35፥34፤ ኢዮ35፥11፤መዝ 39፥11፤ኢሳ28፥26
94፥11 መዝ139፥2 ፤ምሳ15፥26፤ማቴ9፥4 ፤1ቆሮ3፥20
94፥12 ዘዳ8፥3፤ 1ሳሙ12፥23፤ኢዮ 5፥17፤1ቆሮ11፥32፤ ዕብ12፥5
94፥13 መዝ7፥15፤ 55፥23፤86፥7
94፥14 ዘዳ31፥6፤ መዝ37፥28፤ሮሜ 11፥2
94፥15 መዝ7፥10፤ 11፥2፤36፥10፤97፥2
94፥16 ዘኍ10፥35፤ መዝ17፥13፤59፥2፤ ኢሳ14፥22
94፥17 መዝ31፥17 ፤124፥2
94፥18 ዘዳ32፥35፤ ኢዮ12፥5 94፥19 ኢዮ6፥10፤መክ11፥10 94፥20 መዝ58፥2፤ ኤር22፥30፤36፥30 94፥21 ዘፍ18፥23፤መዝ56፥6፤106፥38፤ ምሳ17፥15:26፤28፥21፤ኢሳ5፥20:23፤ማቴ27፥4 94፥22 2ሳሙ 22፥3፤መዝ18፥2፤61፥2 94፥23 ዘፀ32፥34፤መዝ9፥5፤37፥35፤ 54፥5፤145፥20

ሳይሆን) እና እግዚአብሔርም የደረሰባቸውን ግፍ ሁሉ ተመልክቶ ለትዕቢተኞች የሚገባቸውን ቅጣት እንዲሰጥ የሚማጸን ነው። ስለዚህ ከመዝ92-100 ሁሉ የተለየ ነው ማለት ነው (የመዝ93 መግቢያ ይመ)። ከሦስት ቍጥሮች በኋላ የሚገኘው የመዝሙሩ ክፍል (ቍ1-3 መግቢያ ነው) እያንዳንዳቸው አራት ቍጥር ባላቸው አምስት አንጓዎች የተደራጀ ነው።

*94፥1-3፤* ትክክለኛ ዳኛ ለሆነው ለእግዚአብሔር በመግቢያ ላይ የቀረበ ልመና ነው።

94፥1 *በቀል፤* ለክፉ ሥራ የሚገባውን ቅጣት የምትሰጥ ማለት ነው (ዘዳ 32፥35 እና ማብ እንዲሁም ዘዳ32፥41 ይመ)።

94፥2 *ትዕቢተኞች፤* ቍ4-7 ይመ።

94፥3 *እስከ መቼ፤* የ6፥3 ማብ ይመ፤ እንዲሁም በመጽሐፈ መዝሙር መግቢያ ላይ "ትምህርተ መለኮት" የሚለውን ይመ።

*94፥4-7፤* በክፉዎች ላይ የቀረበ ክስ ነው።

94፥4 *የእብሪት ቃላት ... ጕራ፤* የክፉዎችን እብሪተኝነት በተመለከተ 10፥2-11 እና ማብ ይመ።

94፥5 *ሕዝብህን ... ርስትህን፤* በመካከላቸው ያሉትን ረዳት የለሾችና ደካሞች ለማለት ነው (ቍ6 ይመ)።

94፥7 *አሉ፤* የ3፥2፤ የ10፥11 ማብ ይመ። *ያዕቆብ፤* እስራኤል ለማለት ነው (ዘፍ32፥28 ይመ)።

*94፥8-11፤* "ደነዝ ... አእምሮ ቢሶች" (92፥6-9 ይመ) ለሆኑ ክፉዎች የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ነው።

94፥10 *ተግሣጽ፤* አጥፊውን እየቀጣ በትክክለኛው መንገድ እንዲይዙ ያደርጋል (ዘሌ26፥18፤ ኤር31፥18 ይመ)። *የሚያስተምር፤* የፍጥረታትን ሥርዐት የሚያሳውቅ ማለት ነው (ኢሳ 28፥26 ይመ)።

94፥11 *እግዚአብሔር ... ያውቃል፤* ከንቱ ከሆነው የሰዎች አስተሳሰብ በተቃራኒው እግዚአብሔር ዐዋቂ ነው (ቍ7 ይመ)።

*94፥12-15፤* ሕይወታቸው በእግዚአብሔር ሕግ የሚመራ ሰዎች የተባረኩ ናቸው (መዝ1 ይመ)፤ ከዚህ በተቃራኒው ክፉዎችና እብሪተኞች የእግዚአብሔር ፍርድ ይጠብቃቸዋል።

94፥12 *ምስጉን፤፤* የ1፥1 ማብ ይመ። *የምትገሥጸው ... የምታስተምረው፤* ቍ10 ይመ። በዚህ ቦታ ጸሐፊው የሚናገረው እግዚአብሔር ሕዝቡ በሕጉ መሠረት እንዲኖር የሚያርምና የሚያስተምር መሆኑን ነው።

94፥14 *ሕዝቡን ... ርስቱን፤* ቍ5 ይመ፤ እግዚአብሔር ደካሞችንና የእርሱ የሆኑትን ያለ ትክክለኛ ፍርድ ለሚያንገላቱ ጠላቶች አሳልፎ አይሰጥም። ጳውሎስ በሮሜ 11፥1-2 ላይ ይህንን ንባብ ሳይጠቅስ አልቀረም።

94፥15 *ይመሠረታል፤* ወይም፣ "እንደ ገና መልሶ ያቆማል" ማለት ነው። *ልባቸው፤* የ4፥7 ማብ ይመ። *ይከተሉታል፤* ልበ ቅን ለሆኑ ሰዎች የእግዚአብሔር ፍርድ ትክክለኛ ዳኝነትን እንደሚያስገኝ ጸሐፊው የሚናገር ይመስላል።

*94፥16-19፤* አቤቱታን በትክክል የሚቀበልና የሚያደምጥ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

94፥17 *ወደ ዝምታው ዓለም፤* የ30፥1 ማብ ይመ። እግዚአብሔር መዝሙረኛውን ባይረዳው ኖሮ ክፉዎች ገድለው በቀበሩት ነበር፤ አሁን ግን ጕድጓድ የተማሰው ለክፉዎች ሆነ (ቍ13 ይመ)።

94፥18 *ባልሁ ጊዜ፤* በክፉዎች መከበቡን ባወቀ ጊዜ ማለት ነው (የ38፥16 ማብ ይመ)። *ምሕረትህ፤* የ6፥4 ማብ ይመ።

94፥19 *ነፍሴ፤* የ6፥3 ማብ ይመ።

*94፥20-23፤* የእግዚአብሔር ትክክለኛ ፍርድ እንደሚሰፍን ያለውን እምነት ይገልጻል።

94፥20 *የጥፋት ዙፋን፤* ግፍ የሚፈጸምበት የሥልጣን መንበር ነው። ጸሐፊው ሥልጣን በመጨበጡ ሰዎች፣ ግፍ እየተፈጸመ መሆኑን ይናገራል፤ በሥልጣናቸው ዘመን ፍትሕና ትክክለኛ ዳኝነት አላየም።

94፥21 *ጻድቁ፤* የ1፥5 ማብ ይመ።

በክፋታቸውም ያጠፋቸዋል፤
*እግዚአብሔር* አምላካችን ይደመስሳቸዋል።

## መዝሙር 95

**የዕለቱ መዝሙር**

[1]ኑ፤ ደስ እያለን *ለእግዚአብሔር* እንዘምር፤
በድነታችንም ዐለት እልል እንበል።
[2]ምስጋና ይዘን ፊቱ እንቅረብ፤
በዝማሬም እናወድሰው።
[3]*እግዚአብሔር* ታላቅ አምላክ ነውና፤
ከአማልክትም ሁሉ በላይ ታላቅ ንጉሥ
ነው።
[4]የምድር ጥልቆች በእጁ ናቸው፤
የተራራ ጫፎችም የእርሱ ናቸው።
[5]እርሱ ፈጥሮአታልና፣ ባሕር የእርሱ ናት፤
እጁም የብስን አበጀ።
[6]ኑ፤ እናምልከው፤ እንስገድለትም፤
በፈጣሪያችን *በእግዚአብሔር* ፊት
እንንበርከክ፤
[7]እርሱ አምላካችን ነውና፤
እኛም በእጁ ጥበቃ ሥር ያለን በጎቹ፣
የመሰማሪያውም ሕዝብ ነን።
ዛሬ ድምፁን ብትሰሙ፣
[8]በምድረ በዳ በነበራችሁበት ቀን በማሳህ፣^
በመሪባም* እንዳደረጋችሁት፣
ልባችሁን አታደንድኑ።
[9]ሥራዬን ቢያዩም፣
አባቶቻችሁ በዚያ ፈተኑኝ፤
ተፈታተኑኝም።
[10]ያን ትውልድ አርባ ዓመት ሙሉ
ተቈጣሁት፤
እኔም፣ "ልቡ የሸፈተ ሕዝብ ነው፤
መንገዴንም አላወቀም" አልሁ።
[11]ስለዚህ፣ "ፈጽሞ ወደ ዕረፍቴ
አይገቡም" ብዬ፣
በቍጣዬ ማልሁ።

## መዝሙር 96

**እግዚአብሔር፤ ንጉሥም ዳኛም**

96፥1-13 ተጓ ምብ-1ዜና16፥23-33

[1]*ለእግዚአብሔር* አዲስ ዝማሬ ዘምሩ፤
ምድር ሁሉ፤ *ለእግዚአብሔር* ዘምሩ።

95፥1 2ሳሙ22፥47፤መዝ5፥11፤34፥1፤8 0፥2፤81፥1፤ኢሳ44፥23፤ሶፎ3፥14
95፥2 መዝ42፥4፤81፥2፤100፥2፤ሚክ6፥6፤ኤፌ5፥19
95፥3 መዝ47፥2፤48፥1፤86፥10፤96፥4፤97፥9፤145፥3፤147፥5
95፥4 መዝ63፥9
95፥5 ዘፍ1፥9፤መዝ146፥6
95፥6 2ሳሙ12፥16፤2ዜና6፥13፤መዝ22፥29፤100፥3፤149፥2፤ኢሳ17፥7፤54፥5፤ዳን6፥10-11፤ሆሴ8፥14፤ፊል2፥10
95፥7 መዝ74፥1
95፥8 ዘፀ17፥7፤ዘዳ33፥8፤መዝ78፥40፤ማር10፥5፤ዕብ3፥8፤15፤4፥7
95፥9 ዘኍ14፥22፤1ቆሮ10፥9
95፥10 ዘፀ16፥35፤ዘኍ14፥34፤ዘዳ8፥6፤መዝ58፥3፤119፥67፤176፤ምሳ12፥26፤16፥29፤ኢሳ53፥6፤ኤር31፥19፤50፥6፤ሕዝ34፥6፤ሐሥ 7፥36፤ዕብ3፥17
95፥11 ዘኍ14፥23፤ዘዳ1፥35፤ዕብ3፥7-11፤4፥3
96፥1 መዝ30፥4፤33፥3፤40፥3፤98፥1፤144፥9፤149፥1፤ኢሳ42፥10፤ራእ5፥9

^8 ማሳህ *ፈተና* ማለት ነው።
*8 መሪባ *ጠብ* ማለት ነው።

***መዝ95፤*** በቤተ መቅደስ የተሰበሰቡት እስራኤላውያን እግዚአብሔርን እንዲያመልክ በአንድ በካህን ወይም ሌዋዊ የቀረበ ጥሪ ነው (የመዝ93 መግቢያን ይመ)። መዝሙሩ ሁለት ክፍሎች አሉት፤ (1) የምድር ሁሉ ጌታ የሆነውን እግዚአብሔርን ለማመስገን የቀረበ ጥሪ (ቍ1-5)፤ (2) ራስን በመስጠትና ከልብ በመታዘዝ እግዚአብሔር የሕዝቡ ንጉሥ መሆኑን እንዲያውቁ የቀረበ ጥሪ ነው (ቍ6-11)። እያንዳንዱ ክፍል ደግሞ ሁለት ንዑስ ክፍል ያለው ሲሆን፣ የመዝሙሩ ሐሳብ እያደገ መጥቶ ከመጨረሻው ከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚደርሰው በመጨረሻው ክፍል ላይ ነው፤ ከመዝ96 ጋር ያነጻጽሩ።

*95፥1-2፤* እግዚአብሔርን ለማመስገን የቀረበ ጥሪ ነው።

95፥1 *በድነታችን ዐለት፤* የ18፥2 ማብ ይመ።

*95፥3-5፤* እስራኤል እግዚአብሔርን ማምለክ ያለበት ለምንድን ነው? ምክንያቱም እግዚአብሔር ከአማልክት ሁሉ በላይ ከፍ ያለና ምድርንም ሁሉ በእጁ ውስጥ የያዘ ነው። የጥንቱ አረማዊ ዓለም የተለያዩ ሰዎችን፣ የተለያዩ መልክዐ ምድራዊ አቀማመጦችን፣ የተለያዩ የዓለም ክፍሎችን (ሰማይን፣ ምድርን፣ ከምድር በታች ያለውን ዓለም) የሚወክሉ የተለያዩ አማልክት ነበሩት፤ ከዚህ በተጨማሪ የተለያዩ የሕይወት ፈርጆችን (ለምሳሌ ጦርነትን፣ ልምላሜን፣ እደ ጥበብን) የሚወክሉ አማልክትም ነበሯቸው።

95፥4-5 *ጥልቆች ... የተራራ ጫፎች ... ባሕር ... የብስ፤* ዓለምን በሙሉ ማለትም ከጫፍ እስከ ጫፍና በዚህም መካከል ያለውን ሁሉ ማለት ነው፤ በጥቅሉ የእርሱ ያልሆነ ምንም ነገር የለም ለማለት ነው።

*95፥6-11፤* ታዛዥ በሆነ ልብ ራስን ለእግዚአብሔር መስጠት አስፈላጊ መሆኑን የሚያሳስብ ምክር ነው፤ ምክንያቱም በእግዚአብሔር ፊት መንበርከክ ብቻ በቂ አይደለም። አዲስ ኪዳን ይህን ክፍል ከኢየሱስ ጋር እንዴት እንዳዛመደው ዕብ3፥7-4፥13 ይመ።

*95፥6-7፤* በእግዚአብሔር ፊት በመንበርከክ ራሳቸውን ለእርሱ የሰጡ መሆናቸውን እንዲያውጁ የቀረበ ጥሪ ነው።

95፥6 *ፈጣሪያችን፤* የሁሉ ነገር ፈጣሪና (ዘፍ 1 ይመ) የእስራኤልም ታዳጊ እንደ መሆኑ፣ እግዚአብሔር በምድር ሁሉ ካሉት ሕዝቦች መካከል እስራኤልን የራሱ እንድትሆን አድርጓታል (ኢሳ45፥9-13፤ 51፥12-16 ይመ)።

95፥7 *የመሰማሪያውም ሕዝብ፤* 100፥3፤ ኤር 23፥1፤ ሕዝ 34፥21 ይመ። ነገሥታት የሕዝቦቻቸው፣ "እረኞች" (የ23፥1 ማብ ይመ) ተደርገው ስለሚቈጠሩ ግዛታቸው የእነርሱ፣ "ማሰማሪያ" ተደርጐ ይታያል (ኤር25፥36፤ 49፥20፤ 50፥45 ይመ)። ዛሬ ድምፁን ብትሰሙ፤ በሃይማኖታዊ በዓላት ላይ ቅዳሴ ሲደረግ ወይም በመዝ50 እና በመዝ78 ላይ በተጠቀሰው ሁኔታ ማለት ነው።

95፥8 *ማሳህ ...መሪባ፤* አግራጭ ትርጒሙን ይመ፤ የቅዳሴው መሪ እስራኤል በምድረ በዳ በእግዚአብሔር ላይ ያመፀችበትን ጊዜ ያስታውሳል (ዘፀ17፥7፤ ዘኍ20፥13 ይመ)።

95፥9 *ሥራዬን ቢያዩም፤* በግብፅ ምድርና በቀይ ባሕር ያደረኩትን እንዲሁም በምድረ በዳ መና ያዘነብኩትን ልብ ቢሉ ማለት ነው (ዘፀ 16እና ዘኍ14፥11 ይመ)።

95፥10 *ያን ትውልድ፤* ከግብፅ ምድር ወጥተው በሲና ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን ያደረጉትን እስራኤላውያን ማለት ነው (ዘኍ32፥13 ይመ)። *አርባ ዓመት፤* የእስራኤል ዐመፀኝነት የመጨረሻውን መጥፎ ገጽታ የያዘው በከነዓን ላይ ለመዝመት አሻፈረኝ ባለችና ወደ ግብፅም ለመመለስ በከጀለች ጊዜ ነው፤ ይህም እስራኤል ምን ያህል እምነተ ቢስ እንደ ነበረች ያሳያል (ዘኍ14፥1-4 ይመ)፤ በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር 40 ዓመት ሙሉ በምድረ በዳ እንድትንከራተት ፈረደባት (ዘኍ14፥34 ይመ)። *ተቈጣሁት፤* የ2፥5 ማብ ይመ። *ሕዝብ ... መንገዴን፤* በዘኍ 14፥11 ላይ እግዚአብሔር የተናገረውን ነገር በድጋሚ የሚናገር ንባብ ነው። *ልቡ፤* የ4፥7 ማብ ይመ። *መንገዴን፤* 25፥4 እና ማብ ይመ።

95፥11 *ማልሁ፤* ዘኍ14፥28 ይመ። *ፈጽሞ ወደ ዕረፍቴ አይገቡም፤* የዘኍ14፥30 ቋንቋ፣ "አንዳችሁም ወደ ምድሪቱ አትገቡም" የሚል ቢሆንም የተስፋዪቱ ምድር እግዚአብሔር ለሕዝቡ፣ "ዕረፍትን" የሚሰጥባት ምድር በመሆኗ ሁለቱም አባባሎች ተመሳሳይ ትርጒም አላቸው (ኢሱ1፥13፥15፤ ዘፀ33፥14፤ ዘዳ 12፥10፤ 25፥19 ይመ)። *ዕረፍቴ፤* በዚህ ቦታ ይህ ቃል የሚያመለክተው እስራኤል የምትወርሰውን ለምለም ምድር ሲሆን፣ በዚህ ምድር እስራኤል ከውጭ ጠላትና ከውስጥ መዓት ተጠብቃ በሰላም የምትኖር መሆኗን ነው (1ነገ5፥4 ይመ)።

***መዝ96፤*** እግዚአብሔር ብቸኛ አምላክና የዓለምም ንጉሥ መሆኑን እንዲያውጁ ለሕዝቦች ሁሉ የቀረበ ጥሪ ነው፤ በአዲስ ኪዳን ያሉ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ያላቸውን ዐይነት ተልእኮ የብሉይ ኪዳንም የእግዚአብሔር ሕዝቦች እንደ ነበራቸው የሚያስገነዝብ ነው (ማቴ28፥16-28 ይመ)። (የመዝ93 እና 95 መግቢያን ይመ)። ይህ መዝሙር ለየት ባለ መልኩ በ1ዜና16፥23-33 ላይ ቀርቦአል። መዝሙሩ ሁለት ክፍሎች አሉት:- (1) የምስጋና መዝሙር እንዲዘምሩ ለሕዝቦች ሁሉ የቀረበ ጥሪ (ቍ1-6)፤ (2) እግዚአብሔርን እንዲያመልኩና የጽድቅ አገዛዙንም ለዓለም ሁሉ እንዲያወሩ ለሕዝቦች ሁሉ የቀረበ ጥሪ (ቍ7-13)። እያንዳንዱ ክፍል ደግሞ ሁለት ንዑስ ክፍሎች ያሉት ሲሆን የመጨረሻው ክፍል እያደገ የመጣውን የመዝሙሩን መሪ ሐሳብ ከመጨረሻው ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያደርሰዋል። ከመዝ95 አወቃቀር ጋር ያነጻጽሩ።

*96፥1-3፤* የእግዚአብሔርን ክብር በሕዝቦች መካከል በዝማሬ እንዲያወድሱት ለምድር ነዋሪዎች ሁሉ የቀረበ ጥሪ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ "ዘምሩ ... ዘምሩ ...ዘምሩ" የሚለው ቃል ሦስት ጊዜ ተደጋግሞ ተጠቅሶአል፤ ይህም በብሉይ ኪዳን ሥር

²ለእግዚአብሔር ዘምሩ፤ ስሙንም ባርኩ፤
ማዳኑንም ነጋ ጠባ አውሩ።
³ክብሩን በሕዝቦች መካከል፣
ድንቅ ሥራውንም በሰዎች ሁሉ ፊት
ተናገሩ።

⁴እግዚአብሔር ታላቅ ነውና፤ ውዳሴም
የሚገባው ነው፤
ከአማልክትም ሁሉ በላይ ሊፈራ ይገባዋል።
⁵የሕዝብ አማልክት ሁሉ ጣዖታት ናቸው፤
እግዚአብሔር ግን ሰማያትን ሠራ።
⁶ክብርና ግርማ በፊቱ ናቸው፤
ብርታትና ውበትም በመቅደሱ ውስጥ
አሉ።

⁷የሕዝቦች ወገኖች ሆይ፤ ለእግዚአብሔር
ስጡ፤
ክብርንና ብርታትን ለእግዚአብሔር
ስጡ።
⁸ለስሙ የሚገባ ክብርን ለእግዚአብሔር
ስጡ፤
ቍርባንን ይዛችሁ ወደ አደባባዩ ግቡ።
⁹በተቀደሰ ውበት ለእግዚአብሔር ስገዱ፤
ምድር ሁሉ፤ በፊቱ ተንቀጥቀጡ።
¹⁰በሕዝቦች መካከል፣ "እግዚአብሔር
ነገሠ፤" በሉ
ዓለም በጽኑ ተመሥርታለች፤
አትናወጥም፤
እርሱ ለሕዝቦች በእኩልነት ይፈርዳል።
¹¹ሰማያት ደስ ይበላቸው፤ ምድርም ሐሤት
ታድርግ፤
ባሕርና በውስጧ ያለው ሁሉ ያስተጋባ፤
¹²መስኩና በላዩ ያለው ሁሉ ይፈንጥዝ፤
ያን ጊዜ የዱር ዛፎች ሁሉ በደስታ
ይዘምራሉ፤
¹³እርሱ ይመጣልና በእግዚአብሔር ፊት
ይዘምራሉ፤
በምድር ላይ ሊፈርድ ይመጣል፤
በዓለም ላይ በጽድቅ፣
በሕዝቦችም ላይ በእውነት ይበይናል።

## መዝሙር 97
## የእግዚአብሔር ድል አድራጊነት

¹እግዚአብሔር ነገሠ፤ ምድር ደስ ይበላት፤
በሩቅ ያሉ የባሕር ጠረፎች ሐሤት
ያድርጉ።

96፥2 መዝ27፥1፤ 68፥4፤71፥15
96፥3 መዝ8፥1፤ 71፥17፤ራእ15፥3
96፥4 ዘዳ28፥58፤ 1ዜና16፥25፤መዝ 48፥1፤89፥7፤95፥3
96፥5 ዘፍ1፥1፤ዘሌ 19፥4፤2ዜና2፥12
96፥6 መዝ21፥5፤ 29፥1፤89፥17
96፥7 መዝ22፥27፤ 29፥1
96፥8 መዝ45፥12፤ 51፥19፤65፥4፤72፥10 ፤84፥10፤92፥13፤ 100፥4
96፥9 ዘፀ15፥14፤ 23፥25፤መዝ33፥8፤ 93፥5፤114፥7፤ዮና1፥9
96፥10 መዝ24፥2፤ 58፥11፤67፥4፤78፥69 ፤93፥1፤97፥1፤98፥9፤ 119፥90
96፥11 መዝ97፥1፤ ኢሳ49፥13፤ራእ 12፥12
96፥12 መዝ65፥13 ፤ኢሳ44፥23፤55፥12 ፤ሕዝ17፥24
96፥13 መዝ7፥11፤ 86፥11፤ሐሥ17፥31፤ራእ19፥11
97፥1 ዘፀ15፥18፤ አስ10፥1፤መዝ93፥1፤96፥10፡11፤99፥1፤ኢሳ 24፥23፤52፥7

ዐተ ቅዳሴ ውስጥ ሰዎችን ለአምልኮ ለማነሣሣት የተለመደ ጥሪ ነው (ቍ7-9 እና ማብ፤ 103፥20-22፤118፥2-4፤ 135፥1፤136፥1-3 ይመ)።

96፥1 *አዲስ ዝማሬ፤* የ33፥3 ማብ ይመ፤ *ምድር ሁሉ፤* ቍ9 ይመ፤ ወይም፣ "ምድሪቱ ሁሉ" ማለት ነው፤ በዚህ አጠቃቀሙ ጥሪው የቀረበው ለእስራኤል ሁሉ ነው። ነገር ግን የዚህ መዝሙር ዓለም አቀፋዊ ባሕርይ እንደሚያመለክተው (ቍ7 ይመ) መዝሙረኛው የዓለምን ሕዝቦች በሙሉ ለማካተት ያሰበ ይመስላል (97፥ 1፤ 100፥1 እና ማብ፤ 117፥1 እንዲሁም የ9፥1 ማብ ይመ)።

96፥2 *ስሙን፤* ቍ8፤ የ5፥11 ማብ ይመ። *ማዳኑን ... አውሩ፤* ሕዝቡን ነጻ የሚያወጣ እግዚአብሔር ብቻ እንደ ሆነ (3፥8፤ 85፥9 ይመ) ዐውጁ (40፥9 እና ማብ ይመ) ማለት ነው።

96፥3 *ክብሩን፤* የ85፥9 ማብ ይመ። *ድንቅ ሥራውንም፤* የ71፥16-17 ማብ ይመ።

*96፥4-6፤* "ምድር ሁሉ" እግዚአብሔርን ማመስገን ያለበት አምላክ እርሱ ብቻ ስለሆነ ነው መዝ115 ይመ።

96፥4 *ሊፈራ፤* የዘፍ20፥11 ማብ ይመ።

96፥5 *ሰማያትን ሠራ፤* በአረማውያን ዐይን የአማልክት ማደሪያ ተደርጉ የሚታየውን ሰማያት የፈጠረ እግዚአብሔር በመሆኑ እርሱ ከአማልክት ሁሉ በላይ ከፍ ያለ ነው (97፥7 ይመ)።

96፥6 *ክብርና ግርማ ... ብርታትና ውበት፤* የእግዚአብሔርን ባሕርይ የሚገልጹ ጥንድ ጠባያት ሲሆኑ፣ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት በሚያገለግሉ ሰዎች ተመስለው ቀርበዋል። እግዚአብሔር ኀያልና ገናና እንዲሁም የምድር ሁሉ ጌታ መሆኑን ያውጃሉ። ለተመሳሳይ ሰውኛ አገላለጽ 23፥6 ይመ። *ክብር፤* የዕብራይስጡ ቃል "የሚያንጸባርቅ ውበት" የሚል ፍቺ አለው።

*96፥7-9፤* እግዚአብሔርን ያመልኩ ዘንድ ለሕዝቦች ሁሉ የቀረበ ጥሪ ነው (29፥1-2 እና ማብ ይመ)። በ29፥2 ላይ ያሉት ዐረፍተ ነገሮች በዚህ መዝሙር ውስጥ ተስፋፍተዋል።

96፥8 *አደባባዩ፤* የቤተ መቅደሱን አደባባይ ለማለት ነው (84፥2፡10፤ 2ነገ21፥5፤ 23፥11-12 ይመ)።

96፥9 *ተንቀጥቀጡ፤* በመፍራት ትርበድበድ ማለት ነው (ቍ4 ይመ)።

*96፥10-13፤* ሕዝቦች ሁሉ የእግዚአብሔርን የጽድቅ መንግሥት እንዲያውጁ የቀረበ ጥሪ ነው።

96፥10 *እግዚአብሔር ነገሠ፤* 93፥1 እና ማብ ይመ። *ዓለም ... በእኩልነት፤* እንደ ብሉይ ኪዳን አስተያየት የዓለም ሥርዐት አንድ ነው፤ ይህ አንድ ሥርዐት ሥጋዊና (ቍሳዊ) ሞራላዊ ገጽታዎችን የሚያቅፍ ነው፤ እነዚህ ሁለት ገጽታዎች የተፈጠሩት (የተመሠረቱት) በእግዚአብሔር በመሆኑ ሁለቱም በእግዚአብሔር አገዛዝ ውስጥ የጸና ቦታ አላቸው። እግዚአብሔር በተፈጥሮና በሰው (እንዲሁም በመፍጠርና በማዳን) ላይ ያለው ሥልጣን ሁልጊዜ በአንድ ትንፋሽ ተነግሮ እናገኘዋለን፤ የእግዚአብሔር "ጽድቅ"፣ "ታማኝነት" እና "ፍቅር" ለሁለቱም ገጽታዎች ተሰጥቶአል። የፍጥረት ሥርዐት በእግዚአብሔር፣ "መልካምነት" (ዘፍ1 ይመ) ላይ የጸና በመሆኑ በብሉይ ኪዳን የቅኔ መጻሕፍት ውስጥ የእግዚአብሔር አገዛዝ፣ "በጽድቅ"፣ "በቅንነት" እና "በእውነት" ላይ የተመሠረተ ስለመሆኑ በግልጽ ተጠቅሶአል (ቍ13፤ 11፥3፤ 33፥4-11፤ 36፥5-9፤ 57፥10፤65፥6-7፤ 71፥19፤ 74፥13-14፡16-17፤ 75፥3፤ 82፥5፤ 93፥3-4፤ 119፥89-91፤ እና ማብ ይመ)። *ይፈርዳል፤* ቍ13 እና ማብ ይመ።

*96፥11-12፤* የእግዚአብሔር መንግሥት አንድ በመሆኑ (ቍ10 እና ማብ ይመ) የእግዚአብሔር አገዛዝ በፍጥረታቱ ላይ ጽድቅን ሲያሰፍን ፍጥረታቱ ሁሉ ሐሤት ያደርጋሉ (የ65፥13 ማብ፤ እንዲሁም 97፥7-9 ይመ)። ይህ የአሁኑ ዓለም የእግዚአብሔርን ማዳን በተስፋ የሚጠባበቅ መሆኑን ለመመልከት ሮሜ 8፥21-22 እና ማብ ይመ።

96፥13 *ይመጣል ... ይመጣል ... ይበይናል፤* እግዚአብሔር በሁሉ ነገር ላይ ስለ ነገሠና የታሪክም ጌታ ስለ ሆነ፣ እስራኤል የእግዚአብሔርን መምጣት በተስፋ እየተጠባበቀች ትኖራለች፤ በሚወጣውም ዘመን ክፋትን ሁሉ አስወግዶ ጽድቁን በምድር ሁሉ ላይ ያሰፍናል። *ጽድቅ፤* የ4፥1 ማብ ይመ።

*መዝ97፤* የእግዚአብሔር የጽድቅ መንግሥት በምድር ሁሉ ላይ በመስፈኑ የቀረበ የምስጋና መዝሙር ነው (የመዝ93 እና 95 መግቢያ ይመ)። የመዝሙሩ ሁለት ዐቢይ ክፍሎች (ቍ1-6፡ 8-12) በአንድ ማእከላዊ ቍጥር (ቍ7፤ የ6፥6 ማብ ይመ) የተጣመሩ ሲሆን ይህ ማእከላዊ ቍጥር የመዝሙሩን መሪ ሐሳብ የሚያጕለምስ ነው (ቍ7፤ የ6፥6 ማብ ይመ)። የሁለቱ ዐቢይ ክፍሎች የመግቢያ ጥቅሶች (ቍጥሮች) በአንድ መሪ ሐሳብ ተሳስረዋል፤ ይኸውም ቍ1 ላይ "ደስ አላት ... ሐሴት ያድርጉ"፤ ቍ8 ላይ "ሐሴት አደረገች ... ደስ አላቸው" የሚለው መመልከት ይቻላል። በብሉይ ኪዳን የቅኔ መጻሕፍት ውስጥ ሐሳብን እንዲህ ባለው መንገድ እያገላበጡ ማስቀመጥ የተለመደ ዘይቤ ነው።

*97፥1-6፤* ለሕዝቦች ሁሉ የተሰጠ ምስክርነት ነው፤ የምድር ሕዝቦች ወለል ብሎ የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ክብርና ግርማ በሚገባ ስለ ተመለከቱ (ቍ2-6)፣ እነርሱም ከእስራኤል ጋር በእግዚአብሔር መንገሥ ሐሴት ሊያደርጉ ይገባል።

97፥1 *እግዚአብሔር ነገሠ፤* 93፥1 እና ማብ ይመ። *ምድር፤* 96፥1፤99፥1፤117፥1 እንዲሁም የ9፥1 ማብ ይመ። *በሩቅ ያሉ የባሕር ጠረፎች፤* ራቅ ብለው ያሉ አገሮች እንኳን በመር

2 ደመናና ጥቅጥቅ ያለ ጭጋግ በዙሪያው
አለ፤
ጽድቅና ፍትሕ የዙፋኑ መሠረት
ናቸው።
3 እሳት በፊቱ ይሄዳል፤
በዙሪያው ያሉትንም ጠላቶቹን ይፈጃል።
4 መብረቁ ዓለምን አበራ፤
ምድርም አይታ ተንቀጠቀጠች።
5 ተራሮች በእግዚአብሔር ፊት፣
በምድርም ሁሉ ጌታ ፊት እንደ ሰም
ቀለጡ።
6 ሰማያት ጽድቁን ያውጃሉ፤
ሕዝቦችም ሁሉ ክብሩን ያያሉ።
7 ለተቀረጸ ምስል የሚሰግዱ፣
በጣዖታትም የሚመኩ ሁሉ ይፈሩ፤
እናንተ አማልክት ሁሉ፤ ለእርሱ ስገዱ።
8 እግዚአብሔር ሆይ፤ ስለ ፍርድህ፣
ጽዮን ሰምታ ደስ አላት፤
የይሁዳም ሴት ልጆች ሐሤት አደረጉ።
9 እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ በምድር
ሁሉ ላይ ልዑል ነህና፤
ከአማልክትም ሁሉ በላይ እጅግ ከፍ
ያልህ ነህ።
10 እግዚአብሔርን የምትወዱ ክፉትን ጥሉ፤
እርሱ የታማኞቹን ነፍስ ይጠብቃልና፤
ከዐመፀኞችም እጅ ይታደጋቸዋል።
11 ብርሃን ለጻድቃን፣
ሐሤትም ልባቸው ለቀና ወጣ።
12 እናንተ ጻድቃን በእግዚአብሔር ደስ
ይበላችሁ፤
ቅዱስ ስሙንም አመስግኑ።

## መዝሙር 98

### የዓለም ሁሉ ዳኛ

መዝሙር

1 ለእግዚአብሔር አዲስ ዝማሬ አቅርቡ፤
እርሱ ድንቅ ነገሮችን አድርጎአልና፤
ቀኝ እጁ፣ ቅዱስ ክንዱም፣
ማዳንን አድርገውለታል።
2 እግዚአብሔር ማዳኑን አሳወቀ፤
ጽድቁንም በሕዝቦች ፊት ገለጠ።
3 ለእስራኤል ቤት ምሕረቱን፣
ታማኝነቱንም አሰበ፤
የምድር ዳርቻዎችም ሁሉ፣
የአምላካችንን ማዳን አዩ።

97፥2 ዘፀ19፥9፤ኢዮ22፥14፤መዝ89፥14
97፥3 2ሳሙ22፥9፤ ኢሳ9፥19፤ዳን7፥10፤ ኢል1፥19፤2፥3፤ዕን3፥5
97፥4 2ሳሙ22፥8፤ ኢዮ36፥30፤መዝ18፥7፤104፥32፤ራእ6፥12
97፥5 ኢሱ3፥11፤ መዝ22፥14፤46፥2፡6
97፥6 መዝ19፥1፤ 50፥6፤98፥2
97፥7 ዘፀ12፥12፤ዘሌ26፥1፤ዘዳ5፥8፤መዝ16፥4፤ኢሳ42፥17፤ ኤር10፥14፤ዕብ1፥6
97፥8 መዝ9፥2፤ 48፥11
97፥9 ኢዮ34፥29፤ መዝ7፥8፤47፥9
97፥10 ኢዮ28፥28፤ መዝ31፥23፤34፥7፤37፥28፡40፤145፥20፤ምሳ2፥8፤ኤር15፥21፤20፥13፤ዳን3፥28፤6፥16፤ አሞ5፥15፤ሮሜ12፥9
97፥11 ኢዮ22፥28፤ መዝ7፥10፤11፥5
97፥12 ኢዮ22፥19፤ ዘፀ3፥15፤መዝ99፥31 104፥34፤ኢሳ41፥16፤ ፊል4፥4

98፥1 ዘፀ15፥1፡6፤ኢሱ4፥24፤ኢዮ40፥9፤መዝ30፥4፤44፥3፤96፥1፡3፤ ኢሳ12፥5፤51፥9 ፤52፥10፤53፥1፤59፥16፤63፥5፤ ሉቃ1፥51
98፥2 መዝ67፥2፤ 97፥6፤ኢሳ52፥10፤ሉቃ3፥6
98፥3 ዘፍ49፥10፤ 1ዜና16፥15፤መዝ48፥10፤50፥23

ክብ ሊደረስባቸው ተችሎአል (1ነገ9፥26-28፤ 10፥22፤ ኢሳ60፥9፤ ዮና1፥3 ይመ)።

*97፥2-6፤* የእግዚአብሔር ገናና ክብር በሰማያት በተለይም በሚያስፈራው ነጐድጓድ ላይ ተገልጦአል (18፥7-15 እና ማብ፤ የመዝ29 መግቢያ ይመ)።

97፥2 *ደመናና ጥቅጥቅ ያለ ጭጋግ፤* ፀሓይን የሸፈነውና (የከለለውና) በሰማያትም ላይ እንደ መጋረጃ የተዘረጋው ጥቁር ደመና እንደ እሳት የሚያበራውና እንደ መብረቅ የሚያንጸባርቀው የእግዚአብሔር ክብር ከፍጥረታት ዐይን መከለል (መሰወር) እንዳለበት የሚያሳስብ ግሩም ምስሌያዊ መግለጫ ነው (ዘፀ19፥9፤ 1ነገ8፥12 ይመ)። ልክ እንዲሁ ቅድስተ ቅዱሳን የተባለው ስፍራ በመጋረጃ ተለይቶ በጨለማ ውስጥ እንዲቀመጥ ተደርጓል (ዘፀ26፥33፤ 2ዜና3፥14 ይመ)። *ጽድቅ፤* ቍ6 እንደዚሁም የ4፥1 ማብ ይመ። *የዙፋኑ መሠረት፤* እግዚአብሔር የሚገዛው በኀይሉ ነው (66፥7 ይመ)፤ መንግሥቱ የቆመው ግን በጽድቅና በፍትሕ ላይ ነው፤ ይህንንም ሰማያት ያውጃሉ (ቍ6 እና ማብ ይመ)።

97፥3 *እሳት፤* ነጐድጓዳማ በሆነ ደመና ውስጥ የሚገለጠውን የመብረቅ ብልጭታ (ቍ4 ይመ) ዓለምን በሚያበራ መብረቅ የተገለጠ እሳት ሲሆን እሳት የእግዚአብሔርን የፍርድ ቍጣ ያመለክታል (21፥9፤ 50፥3፤ 83፥14፤ ዘዳ4፥24፤ 9፥3፤ 32፥22፤ 1ነገ19፥12፤ ኢሳ10፥17፤ 30፥27፡30 ይመ)።

97፥4 *ምድር፤* በዚህ ቦታ ምናልባት ያለንባትን ምድር ሳያመለክት አይቀርም።

97፥6 *ጽድቁን ያውጃሉ፤* የተንጣለለው ሰማይ ስለ እግዚአብሔር የሚናገረው ነገር አለው (19፥1-4 ይመ)፤ የዓለማት ሥርዐት እግዚአብሔር የጽድቅ አምላክ መሆኑንም ይመሰክራሉ (የ96፥10 ማብ ይመ)። *ሕዝቦችም ሁሉ ... ያያሉ፤* ቍ2-6 ጥቅስ ወይም ለሰዎች ሁሉ ስለተሰጠው መገለጥ ይናገራል።

*97፥7፤* የመዝሙሩ ማእከል ከመሆኑም በላይ (የ6፥6 ማብ ይመ) የመዝሙሩን ዐቢይ ሐሳብ በተለየ መልክ የሚያቀርብ ነው። የእግዚአብሔርን ታላቅነት የሚያውቁ ሁሉ ሐሤት ያደርጋሉ፤ የሐሰት አማልክትን የሚከተሉ ያፍራሉ፣ ይዋረዳሉም። *ስገዱ፤* ሕዝቡ በሞኝነት የሚያመልካቸው አማልክት ራሳቸው ለእግዚአብሔር ወድቀው እንዲሰግዱ በምፀት የሚናገር ነው (ቍ9፤ እንዲሁም 29፥1 እና ማብ ይመ)።

*97፥8-12፤* እግዚአብሔር በመንገሡ ጽዮን ደስታዋን ትገልጻለች (ቍ8-9 ይመ)፤ ክፉትን የሚጠሉ ብቻ በእግዚአብሔር የጽድቅ አገዛዝ (ቍ11-12) ሐሤት እንደሚያደርጉ ያሳስባል።

97፥8 *ጽዮን ሰምታ፤* እግዚአብሔር፣ "በጽድቅ" (ቍ6) እንደ ነገሠ (ቍ1) ሰምታ ለማለት ነው። *ፍርድ፤* እግዚአብሔር በሰዎች ጕዳይ ውስጥ ገብቶ የሚያደርገውን የጽድቅ ሥራ (105፥7፤ኢሳ26፥9 ይመ) በተለይም በእስራኤል መካከል የፈጸመውን የማዳን ሥራ (48፥11፤ 105፥5፤ ዘዳ33፥21 ይመ) የሚያመለክት ነው።

97፥9 *ልዑል፤* የዘፍ14፥19 ማብ ይመ።

97፥10 *የታማኞቹን ነፍስ፤* የ4፥3 ማብ ይመ።

97፥11 *ብርሃን፤* 27፥1 እና ማብ ይመ፤ እንዲሁም 36፥9 ይመ። *ጻድቃን፤* ቍ12፤ እንዲሁም የ1፥5 ማብ ይመ። *ልባቸው ለቀና፤* የ4፥7 ማብ ይመ።

97፥12 *ስሙን፤* የ30፥4 ማብ ይመ።

*መዝ98፤* የእግዚአብሔርን የጽድቅ መንግሥት በደስታና በምስጋና ለማክበር የቀረበ ጥሪ ነው። የመዝሙሩ መግቢያና (መጀመሪያና) መዝጊያ (መደምደሚያ) በመዝ96 ላይ የተነገረውን አሳብ መልሶ ያስተጋባል (የመዝ93 እና 95 መግቢያን ይመ)። ሦስቱ አንጓዎች ጥሪውን እያሳደጉ በመምጣት የመጨረሻው ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያደርሱታል፤ በመጀመሪያ ጥሪው የቀረበው ለአምልኮ ወደ ቤተ መቅደስ ለመጡ ማኅበረ ምዕመናን ነው፤ ቀጥሎም በምድር ላይ ለሚኖሩ ሕዝቦች ሁሉ ነው፤ ከዚያም ለፍጥረታት በሙሉ ነው። የመጀመሪያው አንጓ እግዚአብሔር በቀድሞ ዘመን ጽድቁን ስለመግለጡ (ቍ2) የሚያሳስብ ነው፤ የመጨረሻው አንጓ ደግሞ ወደ ፊት ስለሚመጣው፣ "የጽድቅ" (ቍ9) መንግሥቱ ይናገራል፤ መካከለኛው አንጓ፣ "በእግዚአብሔር እልል በሉ" (ቍ4፡6) በሚለው የደስታ ንግግር የታጀበ ነው።

*98፥1-3፤* እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ ያደረገው የማዳን ሥራ በዝማሬ ለማወደስ የቀረበ ጥሪ ነው።

98፥1 *አዲስ ዝማሬ፤* የ33፥3 ማብ ይመ። *ድንቅ ነገሮችን፤* የ9፥1 ማብ ይመ።

98፥2 *አሳወቀ ... በሕዝቦች ፊት ገለጠ፤* እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል የሚያደርገው የማዳን ሥራ ለሌሎች ሕዝቦችም ማንነቱን የሚያስታውቅበት መንገድ ነው፤ በዚህ መልኩ ሲታይ እግዚአብሔር የራሱ ወንጌላዊ ነው ማለት ነው (የ46፥10 ማብ፤ ኢሳ 52፥10 ይመ)። *ማዳኑን ... ጽድቁን፤* የእግዚአብሔር የማዳን ሥራ የእርሱን ጽድቅ ይገልጣል (የ4፥1፤ 71፥24 ማብ ይመ)።

98፥3 *ምሕረቱን፣ ታማኝነቱንም፤* ፍቅርና ታማኝነት ለማለት ነው (የ36፥5 እና የ3፥7 ማብ ይመ)። እንዲህ ያለው ድርብ አገላለጽ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን እንደሚጠብቅ የሚያረጋግጥ ነው (የ6፥4 ማብ ይመ)።

*98፥4-6፤* ምድር ሁሉ እግዚአብሔርን ለማመስገን በሚደረገው ክብረ በዓል ላይ በአንድነት እንዲነሡ የሚያሳስብ ጥሪ ነው።

4 ምድር ሁሉ *ለእግዚአብሔር* እልል በሉ፤
ውዳሴን አፍልቁ፤ በደስታና በዝማሬ
አመስግኑ፤
5 *ለእግዚአብሔር* በገና ደርድሩለት፤
በበገናና በዝማሬ ድምፅ ዘምሩለት፤
6 በእንቢልታና በመለከት ድምፅ፣
በንጉሡ *በእግዚአብሔር* ፊት እልል
በሉ።

7 ባሕርና በውስጧ ያለው ሁሉ፣
ዓለምና የሚኖሩባትም ሁሉ ያስገምግሙ።
8 ወንዞች በእጃቸው ያጨብጭቡ፤
ተራሮችም በአንድነት ይዘምሩ፤
9 እነዚህ *በእግዚአብሔር* ፊት ይዘምሩ፤
እርሱ በምድር ላይ ሊፈርድ ይመጣልና፤
በዓለም ላይ በጽድቅ፣
በሕዝቦችም ላይ በእውነት ይበይናል።

## መዝሙር 99

### ጻድቅና ቅዱስ አምላክ

1 *እግዚአብሔር* ነገሠ፤
ሕዝቦች ይንቀጥቀጡ፤
በኪሩቤል ላይ በዙፋን ተቀምጦአል፤
ምድር ትናወጥ።
2 *እግዚአብሔር* በጽዮን ታላቅ ነው፤
ከሕዝቦችም ሁሉ በላይ ከፍ ከፍ
ብሎአል።
3 ታላቁንና አስፈሪውን ስምህን ይወድሱ፤
እርሱ ቅዱስ ነው።

4 ፍትሕን የምትወድ፣ ኀያል ንጉሥ ሆይ፤
አንተ ትክክለኛነትን መሠረትህ፤
ፍትሕንና ቅንነትንም፣
ለያዕቆብ አደረግህ።
5 አምላካችንን *እግዚአብሔርን* ከፍ ከፍ
አድርጉት፤
በእግሩ መርገጫ ስገዱ፤
እርሱ ቅዱስ ነውና ።

6 ሙሴና አሮን ካህናቱ ከሆኑት መካከል
ነበሩ፤
ሳሙኤልም ስሙን ከጠሩት መካከል
አንዱ ነበረ፤
እነርሱ ወደ *እግዚአብሔር* ተጣሩ፤
እርሱም መለሰላቸው።
7 ከደመና ዐምድ ውስጥ ተናገራቸው፤
እነርሱም ሥርዐቱንና የሰጣቸውን
ድንጋጌ ጠበቁ።

98፥4 መዝ20፥5፤ ኢሳ12፥6፤44፥23፤ 52፥9፤54፥1፤55፥12
98፥5 መዝ33፥2፤ 92፥3፤147፥7፤ኢሳ 51፥3
98፥6 ዘፀ19፥13፤ዘኍ 10፥2፤2ሳሙ6፥15፤ መዝ2፥6፤20፥5፤47፥7 ፤100፥1፤ኢሳ12፥6
98፥7 መዝ24፥1፤ 93፥3
98፥8 2ነገ11፥12፤ መዝ148፥9፤ኢሳ 44፥23፤55፥12
98፥9 መዝ96፥10
99፥1 ዘፀ15፥14፤ 25፥22፤2ሳሙ6፥2፤ 1ዜና16፥30፡31፤መዝ 97፥1
99፥2 ዘፀ15፥1፤ መዝ2፥6፤46፥10፤48፥ 1፤97፥9፤113፥4፤ 148፥13
99፥3 ዘፀ15፥11፤ዘሌ 11፥44፤መዝ30፥4፤33 ፥2፤76፥1፤97፥12፤ 103፥1፤106፥47፤111 ፥10፤145፥21፤148፥5 ፤ራእ4፥8
99፥4 ዘዳ18፥19፤ 1ነገ10፥9፤መዝ2፥6፤9 8፥9፤ራእ15፥3
99፥5 ዘፀ15፥2 99፥6 ዘፀ24፥6፤28፥1፤1ሳሙ7፥5፤መዝ4፥3፤91፥15
99፥7 ዘፀ13፥21፤ 19፥9፤ዘኍ11፥25

*98፥4፤* 100፥1 ይመ። *ምድር ሁሉ፤* በምድር ላይ የሚኖሩ ሕዝቦች ሁሉ ማለት ነው (96፥1 እና ማብ፤ እንዲሁም 99፥1 ይመ)።

98፥5 *በገና፤* የዘፍ31፥27 ማብ ይመ።

98፥6 *እምቢልታ፤* በጣም ረጅምና ቀጥ ያለ የሙዚቃ መሣሪያ ነው (በዳዊት መዝሙራት ወይም በመጽሐፈ መዝሙር ውስጥ በዚህ ስፍራ ብቻ የተጠቀሰ ቃል ነው፤ የዘኍ10፥2-3፡10 ማብ ይመ)። *በመለከት፤* በጣም የተለመደ የእምቢልታ ዐይነት ነው (47፥5፤ 81፥3፤ 150፥3 እና ኢዮ2፥1 ማብ ይመ)።

*98፥7-9፤* ፍጥረት ሁሉ ለምስጋና እንዲያመጡ የቀረበ ጥሪ ነው (የ96፥11-12 ማብ ይመ)።

98፥7 *ባሕር ...ዓለም፤* የፍጥረታት መኖሪያና መስማሪያ ከሆኑት ውስጥ እነዚህ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

98፥8 *ወንዞች ... ተራሮች፤* ከወንዞች እስከ ተራሮች እንዲሁም በምድር ላይ የሚኖሩ ማናቸውም ፍጥረታት ሁሉ ያጨብጭቡ ይዘምሩ (የ65፥13 ማብ ይመ)።

98፥9 *ሊፈርድ ይመጣል፤* 96፥13 እና ማብ ይመ። እስራኤል ባለፈው ዘመንም ሆነ (ቍ1-3 ይመ) በሚመጣው ዘመን፣ በእግዚአብሔር የጽድቅ ሥራ (ማዳን) ላይ ተመሥርታ ትኖራለች።

*መዝ99፤* እግዚአብሔር በጽዮን ታላቅና ቅዱስ ንጉሥ ሆኖ በመንገሡ እርሱን ለማመስገን የቀረበ ዝማሬ ነው። ባለቅኔው የግጥሙን ዋና ሐሳብ ለማስፋፋት ሲል፣ "ሰባት" ቍጥርን ልዩ በሆነ መልክ ይጠቀማል፤ ሰባት ጊዜ፣ "የእግዚአብሔርን" ስም ይጠቅሳል፤ ሰባት ጊዜ ደግሞ እግዚአብሔርን በሚያመለክት ተውላጠ ስም (በዕብራይስጥ) ይጠቀማል (የመዝ93 መግቢያን ይመ)። ባለቅኔው የሰባት ቍጥርን ተምሳሌታዊ ይዘት (ፍጹምነትን የሚያመለክት ቍጥር ነው) በሚያስደንቅ ሁኔታ ተጠቅሞአል። የመዝሙሩ ቅርጽ (በዕብራይስጥ) እኩኩል ሲሆን እያንዳንዳቸው ሦስት መስመር ያላቸው አራት አንጓዎች አሉት፤ እያንዳንዱ ዐቢይ ክፍል የሚደመደመው በዐቢይ አዝማች ነው (ቍ5፡9)። "እርሱ ቅዱስ ነው" (በቍ3፡5 ተስፋፍቶ ደግሞ በቍ9 ላይ) የሚለው ሐረግ ሦስት ጊዜ የተጠቀሱ በመሆኑ ምናልባት በቅዳሴ ሥርዐት ላይ የነበረውን ልማድ ሳያመለክት አይቀርም (ኢሳ6፥3፤ ራእ4፥8፤ መዝ96፥1-3፡7-9 እና ማብ ይመ)። የመዝሙሩ ሁለተኛ ክፍል በመዝሙሩ ሁለተኛ አንጓ ውስጥ የተጠቀሰውን ዋና ሐሳብ ያብራራል።

*99፥1-3፤* በጽዮን የነገሠው አምላክ በሕዝቦች ሁሉ ላይ ጌታ በመሆኑ ሕዝቦች ሁሉ እርሱ ማን እንደ ሆነ ሊያውቁት ይገባል።

99፥1 *እግዚአብሔር ነገሠ፤* 9፥1 እና ማብ ይመ። *ይንቀጥቀጡ ...ትናወጥ፤* እግዚአብሔርን በመፍራትና በማክበር ማለት ነው። *ኪሩቤል፤* 80፥1 እና የዘፀ25፥18 ማብ ይመ።

99፥3 *ይወድሱ፤* እርሱ ታላቅ ንጉሥ በመሆኑ ሊፈራና (ቍ1) ሊከበር ይገባዋል። *ቅዱስ፤* ቍ5፡9፤ የዘሌ11፥44 ማብ ይመ።

*99፥4-5፤* እግዚአብሔር ለእስራኤል ባደረገው በጎነት የእርሱን አገዛዝ ባሕርይ (ምንነት) አሳይቶአል።

*99፥4፤* 103፥6-12 ይመ። *ፍትሕን የምትወድ ኀያል፤* ኀይልና ፍትሕ የእግዚአብሔር መንግሥት ዋና ዋና ባሕርያት ናቸው። *ትክክለኛነትን መሠረትህ፤* ዙፋንህ አድርገህ አቆምህ ለማለት ነው (9፥7-8፤ 97፥2፤ 2ሳሙ7፥13 ይመ)። *ያዕቆብ፤* የእስራኤል ሌላ ስሙ ነው (ዘፍ32፥28 ይመ)። *ፍትሕንና ቅንነትንም፤* በ97፥2 ላይ እንደ ተመለከተው ፍትሕና ጽድቅ ማለት ነው። ሰማያት የእግዚአብሔርን ጽድቅ ቢያውጁም (97፥6 እና ማብ ይመ)፣ የእግዚአብሔር ጽድቅ ልዩ በሆነ መንገድ የሚገለጠው (98፥2 እና ማብ ይመ)፣ እግዚአብሔር ለእስራኤል በሚያደርገው የማዳን ሥራ ውስጥ ነው።

*99፥5፤* ቍ9 ይመ። የመዝ42-43 መግቢያ ይመ። *በእግሩ መርገጫ፤* የእግዚአብሔር የእግሩ መርገጫ ሲሆን (2ዜና9፥18)፣ ተምሳሌታዊ በሆነ መንገድ የሰማዩን ዙፋን ከምድር ዙፋን ጋር የሚያገናኝ ነው፤ እግዚአብሔር በሰማይ ዙፋን ላይ ሲቀመጥ የምድር ዙፋኑ የእግሩ መርገጫ ይሆናል (እዚህ ላይ ቅዱስ ተራራውን ያመለክታል፤ ቍ9፤ 132፥7፤ 1ዜና28፥2፤ ሰቆ2፥1 ይመ)።

*99፥6-7፤* እግዚአብሔር በእስራኤል መካከል አማላጅ ካህናትን ያስቀመጠ ሲሆን፣ እነርሱም (1) በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል በመሆን ወደ እግዚአብሔር የሚጣሩ ሰዎችን (ቍ6) ከእርሱ ጋር እንዲያገናኙ የተሾሙና (2) የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከተረዱ በኋላ የእስራኤልን ሕዝብ እንዲመሩ ኀላፊነት የተሰጣቸው ናቸው።

99፥6 *ሙሴና አሮን ... ሳሙኤልም፤* በዚህ ቦታ እነዚህ ሦስት ሰዎች ከእስራኤል ሕዝብ መካከል ታላቅ መከራና መዓት በተከሠተ ጊዜ፣ እግዚአብሔር እንደ መካከለኛ (እንደ አማላጅ) የተጠቀመባቸውን ሰዎች ሁሉ የሚወክሉ ናቸው። *ካህናቱ ... ስሙን ከጠሩት፤* ካህናት ያላቸው የማስታረቅ አገልግሎት አጽንኦት ተሰጥቶታል (ዘፀ17፥11 እና ማብ፤ 32፥11-13፡31-32 ዘኍ14፥13-19፤ 21፥7፤ 1ሳሙ7፥5፡8-9፤ 12፥19፡23፤ ኤር15፥1 ይመ)። *መለሰላቸው፤* ቍ8 ይመ፤ በቍ6-7 ላይ ለተጠቀሰው ማብ እግዚአብሔር የሰጠውን ምላሽ ይመ።

99፥7 *ከደመና ዐምድ ውስጥ ሆኖ ተናገራቸው፤* የእስራኤልን ሕዝብ ሁሉ የሚያመለክት ቢሆንም ("ተናገራቸው")፣ ከዚህ ይልቅ ግን ይህ መዝሙር እግዚአብሔር ከሙሴና (ዘፀ33፥9

6የምድረ በዳ እርኩም መሰልሁ፤
በፍርስራሽ መካከል እንዳለ ጒጒት
ሆንሁ።
7ያለ እንቅልፍ አድራለሁ፤
በቤቴ ጒልላት ላይ እንዳለ ብቸኛ ወፍ
ሆንሁ።
8ጠላቶቼ ቀኑን ሙሉ ይዘልፉኛል፤
የሚያክፋፉኝም ስሜን እንደ ርግማን
ቈጥረውታል።
9ዐመድ እንደ እህል ቅሜአለሁና፤
መጠጤንም ከእንባ ጋር ቀላቅያለሁ።
10ከቊጣህና ከመዓትህ የተነሣ፣
ወደ ላይ አንሥተኸኝ የነበርሁትን
መልሰህ ባልኸኝ።
11ዘመኖቼ እንደ ምሽት ጥላ ናቸው፤
እኔም እንደ ሣር ደርቄአለሁ።

12*እግዚአብሔር* ሆይ፤ አንተ ግን ለዘላለም
በዙፋንህ ተቀምጠሃል፤
ስምህም ከትውልድ እስከ ትውልድ
ይኖራል።
13ትነሣለህ፤ ጽዮንንም በርኅራኄ ዐይን
ታያለህ፤
ለእርሷ በጎነትህን የምታሳይበት ዘመን
ነውና፤
የተወሰነውም ጊዜ ደርሶአል።
14አገልጋዮችህ በድንጋዮቿ ደስ ይሰኛሉ፤
ለዐፈሯም ይሳሳሉ።
15ሕዝቦች *የእግዚአብሔርን* ስም፣
የምድርም ነገሥታት ሁሉ ክብርህን
ይፈራሉ።
16*እግዚአብሔር* ጽዮንን መልሶ ይሠራታልና፤
በክብሩም ይገለጣል።

17እርሱ ወደ ችግረኞች ጸሎት
ይመለከታል፤
ልመናቸውንም አይንቅም።

18ወደ ፊት የሚፈጠር ሕዝብ *እግዚ
አብሔርን* ያወድስ ዘንድ፣
ይህ ለመጪው ትውልድ እንዲህ
ተብሎ ይጻፍ፤
19"*እግዚአብሔር* በከፍታ ላይ ካለው
መቅደሱ ወደ ታች ተመልክቶአልና፤
ከሰማይም ሆኖ ምድርን አይቶአል፤
20ይኸውም የእስረኞችን ጩኸት ይሰማ
ዘንድ፣
ሞት የተፈረደባቸውንም ያድን ዘንድ
ነው።"

21ስለዚህ *የእግዚአብሔር* ስም በጽዮን፣
ምስጋናውም በኢየሩሳሌም ይታወጃል፤
22ይህም፣ ሕዝቦችና መንግሥታት፣
*እግዚአብሔርን* ለማምለክ በአንድነት
ሲሰበሰቡ ይሆናል።

23ብርታቴን መንገድ ላይ ቀጨው፤[w]
ዕድሜዬንም ባጭሩ አስቀረው።
24እኔም እንዲህ አልሁ፤
"አምላኬ ሆይ፤ በዘመኔ እኵሌታ
አትውሰደኝ፤
ዘመናትህ ከትውልድ እስከ ትውልድ
ይኖራሉ።
25አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ፤

102፥6 ዘሌ14፥15-17፤ኢዮ30፥29፤ኢሳ34፥11፤ሶፎ2፥14
102፥7 መዝ38፥11፤77፥4
102፥8 ዘዐ22፥28፤መዝ31፥11፤42፥10፤ኢሳ65፥15፤ኤር24፥9፤25፥18፤42፥18፤44፥12፤ሕዝ14፥8፤ዘካ8፥13፤ሉቃ22፥63-65፤23፥35-37
102፥9 መዝ6፥6፤42፥3፤80፥5፤ኢሳ44፥20
102፥10 መዝ7፥11፤38፥3
102፥11 ዜና29፥15፤ኢዮ8፥12፤14፥2፤መዝ39፥6፤ያዕ1፥10
102፥12 ዘፀ3፥15፤15፥18፤መዝ135፥13፤ኢሳ55፥13፤63፥12
102፥13 ዘፀ13፥10፤ዘዳ32፥36፤1ነገ13፥26፤መዝ44፥26፤77፥7፤119፥126፤ኢሳ54፥8፤60፥10፤ዳን8፥19፤ዘካ10፥6፤ሐሥ1፥7
102፥15 1ነገ8፥43፤መዝ67፥7፤76፥12፤138፥4፤148፥11፤ኢሳ2፥2
102፥16 መዝ8፥1፤51፥18፤ኢሳ60፥1-2
102፥17 1ነገ8፥29፤መዝ4፥1፤6፥9
102፥18 መዝ22፥31፤ሮሜ4፥24
102፥19 መዝ53፥2
102፥20 መዝ68፥6፤ሉቃ4፥19
102፥21 መዝ9፥14፤22፥22
102፥22 መዝ22፥27፤ኢሳ49፥22-23፤ዘካ8፥20-23
102፥23 መዝ39፥5 102፥24 ዘፍ21፥33፤ኢዮ36፥26፤መዝ90፥2
102፥25 ዘፍ1፥1፤2ዜና2፥12፤መዝ8፥3፤ዕብ1፥10-12

[w]23 *ወይም በኀይሉ ብርታቴን ቀጨው*

የ90፥4-5 ማብ ይመ።

102፥6 *እርኩም ... ጒጒት፤* ከዘሌ11፥16-18 ጋር ያነጻጽሩ፤ እርኩምና ጒጒት ከፍርስራሽና ከምድረ በዳ ጋር በተያያዘ ይነገራሉ (ኢሳ34፥11፡15፤ ኤር50፥39፤ ሶፎ2፥14 ይመ)።

102፥8 *ጠላቶቼ ... ይዘልፉኛል፤* 109፥25 ይመ፤ እንዲሁም የ5፥9፤39፥8 ማብ ይመ። *ስሜን እንደ ርግማን ቈጥረውታል፤* "አንተም እንደዚያኛው ሁን" እያሉ (ማለትም እንደ መርገም ሁን) ይሰድቡኛል ማለት ነው።

102፥9 *መጠጤንም ከእንባ ጋር ቀላቅያለሁ፤* እንባ እንደ ምግብና እንደ መጠጥ ሆኖ ስለመጠቀሱ በ42፥3፤80፥5 ላይ ይመ።

102፥10 *ከቊጣህና ከመዓትህ የተነሣ፤* የ2፥5 ማብ ይመ።

*102፥11፤* የቍ3-4 ማጠቃለያ ነው።

*102፥12-17፤* ዘላለማዊው ንጉሥ የችግረኞችን ጸሎት (ቍ17) የሚሰማና ጽዮንንም መልሶ የሚሠራት መሆኑን የሚያረጋግጥ ክፍል ነው (83፥8 ማብ ይመ)።

102፥12 *ለዘላለም በዙፋንህ ተቀምጠሃል፤* ከዚህ ቀደም ብሎ ላለው የመዝሙራት ስብስብ (መዝ92-100) ማእከላዊ ሐሳብ ነው። እግዚአብሔር ከዘላለም እስከ ዘላለም የሚገዛና ምን ጊዜም ሳይለወጥ በአምላክነቱ ጸንቶ የሚኖር (ቍ27) በመሆኑ አዳኝነቱን ለመፈለግ ዐይኖቻቸውን ወደ እርሱ የሚያነሡ ሁሉ አያፍሩም። *ስምህም፤* የ30፥4 ማብ ይመ።

*102፥13፤* ይህ ቍጥርና ቍ16 በአንጓው ውስጥ ሌላ ቅንብብ የሚፈጥሩ ናቸው። እነዚህ ሁለት ቍጥሮች እንደሚያመለክቱት (ቍ14 ይመ)፣ መዝሙረኛው መከራ የደረሰበት ወደ ባቢሎን ምርኮ በመሄዱ ነው። *ትነሣለህ፤* የ3፥7 ማብ ይመ። *የምታሳይበት ዘመን፤* እግዚአብሔር ለፍርድና ለትድግና የወሰነውን ጊዜ የሚያሳይ ነው (75፥2፤ ዘፀ9፥5፤ 2ሳሙ24፥15፤ ዳን11፥27፡35 ይመ)። መዝሙረኛው እንዲህ በማለት የተናገረው ምናልባት ከነቢያት በአንዱ አስቀድሞ የተነገረው ትንቢት የሚፈጸምበት ጊዜ መድረሱን ለማመልከት ይሆናል።

102፥14 *አገልጋዮችህ በድንጋዮቿ ደስ ይሰኛሉ፤* የእግዚአብሔር ከተማ የሆነችው ጽዮን (46፥4፤ 48፥1-2፡8፤ 87፥3፤ 101፥8፤ 132፥13 ይመ) በእግዚአብሔር አገልጋዮች ይህን ያህል የተወደደች ከሆነች (መዝ126፤ 137 ይመ)፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ያላት መወደድ የቱን ያህል ይሆን!

*102፥15፤* የ46፥10 ማብ ይመ። *ስም፤* የ5፥11 ማብ ይመ።

102፥16 *በክብሩም ይገለጣል፤* ቍ15 እና የ46፥10 ማብ ይመ፤ እንዲሁም ኢሳ40፥1-5 ይመ)። ይህ ተስፋ ሙሉና ፍጹም ሆኖ የሚገለጠው፣ "በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም" ነው (ራእ21 ይመ)።

*102፥18-22፤* እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚያደርገው ማዳን፣ ምስጋናና ውዳሴ ያመጣለት ዘንድ ተጽፎ ይቀመጥ።

102፥18 *ይጻፍ፤* የእግዚአብሔር የማዳን ሥራው ተጽፎ እንዲቀመጥ፣ መዝሙረኛው ያሳሰበው በዚህ ቦታ ብቻ ነው፤ የተለመደው ግን ለመጭው ትውልድ በቃል ማስተላለፍ ነበር (22፥30፤ 44፥1፤ 78፥1-4 ይመ)። ያልተፈጠረው ካለመኖር ወደ መኖር መምጣትና መሆን የሚቻለው በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ፈቃድና ችሎታ ብቻ ነው (51፥10፤ 104፥30፤ 139፥13)።

102፥20 *የእስረኞችን ... ሞት የተፈረደባቸውን፤* ምናልባት የጦር ምርኮኞችን ለማለት ይሆናል፤ ይበልጥ ግን ወደ ባቢሎን ምርኮ የሄዱትን የሚያመለክት ነው (79፥11 እና ማብ ይመ)።

102፥21 *ምስጋናውም፤* የ9፥1 ማብ ይመ።

*102፥22፤* የ46፥10 ማብ ይመ፤ እንዲሁም 47፥9 እና ማብ ደግሞም 96፤ 98፤ 100 ይመ። በዚህ ቦታ ያለው ትንቢታዊ አገላለጽ የኢሳ2፥2-4፤ የሚክ4፥1-3 ትንቢታዊ ጥላ ያጠላበት ሳይሆን አይቀርም።

*102፥23-28፤* ማጠቃለያ ሐሳብ ነው።

*102፥23-24፤* ቍ3-11 ይመ።

*102፥24-27፤* ቍ12 እና ማብ ይመ። ቍ25-27 ያለውን ሐሳብ አዲስ ኪዳን በእንዴት ያለ መልክ ከክርስቶስ ጋር እንዳዛመደው ዕብ1፥10-12 እና የዕብ1፥10 ማብ ይመ።

ስማያትም የእጆችህ ሥራ ናቸው።
26 እነርሱ ይጠፋሉ፤ አንተ ግን ጸንተህ
ትኖራለህ፤
ሁላቸው እንደ ልብስ ያረጃሉ፤
እንደ መጐናጸፊያም ትለውጣቸዋለህ፤
እነርሱም ወዲያ ይጣላሉ።
27 አንተ ግን ያው አንተ ነህ፤
ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም።
28 የአገልጋዮችህ ልጆች ተደላድለው
ይኖራሉ፤
ዘራቸውም በፊትህ ጸንቶ ይኖራል።

## መዝሙር 103

### እግዚአብሔር ፍቅር ነው

የዳዊት መዝሙር

1 ነፍሴ ሆይ፤ *እግዚአብሔርን* ባርኪ
የውስጥ ሰውነቴም ሁሉ ቅዱስ ስሙን
ባርኪ።
2 ነፍሴ ሆይ፤ እግዚአብሔርን ባርኪ፤
ውለታውንም ሁሉ አትርሺ፤
3 ኀጢአትሽን ሁሉ ይቅር የሚል፣
ደዌሽንም ሁሉ የሚፈውስ፣
4 ሕይወትሽን ከጥፋት ጕድጓድ የሚያድን፣
ምሕረትንና ርኅራኄን የሚያቀዳጅሽ፣
5 ጕልማሳነትሽም እንደ ንስር ይታደስ
ዘንድ፣
ምኞትሽን በበጎ ነገር የሚያረካ እርሱ
ነው።
6 *እግዚአብሔር* ለተጨቈኑ ሁሉ፣
ቅን ፍርድንና ፍትሕን ይሰጣቸዋል።
7 *መንገዱን* ለሙሴ፣
ሥራውንም ለእስራኤል ሕዝብ አሳወቀ።
8 *እግዚአብሔር* መሓሪና ይቅር ባይ፣
ለቍጣ የዘገየ፣ ፍቅሩም የበዛ ነው።
9 እርሱ ሁልጊዜ በደልን አይከታተልም፤
ለዘላለምም አይቈጣም።
10 እንደ ኀጢአታችን አልመለሰልንም፤
እንደ በደላችንም አልከፈለንም።
11 ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል፣
እንዲሁ ለሚፈሩት ምሕረቱ ታላቅ ናት።
12 ምሥራቅ ከምዕራብ እንደሚርቅ፣
መተላለፋችንን በዚያው መጠን ከእኛ
አስወገደ።
13 አባት ለልጆቹ እንደሚራራ፣
*እግዚአብሔር* ለሚፈሩት እንዲሁ
ይራራል።
14 እርሱ አፈጣጠራችንን ያውቃልና፤
ትቢያ መሆናችንንም ያስባል።
15 ሰው እኮ ዘመኑ እንደ ሣር ነው፤
እንደ ዱር አበባ ያቈጠቍጣል፤
16 ነፋስ በነፈሰበት ጊዜ ግን ድራሹ ይጠፋል፤
ምልክቱም በቦታው አይገኝም።
17 *የእግዚአብሔር* ምሕረት ግን፣

102፥26 ኢሳ13፥10፡13፤34፥4፤51፥6፤ሕዝ32፥8፤ኢዩ2፥10፤ማቴ24፥35፤2ጴጥ3፥7-10፤ራእ20፥11
102፥27 ዘኍ23፥19፤መዝ9፥7፤ዕብ13፥8፤ያዕ1፥17
102፥28 መዝ25፥13፤69፥36፤89፥4
103፥1 መዝ28፥6፤30፥4፤104፥1
103፥2 ዘዳ6፥12፤መዝ77፥11፤106፥11፤117፥1
103፥3 ዘፀ15፥26፤34፥7፤ቈላ3፥13፤1ጴጥ2፥24፤1ዮሐ1፥9
103፥4 መዝ8፥5፤23፥6፤34፥22፤56፥13፤ኢሳ43፥1
103፥5 ዘፀ19፥4፤ኢዮ33፥25፤መዝ90፥14፤104፥28፤119፥25፡93፤2ቆሮ4፥16
103፥6 መዝ9፥8፤65፥5፤74፥21፤ኢሳ9፥7፤ሉቃ4፥19
103፥7 ዘፀ33፥13፤መዝ99፥7፤106፥22፤147፥19
103፥8 ዘፀ22፥27፤መዝ86፥15፤ሚክ7፥18-19፤ያዕ5፥11
103፥9 መዝ30፥5፤79፥5፤ኢሳ57፥16፤ኤር3፥5፡12፤ሚክ7፥18
103፥10 ዕዝ9፥13፤ሮሜ6፥23

103፥11 2ዜና6፥31 ፤መዝ13፥5፤57፥10፤100፥5፤106፥45፤117፥2፤ሰቆ3፥22፤ኤፌ3፥18 103፥12 2ሳሙ12፥13፤ሮሜ4፥7፤ኤፌ2፥5 103፥13 ሚል3፥17፤1ዮሐ3፥1 103፥14 ዘፍ2፥7፤መዝ119፥73፤139፥13-15፤146፥4፤ኢሳ29፥16 103፥15 ኢዮ14፥2፤መዝ37፥2፤90፥5፤102፥11፤ኢሳ40፥6፤ያዕ1፥10 103፥16 ኢዮ7፥8፤ኢሳ40፥7፤ሐጌ1፥9 103፥17 ዘፍ48፥11፤ዕዝ9፥12

102፥26 *እንደ ልብስ፤* በመጀመሪያ ሥነ ፍጥረቱ እግዚአብሔር የክብሩን ብርሃን ተጐናጽፎአል (8፥1፡3-4፤ 19፥1፤ 29፥3-9፤ 104፥1፡31፤ ኢሳ6፥3፤ እንዲሁም ኢዮ38-41 በተለይ ደግሞ 40፥10 ይመ)። ነገር ግን ከፈጠራቸው ነገሮች ሁሉ በላይ ገኖና ጸንቶ የሚኖር ነው፤ የመጀመሪያ ሥነ ፍጥረቱ ለአዲስ ሥነ ፍጥረቱ ቦታ ይለቃል፤ እርሱ ግን መቼም አይለወጥም (ኢሳ 65፥17፤ 66፥22 ይመ)።

*102፥28፤* እግዚአብሔር ከቶ የማይለወጥ አምላክ በመሆኑ (ቍ27)፣ የእስራኤል የወደፊት ዋስትና የሚያስተማምን ነው (ሚል3፥6 ይመ)። *በፊትህ ... ይኖራል፤* ወይም "በተስፋዪቱ ምድር ይቀመጣሉ" (69፥36፤ እንዲሁም 37፥3፡29፤ ኢሳ65፥9 ይመ) *በፊትህ ጸንቶ ይኖራል፤* 2ሳሙ7፥24 ይመ።

*መዝ103፤* እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያሳየውን ፍቅርና ርኅራኄ የሚያወድስ ዝማሬ ነው (የ101 መግቢያን ይመ)። መዝሙሩ የተቀነበበው እግዚአብሔርን አመስግኑ በሚለው ጥሪ ነው (ቍ1-2፡ 20-22)። የምስጋናው ጥሪ በሁለት እኩል ባልሆኑ ክፍሎች ቀርቦአል (1) የመጀመሪያው ሦስት ቍጥሮች (ከቍ3-5) መዝሙረኛው ከእግዚአብሔር ስለ ተቀበለው ምሕረት ሲናገሩ (2) የተቀሩት 14 ቍጥሮች ደግሞ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ለእስራኤል ያደረገውን ይቅርታና ምሕረት ያስታውሳሉ (ቍ6-19)። የመዝሙሩ ዐቢይ ክፍል (ቍ6-19) በስድስት በስድስት ቤት የተዘጋጀ ሲሆን በቍ6 እና 19 ተቀንብቦአል፤ ቍ6 እና 19 የእግዚአብሔርን አገዛዝ አጠቃላይ ባሕርይ ይገልጻሉ። በስድስት በስድስት ቤት የተዘጋጀው ዐቢይ ክፍል በሁለት እኩል ቦታ ይከፈላል (ቍ7-12፡ 13-18)። የመጀመሪያው ክፍል እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያደረገውን በጉነት የሚያመሰግን ሲሆን፣ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ እግዚአብሔር ትቢያ ለሆነው ሰው ያሳየውን ርኅራኄ የሚናገር ነው። እንደ መዝሙር 33 ሁሉ የዚህም መዝሙር ርዝመት የተወሰነው የዕብራይስጡን የፊደል ገበታ መሠረት በማድረግ ነው (የመዝ33 መግቢያን ይመ)።

*103፥1-2፤* እግዚአብሔርን ለማመስገን የቀረበ ጥሪ ሲሆን ጥሪው የቀረበው ለውስጣዊ ሕዋሳቶች ወይም ሰውነቶች ነው ቍ20-22 ጋር ያነጻጽሩ።

103፥1-2፡22 *ነፍሴ ሆይ፤* አንድ ሰው ራሱን አስመልክቶ የሚናገርበት የተለመደ አባባል ነው (104፥1፡35፤ 116፥7 ይመ)። *ነፍሴ፤* የ6፥3 ማብ ይመ።

*103፥3-5፤* መዝሙረኛው ስለ ተደረገለት በጎ ነገር ደጋግሞ ያመሰግናል።

103፥4 *የሚያድን፤* "የሚዋጅ" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ቃል ነው። *ጕድጓድ፤* መቃብር ለሚለው ቃል ተለዋዋጭ ሆኖ የገባ ቃል ነው (የ30፥1 ማብ ይመ)። *ምሕረትንና ርኅራኄን፤* የዚህ መዝሙር ቍልፍ ቃላት ናቸው (ቍ8፡11፡13፡17 ይመ)። *ምሕረት፤* ቍ8፡11፡17፤ እንዲሁም የ6፥4 ማብ ይመ።

103፥5 *ጕልማሳነትሽም እንደ ንስር ይታደስ ዘንድ፤* እንደ ንስር በፍጹም ብርታት እንዲኖር ነው (ኢሳ40፥31 ይመ)።

*103፥6-19፤* እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለውን ፍቅርና ርኅራኄ የሚያሳይ ክፍል ነው።

*103፥6፤* ይህ ቍጥር ከቍ19 ጋር በመሆን እስራኤል ከእግዚአብሔር ያገኙትን የተትረፈረፈ በረከት በግልፅ ያሳያል። *ቅን ፍርድን፤* ቍ17 ይመ፤ እንዲሁም የ4፥1 ማብ ይመ።

*103፥7-12፤* እግዚአብሔር ለኀጢአተኛ ሕዝቡ ያለውን ርኅራኄ ያሳያል።

*103፥7-8፤* 99፥7፤ ዘፀ33፥13 ይመ፤ እንዲሁም የዘፀ34፥6-7 ማብ ይመ።

103፥7 *መንገዱን፤* 25፥10 እና ማብ ይመ።

103፥9 *አይቈጣም፤* የ2፥5 ማብ ይመ።

*103፥11-12፤* ስፍር ቍጥር የሌለው የእግዚአብሔር ፍቅር የእስራኤልን ኀጢአት ይቅር በማለት በግልጽ ታይቶአል።

*103፥11፤* 36፥5-9 ይመ። *እንዲሁ ... ታላቅ ናት፤* የተንሰራፋ ነው። *ለሚፈሩት፤* ቍ13፡17-18፤ እንዲሁም 34፥8-14 እና ማብ ይመ።

*103፥12፤* ኢሳ1፥18፤ 38፥17፤ 43፥25፤ ኤር31፥34፤ 50፥20፤ ሚክ7፥18-19 ይመ።

*103፥13-18፤* ትቢያ ለሆኑ ሕዝቦች እግዚአብሔር ያለውን የበዛና የተትረፈረፈ ምሕረት ያመለክታል፤ ይህም ምናልባት በሉቃ1፥50 ላይ የተጻፈውን የሚያስተጋባ ነው።

103፥14 *ትቢያ መሆናችንንም፤* የ78፥39 ማብ ይመ።

*103፥17፤* ወሰን የሌለው የእግዚአብሔር ፍቅር ዘመኑ

ከዘላለም እስከ ዘላለም በሚፈሩት ላይ
ነው፤
ጽድቁም እስከ ልጅ ልጅ ድረስ
በላያቸው ይሆናል፤
18ኪዳኑን በሚጠብቁት ላይ፣
ትእዛዙንም ለመፈጸም በሚተጉት ላይ
ይሆናል።

19እግዚአብሔር ዙፋኑን በሰማይ አጽንቶአል፤
መንግሥቱም ሁሉን ትገዛለች።

20እናንተ ለቃሉ የምትታዘዙ መላእክቱ፤
ትእዛዙንም የምትፈጽሙ እናንተ ኀያላን፤
እግዚአብሔርን ባርኩ።
21እናንተ ፈቃዱን የምትፈጽሙ አገልጋዮቹ፤
ሰራዊቱ ሁሉ፣ እግዚአብሔርን ባርኩ።
22እናንተ በግዛቱ ሁሉ የምትኖሩ፣
ፍጥረቱ ሁሉ፣ እግዚአብሔርን ባርኩ፤

ነፍሴ ሆይ፤ እግዚአብሔርን ባርኪ።

## መዝሙር 104

### የፍጥረት መብት

1ነፍሴ ሆይ፤ እግዚአብሔርን ባርኪ፤

እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ፤ አንተ እጅግ
ታላቅ ነህ፤
ክብርንና ግርማን ለብሰሃል።
2ብርሃንን እንደ ሸማ ተጐናጽፈሃል፤
ሰማያትንም እንደ ድንኳን መጋረጃ
ዘረጋህ፤
3የእልፍኝህን አግዳሚ በውሆች ላይ
አኖርህ፤
ደመናትን ሠረገላህ አደረግህ፤
በነፋስ ክንፍ ትሄዳለህ።
4መላእክትህን[a] መንፈስ፣
አገልጋዮችህንም የእሳት ነበልባል
ታደርጋለህ።
5ለዘላለም እንዳትናወጥ፣
ምድርን በመሠረቷ ላይ አጸናሃት።
6በጥልቅ እንደ ልብስ ሸፈንሃት፤
ውሆችም ከተራሮች በላይ ቆሙ።
7በገሥጽሃቸው ጊዜ ግን ፈጥነው ሄዱ፤
የነጐድጓድህንም ድምፅ በሰሙ
ጊዜ ሸሹ።
8በተራሮች ላይ ፈሰሱ፤
ወዳዘጋጀህላቸው ስፍራ፣
ወደ ሸለቆዎች ወረዱ።
9ተመልሰው ምድርን እንዳይሸፍኑ፣
አልፈውም እንዳይመጡ ድንበር
አበጀህላቸው።

103፥18 ዘኍ15፥40፤ ዘዳ29፥9፤ መዝ119፥52፤ ዮሐ14፥15
103፥19 መዝ22፥28፤ 47፥8፤ 66፥7፤ 80፥1፤ 113፥5፤ ዳን4፥17
103፥20 ነህ9፥6፤ መዝ28፥6፤ 29፥1፤ 107፥25፤ 135፥7፤ 148፥8፤ ሉቃ2፥13፤ ዕብ1፥14
103፥21 1ነገ22፥19፤ ነህ7፥73
103፥22 ቍ 1፤ መዝ 19፥1፤ 67፥3፤ 104፥1፤ 145፥10፤ 150፥6
104፥1 ኢዮ40፥10፤ መዝ103፥22
104፥2 ኢዮ9፥8፤ 37፥18፤ መዝ18፥12፤ 19፥4፤ ኢሳ40፥22፤ 42፥5፤ 44፥24፤ 49፥18፤ ኤር43፥12፤ 51፥15፤ ዘካ12፥1፤ 1ጢሞ 6፥16
104፥3 ዘዳ33፥26፤ 2ነገ2፥11፤ መዝ18፥10፤ 24፥2፤ ኢሳ19፥1፤ አሞ 9፥6፤ ናሆ1፥3
104፥4 ዘፍ3፥24፤ 2ነገ2፥11፤ መዝ148፥8፤ ዕብ1፥7
104፥5 ዘፀ31፥17፤ 1ሳሙ2፥8፤ ኢዮ26፥7፤ መዝ24፥1-2፤ 102፥25፤ 121፥2
104፥6 ዘፍ1፥2፤ 7፥19፤ 2ጴጥ3፥6 104፥7 ዘፀ9፥23፤ መዝ18፥15፤ 29፥3
104፥8 መዝ33፥7 104፥9 ዘፍ1፥9፤ መዝ16፥6

[a]4 መልእክተኞቹን ወይም አገልጋዮቹን

አጭር የሆነውን የሰውን ዕድሜ የሚያልፍ ነው (ቍ 11 ይመ)። *እስከ ልጅ ልጅ ፤* የ109፥12 ማብ ይመ።

*103፥19፤* ቍ6 እና ማብ፤ እንዲሁም 9፥4፥7፤ 11፥4፤ 47፥2፥7-8፤ 123፥1 ይመ።

*103፥20-22፤* እግዚአብሔርን ለማመስገን በመደምደሚያ ላይ የቀረበ ጥሪ ሲሆን፣ ጥሪው የቀረበው ለሥነ ፍጥረት ሁሉ ነው (ከቍ1-2 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ለምስጋና የሚደረግ ጥሪ፣ በመዝሙራት መጽሐፍ ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ ምስጋናው የሚልቅበት (የሚጠዝበት) ነው (መዝ148-150 ይመ)። የ9፥1 ማብ ይመ። *ባረኩ ... ባረኩ ... ባረኪ ፤* የ96፥1-3 ማብ ይመ። የመጨረሻው ስንኝ (መስመር) ምናልባት በመዝሙሩ አርታኢያት የተጨመረ ሳይሆን አይቀርም (መዝ104፥1፡35 ይመ)።

103፥20 *ፈቃዱን የምትፈጽሙ ፤* 91፥11 ዕብ1፥14 ይመ።

103፥21 *የሰማይ ሰራዊቱ ፤* በዚህም ቦታ ሆነ በመዝ148፥2 ላይ ቃሉ መላእክትን የሚመለከት ነው።

103፥22 *ፍጥረቱ ሁሉ ፤* 65፥13፤ 96፥11-12 እና ማብ ይመ።

*መዝ104፤* የሁሉ ፈጣሪ ለሆነው አምላክ የቀረበ ዝማሬ ነው። ዘፍ1 ከባቢሉን ምርኮ በፊት በነበረው በዚህ መዝሙር ጸሓፊ ላይ ተጽዕኖ እንዳደረገ ማየት ይቻላል፤ ጸሓፊው ዘፍ 1ን በራሱ መንገድ ለራሱ ዐላማ ተጠቅሞበታል (ከዚህ ቀጥሎ ያለውን አንቀጽ ይመ)። ዘፍ1 የሚተርከው ፍጥረታትን የፈጠረና ያበጀ እግዚአብሔር መሆኑን ሲሆን፣ መዝሙረኛው ግን በዙሪያው የሚታየውን ሥነ ፍጥረት የእግዚአብሔርን ገናና ክብር በይፋ እንደሚያውጅ ይናገራል። በዚህ መዝሙር ውስጥ ጸሓፊው እግዚአብሔርን ያቀረበው የማይታየው መለኮታዊ ባሕሪው በሥነ ፍጥረት አማካይነት እንደ ተገለጠና ሥነ ፍጥረትንም እንደ ልብስ የተከናነባቸው አድርጎ ነው (የመዝ101 መግቢያን ይመ)። መዝሙረኛው የቍጥር አንድን አንጓ መግቢያ በመከተል፣ የመዝሙሩን ዋና አካል በሦስት-በአምስት-በዘጠኝ እንደ ገና ደግሞ በአምስት-በሦስት አንጓዎች እየከፈለ በአንድ ማእከላዊ ነጥብ ዙሪያ ያስቀምጠዋል። የመጀመሪያው አንጓ በሰማያውያን አካላት ክልል ውስጥ ስላሉት ፍጥረታት (ቍ2-4) የሚናገር ሲሆን፣ አምስተኛው አንጓ ደግሞ ስለ ውሆች ይናገራል (ቍ24-26)። ሁለተኛው የምድርን ጽኑ መሠረትና አስተማማኝ ዳር ድንበሯን (ቍ5-9)፣ አራተኛው ከፀሓይና ከጨረቃ መዘዋወር የተነሣ ሕግንና ሥርዐትን ጠብቆ በምድር ላይ የሚከናወኑትን የወቅቶች መፈራረቅ (ቍ19-24) በአድናቆት ይገልጻል። በመካከል ላይ ያለው (በሦስት በሦስት ቤት የተደራጀ) ባለ ዘጠኝ ቍጥር አንጓ (ቍ10-18) በምድር ላይ ያለውን ሕይወት በአንክሮ ያስቀምጠዋል። ዋናውም የመዝሙሩ አካል ምድራዊ ሕይወት የተሟላ ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር እንዴት አድርጎ እንደሚንከባከበው ያሳያል። ሁለቱ የመደምደሚያ ቍጥሮች (ቍ31-32) ከቍጥር ጋር ጣራና ግድግዳ በመሆን መዝሙሩን ከላይ እስከ ታች ያዋቅራሉ። "ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን አመስግኚ" (ቍ33-35) የሚለው የመዝሙሩ አርታኢያዎች በኋላ የጨመሩት ሳይሆን አይቀርም።

*104፥11* መግቢያና የመዝሙሩ ፍሬ ሐሳብ ነው። *ለብሰሃል ፤* የ102፥26 ማብ ይመ።

*104፥1-4፤* የሰማይ አካላትን የሚመለከት ክፍል ነው።

104፥2 *ብርሃንን ፤* ከዘፍ1 የመጀመሪያ ቀን ፍጥረት ጋር ያነጻጽሩ። *ሰማያትን ፤* ከዘፍ1 ሁለተኛ ቀን ፍጥረት ጋር ያነጻጽሩ። *እንደ ድንኳን ፤* ከምድር በላይ ብርሃንን የሚሰጡ አካላትን ማለት ነው።

104፥3 *የእልፍኝህን ፤* እግዚአብሔር በሰማያት ያለውን መኖሪያ ምስላዊ በሆነ መንገድ የሚገልጽ ነው (ቍ13 ይመ)። ይህ ቃል በነጠላ ቍጥር ሲጠቀስ በዕብራይስጥ ቋንቋ የሚያመለክተው፣ ከዋናው ቤት ጣራ ላይ የሚሠራውን ልዩ ክፍል ወይም ቤት ነው (በ1ነገ17፥19፤ በ2ነገ1፥2 ላይ ተጽፎ እንደሚገኘው ዐይነት ማለት ነው። *በውሆች ፤* "በድንኳኑ" በላይ ያሉ ውሆች ሲሆን (ቍ2፤ ዘፍ1፥7 ይመ) በብሉይ ኪዳን ምስላዊ አገላለጽ መሠረት እግዚአብሔር ዝናብን የሚሰጠው ከዚህ ነው ተብሎ ይታመናል (ቍ13 እንዲሁም 36፥8 እና ማብ ይመ)። *ደመናትን ሰረገላህ አደረግህ ፤* 18፥7-15፤ 68፥4፤ 77፥16-19 እና ማብ ይመ።

104፥4 *መንፈስ ... የእሳት ነበልባል ፤* በዚህ ቦታ ነፋሳትና መብረቅ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የሚፈጽሙ መልእክተኞች ሆነው በሰውኛ የአነጋገር ዘይቤ ተገልጸዋል (148፥8 ይመ፤ ከ103፥21 ጋር ያነጻጽሩ)።

*104፥5-9፤* የምድር መሠረት ጸንቶ የቆመ መሆኑን የሚያረጋግጥ ክፍል ነው (ቍ5:9)።

104፥5 *ምድር ፤* ዘፍ1፥10 ይመ። *በመሠረቷ ፤* 24፥21 እና ማብ ይመ። *ለዘላለም እንዳትናወጥ ፤* በጽኑ መሠረት ላይ ማለት ነው (93፥1፤ 96፥10 ይመ)።

104፥7 *በገሥጽሃቸው ጊዜ ፤* የ76፥6 ማብ ይመ። *ፈጥነው ሄዱ ፤* ከዘፍ1 ሦስተኛ ቀን ፍጥረት ጋር ያነጻጽሩ።

104፥9 *ድንበር አበጀህላቸው ፤* ምድር ፈጽሞ በባሕር እንዳትጥለቀለቅ ነው (ከቍ5 ጋር ያነጻጽሩ፤ 33፥7 እና ማብ ይመ፤ እንዲሁም ዘፍ9፥15 ይመ)።

10 ምንጮችን በሸለቆ ውስጥ እንዲሄዱ
አደረግህ፤
በተራሮችም መካከል ይፈሳሉ፤
11 የዱር እንስሳትም ከዚያ ይጠጣሉ፤
የሜዳ አህዮችም ጥማቸውን ይቈርጣሉ።
12 የሰማይ ወፎች ጎጇቸውን በወንዞቹ ዳር
ይሠራሉ፤
በቅርንጫፎችም መካከል ይዘምራሉ።
13 ከላይ ከእልፍኝህ ተራሮችህን ታጠጣለህ፤
ምድርም በሥራህ ፍሬ ትረካለች።
14 ከምድር ምግብን ታወጣ ዘንድ፣
ለእንስሳት ሣርን፣
ለሰው ልጆች ሥራ ዕፀዋትን ታበቅላለህ፤
15 የሰውን ልብ ደስ የሚያሰኝ ወይን፣
ፊቱን የሚያወዛ ዘይት፣
ልቡን የሚያበረታ እህል በዚህ ይገኛል።
16 ደግሞም *የእግዚአብሔር* ዛፎች፣
እርሱ የተከላቸውም የሊባኖስ
ዝግባዎች ጠጥተው ይረካሉ፤
17 ወፎች ጎጆአቸውን በዚያ ይሠራሉ፤
ሽመላ በጥዶቹ ውስጥ ማደሪያ ታገኛለች።
18 ረጃጅሙ ተራራ የዋልያ መኖሪያ፣
የዐለቱም ዋሻዎች የሽኮኮ መሸሸጊያ
ናቸው።
19 ጨረቃን የወቅቶች መለያ አደረግሃት፤
ፀሓይም የምትጠልቅበትን ጊዜ
ታውቃለች።
20 ጨለማን ታመጣለህ፤ ሌሊትም ይሆናል፤
የዱር አራዊትም ሁሉ በዚህ ጊዜ
ወጥተው ይራወጣሉ።
21 የአንበሳ ግልገሎች ምግብ ፍለጋ ይጮኻሉ፤
የሚበሉትንም ከእግዚአብሔር ይሻሉ።
22 ፀሓይ በወጣች ጊዜም ይመለሳሉ፤
በየጕሬአቸውም ገብተው ይተኛሉ።
23 ሰውም ወደ ሥራው ይሄዳል፤
እስኪመሽም በተግባሩ ላይ ይሰማራል።
24 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ሥራህ እንዴት
ብዙ ነው!
ሁሉን በጥበብ ሠራህ፤
ምድርም በፍጥረትህ ተሞላች።
25 ይህች ባሕር ሰፊና የተንጣለለች ናት፤
ታላላቅና ታናናሽ እንስሳት፣
ስፍር ቍጥር የሌላቸውም ነፍሳት
በውስጧ አሉ።
26 መርከቦች በላይዋ ይመላለሳሉ፤
አንተ የፈጠርኸውም ሌዋታን በውስጧ
ይፈነጫል።
27 ምግባቸውን በወቅቱ ትሰጣቸው ዘንድ፣
እነዚህ ሁሉ አንተን ተስፋ ያደርጋሉ።
28 በሰጠሃቸውም ጊዜ፣
አንድ ላይ ያከማቻሉ፤
እጅህንም ስትዘረጋ፣
በመልካም ነገር ይጠግባሉ።
29 ፊትህን ስትሰውር፣
በድንጋጤ ይሞላሉ፤
እስትንፋሳቸውንም ስትወስድባቸው
ይሞታሉ፤
ወደ ዐፈራቸውም ይመለሳሉ።
30 መንፈስህን ስትልክ፣
እነርሱ ይፈጠራሉ፤
የምድርንም ገጽ ታድሳለህ።
31 *የእግዚአብሔር* ክብር ለዘላለም ጸንቶ
ይኑር፤
*እግዚአብሔር* በሥራው ደስ ይበለው፤
32 እርሱ ምድርን ሲመለከት፣ ትንቀጠቀጣለች፤
ተራሮችም እርሱ ሲዳስሳቸው ይጤሳሉ።
33 በሕይወት ሳለሁ *ለእግዚአብሔር*
እዘምራለሁ፤
ቆሜ እስከ ሄድሁ ድረስም ስምሳኬን
እወድሳለሁ።
34 እኔ *በእግዚአብሔር* ደስ እንደሚለኝ፣
የልቤ ሐሳብ እርሱን

104፥10 መዝ107፥33፤ኢሳ41፥18
104፥11 ቍ13፤ ዘፍ16፥12፤ኢሳ32፥14፤ኤር14፥6
104፥13 ቍ17፤ ማቴ8፥20፤13፥32
104፥13 ዘሌ26፥4፤ መዝ135፥7፤147፥8፤ ኤር10፥13፤አሞ9፥6፤ ዘካ10፥1
104፥14 ዘፍ1፥30፤ ኢዮ28፥5፤38፥27፤ መዝ147፥8
104፥15 ዘፍ14፥18፤ዘዳ8፥3፤መሳ9፥13፤ መዝ23፥5፤92፥10፤ ማቴ6፥11፤ሉቃ7፥46
104፥16 ዘፍ1፥11፤ መዝ72፥16
104፥17 ቍ12
104፥18 ዘዳ14፥5፤ ምሳ30፥26
104፥19 ዘፍ1፥14፤ መዝ19፥6
104፥20 መዝ50፥10፤74፥16፤ኢሳ45፥7፤ አሞ5፥8
104፥21 መዝ145፥15፤ኢዩ1፥20፤አሞ3፥4፤ማቴ6፥26
104፥22 ኢዮ37፥8
104፥23 ዘፍ3፥19፤ መሳ19፥16
104፥24 ዘፍ1፥31፤ መዝ24፥1፤40፥5፤ 50፥10-11
104፥25 መዝ69፥34፤ሕዝ47፥10
104፥26 ዘፍ1፥21፤ ኢዮ3፥8፤40፥20፤41፥1፤መዝ107፥23፤ሕዝ27፥9፤ዮና1፥3
104፥27 ኢዮ36፥31፤መዝ145፥15፤147፥9
104፥28 መዝ103፥5፤145፥16፤ኢሳ58፥11
104፥29 ዘዳ31፥17፤ኢዮ7፥21
104፥30 ዘፍ1፥2
104፥31 ዘፍ1፥4፤ ዘፀ40፥35፤መዝ8፥1፤ሮሜ11፥36 104፥32 ዘፀ19፥18፤መዝ97፥4፤ 144፥5 104፥33 ዘፀ15፥1፤መዝ108፥1 104፥34 መዝ2፥11፤ 9፥2፤32፥11

*104፥10-18፤* ምድር ሕይወት የሚያብብባት ገነት ናት፤ ይህ ክፍል የመዝሙሩ እምብርት ሲሆን ጸሓፊው ሥነ ፍጥረትን በአንክሮ ይመለከታል (ምድር በሰማይና ቍ2-4 በባሕር ቍ24-26 የተከበበች ናት)። ከዘፍ1 ሦስተኛውና ስድስተኛው ቀን ፍጥረታት ጋር ያነጻጽሩ።

*104፥10-12፤* የነጌብን በረሓዎች ውሃ እንዲያጠጡ ከታች የተሰጡ በረከቶች ናቸው።

*104፥13-15፤* የታረሰውን ደጋማ የእስራኤል ምድር ውሃ እንዲያጠጡ ከላይ የተሰጡ በረከቶች ናቸው።

104፥13 *ከላይ ከእልፍኝህ፤* ቍ3 እና ማብ ይመ።

104፥15 *ልብ ... ልቡን፤* የ4፥7 ማብ ይመ። *ዘይት፤* የወይራ ዘይት ነው። *ፊቱ የሚያወዛ፤* በምግብነት የሚገለገልበት ሲሆን (1ነገ17-12 ይመ) ይህም የሰው ልጅ ፊት ጤናማ እንዲሆን ወይም በቅባትነት መልክ ሊጠቀምበት ይችላል (አስ2፥12 ይመ)።

*104፥16-18፤* ውሃ የጠገበችው የሊባኖስ ምድር ከታላላቅ ዛፎች፣ ከአዕዋፍና ከእንስሳቷ መንጋ ጋር ስትታይ የእግዚአብሔር ሥነ-ፍጥረት በሚያስደንቅ ሁኔታ ባሞሩ ተጠቃሎ የሚታይባት የመናፈሻ ስፍራ ናት ማለት ይቻላል (72፥16፤ 2ነገ14፥9፤ 19፥23፤ ኢሳ 10፥34፤ 35፥2፤ 40፥16፤ 60፥13፤ ኤር22፥6፤ ሆሴ14፥7 ይመ)።

*104፥19-23፤* በጨረቃና በፀሓይ መንቀሳቀስ ምክንያት በምድር ላይ ሥርዐትን የጠበቀ ሕይወት ይታያል፤ ከዘፍ1 አራተኛ ቀን ፍጥረታት ጋር ያነጻጽሩ።

104፥21፡23 *የአንበሳ ... ሰው፤* እንስሳት በአጠቃላይ የሚወክለው አንበሳ የጨለማው ንጉሥ ሲሆን፣ ሰው ደግሞ የቀን ወይም የብርሃን ንጉሥ ነው።

*104፥24-26፤* በውሆች ግዛት ውስጥ የተካተቱትን ፍጡራን ይመለከታል። ከዘፍ1 አምስተኛ ቀን ፍጥረታት ጋር ያነጻጽሩ። በባሕር ግዛት ውስጥ የሚገኘው ሥነ ፍጥረት በአወቃቀር ረገድ ሲታይ በሰማይ ግዛት ውስጥ ከሚገኘው ጋር ተመሳሳይነት አለው (ቍ2-4)፤ ይህም ሌላው የምድር ግዛት ዳር ድንበር ሆኖ ይገኛል።

104፥25 *በውስጧ፤* ዘፍ1፥20-21 ይመ።

104፥26 *ሌዋታን፤* ይህ አስፈሪ የጥልቁ ፍጥረት የባሕር ውስጥ አውሬ ሲሆን፣ ምንም የማይጐዳ የእግዚአብሔር ፍጥረት ሆኖ በሰፊው ውቅያኖስ ላይ ይንቦጫረቃል (ኢዮ3፡8 እና ማብ ይመ)።

*104፥27-30፤* ይህ እንስሳት በብዛት የሚርመሰመሱበት ስፍራ በእግዚአብሔር ቸርነት የተሟላለት ቦታ ሆኖአል። ከዘፍ1 ስድስተኛ ቀን ፍጥረታት ጋር ያነጻጽሩ።

104፥29 *ፊትህን ስትሰውር፤* የ13፥1 ማብ ይመ።

104፥30 *ይፈጠራሉ፤* የ102፥18 ማብ ይመ።

104፥31 *የእግዚአብሔር ክብር፤* በሥነ ፍጥረቱ አማካይነት የሚገለጠውን ማለት ነው።

*104፥32፤* እግዚአብሔር ከፍጥረቱ ሁሉ በላይ ታላቅ አምላክ ስለ ሆነ፣ በማየት ወይም በመዳሰስ ብቻ እንዲልነበሩ ለማድረግ ኀይልና ሥልጣን አለው።

*104፥33-35፤* የመዝሙሩ አጠቃላይ መደምደሚያ ነው።

*104፥33፤* እግዚአብሔርን ለማመስገን ቃል የተገባበት ቦታ ነው፤ ምስጋናው የሚቀርበው በዝማሬ ነው፤ የ7፥17 ማብ ይመ።

104፥34 *የልቤ ሐሳብ፤* ከፍ ብሎ ያለውን ዝማሬ የሚያመ

ደስ ያሰኘው።
35ኀጥአን ከምድር ገጽ ይጥፉ፤
ዐመፀኞች ከእንግዲህ አይገኙ።

ነፍሴ ሆይ፤ *እግዚአብሔርን* ባርኪ፤

ሃሌ ሉያ።[ሀ]

## መዝሙር 105

### የእስራኤል ድንቅ ታሪክ

105፥1-15 ተጓ ምብ-1ዜና 16፥8-22

1*እግዚአብሔርን* አመስግኑ፤ ስሙንም ጥሩ፤
ሥራውንም በሕዝቦች መካከል ግለጡ።
2ተቀኙለት፤ ዘምሩለት፤
ድንቅ ሥራዎቹንም ሁሉ ተናገሩ።
3በቅዱስ ስሙ ተጓደዱ፤
*እግዚአብሔርን* የሚሹት ልባቸው ደስ
ይበለው።
4*እግዚአብሔርንና* ብርታቱን ፈልጉ፤
ፊቱንም ዘወትር ፈልጉ።

5ያደረጋቸውን ድንቅ ሥራዎች፣
ታምራቱንና ከአፉ የወጣውን ፍርድ
አስቡ፤
6እናንተ የአገልጋዩ የአብርሃም ዘሮች፣
ለራሱም የመረጣችሁ የያዕቆብ ልጆች
ሆይ፤ አስታውሱ።
7እርሱ *እግዚአብሔር* ስምላካችን ነው፤
ፍርዱም በምድር ሁሉ ላይ ነው።

8ኪዳኑን ለዘላለም፣
ያዘዘውንም ቃል እስከ ሺህ ትውልድ
ያስታውሳል።
9ከአብርሃም ጋር ያደረገውን ኪዳን፣
ለይስሐቅም በመሐላ የተሰጠውን ተስፋ
አይረሳም።
10ይህንም ለያዕቆብ ሥርዐት አድርጎ፣
ለእስራኤልም የዘላለም ኪዳን አድርጎ
አጸናለት፤
11እንዲህም አለ፤ "የርስትህ ድርሻ አድርጌ፣
የከነዓንን ምድር እሰጥሃለሁ።"

104፥35 ኢዮ7፥10፤ መዝ28፥6፤37፥38፤10 5፥45፤106፥48
105፥1 1ዜና16፥34፤መዝ80፥18፤99፥6፤16፥13፤ኢሳ2፥32፤ሐሥ2፥21
105፥2 መዝ7፥17፤18፥49፤27፥6፤30፥4፤33፥3፤59፥17፤71፥22፤75፥1፤96፥1፤146፥2
105፥3 መዝ89፥16
105፥4 መዝ24፥6
105፥5 ዘዳ7፥18፤መዝ40፥5
105፥6 ቍ42፤ዘዳ10፥15፤መዝ106፥5
105፥8 ዘፍ9፥15፤መዝ106፥45፤111፥5፤ሕዝ16፥60፤ሉቃ1፥72
105፥9 ዘፍ12፥7፤15፥18፤22፥16-18፤ሉቃ1፥73፤ገላ3፥15-18
105፥10 ዘፍ28፥13-15፤ኢሳ55፥3
105፥11 ዘፍ12፥7፤ዘኍ34፥2
105፥12 ዘፍ23፥4፤ዘዳ7፥7፤ዕብ11፥19
105፥13ዘፍ15፥13-16፤ዘኍ32፥13፤33፥3-49
105፥14ዘፍ12፥17-20፤20፥3፤35፥5፤መዝ9፥5
105፥15 ዘፍ20፥7፤26፥11፤1ሳሙ12፥3
105፥16 ዘፍ12፥10፤ዘሌ26፥26፤ኢሳ3፥1፤ሕዝ4፥16
105፥17 ዘፍ37፥28፤ሐሥ7፥9
105፥18 ዘፍ40፥15
105፥19 ዘፍ12፥10፤40፥20-22፤41፥40
105፥20 ዘፍ41፥14
105፥22 ዘፍ41፥40፤43-44
105፥23 ዘፍ46፥6፤47፥28፤መዝ78፥51፤

12በቍጥር አነስተኞች ሆነው ሳሉ፣
እጅግ ጥቂትና ባይተዋሮች ሳሉ፣
13ከሕዝብ ወደ ሕዝብ ሲንከራተቱ፣
ከአንዱ መንግሥት ወደ ሌላው
ሲቅበዘበዙ፣
14ማንም ግፍ እንዲፈጽምባቸው አልፈቀደም፤
ስለ እነርሱም ነገሥታትን እንዲህ ሲል
ገሠጸ፤
15"የቀባኋቸውን አትንኩ፤
በነቢያቴም ላይ ክፉ አታድርጉ።"

16በምድሪቱ ላይ ራብን ጠራ፤
የምግብንም አቅርቦት ሁሉ አቋረጠ፤
17በባርነት የተሸጠውን ሰው፣
ዮሴፍን ከእነርሱ አስቀድሞ ላከ።
18እግሮቹ በእግር ብረት ተላላጡ፤
በዐንገቱም የብረት ማነቆ ገባ።
19የተናገረው ቃል እስኪፈጸምለት፣
*የእግዚአብሔር* ቃል ፈተነው።
20ንጉሥ ልኮ አስፈታው፤
የሕዝቦችም ገዥ ነጻ አወጣው።
21የቤቱ ጌታ፣
የንብረቱም ሁሉ አስተዳዳሪ አደረገው፤
22ይኸውም ሹማምቱን በራሱ መንገድ
ይመራ ዘንድ፣
ታላላቆቹንም ጥበብ ያስተምር ዘንድ
ነበር።

23እስራኤል ወደ ግብፅ ገባ፤
ያዕቆብ በካም ምድር መጻተኛ ሆነ።
24*እግዚአብሔር* ሕዝቡን እጅግ አበዛ፤
ከጠላቶቻቸውም ይልቅ አበረታቸው፤
25ሕዝቡን እንዲጠሉ፣
በባሪያዎቹም ላይ እንዲያሤሩ ልባቸውን
ለወጠ።

ሐሥ7፥15፤13፥17 105፥24 ዘፀ1፥7፡9፤ ሐሥ7፥17
105፥25 ዘፀ1፥6-10 ፤4፥21፤ሐሥ7፥19

[ሀ]35 *እግዚአብሔር ይመስገን የሚሉ ትርጕሞች አሉ፤ በሰብዓ ሊቃናት ትርጕም ይህ መሥመር በመዝ105 መጀመሪያ ላይ ይገኛል።*

ለክት ነው (19፥14 እና ማብ ይመ)።

*104፥35፤* ምድር ከሚያበላሿት ማናቸውም ክፉ ነገር ሁሉ ትጽዳ (ከራእ21፥27 ጋር ያነጻጽሩ)። *ሃሌ ሉያ፤* በዚህ መዝሙር ውስጥ ለመጨረሻ ጊዜ የተነገረው በዚህ ቦታ ነው፤ ምናልባት የዚህ መዝሙር መደምደሚያ ሳይሆን፣ የመዝሙር 105 መግቢያ ሊሆን ይችላል።

*105፤* የከነዓንን ምድር ለዘሮቹ በመስጠት ለአብርሃም የገባውን ቃል ኪዳን የፈጸመና የማዳን ሥራውንም ሁሉ በተግባር የገለጸ በመሆኑ፣ የእስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔርን እንዲያመልኩና እንዲታመኑ ለማድረግ የቀረበ ማበረታቻ ነው። መዝሙሩ የተዘጋጀው በአንድ ሌዋዊ ሲሆን እስራኤላውያን ከሚያከብሯቸው በዓላት በአንዱ ቀን ይኸውም በዳስ በዓል (ዘሌ23፥34 ይመ) ወይም በመከር በዓል (ዘፀ23፥16፤ ዘሌ23፥15-21፤ ዘኍ28፥26፤ ዘዳ16፥9-12፤ 26፥1-11 ይመ) ወቅት የሚዘመር ነው።

*105፥1-4፤* እግዚአብሔርን እንዲያመልኩና በእርሱም እንዲታመኑ የሚቀርብ ጥሪ ነው።

105፥1 *አመስግኑ፤* በውዳሴ (የመዝ100 ርእስ ይመ)። *ጥሩ፤* በጸሎት (ቍ4 ይመ)።

105፥2 *ድንቅ ሥራዎቹንም፤* ቍ5 ይመ። ("ድንቅ")፤ እንዲሁም የ9፥1 ማብ ይመ።

105፥3፡25 *ልባቸው፤* የ4፥7 ማብ ይመ።

*105፥5-7፤* የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ ለማስታወስ የቀረበ የማበረታቻ ቃል ነው።

105፥5 *አስታውሱ፤* እግዚአብሔርን እንዲያመልኩና እንዲታመኑ የሚያነሣሣ ንግግር ነው፤ እግዚአብሔር እንዴት እንዳስታወሳቸው እንዲያስታውሱ (እንዲያስተውሉ) መዝሙረኛው ይመክራቸዋል (ቍ8-11 ይመ)። *ፍርድ፤* ቍ7 ይመ፤ እንዲሁም የ48፥11፤ 97፥8 ማብ ይመ። *የሰጠውን፤* እንደ እግዚአብሔርነቱ፣ እንደ አምላክነቱ ያዛል፤ ትእዛዙም በትክክል ይፈጸማል።

*105፥8-11፤* እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውን ቃል ኪዳን ያሳስባል (ቍ42-45 ይመ)።

105፥8 *ኪዳኑን፤* ተስፋ የተሰጠበት ይህ ኪዳን በዘፍ 15፥9-21 ላይ ይገኛል። ይህ ቍጥርና ቍጥር9 በሉቃ1፥72-73 ላይ ሳያስተጋባ አይቀርም። *እስከ ሺህ ትውልድ፤* ዘፀ20፥6፤ ዘዳ7፥9፤ 1ዜና 16፥15 ይመ።

መዝ105፥10 *ሥርዐት አድርጎ፤* ወዲያ ወዲህ የማይል ጽኑ መመሪያ ሲሆን ወደ ፊት የሚያደርጋቸው ነገሮች ሁሉ በዚህ መመሪያ የተገዙ ናቸው (ቍ45 ማብ ይመ)።

*105፥12-41፤* እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ቃል ኪዳን ከገባ ጊዜ ጀምሮ በሕዝቡ መካከል ያደረገውን የማዳን ሥራ የሚያስታውስ ነው (ቍ11 እንዲሁም ዘፍ15፥9-20 ይመ)።

*105፥14-15፤* ዘፍ20፥2-7 ይመ፤ እንዲሁም የዘፍ20፥7 ማብ ይመ።

*105፥23፡27፤ ከካም ምድር፤* 78፥51 እና ማብ ይመ።

105፥25 *ልባቸውን ለወጠ፤* ምን ጊዜም ቢሆን የእስራኤል ዕጣ ፈንታ ያለው በእግዚአብሔር እጅ ነው፤ በመሆኑም በእስራ

26ባሪያውን ሙሴን፣
 የመረጠውንም አሮንን ላከ::
27እነርሱም ታምራታዊ ምልክቶችን
  በመካከላቸው፣
 ድንቅ ነገሮቹንም በካም ምድር አደረጉ::
28ጨለማን ልኮ ምድሪቱን ጽልመት
  አለበሰ፤
 እነርሱም በቃሉ ላይ ማመፅን ተዉ::
29ውሃቸውን ወደ ደም ለወጠ፤
 ዓሦቻቸውንም ፈጀ::
30ምድራቸውም፣ የነገሥታታቸው
  እልፍኝ ሳይቀር፣
 ጓጉንቸር ተርመሰመሰባቸው::
31እርሱ በተናገረ ጊዜ የዝንብ መንጋ መጣ፤
 ትንኞችም ምድራቸውን ወረሩ::
32ዝናባቸውን በረዶ አደረገው፤
 ምድራቸውም ሁሉ መብረቅ አወረደ::
33ወይናቸውንና በለሳቸውን መታ፤
 የአገራቸውንም ዛፍ ከተከተ::
34እርሱ በተናገረ ጊዜ አንበጣ መጣ፤
 ስፍር ቍጥር የሌለውም ኩብኩባ
  ከተፍ አለ፤
35የምድሪቱንም ዕፀዋት ሁሉ በላ፤
 የመሬታቸውንም ፍሬ ሙጥጥ አደረገ፤
36ደግሞም በአገራቸው ያለውን በኵር
  ሁሉ፣
 የኀይላቸውንም ሁሉ በኵራት መታ::
37የእስራኤልንም ሕዝብ ብርና ወርቅ
  ጭኖ እንዲወጣ አደረገ፤
 ከነገዶቻቸውም አንድም አልተደናቀፈም::
38እጅግ ፈርተዋቸው ነበርና፣
 ወጥተው ሲሄዱ ግብፅ ደስ አላት::
39ደመናን እንደ መጋረጃ ዘረጋላቸው፤
 እሳትም በሌሊት አበራላቸው::
40በለመኑትም ጊዜ፣ ድርጭት አመጣላቸው፤
 የሰማይንም እንጀራ አጠገባቸው::
41ዐለቱን ሰነጠቀ፤ ውሃም ተንዶለዶለ፤
 እንደ ወንዝም በበረሓ ፈሰሰ::
42ለባሪያው ለአብርሃም የሰጠውን፣
 ቅዱስ የተስፋ ቃሉን አስቦአልና::
43ሕዝቡን በደስታ፣
 ምርጦቹንም በእልልታ አወጣቸው::
44የሌሎችን ሕዝቦች ምድር ሰጣቸው፤
 የእነዚህንም የድካም ፍሬ ወረሱ፤
45ይህም ሥርዐቱን ይጠብቁ ዘንድ፣
 ሕጉንም ይፈጽሙ ዘንድ ነው::
 ሃሌ ሉያ::[#]

## መዝሙር 106

### ብሔራዊ ኑዛዜ

106፥1:47-48 ተጓ ምብ-1ዜና 16፥34-36

1ሃሌ ሉያ[+]
 ቸር ነውና፣ እግዚአብሔርን አመስግኑ፤
 ምሕረቱም ለዘላለም ነውና::
2ስለ እግዚአብሔር ታላቅ ሥራ ማን
  ሊናገር ይችላል?
 ምስጋናውንስ ሁሉ ማን ተናግሮ
  ይጨርሳል?

105፥26 ዘፀ3፥10፤ 4፥16፤ዘኍ16፥5፤ 17፥5-8፤33፥1
105፥27 ቍ28-37፤ ዘፀ3፥20፤4፥17፤7፥8-12:51፤10፥1፤ዳን4፥3
105፥28 ዘፍ1፥4፤ ዘፀ7፥22፤10፥22
105፥29 ዘፀ7፥21፤ 78፥44
105፥30 ዘፀ8፥2:6
105፥31 ዘፀ8፥16-18:21-24፤መዝ78፥45፤107፥25፤148፥8
105፥32 ዘፀ9፥22-25፤ኢዮ38፥22፤መዝ 78፥47
105፥33 ዘፀ10፥5:12፤መዝ78፥47
105፥34 ዘፀ10፥4:12-15፤1ነገ8፥37፤ መዝ107፥25፤ኢል 1፥6
105፥36 ዘፀ4፥23፤ 12፥12
105፥37 ዘፀ3፥21:22
105፥38 ዘፀ15፥16
105፥39 ዘፀ13፥21፤ መዝ78፥14፤1ቆሮ 10፥1
105፥40 ዘፀ16፥4:13፤መዝ78፥18፤ ዮሐ6፥31
105፥41ዘኍ20፥11፤1ቆሮ10፥4
105፥42 ዘፍ12፥1-3፤13፥14-17፤ 15፥13-16
105፥43 ዘፀ15፥1-18፤መዝ106፥12
105፥44 ዘፀ32፥13፤ ዘዳ6፥10-11፤ኢሱ11፥16-23፤12፥8፤13፥6-7፤መዝ78፥55፤111፥6 105፥45 ዘዳ4፥40፤ 6፥21-24፤መዝ78፥5-7፤104፥35 106፥1 ዕዝ3፥11፤መዝ22፥23፤ 103፥2፤119፥68፤ 136፥1-26፤ኤር33፥11 106፥2 መዝ71፥16

[#]45 *እግዚአብሔር ይመስገን* የሚሉ ትርጕሞች አሉ::
[+]1 *እግዚአብሔር ይመስገን* ማለት ሳይሆን በቍ48 ላይም በድጋሚ ተጠቅሶአል::

ኤል ላይ መከራና ስደት የሚደርሰው እግዚአብሔር ሲፈቅድ ብቻ ነው፤ ከሕዝቡ ታሪክ በስተ ጀርባ ምስጢራዊ በሆነ መንገድ የሚ ሠራው እግዚአብሔር ስለ መሆኑ በብሉይ ኪዳን ተደጋግሞ ተገልጦአል (ዘፀ4፥21፤ ኢሱ11፥20፤ 2ሳሙ24፥1፤ ኢሳ10፥5-7፤ 37፥26-27፤ ኤር34፥22 ይመ)::

105፥26:42 *ባሪያውን፤* 78፥70 እና ማብ ይመ::

*105፥28-36፤* በግብፅ ላይ የወረደውን መቅሠፍት አንድ በአንድ የሚያወሳ ክፍል ነው:: በዚህ የግጥም ስብስብ ውስጥ ሰባቱ መቅሠፍቶች (ሰባት ቍጥር የፍጹምነት ምሳሌ ነው) በዘፀ7-11 ላይ የተዘረዘሩትን ዐሥር መቅሠፍቶች ወክለው ቀርበዋል:: መዝሙረኛው ሦስቱን መቅሠፍቶች ሳይጠቅስ ከመቅረቱ በቀር (የእንስሳትን እልቂትና አሠቃቂ ቍስል በሕያዋን ሁሉ ላይ መውረዱን) በዘፀአት የተጻፈውን ቅደም ተከተል ጠብቆአል፤ ነገር ግን ሦስተኛውና አራተኛው መቅሠፍት (ቅማል እና ተናካሽ ዝንብ) በአንድነት አቅርቦአቸዋል፤ ይህንንም ያደረገው ነገሩን በሰባት ቍጥር ለመወሰን ፈልጎ ነው::

105፥39 *እንደ መጋረጃ፤* በሌሎች ቦታዎች ላይ ደመና የእግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል መገኘት ምልክት በመሆን አገልግሎአል:- (1) እስራኤላውያን በምድረ በዳ በተጓዙ ጊዜ ይመራቸው ነበር (78፥14፤ ዘፀ13፥21፤ ዘኍ9፥17፤ ነህ9፥12:19)፤ (2) ከሚከታተሏቸው ግብፃውያን እንደ ጥቍር መከለያ በመሆን ይጋርዳቸው ነበር (ዘፀ14፥19-20)፤ (3) እግዚአብሔር አምላክ በአስፈሪ ክብሩ በተገለጠ ጊዜ ይሸፍናቸው ነበር (ዘፀ16፥10፤ 24፥16፤ 34፥5፤ 40፥34-35:38፤ ዘኍ11፥25፤ 12፥5፤ 16፥42፤ ዘዳ31፥15፤ 1ነገ8፥11):: መዝሙረኛው ደመና ሌላም አገልግሎት እንደ ነበረው ይናገራል፤ ይኸውም የፀሓይ ትኩሳት ሕዝቡን እንዳያቃጥል በክንፉ ጥላ (17፥8 እና ማብ ይመ) ውስጥ ይሸሽጋቸው ነበር::

105፥40 *የሰማይን እንጀራ፤* 78፥24-25 እና ማብ ይመ::

105፥41 *እንደ ወንዝ፤* በወቅቱ የተፈጸመው ታምር ምን ያህል ታላቅ እንደ ሆነ ለማሳየትና የአንባቢንም ትኩረት ለመሳብ የገባ አገላለጽ ነው፤ በምድረ በዳ የተፈጸመው ይህ ታምር ሲሆን፣ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያሳየውን የማዳኑን ኀይልና የፍቅሩንም ታላቅነት የሚያጠቃልል የመጨረሻ ቃል ነው (114፥8፤ ኢሳ 43፥19-20 ይመ፤ ከኢሳ50፥2 ጋር ያነጻጽሩ)::

*105፥42-45፤* ማጠቃለያና መደምደሚያ ነው::

105፥44፤ *ምድር ሰጣቸው፤* ቍ11 ይመ::

105፥45 *ሥርዐቱን፤* እስራኤል ለእግዚአብሔር የገባችውን ቃል መጠበቅ ትችል ዘንድ፣ እግዚአብሔር ሕጉን ወይም ሥርዐቱን ጠብቆ አሳይቶአታል (ቍ10):: እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል የሚፈጽመው የማዳን ሥራ ለቅዱስ ሕጉና ሥርዐቱ ታዛዥ የሆኑ ሕዝቦች የመፍጠር ግብ አለው::

*106፤* የእስራኤልን የረጅም ዘመናት የዐመፀኝነት ታሪክ በንስሓ መልክ የሚያቀርብና እግዚአብሔርም ሕዝቡን እንደ ገና እንዲያድን ለእግዚአብሔር የቀረበ የልመና ጸሎት ነው:: ከርዝማኔው፣ በቅኔ ዘዬውና በፍሬ ሐሳቡ ከመዝሙር 105 ጋር ተመሳሳይነት አለው (መዝ78፤ ነህ9፥5-37 ይመ):: ይህ መዝሙር የተጻፈው አንዳንድ አይሁዶች ከምርኮ ከተመለሱ በኋላ በኢየሩሳሌም በሚኖር በአንድ ሌዋዊ ሳይሆን አይቀርም:: የመጀመሪያው አንድ ስንኝና የመጨረሻዎቹ ሁለት ስንኞች ቀደም ብሎ ከተዘጋጀ ጽሑፍ ላይ ሳይወሰዱ (ሳይቀዱ) እንዳልቀረ ይገመታል (1ዜና 16፥34-36 ይመ):: እነዚህም ("ሃሌ ሉያ" ... ከሚለው ቃል ጋር) የተጨመሩት፣ ምናልባት የመዝሙሩን መጽሐፍ መልክና ቅርጽ እንዲኖረው ያደረጉት ሰዎች (አርታኢዎች) መጽሐፉን በመዝ 106 እና 107 መካከል ከፍለው በለዩ ጊዜ ቀደም ብሎ ከተጻፈው ከዳዊት መዝሙር ወስደው ያስገቡት ሳይሆን እንዳልቀረ ይገመታል (የመዝሙር 101 መግቢያን ይመ)::

*106፥1-5፤* መግቢያ ነው::

106፥1 *አመስግኑ፤* በውዳሴ ማለት ነው (የመዝሙር 100 ርእስ ማብ ይመ):: በቃለ ቅዳሴ ጊዜ የተለመደና የምስጋና ጥሪ ነው (መዝ107፥1፤ 118፥1:29፤ 136፥1-3):: *ምሕረቱ፤* የ6፥4 ማብ ይመ::

106፥2 *ማን ሊናገር ይችላል?* በእውነትና በጽድቅ ለማለት ነው:: *ምስጋናውን፤* ኀያል ሥራዎቹን በተመለከተ የሚቀርብ

[3]ፍትሕ እንዳይዛነፍ የሚጠብቁ፣
ጽድቅን ሁልጊዜ የሚያደርጉ የተባረኩ
ናቸው::
[4]እግዚአብሔር ሆይ፤ ለሕዝብህ ሞገስ
ስታደል አስበኝ፤
በምታድናቸውም ጊዜ ርዳኝ፤
[5]ይኸውም የምርጦችህን ብልጽግና አይ
ዘንድ፣
በሕዝብህ ደስታ ደስ ይለኝ ዘንድ፣
ከርስትህም ክብር የተነሣ እንደድ
ዘንድ ነው::

[6]እኛም እንደ አባቶቻችን ኀጢአት
ሠራን፤
በደልን፤ ክፉም አደረግን::
[7]አባቶቻችን በግብፅ ሳሉ፣
ታምራትህን አላስተዋሉም፤
የምሕረትህን ብዛት አላሰቡም፤
በባሕሩ አጠገብ፣ ገና ቀይ ባሕር[ሀ]
አጠገብ ዐመፁብህ::
[8]እርሱ ግን የኀይሉን ታላቅነት ለማሳወቅ፣
ስለ ስሙ አዳናቸው::
[9]ቀይ ባሕርን ገሠጸ፤ እርሱም ደረቀ፤
በምድረ በዳ እንደሚታለፍ በጥልቅ
ውሃ መካከል መራቸው::

[10]ከባለጋራቸው እጅ አዳናቸው፤
ከጠላትም እጅ ታደጋቸው::
[11]ባላንጦቻቸውን ውሃ ዋጣቸው፤
ከእነርሱም አንድ አልተረፈም::
[12]ከዚህ በኋላ የተስፋ ቃሉን አመኑ፤
በዝማሬም አመሰገኑት::

[13]ነገር ግን ያደረገውን ወዲያውኑ ረሱ፤
በምክሩም ለመሄድ አልታገሡም::
[14]በምድረ በዳ እጅግ መመኘት አበዙ፤
በበረሓም እግዚአብሔርን ተፈታተኑት::
[15]እርሱም የለመኑትን ሰጣቸው፤
ዳሩ ግን የሚያኰስምን ሕመም
ሰደደባቸው::

[16]በሰፈር በሙሴ ላይ፣
ለእግዚአብሔር በተቀደሰውም በአሮን
ላይ ቀኑ::

[17]ምድር ተከፍታ ዳታንን ዋጠች፤
የአቤሮንን ወገን ሰለቀጠች::
[18]እሳት በጉባኤያቸው መካከል ነደደ፤
ነበልባሉም ክፉዎችን ፈጅቶ አስወገደ::
[19]በኮሬብ ጥጃ ሠሩ፤
ቀልጦ ለተሠራ ምስልም ሰገዱ::
[20]ክብራቸው የሆነውንም፣ ሣር በሚበላ፣
በበሬ ምስል ለወጡ::
[21]በግብፅ ታላቅ ነገር ያደረገውን፣
ያዳናቸውን አምላክ ረሱ፤
[22]እርሱ ግን በካም ምድር ድንቅ ሥራ፣
በቀይ ባሕርም አስደናቂ ነገር አደረገ::
[23]ስለዚህ በመቅሠፍቱ እንዳያጠፋቸው
ይመለስ ዘንድ፣
እርሱ የመረጠው ሙሴ በመካከል ገብቶ፣
በፊቱ ባይቆም ኖሮ፣
እንደሚያጠፋቸው ተናግሮ ነበር::
[24]ከዚያም በኋላ መልካሚቱን ምድር ናቁ፤
የተስፋ ቃሉንም አላመኑም::
[25]በድንኳኖቻቸው ውስጥ አጒረመረሙ፤
የእግዚአብሔርንም ድምፅ አላዳመጡም::
[26]በምድረ በዳ ሊጥላቸው፣
እጁን አንሥቶ ማለ፤
[27]ዘራቸውንም በሕዝቦች መካከል ሊጥል፣
ወደ ተለያየ ምድርም እንደሚበትናቸው
ማለ::

[28]ራሳቸውን ከብዔል ፌጎር ጋር አቈራኙ፤
ለሙታን የተሠዋውን መሥዋዕት በሉ፤
[29]በሥራቸውም እግዚአብሔርን አስቈጡት፤
ቸነፈርም በላያቸው መጣ::
[30]ፊንሐስም ተነሥቶ ጣልቃ ገባ፤
ቸነፈሩም ተገታ፤
[31]ይህም ከትውልድ እስከ ትውልድ፣
ለዘላለም ጽድቅ ሆኖ ተቈጠረለት::

106፥3 መዝ15፥2፤ 112፥5፤ሆሴ12፥6
106፥4 ዘፍ50፥24፤ መዝ25፥6:7፤77፥7
106፥5 ዘፀ34፥9፤ ዘዳ30፥15፤መዝ1፥3፤ 20፥5፤27፥6፤47፥5፤ 105፥6፤118፥15
106፥6 1ነገ8፥47፤ 2ዜና30፥7፤ነህ1፥7፤ ሮሜ3፥9
106፥7 ዘፀ14፥11-12፤መሳ3፥7፤መዝ 78፥42
106፥8 ዘፀ9፥16፤ 14፥30:31፤መዝ23፥3 ፤80፥3፤107፥13፤ኢሳ 25፥9፤ኢል2፥32
106፥9 ዘፀ14፥21፤ መዝ18፥15፤78፥13፤ ኢሳ50፥2፤63፥11-14 ፤ናሆ1፥4
106፥10 ዘፀ14፥30፤ መዝ78፥42:53፤ 107፥2:13፤ኢሳ35፥9፤ 62፥12
106፥11 ዘፀ14፥28
106፥12 ዘፀ15፥1-21፤105፥43
106፥13 ዘፀ15፥24፤ 16፥28፤ዘኍ27፥21
106፥14 ዘፀ17፥2፤ መዝ68፥7፤78፥40፤ ፥9
106፥15 ዘፀ16፥13፤ ዘኍ11፥33፤መዝ 78፥29
106፥16 ዘኍ16፥1-3
106፥17 ዘፀ15፥12፤ ዘኍ16፥1፤ዘዳ11፥6
106፥18 ዘሌ10፥2
106፥19 ዘፀ32፥4፤ ሐሥ7፥41
106፥20 ኤር2፥11፤ ሮሜ1፥23
106፥21 ዘዳ10፥21 ፤መዝ75፥1፤78፥11
106፥22 ዘፀ3፥20፤ ዘዳ4፥34፤መዝ78፥51
106፥23 ዘፀ32፥10: 11-14፤ዘኍ11፥2፤ ዘዳ9፥19
106፥24 ዘኍ14፥11 :30-31፤ዘዳ8፥7፤ኤር 3፥19፤ዕብ3፥18-19
106፥25 ዘፀ15፥24፤ዘዳ1፥27፤1ቆሮ10፥10 106፥26 ዘኍ14፥23 ፤ዘዳ2፥14፤ዕብ3፥17፤4፥3 106፥27 ዘሌ26፥33 106፥28 ዘኍ 23፥28 106፥29 ዘኍ16፥46፤25፥3:8፤መዝ64፥2፤141፥4 106፥30 ዘፀ6፥25፤ዘኍ25፥8 106፥31 ዘፍ15፥6፤ዘኍ25፥11-13፤መዝ49፥11

[ሀ]7 በዕብራይስጥ *ያም ሱፍ* የሚባል ሲሆን *የደንገል ባሕር* ማለት ነው፤ በቍ9 እና 22 ላይም ይገኛል::

ውዳሴ ነው (ቍ47 ይመ፤ እንዲሁም የ9፥1 ማብ ይመ)::

106፥3 *የተባረኩ፤* የ1፥1 ማብ ይመ:: *ፍትሕ ... ጽድቅን፤* 36፥6 እና ማብ ይመ፤ እንዲሁም የ3፥7 ማብ ይመ:: ይህ ቍጥር በቍ2 ላይ የተነሣሣን ጥያቄ የሚመልስ ነው::

106፥4 *አስበኝ፤* በቍጥር 3 ላይ እንደ ተገለጸው ቀና በሆነው የሕይወት መንገድ ለመመራት ወስኛለሁና ተመልከተኝ ማለቱ ነው:: *ሞገስ ስታደል፤* ወይም "በምታሳየው ሞገስ" (ቍ44-46 ይመ):: *በምታድናቸውም ጊዜ፤* ወይም "በማዳንህ" እግዚአብሔር ለሕዝቡ በሚያሳየው፣ "በታላቁ ፍቅሩ" (ቍ45) ውስጥ እርሱንም እንዲያስበው መዝሙረኛው ይጸልያል::

106፥5 *ብልጽግና ... ደስታ ... ክብር፤* ደረጃ በደረጃ የሚመጣ እርስ በርሱ የተያያዘ ምክንያትና ውጤት ነው (ቍ40 ይመ)::

*106፥6-43፤* ዐመፅ የተሞላበትን የእስራኤልን ታሪክ የሚገልጽ ክፍል ነው::

*106፥6፤* አንድ በአንድ ለተዘረዘረው ኀጢአትና በደል እንደ መግቢያ ሆኖ የሚያገለግል ንስሓ ነው:: *እኛም፤* እግዚአብሔር የምሕረት ፊቱን ወደ ሕዝቡ እንዲመልስ በሚጸልይበት ጊዜ፣ መዝሙረኛው ለእርሱም ምሕረት እንዲያደርግለት ራሱን ከወገኖቹ ጋር አንድ አድርጎ ያቀርባል (ሕዝ9፥6-7)::

106፥7:22 *ታምራትህን፤* በግብፅ ላይ እንዳወረደው መቅሠፍት ያለውን ማለት ነው (የ9፥1 "ድንቆች" የሚለውን ይመ)::

106፥10 *አዳናቸው፤* አወጣቸው፣ ታደጋቸው፣ ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው::

106፥13 *ምክሩ፤* በራሱ ጊዜ ሊያደርጋቸው ያቀዳቸውን ነገሮች ማለት ነው::

*106፥16-18፤* ዘኍ16፥1-35 ይመ::

106፥19 *በኮሬብ፤* የዘፀ3፥1 ማብ ይመ::

106፥20 *ክብራቸው፤* 1ሳሙ15፥29፤ ኤር2፥11 ይመ::

106፥22 *በካም ምድር፤* 78፥51 እና ማብ ይመ::

106፥23 *መቅሠፍቱ፤* የ2፥5 ማብ ይመ:: *በመካከል ገብቶ፤* ዘፀ32፥11-14:31-32::

106፥24 *መልካሚቱን ምድር፤* ይህ በኤር3፥19፤ 12፥10፤ ዘካ7፥14 ላይ ተገልጾአል፤ እንዲሁም ዘዳ8፥7-9፤ሕዝ20፥6 ይመ::

106፥26-27 *እንዲወድቁ ... ወደቁ፤* የ13፥4 ማብ ይመ::

*106፥28-31፤* ዘኍ25 ይመ::

106፥31 *ጽድቅ ሆኖ ተቈጠረለት፤* የአብርሃም እምነቱ ጽድቅ ሆኖ እንደ ተቈጠረለት ሁሉ (ዘፍ15፥16)፣ ፊንሐስም ለእግዚአብሔር የነበረው ቅናት (ዘኍ25፥7-8) እንደዚሁ ጽድቅ ሆኖ የተቈጠረለት መሆኑን መዝሙረኛው ይገልጻል (ዘኍ25፥7-8

32ደግሞም በመሪባ ውሃ አጠገብ እግዚ
አብሔርን አስቈጡት፤
ሙሴም ከእነርሱ የተነሣ ተቸገረ፤
33የእግዚአብሔርንም መንፈስ ስላስመረሩት፣
ሙሴ የማይገባ ቃል ከአንደበቱ አወጣ።†
34እግዚአብሔር ባዘዛቸው መሠረት፣
ሕዝቦችን ከማጥፋት ወደ ኋላ አሉ፤
35እንዲያውም ከሕዝቦቹ ጋር ተደባለቁ፤
ልማዳቸውንም ቀሠሙ፤
36ጣዖቶቻቸውንም አመለኩ፤
ይህም ወጥመድ ሆነባቸው።
37ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውን
ለአጋንንት ሠዉ።
38የወንዶችና የሴቶች ልጆቻቸውን ደም፣
ለከነዓን ጣዖታት የሠዉአቸውን፣
ንጹሕ ደም አፈሰሱ፤
ምድሪቱም በደም ተበከለች።
39በተግባራቸው ረከሱ፤
በድርጊታቸውም አመንዝሮች ሆኑ።
40ስለዚህ የእግዚአብሔር ቍጣ በሕዝቡ ላይ
ነደደ፤
ርስቱንም ተጸየፈ።
41ለአሕዛብ አሳልፎ ሰጣቸው፤
ጠላቶቻቸውም በላያቸው ሠለጠኑ።
42ጠላቶቻቸው ጨቈኗቸው፤
በሥልጣናቸውም ሥር አዋሏቸው።
43እርሱ ብዙ ጊዜ ታደጋቸው፤
እነርሱ ግን ዐመፃን የሙጥኝ አሉ፤
በኀጢአታቸውም ተዋረዱ።
44ሆኖም ጩኸታቸውን በሰማ ጊዜ፣
ጭንቀታቸውን ተመለከተ፤
45ለእነርሱም ሲል ቃል ኪዳኑን አሰበ፤
እንደ ምሕረቱም ብዛት ከቍጣው
ተመለሰ።
46የማረኳቸው ሁሉ፣
እንዲራሩላቸው አደረገ።
47አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ፤ አድነን፤
ለቅዱስ ስምህ ምስጋና እናቀርብ ዘንድ፣
አንተን በመወደስ እንጓደድ ዘንድ፣
ከሕዝቦች መካከል ሰብስበህ አምጣን።
48የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር፣
ከዘላለም እስከ ዘላለም ይባረክ፤
ሕዝብም ሁሉ፣ "አሜን!" ይበል።
ሃሌ ሉያ።

106፥32 ዘፀ17፥7፤ ዘኍ20፥2-13
106፥33 ዘፀ17፥4-7፤23፥21፤ዘኍ20፥8-12፤መዝ51፥11፤107፥11፤ኢሳ63፥10
106፥34 ዘፀ23፥24፤ ዘዳ2፥34፤7፥16፤20፥17፤ኢሱ9፥15፤ መሳ1፥27-36
106፥35 መሳ3፥5-6፤ዕዝ9፥1-2
106፥26 ዘፀ10፥7፤ ዘዳ7፥16
106፥37 ዘፀ22፥20፤ ዘሌ18፥21፤ዘዳ12፥31፤32፥17፤ሕዝ16፥20-21፤1ቆሮ10፥20
106፥38 ዘሌ18፥21፤ዘዳ18፥10፤2ነገ3፥27
106፥39 ዘፍ3፥17፤ ዘሌ18፥24፤ዘኍ15፥39፤ሕዝ20፥18
106፥40 ዘፀ34፥9፤ ዘሌ26፥28፤ዘዳ9፥29
106፥41 መሳ2፥14
106፥42 መሳ4፥3
106፥43ኢሱ10፥14፤መሳ2፥16-19፤6፥1-7፤7፥1-25፤ነህ9፥28፤ መዝ81፥13-14
106፥44 መሳ3፥9
106፥45 ዘፍ9፥15፤ ዘፀ32፥14፤መዝ17፥7፤103፥11፤105፥8፤ሉቃ1፥72
106፥46 ዘፀ3፥21፤1ነገ8፥50
106፥47 መዝ28፥9፤30፥4፤99፥3፤105፥1፤107፥3፤147፥2፤ኢሳ11፥12፤27፥13፤56፥8፤66፥20፤ኤር31፥8፤ሕዝ20፥34፤ሚክ4፥6
106፥48 መዝ41፥13፤72፥19

†33 አንዳንዶች *ራሱን ባለመቈጣጠርና በችኰላ ተናገረ*

ይመ)። *ከትውልድ እስከ ትውልድ ለዘላለም፤* መዝሙረኛው እግዚአብሔር ለፊንሐስ የሰጠውን "የዘላለም ክህነት ቃል ኪዳን" ይጠቅሳል፤ ፊንሐስ እንዲህ ያለ ክህነት የተቀበለው ባሳየው ቅናት ምክንያት ነው (ዘኍ25፥13)።

106፥32 *በመሪባ፤* የዘፀ17፥7 ማብ ይመ።

106፥33 *የእግዚአብሔርንም መንፈስ ስላስመረሩት፤* እስ ራኤላውያን በምድረ በዳ ሲንከራተቱ ሳለ፣ የእግዚአብሔር መን ፈስ ሥራውን ይሠራ እንደ ነበር በዘፀ31፥3፤ ዘኍ11፥17፤ 24፥2፤ ነህ9፥20፤ ኢሳ63፥10-14 ላይ ይመ።

*106፥34-39፤* እስራኤላውያን ከዘመነ መሳፍንት አንሥቶ እስከ ባቢሎን ምርኮ ድረስ ከፈጸሟቸው ኀጢአቶች ሁሉ እጅግ የከፋው ዐመፅ ይህ መሆኑን ለማሳየት ጠቅለል ባለ መልክ በዚህ ቦታ የቀረበ ነው።

106፥37 *ለአጋንንት፤* ይህ ቃል በብሉይ ኪዳን መጽሐፍት በዕብራይስጡ ቅጅ ተጽፎ የሚገኘው በዘዳ32፥17 ላይ ብቻ ነው። ቃሉም ሐሰተኞች አማልክትን ለማመልከት የገባ ሲሆን፣ ባቢሎናውያን ጠባቂዎቻችን ናቸው፤ ለሚሏቸው መናፍስት ከሰጧቸው ስም ጋር ይዛመዳል።

*106፥38፤* ከኤር19፥4-5 ጋር ያነጻጽሩ። *ንጹሕ ደም፤* ለሞት ቅጣት የሚያበቃ ከባድ ጥፋት ያልፈጸመ የማንኛውም ሰው ደም ማለት ነው። *ተበከለች፤* መሬት ራሷ ምንም በደል የሌለባቸው የንጹሐን ደም ስለፈሰሰባት ረክሳለች (ዘኍ35፥33፤ ኤር3፥2፡9)።

106፥39 *ረከሱ፤* ዘሌ18፥24፤ ኤር2፥23፤ ሕዝ20፥30-31፤ 22፥3-4 ይመ። *አመንዝሮች ሆኑ፤* ከሐሰተኞች አማልክት ጋር ራሳ ቸውን ስለ ጠበቁ (ሕዝ23፥3፡5-8፤ ሆሴ5፥3፤ 6፥10 ይመ፤ እንዲ ሁም የመሳ2፥17 ማብ ይመ)።

*106፥40-43፤* ከዘመነ መሳፍንት አንሥቶ እስከ ባቢሎን ምርኮ ድረስ የነበሩት የእስራኤል ሕዝቦች የፈጸሙትን በደል የሚያሳይ ሲሆን እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን መሠረት በማድረግ ይህንን ሕዝብ ክፉኛ ቀጥቶታል (ዘሌ26፥25-26፡33፡38፡39፤ ዘዳ 28፥25፡36-37፡48-57፡64-69 ይመ)።

106፥40 *ቍጣ ... ነደደ፤* የ2፥5 ማብ ይመ። *ተጸየፈ፤* 5፥6 ይመ።

*106፥44-46፤* ይህ ክፍል እግዚአብሔር ከርኅራኄው ብዛት የተነሣ ቃል ኪዳኑን ማሰቡን ያመለክታል፤ ይህም ከዘመነ መሳፍንት አንሥቶ እስከ ባቢሎን ምርኮ ድረስ በተግባር ተገልጾ ታይቶአል።

106፥44 *ጩኸታቸውን በሰማ ጊዜ፤* ዘፀ2፥23፤ 3፥7-9፤ ዘኍ20፥16፤ መሳ3፥9፡15፤ 4፥3፤ 6፥6-7፤ 10፥10፤ 1ሳሙ9፥16፤ 2ዜና20፥6-12፤ ነህ9፥27-28 ይመ።

106፥45 *ቃል ኪዳኑን አሰበ፤* 105፥8፡42፤ ዘፀ2፥24፤ ዘሌ 26፥42፡45፤ *ምሕረቱ፤* የ6፥4 ማብ ይመ።

106፥46 *የማረኳቸው ሁሉ እንዲራሩላቸው አደረገ፤* የመ ዝሙረኛው ትረካ የባቢሎንን ምርኮ ማካተቱን በግልጽ ያሳያል (1ነገ 8፥50፤ 2ዜና30፥9፤ ዕዝ9፥9፤ ኤር42፥12 ይመ)። ምንም እንኳ ቀደም ባለው ጊዜ በእስራኤላውያን ማኅበረ ሰብ ላይ የደ ረሰ ምርኮ ቢኖርም ርኅርኄ የተደረገለት ወገን ስለመኖሩ የተወሳ ወይም የተነገረ ነገር የለም።

*106፥47፤* እግዚአብሔር እንዲታደጋቸውና ከተበተኑባቸው ቦታዎች ሁሉ ወደ አገራቸው እንዲመልሳቸው ማኅበረ ሰቡ ያቀረ በው ጸሎት ነው (መግቢያውንና የቍ4 ማብ ይመ)። *ስምህ* የ5፥11 ማብ ይመ። *አንተን በመወደስ እንጓደድ ዘንድ፤* ድል አድራጊ ነትህን እናመሰግን ዘንድ ማለት ነው።

*106፥48፤* የመዝሙሩ አራተኛ መጽሐፍ ማሳረጊያ ውዳሴ። *አሜን፤* የዘዳ27፥15 ማብ ይመ።

*107፤* አጥብቀው የሚሹት ወገኖች የሚያቀርቡትን ጸሎት በማስማትና በማዳን ስለሚገለጠው ጽኑ ፍቅሩ እግዚአብሔርን ለማመስገን የቀረበ ልመና ነው (ስለ መዝሙሩ አወቃቀር የሚቀ ጥለውን አንቀጽ ይመ)። መዝሙሩ እስራኤላውያን ከሚያከብሩ አቸው ዐበይት ሃይማኖታዊ በዓላት በአንዱ፣ የተሰጥዎ ምስጋና እንዲያቀርቡብት የተዘጋጀ ነው። ይህን አስመልክቶ የተሰጡት ትርጓሜዎች በእጅጉ ይለያያሉ፤ ሆኖም ከዚህ በታች የተሰጠው ትርጓሜ ግን ትክክለኛ ነው ተብሎ ይታመናል። ከባቢሎን ምርኮ በኋላ የእግዚአብሔርን ምሕረት በአዲስ መልክ የተለማመደችው እስራኤል (ቍ3፤ እንዲሁም ኤር33፥11 ይመ) በገጠማት ታላቅ መከራ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ተጣርታ (ጮኻ) ስለ ነበር እግዚ አብሔር ከጽኑ ፍቅሩ የተነሣ ጩኸቷን ሰምቶ ስለታደጋት፣ በአንድ ሌዋዊ እየተመራች ምስጋና ታቀርባለች። መዝሙሩ በአቀራረብ ከመዝ104-106 ካሉት መዝሙሮች በቋንቋ ማለትም በቃላት አገባብና አጠቃቀሙ ከመዝ105-106 ጋር የቅርብ ተዛምዶ አለው፤ ከዚህም የተነሣ መዝ105፤ 106፤ 107 (ሦስቱ) ከአንድ ጸሓፊ ብዕር የፈለቁ ናቸው ተብሎ ይታመናል። እግዚ አብሔር "ስለ ስሙ አዳናቸው" (ቍ8) የሚለው ሐረግ በመዝ 105-106 ላይ የተነገሩትን ነገሮች ሁሉ ከመጨረሻው ከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚያደርስ ነጥብ ሲሆን፣ ይህም እግዚአብሔር በሥነ ፍጥረቱ የገለጠውን ብዙ ድንቅ ሥራ (104፥2-26 ይመ) እንዲ ሁም ለእንስሳት ያለውን በጎነት (104፥27-30) በሌላው የሚዛን ክንድ ላይ አስቀምጦ እዩት ይላል።

# አምስተኛ መጽሐፍ
## (መዝሙር 107-150)

## መዝሙር 107
### ከመከራ ሁሉ የሚታደግ አምላክ

1ቸር ነውና እግዚአብሔርን አመስግኑ፤
ምሕረቱም ለዘላለም ነውና።
2እግዚአብሔር የተቤዣቸው፣
ከጠላት እጅ የታደጋቸው ይህን ይበሉ፤
3ከምሥራቅና ከምዕራብ፣ ከሰሜንና
ከደቡብ፣*
ከየአገሩ የሰበሰባቸው እንዲህ ይናገሩ።
4አንዳንዶቹ ጭው ባለ በረሓ ተቅበዘበዙ፤
ወደሚኖሩባት ከተማ የሚያደርስ
መንገድ አጡ።
5ተራቡ፤ ተጠሙ፤
ነፍሳቸውም በውስጣቸው ዛለች።
6በተጨነቁ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ጮኹ፤
እርሱም ከመከራቸው አዳናቸው።
7ወደሚኖሩባትም ከተማ፣
በቀና መንገድ መራቸው።
8እግዚአብሔርን ስለ ምሕረቱ፣
ለሰው ልጆችም ስላደረገው ድንቅ
ሥራ ያመስግኑት፤
9እርሱ የተጠማችውን ነፍስ አርክቶአልና፤
የተራበችውንም ነፍስ በበጎ ነገር
አጥግቦአል።
10አንዳንዶቹ በብረት ሰንሰለት ታስረው
የተጨነቁ፣
በጨለማ፣ በጥልማሞት ውስጥ
የተቀመጡ ነበሩ፤
11በእግዚአብሔር ቃል ላይ በማመፃቸው፣
የልዑልን ምክር አቃለዋልና።
12ስለዚህ በጉልበት ሥራ ልባቸውን አዛለ፤
ተዝለፈለፉ፤ የሚደግፋቸውም
አልነበረም።
13በተጨነቁ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር
ጮኹ፤
እርሱም ከመከራቸው አዳናቸው።
14ከጨለማና ከጥልማሞት አወጣቸው፤
እስራታቸውንም በጠሰላቸው።
15እግዚአብሔርን ስለ ምሕረቱ፣
ለሰው ልጆችም ስላደረገው ድንቅ ሥራ
ያመስግኑት፤
16እርሱ የናሱን በሮች ሰብሮአልና፤
የብረቱንም መወርወሪያ ቈርጦአል።
17አንዳንዶቹ ከዐመፃቸው የተነሣ ቂሎች
ሆኑ፤
ከበደላቸው የተነሣ ችግር ውስጥ ገቡ።

107፥1 1ዜና16፥8፤ 2ዜና5፥13፤7፥3
107፥2 መዝ106፥10፤ኢሳ35፥9
107፥3 ነህ1፥9
107፥4 ቍ36፤ኢሱ 5፥6
107፥5 ዘፀ15፥22፤ 16፥3፤17፥2
107፥6 ዘፀ14፥10
107፥7 ቍ36፤ዕዝ 8፥21
107፥8 መዝ6፥4፤ 75፥1፤105፥1
107፥9 መዝ22፥26 ፤23፥1፤63፥5፤ኢሳ 58፥11፤ኤር31፥25፤ ማቴ5፥6፤ሉቃ1፥53
107፥10 ቍ14፤ ኢዮ36፥8፤መዝ88፥6 ፤102፥20፤143፥3፤ኢሳ 9፥2፤42፥7:16፤49፥9፤ 61፥1፤ሚክ7፥9
107፥11 ዘኍ14፥11 ፤1ነገ22፥5፤2ዜና 36፥16፤መዝ5፥10
107፥12 2ነገ14፥26 ፤መዝ72፥12
107፥13 መዝ106፥8
107፥14 ቍ10፤ ኢዮ36፥8፤መዝ86፥ 13፤116፥16፤ኢሳ9፥2 ፤29፥18፤42፥7፤50፥ 10፤59፥9፤60፥2፤ሉቃ 1፥79፤ሐሥ12፥7
107፥15 ቍ8:21፡ 31፤መዝ6፥4፤75፥1፤105፥1 107፥17 ዘሌ26፥16፤መዝ25፥7፤ 53፥1፤ኢሳ65፥6-7፤ኤር30፥14-15፤ገላ6፥7-8 107፥18 ኢዮ3፥24፤ 6፥6፤17፥16፤33፥22

*3 ዕብራይስጡ ሰሜንና ባሕሩ ይለዋል።

*107፥1-31* እግዚአብሔርን ለማመስገን በመግቢያ ላይ የቀረበ ጥሪ ነው።

*107፥1፤* ለምስጋና ተሰጥዎ የሚቀርብ የተለመደ ጥሪ ነው (106፥1፤ 118፥1:29፤136፥1፤ ኤር33፥11 ይመ)። *አመስግኑ፤* ቍ8: 15:21:31 ይመ፤ እንዲሁም የመዝ100 ርእስ ማብ ይመ። *ምሕረቱም፤* ቍ8:15:21:31:43 ይመ፤ እንዲሁም የ6፥4 ማብ ይመ።

107፥2 *የተቤዣቸው፤* እዚህ ላይ የቃሉ ትርጒም እንደተለመደው የሚሰጠው ፍቺ አወጣቸው ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው።

107፥3 *ከየአገሩ፤* በአሦራውያን እንዲሁም (2ነገ17፥6 ይመ) በባቢሎን ምክንያት ከተበተኑበት አገር ሁሉ ማለት ነው (2ነገ24፥14:16፤ 25፥11:26፤ ኤር52፥28-30 እንዲሁም ነህ1፥8፤ ኢሳ8፥5:9:13፤ 11፥12፤ 43፥5-6፤ ሕዝ11፥17፤ 20፥34 ይመ)። *ደቡብ፤* ቃል በቃል ሲተረጐም፣ "ባሕር" ማለት ነው፤ በኢሳ49፥12 ላይ እንደ ተጻፈው ምዕራብን ያመለክታል፤ ምናልባት ግን በዕብራይስጡ የዚህ ቃል የመጨረሻው ሆሄ ስለጠፋ የቃሉን ትክክለኛ ፍቺ አዛብቶት ይሆናል የሚል ግምት አለ።

*107፥4-9፤* ጭው ባለ ምድረ በዳ ጠፍተው የነበሩትን መታደጉን ያመለክታል፤ እዚህ ላይ ስለ ዐመፃቸው የተወሳ ነገር የለም፤ ነገር ግን እስራኤል ወደ ከነዓን ምድር የገባችው ምድረ በዳውን አቋርጣ ስለ ነበር የዚያን ነዲድ በረሓ፣መከራና ሥቃይ ከነገፈቱ ተግታዋለች። ከዚህም በቀር በስተ ምሥራቅ ባለው በትልቁ የዐረብ ምድረ በዳ የምትዋሰን ሲሆን (በስተ ምዕራብ ደግሞ በሜድትራኒያን ባሕር ትዋሰናለች ቍ23-32 ይመ) የታወቁ ታላላቅ (ሲራራ) ነጋዴዎች ይህንንም አቋርጠው ይጓዙ ነበር።

107፥4:7:36 *ወደ ሚኖሩበት ከተማ፤* ምግብና ውሃ እንደ ልብ የሚገኝባቸው ለሰዎች ኑሮ አስተማማኝ የሆኑ ከተሞች ማለት ነው።

107፥6 *ጮኹ፤* ይህ ቃል በቍ13:19:28 ላይ ተደጋግሞ ይገኛል። የእስራኤል ታሪክ በያህዌ አዳኝነትና ታዳጊነት (መዝ 105 ይመ) እንዲሁም በእስራኤል ሕዝብ ዐመፀኝነት የተሞላ (መዝ 106 ይመ) እንደ ሆነ ሁሉ ከመከራው ጽናት የተነሣ ወደ እግዚአብሔር መጮኽ የተሞላም ታሪክ ነው (የ106፥44 ማብ ይመ)።

107፥7 *በቀና መንገድ፤* ከአደጋም ሆነ ከመከራ ነጻ የሆነና ወደ ታሰበበት ቦታ የሚያደርስ ቀጥ ያለ መንገድ ነው።

107፥9 *የተጠማችውን አርክቶአልና፤ የተራበችውን ... አጥግቦአል፤* ቍ5 እንዲሁም 105፥40-41 ይመ።

*107፥10-16፤* ከባዕድ የባርነት አገዛዝ ቅጣት ነጻ እንደሚወጡ የሚናገር ክፍል ነው። ቅጣቱ የመጣው በኀጢአታቸው ምክንያት ቢሆንም እንኳ (17-20:33-41 ይመ)፣ በመከራቸው ጊዜ ወደ እርሱ የሚጮኹትን እግዚአብሔር ይታደጋቸዋል።

107፥10 *በጨለማ፣ በጥልማሞት ውስጥ፤* የመከራን አስከፊነት የሚገልጽ ምስላዊ አነጋገር ነው (18፥28፤ ኢሳ 5፥30፤ 8፥22፤ 59፥9 ይመ። እንዲሁም የ44፥19 ማብ ይመ)። *እስረኞች፤* ነገሩ እዚህ ላይ በትክክል የሚያመለክተው መራራውን የባዕድ አገር አገዛዝና ባርነት ቢሆንም፣ ይህ ዐይነቱ አገላለጽ ሌሎችንም የመከራ ዐይነቶች የሚያመለክት መሆኑ፣ በሌሎች የብሉይ ኪዳን ባለቅኔዎች ተጽፎ ይገኛል (ኢዮ36፥8፤ ኢሳ28፥22፤ ሰቆ3፥7 ይመ)። ስለዚህ ቃሉ አሻሚ ትርጒም ያለው ይመስላል።

107፥11 *በእግዚአብሔር ... የልዑልን፤* ልዑል እግዚአብሔር ማለት ነው (ዘፍ14፥19 እና ማብ ይመ፤ እንዲሁም የ3፥7 ማብ ይመ)። *ምክር፤* ጥበብን የተሞላ የእግዚአብሔር መመሪያ በቃሉቹ ይገለጣል።

107፥12 *በጉልበት ሥራ ልባቸውን አዛለ፤* ከከባድነቱ የተነሣ መንፈሳቸውን ጭምር የሚያደቅ ከባድ ሥራ ጫነባቸው ማለት ነው። *ተዝለፈለፉ፤* ብርታት አጡ (31፥10፤ 109፥24፤ ነህ 4፥10፤ ኢሳ40፥30፤ ዘካ12፥8 ይመ)።

107፥13 *ጮኹ፤* የቍ6 ማብ ይመ።

*107፥16፤* ይህ ቍጥር ወይ ከኢሳ45፥2 ላይ የተጠቀሰ ነው፤ ወይም ደግሞ ሁለቱም ከአንድ የታወቀ አባባል ጠቅሰዋል ማለት ነው። *የናሱን በሮች፤* የከተማዪቱ ቅጥር በሮች ናቸው፤ የቅጥር በሮች የሚሠሩት ከዕንጨት መሆኑ የታወቀ ነው፤ እዚህ ላይ ግን የጥንካሬውን ብርታት ለመግለጽ በዘይቤያዊ አነጋገር የገቡት ቃላት ናቸው (ኤር1፥18 ይመ)። *የብረቱንም መወርወሪያ፤* የቅጥሩ በሮች ተዘግተው የሚጠብቁባቸው መወርወሪያዎች ናቸው (ዘዳ3፥5፤ ኤር51፥30 ይመ)፤ የሚሠሩትም ከዕንጨት ነው (ነህ 3፥13 ይመ) አንዳንድ ጊዜ ግን ከናስም ይሠራሉ (1ነገ4፥13 ይመ)። በዚያን ወቅት፣ "ሰው ብረት ወይም ናስ መስበር ይችላል?" የሚል አባባል ነበር (ኤር15፥12 ይመ)።

*107፥17-22፤* ከፍተኛ ጉዳት ወይም ጥፋት ከሚያስከትል የበሽታ ቅጣት መታደጉን ይገልጻል (የቍ10-16 ማብ ይመ)።

107፥17 *ቂሎች፤* ኤር4፥22 ይመ። "የማይረቡ፣ ጥበብንና ተግሣጽን ይንቃሉ" (ምሳ1፥7፤ እንዲሁም ቍ43 ይመ)። *ከበደላቸው የተነሣ ችግር ውስጥ ገቡ፤* ዘሌ26፥16:25፤ ዘዳ28፥20-22: 35:58-61 ይመ።

18 ሰውነታቸው የምግብ ዐይነት ሁሉ
ተጸየፈች፤
ወደ ሞትም ደጆች ቀረቡ።
19 በተጨነቁ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ጮኹ፤
እርሱም ከመከራቸው አዳናቸው።
20 ቃሉን ልኮ ፈወሳቸው፤
ከመቃብርም አፋፍ መለሳቸው።
21 እግዚአብሔርን ስለ ምሕረቱ፣
ለሰው ልጆችም ስላደረገው ድንቅ ሥራ
ያመስግኑት፤
22 የምስጋናም መሥዋዕት ያቅርቡለት፤
ሥራውንም ደስ በሚል ዝማሬ
ይግለጹ።
23 አንዳንዶቹ በመርከብ ወደ ባሕር ወረዱ፤
በታላቅም ውሃ ላይ ሥራቸውን
አከናወኑ፤
24 የእግዚአብሔርን ሥራ በዚያ አዩ፤
ድንቅ አድራጎቱንም በጥልቁ ውስጥ
ተመለከቱ።
25 እርሱ ተናግሮ ዐውሎ ነፋስን አስነሣ፤
ነፋሱም ማዕበሉን ከፍ ከፍ አደረገ።
26 ወደ ሰማይ ወጡ፤ ወደ ጥልቅም ወረዱ፤
ከመከራቸውም የተነሣ ሐሞታቸው
ፈሰሰ።
27 እንደ ሰከረ ሰው ዞሮባቸው ወዲያ ወዲህ
ተንገዳገዱ፤
መላው ጠፍቶባቸው የሚያደርጉትን
አጡ።
28 በተጨነቁ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ጮኹ፤
እርሱም ከመከራቸው አዳናቸው።
29 ዐውሎ ነፋሱን ጸጥ አደረገ፤
የባሕሩም ሞገድ ረጭ አለ።
30 ጸጥ በማለቱም ደስ አላቸው፤
ወዳሰቡትም ወደብ አደረሳቸው።
31 እግዚአብሔርን ስለ ምሕረቱ፣
ለሰው ልጆችም ስላደረገው ድንቅ
ሥራ ያመስግኑት፤
32 በሕዝብ ጉባኤ መካከል ከፍ ከፍ
ያድርጉት፤
በሽማግሌዎችም ሸንጎ ይወድሱት።
33 ወንዞችን ወደ ምድረ በዳ፣
የውሃ ምንጮችንም ወደ ደረቅ ምድር
ለወጠ።
34 ከነዋሪዎቿ ክፋት የተነሣ፣
ፍሬያማዋን ምድር በጨው የተበከለች
አደረጋት።
35 ምድረ በዳውን ወደ ውሃ መከማቻ፣
ደረቁንም ምድር ወደ ውሃ ምንጭ
ቀየረ።
36 የተራቡትን በዚያ አስቀመጠ፤
የሚኖሩባትንም ከተማ ሠሩ።
37 በዕርሻውም ዘሩበት፤ ወይንም ተከሉ፤
ብዙ ፍሬም አመረቱ።
38 ይባርካቸዋል፤ እነርሱም እጅግ ይበዛሉ፤
የከብቶቻቸውም ብዛት እንዲያንስ
አያደርግም።
39 በጭንቅ፣ በመከራና በሐዘን፣
ቍጥራቸው አንሶ፣ ተዋርደው ነበር፤
40 በመኳንንቱም ላይ መናቅን አዘነበባቸው፤
መውጫ መግቢያው በማይታወቅ በረሓ
ውስጥም አንከራተታቸው።
41 ችግረኞችን ግን ከጭንቀታቸው መዝዞ
አወጣቸው፤
ቤተ ሰባቸውንም እንደ በግ መንጋ
አበዛ።
42 ልበ ቅኖች ይህን አይተው ሐሤት
ያደርጋሉ፤

107፥19 ቍ13፡28፤ መዝ5፥2፤34፥4
107፥20 ዘፀ15፥26፤ ዘዳ32፥2፤ኢዮ33፥28፤ መዝ16፥10፤30፥3፤56፥13፤147፥15፤ማቴ8፥8፤ሉቃ7፥7
107፥21 ቍ15፤መዝ6፥4፤75፥1
107፥22 ዘሌ7፥12፤ ኢዮ8፥21፤መዝ9፥11፤65፥8፤73፥28፤118፥17
107፥23 መዝ104፥26፤ኢሳ42፥10
107፥24 መዝ64፥9፤111፥2፤143፥5
107፥25 መዝ50፥3፤93፥3፤105፥31
107፥26 ኢሉ2፥11፤ሉቃ8፥23
107፥27 ኢሳ19፥14፤24፥2፤28፥7
107፥28 ቍ19፤መዝ4፥1፤ዮና1፥6
107፥29 መዝ65፥7፤93፥3፤ዮና1፥15፤ሉቃ8፥24
107፥30 ቍ7
107፥31 ቍ15፤መዝ6፥4፤75፥1፤106፥2
107፥32 መዝ1፥5፤22፥22፤26፥12፤30፥1፤34፥3፤35፥18፤99፥5
107፥33 1ነገ17፥1፤ መዝ74፥15፤104፥10፤ ኢሳ41፥15፤42፥15፤50፥2
107፥34 ዘፍ13፥10
107፥35 2ነገ3፥17፤ኢዮ38፥26፤መዝ105፥41፤126፥4፤ኢሳ35፥7፤43፥19፤51፥3
107፥37 2ነገ19፥29፤ኢሳ37፥30
107፥38 ዘፍ12፥2፤49፥25፤ዘዳ7፥13
107፥39 2ነገ10፥32፤መዝ44፥9፤ሕዝ5፥12 107፥40 ዘዳ32፥10፤ኢዮ12፥18 107፥41 1ሳሙ2፥8፤ኢዮ21፥11፤መዝ113፥7-9
107፥42 ኢዮ5፥16፤22፥19፤መዝ97፥10-12፤ሮሜ3፥19

107፥18 *ወደ ሞት ደጆች፤* ሰባት ተከታታይ በሮች ያሉት የሙታን ነፍሳት መኖሪያ ስፍራ አለ ተብሎ በጥንት ቅርብ ምሥራቅ አገሮች የሚታመን ሲሆን፣ እነዚህ በሮች ወደዚያ የወረዱ የሙታን ነፍሳት ወደ ሕያዋን ምድር እንዳይመለሱ የሚያግዱ መዝጊያዎች ናቸው (9፥13 እና የኢዮ38፥17 ማብ እንዲሁም ማቴ16፥18 ይመ)።

107፥19 *ጮኹ፤* የቍ6 ማብ ይመ። *ገላገላቸው፤* ቍ13 ይመ። ከቍ6፥28 ጋር ያነጻጽሩ።

107፥20 *ቃሉን፤* ትእዛዙን ማለት ነው፤ እዚህ ላይ ያሰበውንና ያቀደውን የሚፈጽም መልእክተኛ ሆኖ ቀርቦአል (147፥15፡18 እንዲሁም የ23፥6 ማብ ይመ)።

107፥22 *የምስጋናም መሥዋዕት፤* ዘሌ7፥12-15፤ 22፥29-30 ይመ። *ስለ ሥራውም... ይግለጹ፤* የ7፥17 ማብ ይመ።

*107፥23-32፤* ከባሕር አደጋ መትረፉን የሚናገር ክፍል ነው (የቍ4-9 ማብ ይመ)። የእስራኤል ነጋዴዎች ለንግድ ሥራ በመርከብ ይጓዙ ነበር (ዘፍ49፥13፤ መሳ5፥17፤ 1ነገ9፥26-28፤ 10፥22 ይመ)።

107፥23 *በታላቅም ውሃ፤* 29፥3 ይመ።

107፥24 *ድንቅ ... ብጥልቁ፤* የምሥራቅ ሜድትራኒያን ባሕር ጠረፍ ሕዝቦች የባሕሩን "ኀይለኛ ... ውሃ" (ቍ3) ከጥንት ጀምሮ ከነበረው ዐመፀኛ ውሃ ጋር የሚያያይዙት ሲሆን፣ እግዚአብሔር ይህን ዐመፀኛ ውሃ ሙሉ በሙሉ የሚቈጣጠር አምላክ መሆኑ እስራኤላውያንን ምን ጊዜም ሲያስደንቃቸው ይኖራል፤ ለደኅንነት ጥበቃቸውም ዋስትናቸው አድርገው በታላቅ ቁም ነገር ይመለከቱታል። ስለዚህም አንዳንድ ጊዜ የሜድትራኒያንን ባሕር ክፉኛ የሚያናውጠው ማዕበል (ዮና1፡ ዮሐ27) ከድንቅ ሥራዎቹ እንደ አንዱ ሆኖ እዚህ ላይ ገብቶአል።

107፥30 *ወደብ፤* ምናልባት የንግድ ማዕከል ሳይሆን አይቀርም።

*107፥32፤* ቍ22 ይመ። *በሽማግሌዎችም፤* የዘፀ3፥16 ማብ ይመ።

*107፥33-42፤* እግዚአብሔር የሰጡትን ዘር የሚቀበለውን መልካሙን ምድር (ቍ34) ወደ ምድረ በዳነት ለውጦ (1ነገ17፥1-7፤ 2ነገ8፥1) ሕዝቡን በራብ እንደ ቀጣው፣ ከዚያም እንደ ገና ያንኑ ምድር እንደ ፈወሰውና (ሩት1፥6፤ 1ነገ18፥44-45) የተራበው ሕዝቡ (ቍ36) እንዲኖርበትና ምርት እንዲያፍስበት አድርጎአል። ከዚያ በኋላ ግን በሕዝቡ ላይ ብርቱ ጠላት (እንደ አሦራውያንና 2ነገ17፥3-6፤ እንደ ባቢሎናውያን ያሉ 2ነገ24፥20-27፤ 25፥1-26) አስነሥቶና ሰራዊት አዝምቶ ምድሪቱን እንዳልነበረ በማድረግ ሕዝቡን ወደ ምርኮ አገር ወስዶአቸዋል፤ ይህም ሆኖ ግን የኋላ ኋላ ችግረኞችን (ቍ41) መልሶአቸዋል።

*107፥33-35፤* እዚህ ላይ ምስላዊ በሆነ መልክ የቀረበው ሐሳብ በኢሳ35፥6-7፤ 41፥18፤ 42፥15፤ 43፥19-20፤ 50፥2 ላይ ከተጻፈው ጋር ይመሳሰላል፤ ይህም ምናልባት መዝሙረኛው በኢሳይያስ ጽሑፍ ሳይማረክ እንዳልቀረ ያሳያል።

*107፥40፤* ምናልባት ከኢዮ12፥21፡24 ላይ የተወሰደ ጥቅስ ሊሆን ይችላል። *በመኳንንቱ ላይ መናቅን አዘነበባቸው፤* በረከቱንም ባትረፈረፈላቸው አምላክ ላይ ጀርባቸውን አዞሩ (ዘዳ31፥20፤ 32፥15)፤ ስለዚህም ወደ ምድ ረበዳ መልሶ ሰደዳቸው (ዘዳ32፥10፤ ሆሴ2፥3፡14)።

107፥41 *ችግረኞችን፤* ርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ማለት ነው (ቍ39 ይመ፤ እንዲሁም 9፥18 እና ማብ ይመ)።

*107፥42፤* የመመሪያው (ቍ33-41) መደምደሚያ ነው። ይህ ምናልባት በኢዮ5፥16 ላይ ጻድቅ ... ክፉ ተብሎ የተጻፈውን

ጥመትም ሁሉ አፏን ትዘጋለች።
[43]እንግዲህ ማንም ብልህ ቢሆን፣ ይህን
ነገር ልብ ይበል፤
እርሱም የእግዚአብሔርን ምሕረት
ያስተውላል።

## መዝሙር 108

### የጧት ውዳሴና ብሔራዊ ጸሎት

108፥1-5 ተጓ ምብ-መዝ57፥7-11
108፥6-13 ተጓ ምብ-መዝ60፥5-12

የዳዊት መዝሙር፤ ማኅሌት

[1]አምላክ ሆይ፤ ልቤ ጽኑ ነው፤
እዘምራለሁ፤ በፍጹም ነፍሴም እዘምራለሁ።
[2]በገናም መሰንቆም ተነሡ፤
እኔም ማልጄ እነሣለሁ።
[3]እግዚአብሔር ሆይ፤ በሕዝብ መካከል
አመሰግንሃለሁ፤
በሕዝቦችም መካከል እዘምርልሃለሁ።
[4]ምሕረትህ ከሰማያት በላይ ታላቅ ናትና፤
ታማኝነትህም እስከ ጠፈር ትደርሳለች።
[5]አምላክ ሆይ፤ ከሰማያት በላይ ከፍ ከፍ
በል፤
ክብርህም በምድር ሁሉ ላይ ትንሰራፋ።
[6]ወዳጆችህ ይድኑ ዘንድ፣
በቀኝ እጅህ ታደግ፤ መልስልኝም።
[7]እግዚአብሔር ከመቅደሱ እንዲህ አለ፤
ደስ እያለኝ ሴኬምን እሸንሽናለሁ፤
"የሱኮትንም ሸለቆ እለካለሁ።
[8]ገለዓድ የእኔ ነው፤ ምናሴም የእኔ ነው፤
ኤፍሬም የራስ ቍሬ ነው፤
ይሁዳም በትረ መንግሥቴ።
[9]ሞዓብ መታጠቢያ ገንዳዬ ነው፤
በኤዶምያስ ላይ ጫማዬን
እወረውራለሁ፤
በፍልስጥኤም ላይ በድል አድራጊነት
እፎክራለሁ።"
[10]ወደ ተመሸገችው ከተማ ማን
ይወስደኛል?
ወደ ኤዶምያስስ ማን ያደርሰኛል?
[11]እግዚአብሔር ሆይ፤ የጣልኸን አንተ
አይደለህምን?
አምላክ ሆይ፤ ከሰራዊታችንም ጋር
አልወጣ አልህ!
[12]አሁንም የሰው ማዳን ከንቱ ነውና፣
በጠላታችን ላይ ድልን አቀዳጀን።
[13]እግዚአብሔር ሲረዳን ብርቱ እንሆናለን፤
ጠላቶቻችንንም ከእግሩ በታች
የሚረግጥ እርሱ ነው።

## መዝሙር 109

### በጠላት ላይ የቀረበ ጸሎት

ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር

[1]የምስጋናዬ ምንጭ የሆንህ አምላክ ሆይ፤
ዝም አትበል፤
[2]ክፉዎችና አታላዮች፣
አፋቸውን ከፍተውብኛልና፤
በውሸተኛ አንደበት ተናግረውብኛል።
[3]በጥላቻ ቃል ከበውኛል፤
ያለ ምክንያትም ጥቃት አድርሰውብኛል።
[4]ስወዳቸው ይወነጅሉኛል፤
እኔ ግን እጸልያለሁ።
[5]በበጎ ፈንታ ክፋትን፣
በወደድኋቸው ፈንታ ጥላቻን
ይመልሱልኛል።

107፥43 መዝ103፥11፤ኤር9፥12፤ሆሴ14፥9
108፥1 መዝ18፥49፤112፥7፤119፥30፡112
108፥2 ኢዮ21፥12
108፥4 ዘፀ34፥6፤ዘኍ14፥18፤መዝ36፥5፤106፥45
108፥5 መዝ8፥1፤57፥5
108፥6 ኢዮ40፥14
108፥7 ዘፍ12፥6፤33፥17፤መዝ68፥35፤89፥35፤102፥19
108፥8 መዝ78፥68
108፥9 ዘፍ19፥37፤2ሳሙ8፥1፡13-14
108፥11 መዝ44፥9
108፥12 መዝ118፥8፤146፥3፤ኢሳ10፥3፤30፥5፤31፥3፤ኤር2፥36፤17፥5
108፥13 መዝ44፥5፤ኢሳ22፥5፤63፥3፡6
109፥1 ዘፀ15፥2፤ኢዮ34፥29፤ኤር17፥14
109፥2 መዝ43፥1፤52፥4
109፥3 መዝ35፥7፤69፥4፤ዮሐ15፥25
109፥4 መዝ69፥13፤141፥5
109፥5 ዘፍ44፥4

የሚያስተጋባ ሳይሆን አይቀርም። ይህም በብሉይ ኪዳን የጥበብ መጻሕፍት ተደጋግሞ የቀረበ ማነጻጸሪያ ነው (ምሳ2፥21-22፤ 11፥6-7፤ 12፥6፤ 14፥11፤ 15፥8፤ 21፥18፡29፤ 29፥27፤ ክፉ የሚለው ቃል ግን በዚህ ቦታም ሆነ በሌላ ቦታ አብዛኛውን ጊዜ ተመሳሳይነቱ በኢዮብ መጽሐፍ ከተጻፈው ጋር ነው)።

*107፥43፤* የመዝሙሩ መደምደሚያ ነው። *ማንም ብልህ ቢሆን፤* ዘዳ32፥29፤ ሆሴ14፥9 ይመ። ይህን ከቍ33-42 ላይ የተጻፈውን መመሪያ የሚያመለክት ነው። *የእግዚአብሔርን ምሕረት ያስተውላል፤* ከቍ4-32 ለቀረበው ሐሳብ ፍሬ ነገሩ ይህ ሐረግ ነው።

*108፥1፤* የእግዚአብሔርን ፍቅር የሚያመሰግንና እግዚአብሔርም ከጠላት እንዲታደገው የቀረበ ጸሎት ነው፤ ይህ መዝሙር ከመዝ57፥7-11 እና 60፥5-12 ላይ ተወጣጥቶ የተጻፈ ነው፤ በተመሳሳይ መንገድ አንድ አዲስ መዝሙር ከተለያዩ መዝሙሮች ላይ ተውጣጥቶ እንዴት እንደ ተጻፈ 1ዜና16፥8-36 ይመ። የእግዚአብሔርን ታላቅ ፍቅር አንሥቶ የሚያመሰግን በመሆኑ ይህ መዝሙር ከመዝ103 ጋር ይመሳሰላል (103፥11 ይመ)።

*108ርእስ፤* የመዝ30 ርእስ ማብ ይመ። *የዳዊት፤* ሁለቱም መዝሙሮች የተገኙት (መዝ57፤60) ከእርሱ ነው።

*108፥1-5፤* የእግዚአብሔርን ፍቅር የሚያወድስ ክፍል ሲሆን ምናልባት በዚህ ቦታ ክፍሉ የሚያመለክተው እግዚአብሔርን በመተማመን ወደ እርሱ መቅረብና አቤቱታንም ለእርሱ ማሰማት የሚቻል መሆኑን ነው (ማለትም በቍ7-9፡11 ላይ ለተጠቀሰው እግዚአብሔር፤ እንዲሁም ቍ6፡12 ይመ)፤ የ109፥1 ማብ ይመ።

108፥1 *ነፍሴም፤* ቃል በቃል ሲተረጐም "ክብር" ማለት ነው (የ7፥5 ማብ ይመ)።

*108፥6-13፤* እግዚአብሔር ከጠላት እንዲታደገው የቀረበ ጸሎት ነው (የ60፥5-12 ማብ ይመ)።

*109፤* በሐሰት የቀረበበትን ክስ ተመልክቶ እግዚአብሔር እንዲፈርድለት ወደ እግዚአብሔር የቀረበ ጸሎት ነው። መዝሙረኛው በቍ6-9 ላይ ስለ ጠላቶቹ በነጠላ ቍጥር ሲናገር በሌላ ቦታ ግን የሚናገረው በብዙ ቍጥር ነው፤ ከዚህም የተነሣ አንዳንድ ሰዎች በቍ6-9 ላይ የሚገኘው ሐሳብ ጠላት በመዝሙረኛው ላይ ያወረደውን ርግማን የሚገልጽ ነው ይላሉ። ትክክል መስሎ የሚታየው ግን (1) አንድም መዝሙረኛው እስከ አሁን ድረስ በብዙ ቍጥር ሲናገር ከቆየ በኋላ እዚህ ላይ የጥቅል ስም አድርጎታል ወይም ደግሞ (2) የመዝሙረኛው ጠላቶች፣ የግል ጥላቻው እጅግ በመረረ አለቃ ሥር ተሰብስበው ዘርማንዘሩን ለማጥፋት ቢያሤሩም ሌሎች ተቃዋሚዎች ስለተነሡባቸው ሁኔታው ሌላ መልክ መያዙን የሚያሳይ ሊሆን ይችላል። ይህ መዝሙር በአብዛኛው ከመዝ 35 ጋር ተመሳሳይነት አለው፤ የመዝ 101 ማብ ይመ።

*109ርእስ፤* የመዝሙር 4 ርእስ ማብ ይመ።

*109፥1-5፤* ከሐተኛ ከሳሾች እጅ እግዚአብሔር እንዲታደገው ያቀረበው አቤቱታ ነው።

109፥1 *የምስጋናዬ ምንጭ፤* መዝሙረኛው የሚያወድሰው ይህ አም ላክ የታመነ ታዳጊና ከጠላቶቹም እጅ ጋሻ መከታ ሆኖ የሚከላከልለት ነው (22፥3 እና ማብ፤ እንዲሁም 35፥18፤ 74፥21፤ 76፥10፤ 79፥13፤ 102፥18 ይመ)። *ዝም አትበል፤* ለምን አትፈርድም! (28፥1፤ 35፥22፤ 50፥3፡21፤ 83፥1 ይመ)።

*109፥2-5፤* መዝሙረኛው የደረሰበትን በደል ለሰማያዊው ፈራጅ አንድ በአንድ ያቀረበው አቤቱታ ነው (35፥11-16 ይመ)።

109፥2 *አፋቸውን ከፍተውብኛልና፤* የ5፥9 ማብ ይመ።

109፥4 *እኔ ግን እጸልያለሁ፤* ይህን የሚለው ራሱን ከጠላቶቹ ጋር በማነጻጸር ነው (ቍ16-18 ይመ)። ትክክለኛ ሐሳቡ ግን፣ "ለእነርሱ ጸለይኩላቸው" ማለት ሳይሆን አይቀርም (በ35፥13-14 ላይ እንደ ተጻፈው ማለት ነው)።

*109፥6-15፤* እግዚአብሔር ለመዝሙረኛው ጠላቶች የእጃቸውን በትክክል ይሰጥ ዘንድ የቀረበ የፍትሕ ልመና ነው (የ5፥10 እንዲሁም የ35፥4-10 ማብ ይመ)።

6 ክፉ ሰው[a] በላዩ ሹም፤
ከሳሽም[b] በቀኙ ይቁም።
7 ፍርድ ፊት ሲቆም በደለኛ ሆኖ ይገኝ፤
ጸሎቱም ለፍርድ ትሁንበት።
8 ዕድሜው ይጠር፤
ሹመቱንም ሌላ ይወሰደው።
9 ልጆቹ ድኻ አደጎች ይሁኑ፤
ሚስቱም መበለት ትሁን።
10 ልጆቹ ይንከራተቱ፤ ለማኞችም ይሁኑ፤
ከፈረሰው ቤታቸውም ይሰደዱ።
11 ያለውን ሁሉ ዕዳ ጠያቂ ይውረሰው፤
የድካሙንም ዋጋ ባዕዳን ይቀሙት።
12 ማንም ሰው ምሕረት አያድርግለት፤
ለድኻ አደግ ልጆቹም የሚራራ አይኑር።
13 ዘሩ ተለይቶ ይጥፋ፤
ስማቸውም በሚቀጥለው ትውልድ
ይደምሰስ።
14 የአባቶቹ በደል *በእግዚአብሔር* ፊት
ይታሰብ፤
የእናቱም ኀጢአት አይደምሰስ።
15 መታሰቢያቸውን ከምድር ያጠፋ ዘንድ፣
ኀጢአታቸው ሁልጊዜ *በእግዚአብሔር*
ፊት ይኑር፤
16 ችግረኛውንና ምስኪኑን፣ ልቡም
የቈሰለውን፣
እስከ ሞት አሳደደ እንጂ፣
ምሕረት ያደርግ ዘንድ አላሰበምና።
17 መራገምን ወደደ፤
ወደ እርሱም መጣች፤
በመባረክ ደስ አልተሰኘም፤
በረከትም ከእርሱ ራቀች።
18 መርገምን እንደ ልብስ ለበሳት፤
እርሷም እንደ ውሃ ወደ ውስጥ ሰውነቱ፤
እንደ ዘይትም ወደ ዐጥንቱ ዘለቀች።
19 ገላውን እንደሚሸፍንበት ልብስ፣
ዘወትር እንደሚታጠቀውም መቀነት
ትሁነው።
20 *እግዚአብሔር* ለሚወነጅሉኝ ሰዎች፣
በነፍሴም ላይ ክፉ ለሚናገሩ
የሚከፍላቸው ይኸው ይሁን።
21 አንተ ግን ጌታ *እግዚአብሔር* ሆይ፤
ስለ ስምህ በበጎ ተመልከተኝ፤
ምሕረትህም መልካም ናትና አድነኝ።
22 እኔ ድኻና ችግረኛ ነኝና፤
ልቤም በውስጤ ቈስሎአልና።
23 እንደ ምሽት ጥላ ከእይታ ተሰውሬአለሁ፤
እንደ አንበጣም ረግፌአለሁ።
24 ከጾም የተነሣ ጕልበቴ ዛለ፤
ሰውነቴም ከስቶ ዐመድ ለበሰ።
25 ለመሣለቂያ ሆንሁላቸው፤
ሲያዩኝም ራሳቸውን ይነቀንቃሉ።
26 *እግዚአብሔር* አምላኬ ሆይ፤ ርዳኝ፤
እንደ ምሕረትህም አድነኝ።
27 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ እጅህ ይህን
እንዳደረገች፣
አንተም ይህን እንደ ፈጸምህ ይወቁ።
28 እነርሱ ይራገማሉ፤ አንተ ግን ትባርካለህ፤
በሚነሡበት ጊዜ ይዋረዳሉ፤
ባሪያህ ግን ሐሤት ያደርጋል።
29 የሚወነጅሉኝ ውርደትን ይከናነቡ፤
ዕፍረትንም እንደ ሸማ ይልበሱ።
30 *እግዚአብሔርን* በአንደበቴ እጅግ
አመሰግናለሁ፤
በታላቅ ሕዝብም መካከል አወድሰዋለሁ።
31 በነፍሱ ላይ ከሚፈርዱት ያድነው ዘንድ፣
እርሱ በችግረኛው ቀኝ በኩል
ይቆማልና።

109፥6 1ዜና21፥1፤ ኢዮ1፥6፤ዘካ3፥1
109፥7 መዝ1፥5፤ ምሳ28፥9፤ኢሳ41፥24
109፥8 ኢዮ15፥32፤ ሐሥ1፥20
109፥9 ዘፀ22፥24፤ ኤር18፥21
109፥10 ዘፍ4፥12
109፥11 ዘኍ14፥3፤ ነህ5፥3፤ኢዮ20፥18፤ ኢሳ1፥7፤6፥11፤36፥1፤ ሰቆ5፥2
109፥12 ኢዮ5፥4
109፥13 ዘኍ14፥12፤ኢዮ18፥19፤መዝ9፥21፥10፤ምሳ10፥7
109፥14 ዘፀ20፥5፤ ዘኍ14፥18፤ኢሳ 65፥6-7፤ኤር32፥18
109፥15 ዘፀ17፥14፤ ዘዳ32፥26፤መዝ90፥8
109፥16 ኢዮ20፥19፤መዝ34፥18፤35፥10
109፥17 ምሳ28፥27፤ማቴ7፥2
109፥18 ዘኍ5፥22፤ መዝ10፥7
109፥19 ቍ29፤ መዝ73፥6፤ሕዝ7፥27
109፥20 ዘፀ32፥34፤ መዝ54፥5፤71፥10፤94፥23፤ኢሳ3፥11፤ 2ጢሞ4፥14
109፥21 ዘፀ9፥16፤ መዝ3፥7፤23፥3፤ 69፥16
109፥23 ኢዮ14፥2
109፥24 ኢዮ16፥8፤ መዝ35፥13፤ዕብ 12፥12
109፥25 ኢዮ16፥4፤ መዝ22፥6፤ማቴ27፥39፤ማር15፥29
109፥26 መዝ12፥1፤119፥86
109፥27 ኢዮ37፥7
109፥28 2ሳሙ16፥12፤መዝ66፥4፤ኢሳ 35፥10፤51፥11፤54፥1፤65፥14 109፥29 መዝ35፥26
109፥30 መዝ35፥18 109፥31 መዝ16፥8፤108፥6

[a]6 ወይም *ክፉው*
[b]6 ወይም *ሰይጣን*

109፥6 *ክፉ ሰው ... ከሳሽም፤* የመዝሙረኛው ጠላት መዝሙረኛውን ለመጣል ሲል በሐሰት ይከስዋል፤ እንግዲህ ጠላቱም የእጁን ያገኝ ዘንድ እርሱም ከሳሽ ይነሣበት።

109፥7 *ጸሎቱም፤* ራሱን ለመከላከል የሚያቀርበው ልመና ማለት ነው።

109፥8 *ዕድሜው ይጠር፤* ዳዊትን በሐሰት የሚከሰውና የሚያሳጣው ጠላቱ ዳዊት እንዲሞትለት አጥብቆ እንደሚፈልግ ምንም ጥርጥር የለውም (1ነገ21፥8-15 ይመ)። *ሹመቱንም ሌላ ይውሰደው፤* ጠላቱ ከፍተኛ የአለቅነት ቦታ ያገኘ ሲሆን ምናልባት መዝሙረኛውን ለመጣል እያሤረበት ሳይሆን አይቀርም።

109፥18 *እንደ ውሃ ወደ ውስጥ ሰውነቱ፣ እንደ ዘይት ወደ ዐጥንቱ፤* ርግማን ምግቡና መጠጡ ብቻ ሳይሆን ልብሱም ጭምር ነበር፤ የኖረውም በርግማን ነው (ምሳ4፥17 ይመ)።

109፥21 *ስለ ስምህ፤* የ5፥11፤ 23፥3 ማብ ይመ። *ምሕረትህ፤* ቍ26 እንዲሁም የ6፥4 ማብ ይመ።

*109፥22፤* መዝሙረኛው ስላለበት ሁናቴ የሚያደርገው ገለጻ የቍ16ን ቃል ያስተጋባል። *ድኻና ችግረኛ፤* ተስፋቸው እግዚአብሔር ብቻ የሆኑ ናቸው (የ34፥6 ማብ ይመ)። *ልቤም፤* የ4፥7 ማብ ይመ።

109፥23 *ተሰውሬአለሁ፤* መዝሙረኛው በዘመኑ ሁሉ መከራ የሚያሳየው ሥቃይ እንዳለበት በግልጽ ያሳያል፤ ይህም ጠላቶቹ በእርሱ ላይ እንዲነሡበት ምክንያት ሆኖአቸዋል (ቍ24-25 ይመ፤ እንዲሁም የ5፥9 ማብ ይመ)። *እንደ ምሽት ጥላ፤* 102፥11 ይመ። *ረግፌአለሁ፤* ነህ5፥13፤ ኢዮ38፥13 ይመ።

*109፥26-29፤* ይህ ክፍል የመዝሙሩ መደምደሚያ ሲሆን ከዚህ በፊት የተወሱትን ጭብጦች የሚያስተጋባ ነው።

109፥28 *ባሪያህ፤* በእግዚአብሔር ከተቀቡት መካከል መዝሙረኛው እንደ አንዱ ተደርጎ ተቈጥሮአል (ርእሱንና የመዝ 78፥70 ማብ ይመ)።

*109፥30-31፤* እግዚአብሔርን ስለ አዳኝነቱ ለማመስገን የተገባበት ቦታ ነው (የ7፥17 ማብ ይመ)።

*መዝ110፤* ንጉሥና ካህን የሆነውን መሢሕ በተመለከተ አስቀድሞ የተነገረ ትንቢት ነው። ይህ መዝሙር (በተለይም የቍ1 እና 4 ትንቢቶች) በአዲስ ኪዳን ከክርስቶስ ጋር ተያይዞ በተደጋጋሚ ተጠቅሶአል። ልክ እንደ መዝሙር 2 ሁሉ ይህም መዝሙር ወደፊት ከዳዊት ቤት የሚወለደው ልጅ ሥርዐተ ንግሥ በሚፈጽምበት ጊዜ እንዲዘመር የተዘጋጀ ነው። ከክርስትና ሃይማኖት መምጣት በፊት የነበሩ አይሁድ፣ ይህ መዝሙር ወደ ፊት ይመጣል ተብሎ በተስፋ ስለሚጠበቀው መሲሕ የተነገረ መሆኑን ቀደም ብለው ተረድተዋል። በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በተለይም በጌታ በኢየሱስ ከተሰጠው ትርጕም (ማቴ22፥43-45፤ ማር12፥36-37፤ ሉቃ20፥42-43) እንዲሁም በጴጥሮስ (የሐሥ2፥34-36) እና በዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ (በተለይም ዕብ1፥13፤ 5፥6-10፤ 7፥11-28) በመነሣት በዳዊት መዝሙራት ውስጥ ከተነገሩት ትንቢቶች ሁሉ፣ ይህ መዝሙር በተስፋ ስለሚጠበቀው መሲሕ በቀጥታ የሚናገር መሆኑን ክርስቲያኖች ሁሉ ተስማምተውበታል። ነገሩ እንዲህ ከሆነ፣ ዳዊት ትንቢት የተናገረውና ወደፊት ስለሚነሣው ታላቅ ልጁ የሥርዐተ ንግሥ መዝሙር የደረሰው፣ ነቢያት ስለዚህ ልጅ ምንም ከመናገራቸው በፊት ነው ማለት ነው (2ሳሙ23፥2)። ይሁን እንጂ ዳዊት ይህንን መዝሙር ያዘጋጀው "ጌታዬ" (ቍ1) ብሎ ለጠራው ለልጁ ለሰሎሞን ሥርዐተ ንግሥ ሊሆን ይችላል፤ እንዲህም ማለቱ ሰሎሞን አንድ ቀን የሚይዘው

## መዝሙር 110
## መሲሑ ንጉሥና ካህን

### የዳዊት መዝሙር

1 *እግዚአብሔር* ጌታዬን፣
"ጠላቶችህን ለእግርህ መርገጫ፣
እስከማደርግልህ ድረስ፣
በቀኜ ተቀመጥ" አለው።

2 *እግዚአብሔር* ብርቱ በትርህን ከጽዮን ወደ
ውጭ ይሰዳል፤
አንተም በጠላቶችህ መካከል ሆነህ
ትገዛለህ።
3 ለጦርነት በምትወጣበት ቀን፣
ሰራዊትህ በገዛ ፈቃዱ በጉንህ ይቆማል፤
ከንጋት ማሕፀን፣
በቅዱስ ግርማ ደምቀህ፣
የጉልማሳነትህን ልምላሜ[1] እንደ ጠል
ትቀበላለህ።
4 "እንደ መልከ ጼዴቅ ሥርዐት፤
አንተ ለዘላለም ካህን ነህ" ብሎ፣
*እግዚአብሔር* ምሎአል፤
እርሱ ሐሳቡን አይለውጥም።
5 ጌታ በቀኝህ ነው፤
በቍጣውም ቀን ነገሥታትን ያደቃቸዋል።
6 በሕዝቦች መካከል ይፈርዳል፤
በየአገሩ ያሉትንም ራሶች ከስክሶ
ሬሳ በሬሳ ያደርጋቸዋል።

110፥1 ኢሱ10፥24፤ 1ነገ5፥3፤ማቴ22፥44፤ ማር12፥36፤16፥19፤ ሉቃ20፥42፤ሐሥ 2፥34፤1ቆሮ15፥25፤ ዕብ1፥13፤12፥2
110፥2 ዘፍ49፥10፤ መዝ2፥6፤45፥6፤72፥8 ፤ኢሳ14፥5፤ኤር 48፥17
110፥3 ዘፀ15፥11፤ ሚክ5፥7
110፥4 ዘፍ14፥18፤ ዘኍ23፥19፤ዘካ6፥13፤ ዕብ5፥6፡10፤7፥15-17 ፡21
110፥5 ዘዳ7፥24፤ መዝ2፥5፡12፤16፥8፤ 68፥21፤76፥12፤ኢሳ 60፥12፤ዳን2፥44፤ ሮሜ2፥5፤ራእ6፥17፤ 11፥18
110፥6 መዝ9፥19፤18፥38፤ኢሳ5፥25፤34፥3፤66፥24

[1] 3 *ወይም ጕልማሶችህ እንደ ንጋት ጠዳት ይመጡሉ ማለት ነው።*

መንበር በዕድሜ ከገፋው ከዳዊት የሚበልጥ ስለሚያደርገው ነው። እንዲህ በማድረጉም፣ "ጌታዬ" የሚለው ቃል በልጁ በሰሎሞን ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሳይሆን፣ እርሱ ከሚያውቀው በላይ ሰፋ ያለ ትርጒም ስላለውም ጭምር ነው። እንግዲህ ይህ ነገር በሳሙኤል፣ በነገሥትና በዜና መዋዕል መጻሕፍት ስለ ዳዊት ከተነገረው ጋር ይበልጥ የሚስማማ መስሎ ይታያል (የመዝ101 መግቢያን ይመ)።

*110፥1-3፤* እግዚአብሔር የመረጠውን (የቀባውን) መሲሕ በተቃዋሚዎቹ ሁሉ ፊት ወራሹ ማድረጉን የሚያጸና ውሳኔ ነው (2፥7-12 ይመ)።

*110፥1፤* የመጀመሪያው ትንቢት ነው (የቍ4 ማብ ይመ)። *ጌታዬ፤* የእኔ ንጉሥ ወይም ከእኔ በላይ የሆንህ ማለት ነው፤ ስለዚህ ይህ "ጌታዬ" የተባለው ከዳዊት በላይ ከፍ ከፍ ያለ ስለ መሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም (ማቴ22፥44-45፤ ማር12፥36-37፤ ሉቃ20፥42-44፤ ዮሐ2፥34-35፤ ዕብ1፥13 እና ዐውደ ምንባባቸውን ልብ ብለህ አስተውል)። *ተቀመጥ፤* በክብር ዙፋን ላይ መቀመጥን ያሳያል። *በቀኜ፤* ከአንድ ንጉሥ አጠገብ ያለ የክብር ስፍራ ነው (45፥9፤ 1ነገ2፥19 ይመ)፤ እንግዲህ ከራሱ ከእግዚአብሔር ቀጥሎ ያለው ሁለተኛ የሥልጣን ቦታ ይዞአል ማለት ነው። ጌታ ኢየሱስ ከፍ ያለውን ይህን የክብር ስፍራ መያዙን የሚያመለክቱ በርካታ የአዲስ ኪዳን ክፍሎች አሉ (ማቴ26፥64፤ ማር14፥62፤ 16፥19፤ ሉቃ22፥69፤ ዮሐ2፥33፤ 5፥31፤ 7፥55-56፤ ሮሜ8፥34፤ ኤፌ1፥20፤ ቈላ3፥1፤ ዕብ1፥3፤ 8፥1፤ 10፥12፤ 12፥12 ይመ)። *ጠላቶችህን፤* የ2፥1-3 ማብ ይመ። *የእግርህ መርገጫ እስከማደርግልህ ድረስ፤* ዕብ 10፥12-13 ይመ። በጥንት ዘመን የነበሩ ነገሥታት ድል ባደረጓቸው ነገሥታት ራስ ላይ እግራቸውን በመጫን ምን ያህል ብርቱ እንዲሆኑ ያሳዩ ነበር (ኢሱ10፥24 ይመ)። የነገሥታት የእግር መረገጫ ከዙፋኑ ጋር አብሮ ተያይዞ እንደሚሠራ በ2ዜና 9፥18 ላይ መመልከት ይቻላል። በዚህ ቦታ የተገለጠውን ሐሳብ በ1ነገ 5፥3 ላይ መመልከት ይቻላል። ጳውሎስ ይህን ቃል በ1ቆሮ 15፥25፤ ኤፌ1፥22 ላይ ከክርስቶስ ጋር አያይዞ አቅርቦታል።

110፥2 *ብርቱ በትርህን ከጽዮን ወደ ውጭ ይሰዳል፤* አገዛዝህን የሚቃወም ጠላት ጨርሶ እስኪጠፋ ድረስ የመንግሥትህን ግዛት በዓለም ሁሉ ያሰፋል ማለት ነው። *ከጽዮን፤* የዳዊት መናገሻ ከተማ ናት (2ሳሙ5፥7፡9 ይመ) እንዲሁም እግዚአብሔር እንደ አንድ ታላቅ ንጉሥ ሆኖ የሚገዛባት ከተማም ናት (የ9፥11 ማብ እንዲሁም መዝ 46፤ 48፤ 132፥13-18 ይመ)። የእግዚአብሔር መሲሕ በዓለም ላይ ለሚሰፍነው የእግዚአብሔር መንግሥት እንደራሴው ነው።

110፥3 *በገዛ ፈቃዱ፤* ቃል በቃል ሲተረጐም፣ "በነጻ ፈቃድ የሚቀርብ መሥዋዕት" ማለት ነው። ይህም ማለት አንተን ለመርዳት ሲሉ ራሳቸውን እስከ ሞት ድረስ አሳልፈው ለመስጠት ዝግጁ ሆነው ወደ ጦርነት የሚገቡ ቈራጥ ተዋጊዎች ማለት ነው (መሳ5፥2 ይመ)። እስራኤላውያን በምድረ በዳ ሳሉ ያስለ የሌለ ጥሪታቸውን (ሀብታቸውን) ለመገናኛ ድንኳኑ ሥራ እንደ ሰጡት ዐይነት ማለት ነው (ዘፀ35፥29፤ 36፥3 ይመ፤ እንዲሁም ዕዝ1፥4፤ 2፥68 ይመ)። ልክ እንዲሁ የክርስቶስ ተከታዮችም ራሳቸውን፣ "እንደ ሕያው መሥዋዕት አድርገው እንዲያቀርቡ" ጳውሎስ መክሮአል (ሮሜ12፥1)፤ ራሱን በተመለከተ ደግሞ በመጠጥ ቍርባን መስሎ ተናግሮአል (ፊል2፥17)፤ እንዲሁም 2ቆሮ8፥5 ይመ። *በቅዱስ ግርማ ደምቀህ፤* ይህ ክፍል የሚያወሳው ስለ እግዚአብሔር መሲሕ ከሆነ ክብርንና ግርማ መንግሥትን የሚጐናጸፍ ይልቁንም ደስ ደስ የሚል የወጣትነትን ዘመን እንደ፣ "ንጋት ማሕፀን" እስከ መጨረሻው ይዞ የሚጠብቅ ስለ መሆን አስቀድሞ የተነገረለት ሲሆን፣ በየዕለቱም ጠዋት ጠዋት ጠል እንዲያንጠባጥብ ያለ መሆኑን ያሳያል (በሌላ ቦታ ላይ ይህ ቃል ስለሚሰጠው ትርጒም ኢሳ26፥19 ይመ)። ይህ ክፍል የሚያመለክተው፣ "ወደ እርሱ ስለሚጐርፉት ወጣት ተዋጊዎች ነው" የሚባል ከሆነም ልብስ ተክህኖ ለብሰው በተቀደሰ ጦርነት ላይ ለመካፈል ዝግጁ መሆናቸውን (1ሳሙ21፥4-5፤ 25፥28፤ 2ዜና13፥8፡12፤ 20፥15-21፤ ኢሳ 13፥3-4፤ ኤር6፥4፤ 51፥27 ይመ)፣ እንዲሁም በየማለዳው እንደ ንጋት ጠል ወደ ጦሩ ሰፈር በብዛት መጕረፋቸውን ያሳያል (2ሳሙ17፥11-12 ይመ)። *በቅድስና ግርማ፤* የ29፥2 ማብ ይመ።

*110፥4-7፤* እግዚአብሔር መሲሁን በጽዮን ንጉሥም፣ ካህንም አድርጎ መሾሙንና እርሱን በሚቃወሙት ኀይሎች ላይ ሁሉ ድል እንደሚያጐናጽፈው የተሰጠ ማረጋገጫ ወይም መሐላ ነው።

*110፥4፤* ሁለተኛው ትንቢት ነው (የቍ1 ማብ ይመ)። *ምሎአል፤* የዳዊትን ዘር በዙፋኑ ለዘላለም እንደሚያጸና በመሐላ ከሰጠው ቃል ኪዳን ጋር ይህ አንዱ ነው (89፥35-37 ይመ)። የዚህን መሐላ ብርቱነትና ጽኑነት የዕብራውያን መልእክት ጸሓፊ በሚገባ ገልጾታል (ዕብ6፥16-18፤ 7፥20-22 ይመ)። *በመልከ ጼዴቅ ሥርዐት … ካህን፤* ዳዊትና በዙፋኑ የተተኩ ዘሮቹ የእግዚአብሔር ሕግ በተግባር እንዲተረጐም የሚያደርጉ በመሆናቸው የቃል ኪዳኑን ታቦት አያያዝ (2ሳሙ6፥1-15 በተለይም ቍ14፤ 1ነገ8፥1 ይመ)፣ ሥርዐተ አምልኮ የሚንጸባረቅባቸውን ተግባሮችና የቤተ መቅደሱን ሥራና አገልግሎት (1ነገ5-7፤ 2ነገ12፥4-7፤ 22፥3-7፤ 23፥4-7፤ 2ዜና15፥8፤ 24፥4-12፤ 29፥3-11፤ 34፥8 ይመ) እንዲሁም የካህናቱንና የሌዋውያኑን የዕለት ተዕለት ተግባር ደግሞም በቤተ መቅደስ የሚከናወነውንም የመዝሙር ተሰጥዎ በበላይነት ይቈጣጠራሉ (1ዜና 6፥31፤ 15፥11-16፤ 16፥4-42፤ 23፥3-31፤ 25፥1፤ 2ዜና17፥7-9፤ 19፥8-11፤ 29፥25፡30፤ 31፥2፤ 35፥15-16፤ ዕዝ3፥10፤ 8፥20፤ ነህ12፥24፡36፡45 ይመ) በእነዚህ ሁሉ ተግባሮችና በሊቀ ከህናቱም ላይ እንኳ ሳይቀር የበላይነት ሥልጣን ነበራቸው። ይሁን እንጂ የአሮን ልጆች እንዲያከናውኑት በተሰጣቸው የክህነት አገልግሎት ሥራ ላይ እንዲገቡ አይፈቀድላቸውም፤ (2ዜና26፥16-18 ይመ)። በዚህ ትንቢት ውስጥ ግን የዳዊት ልጅ፣ ንጉሥም ካህንም ሆኖ፣ አብርሃም በነበረበት ዘመን (ዘፍ14፥18 ይመ) በኢየሩሳሌም የልዑል እግዚአብሔር ካህንና አገልጋይ በሆነው በመልከ ጼዴቅ ሥርዐት፣ በጽዮን ተሾሞአል (ንጉሥነትንና ካህንነትን አጣምሮ ስለሚይዝ ሰው ማንነት ዘካ 6፥13 ይመ)። ይህ ስለ ክርስቶስ ካህንነት የተነገረው ሐሳብ የዕብ7 ፍሬ ሐሳብ ሆኖአል። *ለዘላለም፤* ጊዜ ሳይሽረውና ሳይለውጠው ጸንቶ ይኖራል ማለት ነው። ይህ ቃል ምናልባት በተዘዋዋሪ መንገድ በዮሐ 12፥36 ላይ ተመልክቶአል የሚል ግምት አለ።

110፥5 *ጌታ በቀኝህ ነው፤* ጦርነት በምትገጥምበት ጊዜ አንተን ለመርዳት (ቍ2፤ 109፥31 ይመ) በቀኝህ ይሰለፋል። አንዳንዶች የዚህ ሐረግ አድራሽ እግዚአብሔር እንደ ሆነ ይናገራሉ፤ ስለዚህ ቍ1ን የሚረዱት "ጌታ" (የዳዊት ልጅ) በቀኝህ (እግዚአብሔር) ነው በሚለው መልኩ ነው። *በቍጣው ቀን፤* 2፥5 እና ማብ ይመ።

110፥6 *ይፈርዳል፤* መሲሁን ነው። *ሬሳ በሬሳ ያደርጋቸዋል፤* በጦር ሜዳ የሚታየው ሁኔታ የሚገልጽ ምስላዊ አነጋገር ሲሆን፣

[7]መንገድ[ነ] ዳር ካለች ፈሳሽ ውሃ ይጠጣል፤
ስለዚህ ራሱን ቀና ያደርጋል።

## መዝሙር 111[ከ]

### ለመለኮቱ ባሕርያት የቀረበ ጸሎት

[1]ሃሌ ሉያ።

በቅኖች ሸንጎ፣ በጉባኤም መካከል፣
ለእግዚአብሔር በፍጹም ልቤ ምስጋና
አቀርባለሁ።

[2]የእግዚአሔር ሥራ ታላቅ ናት፤
ደስ የሚሰኙባትም ሁሉ ያውጠነጥኗታል።
[3]ሥራው ባለ ክብርና ባለ ግርማ ነው፤
ጽድቁም ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።
[4]ድንቅ ሥራው ሲታወስ እንዲኖር አደረገ፤
እግዚአብሔር ቸር፣ ርኅሩኅም ነው።
[5]ለሚፈሩት ምግብን ይሰጣል፤
ኪዳኑንም ለዘላለም ያስባል።
[6]ለሕዝቡ የአሕዛብን ርስት በመስጠት፣
የአሠራሩን ብርታት አሳይቶአል።
[7]የእጁ ሥራ እውነተኛና ቅን ነው፤
ሥርዐቱም ሁሉ የታመነ ነው፤
[8]ከዘላለም እስከ ለዘላለም የጸና ነው፤
በእውነትና በቅንነትም የተሠራ ነው።
[9]ለሕዝቡ መዳንን ሰደደ፤
ኪዳኑንም ለዘላለም አዘዘ፤
ስሙም የተቀደሰና የተፈራ ነው።
[10]እግዚአብሔርን መፍራት የጥበብ
መጀምሪያ ነው፤
ትእዛዙንም የሚፈጽሙ ጥሩ ማስተዋል
አላቸው፤
ምስጋናውም ለዘላለም ይኖራል።

## መዝሙር 112

### የጻድቅ ሰው ባሕርይ

[1]ሃሌ ሉያ።[ኸ]

እግዚአብሔርን የሚፈራ፣
በትእዛዙም እጅግ ደስ የሚሰኝ
የተባረከ ነው።

[2]ዘሩ በምድር ላይ ኀያል ይሆናል፤
የቅኖች ትውልድ ትባረካለች።
[3]ሀብትና ብልጽግና በቤቱ ይሞላል፤

110፥7 መዝ3፥3፤ 27፥6
111፥1 መዝ1፥5፤ 9፥1፤34፥1፤89፥7፤109፥30፤115፥18፤ 145፥10
111፥2 ኢዮ36፥24፤ መዝ64፥9፤143፥5፤ ራእ15፥3
111፥3 መዝ112፥3 :9፤119፥142
111፥4 ዘጸ4፥31፤ መዝ86፥15
111፥5 ዘፍ1፥30፤ 1ዜና16፥15፤መዝ37፥25፤103፥11፤105፥8፤ ማቴ6፥31-33
111፥6 መዝ64፥9፤ 66፥3:5፤105፥44
111፥7 መዝ19፥7፤ 92፥4፤119፥128
111፥8 መዝ119፥89 :152:160፤ኢሳ40፥8፤ ማቴ5፥18
111፥9 መዝ30፥4፤ 34፥22፤99፥3፤103፥4 ፤130፥7፤ሉቃ1፥49: 68
111፥10 ዘዳ4፥6፤ ኢዮ23፥12፤መዝ19፥9፤28፥6፤89፥52፤119 ፥98:104:130

112፥1 ኢዮ1፥8፤ መዝ1፥1-2፤33፥2፤103፥1:11፤115፥13፤119፥14 :16:47:92፤128፥1 112፥2 መዝ25፥13፤37፥26፤128፥2-4
112፥3 ዘዳ8፥18፤መዝ37፥6፤111፥3

[ነ] ወይም ሥልጣን ለመስጠት ኀይል ያለው ሥልጣን ላይ ያስቀምጠዋል ማለት ነው።
[ከ]መዝሙር111 የግጥሙ መሥመሮች እያንዳንዳቸው ከላይ እስከ ታች በተከታታይ በዕብራይስጥ ፊደሎች ቅደም ተከተል ተቀምጠዋል።
[ኸ]1 እግዚአብሔር ይመስገን ማለት ነው።

የተወሰደውም ከዳዊት የድል ሕይወት ላይ ነው፤ ይህም የእግዚአብሔር መሲሕ መንግሥቱን በሚቃወሙት ኀይሎች ላይ (2፥9፤ ራእ19፥11-12 ይመ) ያለውን ድል አድራጊነት ያሳያል።

110፥7 ... *ከፈሳሽ ይጠጣል፤* በተፋፋመ ውጊያ ላይ ሳለ እንኳ፣ ቀዝቀዝ የሚያደርገውን ነገር ያገኛል፤ ማንም ሊበግረው የማይችለውንም ሀንጉቱን ከፍ ከፍ ያደርጋል (የቍ3 ማብ ይመ)።

*መዝ111፤* የመጀመሪያውና የመጨረሻው ቍጥር እንደሚያሳየው፣ መዝሙሩ ምን ጊዜም ስለማይጓደለው ጽድቁ እግዚአብሔርን ለማመስገን የቀረበ ሲሆን፣ ዝማሬንና ጥበብን የተሞላ ምክርም አጣምሮ የያዘ ነው። ከመዝ112 ጋር ሲነጻጸርም ሁለቱ መዝሙሮች ልክ እንደ መንትያ ልጆች ይገኛሉ፤ ምናልባትም ከአንድ ጸሓፊ ብዕር የፈለቁና ሳይለያዩም አንድ ላይ እንዲቀመጡ ሆን ተብሉ ቦታ የተሰጣቸው ሳይሆኑ አይቀርም። እነዚህ ሁለት መዝሙሮች ከባቢሉን ምርኮ በኋላ ሳይጻፉ እንደማይቀሩ ይገመታል። መዝሙሮቹ፣ "ሃሌ ሉያ፣ ሃሌ ሉያ" ለሚሉትና (መዝ111-118) በተከታታይ ለቀረቡት መዝሙሮች እንደ መግቢያ ያገለግላሉ፤ ይሁን እንጂ የአይሁድን ትውፊተ ተሰጥዎ አጠቃቀም በተመለከተ የመዝ113ን መግቢያ ይመ።

111፥1 *በቅኖች ሸንጎ፤* ምናልባት እጅግ ቅርብ የሆኑትን ሰዎች የሚያመለክት አባባል ሳይሆን አይቀርም (ይህን ስለመሰለው ልዩነት 107፥32ን ይመ)፤ አባባሉ የሚያመለክተውም በእውነት ፈሪሀ እግዚአብሔር ያደረባቸውን ሰዎች ነው፤ ለምሳሌ በ112፥2:4 ላይ እንደተጠቀሱት "ቅኖች" ያሉትን ማለት ነው (11፥7፤ 33፥1፤ 49፥14፤ 97፥11፤ 107፥42፤ 140፥13 ይመ)። *በጉባኤም፤* የ9፥1 ማብ ይመ። *ምስጋና አቀርባለሁ፤* ከቍ2-9 ላለው ምስጋና መግቢያ ነው።

111፥2 *የእግዚአብሔር ሥራ፤* መዝሙሩ እግዚአብሔር በተለይ ለሕዝቡ ያደረገውን በጎነት ያንጸባርቃል። ይህንንም ቍ2:9: ያጠቃልሉታል። *ያውጠነጥኗታል፤* እጅግ ከፍ ያለ ትኩረት ሰጥተው ይመረምሩታል ማለት ነው።

111፥3 *ጽድቁም፤* የቍ4፥1 ማብ ይመ።

111፥4 *ድንቅ ሥራው፤* የ9፥1 ማብ ይመ። *ቸር፣ ሩኅሩኅ፤* ዘፀ34፥6-7 እና ማብ ይመ። ከእነዚህ ተለይተው ለብቻቸው ይቆማሉ። ሁለቱም መዝሙሮች የተቀነበቡት የመዝሙሮቹን ፍሬ ሐሳብ አጕልተው በሚያሳዩት በመጀመሪያውና በመጨረሻው ቍጥሮች ነው። በሁለቱም መዝሙሮች ላይ ፍሬ ነገሩ የተገለጠው በመጀመሪያዎቹ ቍጥሮች ላይ ሲሆን፣ የመደምደሚያዎቹ ቍጥሮች ደግሞ ተጓዳኝ ሐሳቡን ይዘዋል። በሁለቱም መዝሙሮች ላይ የመዝሙሩን ፍሬ ሐሳብ የያዙት ስምንት ቍጥሮች እኩል ሁለት ቦታ መከፈል የሚችሉ ሲሆን እነዚህ ሁለት ክፍሎች እያንዳንዳቸው አራት አራት ቍጥር አላቸው፤ እኩል ሁለት ቦታ የተከፈሉት ቍጥሮች አንድ ዐይነት የፍሬ ሐሳብ ቍርኝት አላቸው (ለምሳሌ 111፥2 እና 111፥6 እንዲሁም ቍ5 እና ቍ9 ያነጻጽሩ)፤ የሁለቱ መዝሙሮች ተመሳሳይ ቍጥሮችም እንደዚሁ አንድ ዐይነት የሆነ ፍሬ ሐሳብ እኩል ይጋራሉ (ለምሳሌ 111፥3-5 ከ112፥3-5 ጋር ያነጻጽሩ)።

111፥5 *ምግብን ይሰጣል፤* ከታላቅ ቸርነቱ የተነሣ ለሕዝቡ የሚያስፈልጋቸውን አትረፍርፎ እንደሚሰጣቸው የሚያሳይ ምሳሌ ነው (በጌታ ጸሎት "የዕለት እንጀራችንን ስጠን ዛሬ" ማቴ6፥11 እንደምንለው ዐይነት ነው)። *ለሚፈሩት፤* ቍ10 እና ማብ ይመ። *ኪዳኑንም፤* ቍ9 ይመ፤ እንዲሁም 105፥8-11 ይመ።

*111፥6፤* ከቍ2 ጋር ያነጻጽሩ።

111፥7 *እውነተኛና ቅን፤* ቍ3 ላይ፣ "ክብርንና ሞገሥን" ከሚለው ጋር ያነጻጽሩ። *ሥርዐቱም ሁሉ የታመነ፤* የ93፥5 ማብ ይመ።

111፥9 *ለሕዝቡ መዳንን ሰደደ፤* እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል ያደረገውን ብዙ ቸርነት የሚያሳይ ሌላ በረከት ነው ("ምግብን ይሰጣል" ቍ5 ከሚለው ጋር ያነጻጽሩ)። *የተቀደሰና የተፈራ፤* በስራው እንደታየው በእርግጥም ቅዱስና የሚያስፈራ ነው። *ስሙም፤* የ5፥11 ማብ ይመ።

*111፥10፤* ጥበበኛ መሆን ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ የሚናገር የመደምደሚያ ቃል ነው። *እግዚአብሔርን መፍራት የጥበብ መጀመሪያ ነው፤* ጥበበኛ መሆን የሃይማኖት መሠረት መሆኑን የሚያስገነዝብ የተለመደና ጥንታዊ የብሉይ ኪዳን ትምህርት ነው (ኢዮ28፥28፤ ምሳ1፥7፤9፥10 ይመ፤ እንዲሁም የዘፍ20፥11 ማብ ይመ)። *ትእዛዙን የሚከተሉ፤* ቃል በቃል ሲተረጉም "የሚያደርጓቸው ወይም የሚፈጽሟቸው" ማለት ነው (በ19፥7-9 ላይ "እግዚአብሔርን መፍራት" የሚለው ሐሳብ "ሕግ"፣ "ሥርዐት" እና "ትእዛዝ" ከሚሉት ሐሳቦች ጋር ተነጻጽሮ ቀርቦአል።

*መዝ112፤* እግዚአብሔርን ስለሚፈራ ሰው የተነገረ ቃል ነው፤ መዝሙሩ የመዝ1 መንፈስ የያዘ ቢሆንም የመዝ 111 ቅርጽ ተከትሎ የተጻፈና ምናልባትም ለዚሁ ማሟያ ወይም ተጨማሪ እንዲሆን ታስቦ የተጻፈ ሊሆን ይችላል (የመዝ111ን መግቢያ ይመ)።

*112፥1፤* የመዝሙሩ ፍሬ ሐሳብ ሲሆን በቍ2-9 ላይ ፍሬ ሐሳቡ በሚገባ ዳብሮአል። ቍ10 የሚያወሳው ግን ተቃራኒውን ሐሳብ ነው። 1፥1-2፤ 128፥1 ይመ። *እግዚአብሔርን የሚፈራ፤* 34፥8-14 እና ማብ ይመ። *የተባረከ ነው፤* የ1፥1 ማብ ይመ።

112፥2 *ትውልድ፤* እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ልጆቹ ይባ ረኩለታል፤ እርሱም በልጆቹ አማካይነት ይባረካል (በረከትን ይቀ በላል፤ ከቍ6 ጋር ያስተያዩ፤ 37፥26፤ 127፥3-5፤ 128፥3 ይመ፤ እንዲሁም የ109፥12 ማብ ይመ)።

112፥3 *ሀብትና ብልጽግና፤* 1፥3፤ 128፥2 ይመ። *ጽድቁም፤*

ጽድቁም ለዘላለም ይኖራል።
4 ቸር፣ ርኅሩኅና ጻድቅ እንደ መሆኑ፣
ለቅን ሰው በጨለማ ውስጥ ብርሃን
ይወጣለታል።
5 ለጋስና ያለ ማንገራገር የሚያበድር፣
ሥራውንም በትክክል የሚያከናውን ሰው
መልካም ይሆንለታል፤
6 ለዘላለም ከስፍራው አይናወጥምና፤
ጻድቅ ሰው[o] ሲታወስ ይኖራል።
7 ክፉ ወሬ አያሸብረውም፤
ልቡ እግዚአብሔርን በመተማመን የጸና
ነው።
8 ልቡ የጸና ነው፤ አይፈራምም፤
በመጨረሻም የጠላቶቹን ውድቀት
ያያል።
9 በልግስና ለድኾች ሰጠ፤
ጽድቁ ለዘላለም ይኖራል፤
ቀንዱም[o] በክብር ከፍ ከፍ ይላል።
10 ክፉ ሰው ይህን በማየት ይበሳጫል፤
ጥርሱን ያፋጫል፤ እየመነመነም
ይጠፋል፤
የክፉዎችም ምኞት ትጠፋለች።

## መዝሙር 113

### ለታላቁና ለመሓሪው ጌታ ምስጋና

1 ሃሌ ሉያ።[n]

112፥4 መዝ5፥12፤ 18፥28
112፥5 መዝ37፥21 ፡26፤ሉቃ6፥35
112፥6 መዝ15፥5፤ 55፥22፤ምሳ10፥7፤ መክ2፥16
112፥7 መዝ28፥7፤ 56፥3-4፤57፥7፤108፥1 ፤ኢሳ12፥2
112፥8 መዝ3፥6፤ 27፥1፤54፥7፤56፥11፤ ምሳ1፥33፤ኢሳ12፥2
112፥9 መዝ75፥10 ፤111፥3፤ሉቃ19፥8፤ ሐሥ9፥36፤2ቆሮ9፥9
112፥10 ኢዮ8፥13፤ መዝ34፥21፤37፥12፤ 86፥17፤ማቴ8፥12
113፥1 መዝ22፥23 ፤34፥22፤103፥21፤13 4፥1
113፥2 መዝ30፥4፤ 48፥10፤115፥18፤131 ፥3፤145፥21፤148፥13 ፤149፥3፤ኢሳ12፥4፤ ዳን2፥20
113፥3 ኢሳ24፥15፤ 45፥6፤59፥19፤ሚል 1፥11
113፥4 መዝ8፥1፤ 57፥11፤99፥2
113፥5 ዘፀ8፥10፤ ኢዮ16፥19፤መዝ 35፥10፤103፥19
113፥6 መዝ11፥4፤ 138፥6፤ኢሳ57፥15

የእግዚአብሔር አገልጋዮች ሆይ፤
አመስግኑት፤
የእግዚአብሔርን ስም አወድሱ።
2 ከአሁን እስከ ዘላለም፣
የእግዚአብሔር ስም የተመሰገነ ይሁን።
3 ከፀሓይ መውጫ እስከ መግቢያው ድረስ፣
የእግዚአብሔር ስም የተመሰገነ ይሁን።
4 እግዚአብሔር ከሕዝቦች ሁሉ በላይ ከፍ
ያለ ነው፤
ክብሩም ከሰማያት በላይ ነው።
5 እንደ ስምላካችን እንደ እግዚአብሔር፣
በላይ በዙፋኑ የተቀመጠ ማን ነው?
6 በሰማይና በምድር ያሉትንስ ለማየት፣
ራሱን ወደ ታች ዝቅ የሚያደርግ ማን
ነው?
7 ድኻውን ከትቢያ ያነሣል፤
ችግረኛውን ከዐመድ ከፍ ከፍ ያደርጋል፤
8 ከመኳንንትም እኩል ስፍራ ይሰጠዋል፤
ከሕዝቡም ሹማምት ጋር ያስቀምጠዋል።
9 መካኒቱን ሴት በቤት ያኖራታል፤
ደስተኛም የልጆች እናት ያደርጋታል።
ሃሌ ሉያ።

113፥7 1ሳሙ2፥8፤ መዝ35፥10፤68፥10፤107፥41፤140፥12
113፥8 2ሳሙ9፥11 113፥9 1ሳሙ2፥5

[o]6 ወይም እግዚአብሔር ቸር ርኅሩኅ ጻድቅ ስለ ሆነ ማለት ነው።
[o]9 በዚህ ስፍራ ክብርን ያመለክታል።
[n]1 እግዚአብሔር ይመስገን ማለት ሲሆን፣ በቍ9 ላይም ይገኛል።

ቍ9 ይመ፤ እንዲሁም የ1፥5 ማብ ይመ። *ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል፤* በየሁኔታው የሚለዋወጥ ተግባር የሌለው መሆኑን የሚያሳይ ነው (ቍ7 ላይ "የጸና" የሚለውን ቃል ይመ)።

112፥4 *ጨለማ፤* የመከራን ጊዜ ለማመልከት በተለዋጭ የገባ ቃል ነው (107፥10 እና ማብ ይመ)። *ጎሕ፤* የ27፥1 ማብ ይመ። *ቸር ሩኅሩኅ፤* ዘፀ34፥6-7 እና ማብ ይመ።

112፥5 *መልካም፤* በጎነትና ብልጽግና ማለት ነው (34፥8-14 እና ማብ ይመ)። *ለጋስና ያለ ማንገራገር የሚያበድር፤* ቍ9 ይመ። እንዲሁም 111፥5 ይመ።

112፥6 *ለዘላለም አይናወጥም፤* የ10፥6 ማብ ይመ። *ሲታወስ ይኖራል፤* ጽድቁ በእግዚአብሔርና በሰው ዘንድ ለዘላለም ጸንቶ የሚኖር የክብር መታሰቢያ ሐውልት አቁሞለታል (ቍ2 እና ማብ ይመ)።

112፥7 *ልቡም፤* ቍ8 ይመ። እንዲሁም የ4፥7 ማብ ይመ። *በመተማመን፤* መዝሙረኛው በእግዚአብሔር ላይ ያለው መተማመን የእግዚአብሔር ጽድቅ ለዘላለም ጸንቶ የሚኖረውን ያህል የጸና ነው (ቍ3 ይመ)። በእግዚአብሔር ጽድቅ መታመንና ጽድቁንም መታዘዝ ማለት የእውነተኛ የእግዚአብሔር ሰው ምልክት ስለመሆኑ 34፥8-14 እና ማብ ይመ።

112፥8 *ውድቀት ያያል፤* "በጨለማ ውስጥ እንኳ ጎሕ ይቀድለታል" (ቍ4)።

112፥9 *በልግስና ... ሰጠ፤* ቍ5 ይመ። *በክብር ከፍ ከፍ ይላል፤* ቅዱስ የእግዚአብሔር ስም በፍርሀትና በአክብሮት ከፍ ከፍ እንደሚል ሁሉ፣ እግዚአብሔርን የሚፈራም ሰው እንደዚሁ በክብር ከፍ ከፍ ይላል።

112፥10 *ክፉ ሰው ይህን በማየት ይበሳጫል፤* የእግዚአብሔር ሰው መሆን ወደ በረከት የሚያደርስ መንገድ መሆኑን ክፉዎች አያስተውሉትም፤ ለእነርሱ የእግዚአብሔር ሰው በመሆን የሚገኝ ምንም በረከት የለም (10፥2-11፤ 107፥42 ይመ)። *ትጠፋለች፤* 1፥4-6 ይመ፤ እንዲሁም መዝ37 ይመ። ከ111፥10 ጋር ያስተያዩ።

*መዝ113፤* ስለ ታላቅ ግርማውና ለትሑታንም ስላሳየው ምሕረት እግዚአብሔርን የሚያመሰግን ዝማሬ ነው (138፥6 ይመ)። ይህ መዝሙር በመጀመሪያ የተጻፈው በቤተ መቅደስ ውስጥ ለሚከናወነው አገልግሎት (ተሰጥዎ) ሳይሆን አይቀርም። ይህ መዝሙር እንደ ፋሲካ፣ በዓለ አምሳ፣ ዳስና አዲስ ጨረቃ በመሳሰሉት በዓላት ላይ የሚዘመር ነው (ዘሌ23፤ ዘኍ10፥10፤ ዮሐ10፥22)። መዝ113 እና 114 የፋሲካ ዕለት ከዋናው ማዕድ በፊት የሚዘመሩ ሲሆኑ፣ መዝ115-118 ድረስ ያሉት ደግሞ ከማዕድ በኋላ የሚዘመሩ ናቸው (የመዝ111 መግቢያን ይመ)።

*113፥1-3፤* አራት ጊዜ ለምስጋና የተደረገ ጥሪ ነው።

113፥1 *የእግዚአብሔርን ስም፤* ቍ2-3 ይመ። በምስጋና አንድን ቃል ወይም ሐረግ ሦስት ጊዜ መደጋገም በተሰጥዎ ዝማሬ የተለመደ ነው (የ96፥1-3 ማብ ይመ)። *ስም፤* የ5፥11 ማብ ይመ።

113፥2 *ከአሁን እስከ ዘላለም፤* እግዚአብሔርን በእውነት የሚያወድሱት ሰዎች ውዳሴ እስከ መጨረሻው የሚዘልቅ እንጂ የሚያቋርጥ አይደለም (ቍ3)።

*113፥4-6፤* እግዚአብሔር ከፍጥረቱ ሁሉ በላይ ከፍ ባለ ስፍራ በዙፋኑ ተቀምጦአል።

*113፥4፤* በመዝ57፥5:11 ላይ ያለውን አዝማች ይመ። *በሕዝቦች ሁሉ ላይ፤* በተዘዋዋሪ በአማልክቶቻቸው ሁሉ ላይ ማለቱ ነው (95፥3፤ 96፥4-5፤ 97፥9፤ እንዲሁም 47፥2:7-8 ይመ)። *ከሰማያት በላይ፤* እጅግ ከፍ ካሉት ፍጥረታት ሁሉ በላይ እንኳ ሳይቀር ማለት ነው (ቍ6 ይመ)።

*113፥5፤* የመልስ አዘል ጥያቄው ማእከል ነው (የ6፥6 ማብ ይመ)። *አምላካችን፤* "የእኛ" አምላክ እንዲሆን ቃል ኪዳን መግባቱ (ዘፍ17፥7፤ ዘፀ19፥5-6፤ 20፥2 ይመ) ምንኛ ያስደንቅ!

*113፥7-9፤* እግዚአብሔር ትሑታንን ከፍ ከፍ ያደርጋቸዋል፤ ግርማው እጅግ ታላቅ የሆነው አምላክ ከምድር ታላላቆችና ኀያላን ጋር ከቶ አያብርም፤ እርሱ አብሮ የሚሆነውና ከፍ ከፍ የሚያደርገውም ድኾችንና ችግረኞችን ነው (1ሳሙ2፥3-8፤ ሉቃ1፥46-55 ይመ)።

*113፥7-8፤* ቃል በቃል ከ1ሳሙ2፥8 ላይ የተወሰደ ይመስላል።

113፥7 *ድኾችን ... ችግረኛውን፤* 9፥18 እና የ34፥6 ማብ ይመ። *ከትቢያ ... ከዐመድ፤* ራስን ዝቅ ዝቅ የማድረግና ራስን የማዋረድ ምልክት ነው (ዘፍ18፥27፤ 1ነገ16፥2 ይመ)፤ በዚህ ቦታ ግን በታላቅ መከራና ችግር ውስጥ መሆንን ሊያመለክት ይችላል (ኢዮ 30፥19፤42፥6፤ ኢሳ47፥1፤ ኤር25፥34 ይመ)።

113፥9 *መካኒቱን፤* በጥንቱ ኅብረተሰብ ውስጥ መካንነት እንደ ትልቅ ውርደት የሚቈጠርና ጥልቅ ሐዘንም የሚያስከትል ነው (ዘፍ30፥1፤ 1ሳሙ1፥6-7:10 ይመ)፤ መካን ሴት በእርጅናዋ ዘመን እንደ ናዖሚ ትሆንና ረጂ፣ ተንከባካቢና አለሁልሽ ባይ ታጣለች (ሩት1፥11-13 ይመ፤ እንዲሁም 2ነገ4፥14 ይመ)። *በቤት፤* ባለ ቤተ ሰብ ያደርጋታል። *ደስተኛም የልጆች እናት፤* ለሣራ (ዘፍ21፥2 ይመ)፣ ለርብቃ (ዘፍ25፥21 ይመ)፣ ለራሔል (ዘፍ30፥23 ይመ)፣ ለሀና (1ሳሙ1፥20)፣ ለሱነማዊቱና (2ነገ4፥17 ይመ) ለሌ

## መዝሙር 114

### ለፋሲካ የቀረበ ውዳሴ

1 እስራኤል ከግብፅ ወጥቶ ሲሄድ፣
የያዕቆብም ቤት ቋንቋው ልዩ ከሆነ
ሕዝብ ተለይቶ ሲወጣ፣
2 ይሁዳ የእግዚአብሔር መቅደስ፣
እስራኤልም ግዛቱ ሆነ።

3 ባሕር አየች፤ ሸሸችም፤
ዮርዳኖስም ወደ ኋላው ተመለሰ።
4 ተራሮች እንደ አውራ በግ፣
ኰረብቶችም እንደ ጠቦት ዘለሉ።

5 አንቺ ባሕር፤ የሸሸሽው
አንቺም ዮርዳኖስ ያፈገፈግሽው
ለምንድን ነው?
6 እናንተ ተራሮች እንደ አውራ በግ፣
ኰረብቶችም እንደ ጠቦት ለምን
ዘለላችሁ?

7 ምድር ሆይ፤ በጌታ ፊት፣
በያዕቆብ አምላክ ፊት ተንቀጥቀጪ፤
8 እርሱ ዐለቱን ወደ ኩሬ፤

114፥1 ዘፀ13፥3፤ 29፥46
114፥2 ዘፀ15፥17፤ መዝ76፥1፤78፥68-69
114፥3፤ ዘፀ14፥21፤ 15፥8፤ኢያ3፥16፤ መዝ77፥16
114፥4 መሳ5፥5
114፥5 ዘፀ14፥21
114፥7 ዘፀ15፥14፤ 1ዜና16፥30
114፥8 ዘፀ17፥6፤ ዘኍ20፥11
115፥1 ዘፀ34፥6፤ መዝ29፥2፤66፥2፤ 96፥8
115፥2 መዝ42፥3
115፥3 ዕዝ5፥11፤ ነህ1፥4፤መዝ103፥19፤ 135፥6፤136፥26፤ ማቴ6፥9
115፥4 2ነገ19፥18 ፤2ዜና32፥19፤ኤር 10፥3-5፤ሐሥ19፥26፤ ራእ9፥20
115፥5 ኤር10፥5

ቋጥኙንም ወደ ውሃ ምንጭ ለወጠ።

## መዝሙር 115

### አንዱ እውነተኛው አምላክ

115፥4-11 ተጓ ምብ-መዝ135፥15-20

1 ለእኛ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ሆይ፤ ለእኛ
ሳይሆን፣
ስለ ምሕረትህና ስለ እውነትህ፣
ለስምህ ክብርን ስጥ።
2 አሕዛብ፣ "አምላካቸው የት አለ?"
ለምን ይበሉ?
3 አምላካችንስ በሰማይ ነው፤
እርሱ ደስ የሚለውን ያደርጋል።
4 የእነርሱ ጣዖታት ግን የሰው እጅ የሠራቸው፣
ብርና ወርቅ ናቸው።
5 አፍ አላቸው፤ አይናገሩም፤
ዐይን አላቸው፤ አያዩም፣
6 ጆሮ አላቸው፤ አይሰሙም፤
አፍንጫ አላቸው፤ አያሸቱትም፤
7 እጅ አላቸው፤ አይዳስሱም፤
እግር አላቸው፤ አይሄዱም፤

ሎችም ሴቶች እንደ ተደረገላቸው ሁሉ ለዚህችም ሴት እግዚ አብሔር ያደረገላት ቸርነት ለደስታዋ ምክንያት ሆኖአታል። *ሃሌ ሉያ!* በመጀመሪያ ቅጅ ላይ ምናልባት የመዝ114 አካል ሳይሆን አይቀርም፤ መዝ114 "ሃሌ ሉያ" የሚል ሐረግ ያጣው ከዚህ የተነሣ ሊሆን ይችላል።

*መዝ114!* እጅግ ውብ ከሆኑት መዘሙራት ውስጥ አንዱ ሲሆን፣ ሕዝበ እስራኤል ከግብፅ ባርነት ነጻ መውጣታቸውን አስ መልክቶ የቀረበ የምስጋና መዝሙር ነው። የተዘጋጀውም ምናል ባት በነገሥታት ዘመን የእስራኤል መንግሥት ከሁለት ከተከፈለ በኋላ ሊሆን ይችላል (ቍ2 ይመ)። በየዓመቱ ከሚከበሩት ዐበ ይት ሃይማኖታዊ በዓላት በአንዱ፣ ካህናት ወይም መዘምራን በቤተ መቅደስ ውስጥ በተሰጥዎ እንዲያዜሙት ወይም እንዲ ቀባበሉት የተዘጋጀ ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም (የመዝ113 መግቢያን ይመ)።

*114፥1-2!* በብሉይ ኪዳን የተፈጸመ ታላቅ ትድግና ነው።

114፥1 *እስራኤል ... የያዕቆብም ቤት!* ለአንድ ሕዝብ የተሰጠ ተመሳሳይ መጠሪያ ነው (ዘፀ19፥3 ይመ)። *ከግብፅ ወጥቶ ሲሄድ!* ከግብፅ ባርነት ነጻ መውጣታቸውንና በምድረ በዳ በሚጓዙበት ጊዜ ሁሉ በመካከላቸው የተፈጸሙትን ታላላቅ ድርጊቶች የሚያስታውስ ነው።

114፥2 *ይሁዳ ... እስራኤል!* የደቡብ የይሁዳና የሰሜኑ የእስራኤል መንግሥት እዚህ ላይ የቀረቡት እንደ አንድ የእግዚ አብሔር ሕዝብ ሆነው ነው። *ሆነ!* ይህ ወሳኝ ድርጊት የተፈ ጸመው እስራኤል በሲና ተራራ ላይ፣ "የካህናት መንግሥት የተቀ ደሰም ሕዝብ" (ዘፀ19፥3-6) ለመሆን ከእግዚአብሔር ጋር በቃል ኪዳን በተጋባችበት ወቅት ነው (ዘፀ19፥3-6)። *የእግዚአብሔር!* ቃል በቃል ሲተረጐም "የእርሱ" ማለት ነው። *መቅደስ!* በዚህ ዓለም ማደሪያው ያደረገው ቤተ መቅደስ የተመሰለው በመገናኛው ድንኳን ኋላም ሰሎሞን በሠራው ቤተ መቅደስ ነው። በዘፀ15፥17 ላይ የተስፋዪቱ ምድር በዚሁ ዐይነት የእግዚአብሔር መቅደስ ተብላለች። *ግዛቱ!* በንጉሥነት የሚገዛው የተለየ መንግሥት ነው። ይህም ከግብፅ ባርነት ከመውጣት ይልቅ ይበልጥ የእግዚ አብሔር ቸርነት/ጸጋ የተገለጠበት ዕፁብ ድንቅ ነገር ነው።

*114፥3-4!* መዝሙረኛው ምስላዊ በሆነ መንገድ በሌሎች ባለቅኔዎች ተገልጾ የነበረውን አስፈሪና አስደንጋጭ ሁናቴ እርሱም ይጠቅሰዋል (18፥7-15፤ 68፥7-8፤ 77፥16-19፤ መሳ5፥4-5፤ ዕን3፥3-10)።

114፥3 *ባሕር ... ዮርዳኖስ!* እግዚአብሔር ቀይ ባሕርንና የዮርዳኖስን ወንዝ በብርቱ ክንዱ ከከፈለ በኋላ፣ ሕዝቡ በደረቅ መሬት አሻገረ፤ በዚህ ቦታ ቀይ ባሕርና የዮርዳኖስ ወንዝ በሰውኛ አገላለጽ ቀርበዋል። *አየች! ሸሸች!* ኀያሉ አምላክ አስፈሪ በሆነው በደመና ዐምድ እየቀረበ መምጣቱን አይተው ሸሹ ማለት ነው።

114፥4 *ዘለሉ!* ወይም ፈነደቁ ማለት ነው፤ ተራሮችና ኰረብቶች እግዚአብሔር እየቀረበ መምጣቱን ባዩ ጊዜ ተንቀጠቀጡ፤ ተርበደበዱም (29፥6 ይመ)።

*114፥7-8!* የትናንቱ ጌታ (ቍ5-6) ይኸውም የያዕቆብ አምላክ አሁንም ከእኛ ጋር አለ።

114፥7 *ተንቀጥቀጪ!* አስፈሪነቱን በማወቅ። *ምድር!* ሥነ-ፍጥረቱ ሁሉ ማለት ነው። *ያዕቆብ!* እስራኤል ከሚለው ስም ጋር ተመሳሳይ ነው። (ዘፍ32፥28 ይመ)።

114፥8 *ዐለቱን ወደ ኩሬ ... ውሃ ... ለወጠ!* በዚህ ሁኔታ ሕይ ወትን ደግፎና አለምልሞ ይዞአል (ዘፀ17፥6፤ ዘኍ20፥11 ይመ)።

*መዝ115!* ለሕዝቡ ስላለው ፍቅርና ለሕዝቡም ስላለው ታማ ኝነት፣ እውነተኛ የሆነውን አንዱን አምላክ እግዚአብሔርን ለማ መስገን የቀረበ ውዳሴ ነው። ይህ መዝሙር የተዘጋጀው በቤተ መቅደስ አገልግሎት የውዳሴ ተሰጥዎ እንዲሆን ታስቦ ነው። መዝሙሩ ምናልባት የተጻፈው ሁለተኛው ቤተ መቅደስ በተመረ ቀበትና (ዕዝ6፥16 ይመ) እስራኤልም ከምርኮ ከተመለሰች በኋላ፣ በሁለት እግሯ ለመቆም በምትውተረተርበት ሰዓት ሳይሆን አይ ቀርም (የመዝ113 መግቢያን ይመ)። በአወቃቀር ረገድ ሲታይ መዝሙሩ አምስት ቦታ ላይ የሚከፈል ሲሆን ሕዝቡና የቤተ መቅደሱ አገልጋዮች በተሰጥዎ የሚቀባበሉት ነው፤ አከፋፈሉም (1) ቍ1-8 ሕዝቡ የሚሉት፤ (2) ቍ9-11 የሌዋውያኑ መዘምራን መሪ የሚለው (አዝማቹ የሚዜመው ምናልባት በሌዋውያኑ መዘምራን ሳይሆን አይቀርም) (3) ቍ12-13 ሕዝቡ የሚሉት። (4) ቍ14-15 ካህናቱ የሚሉት (5) ቍ16-18 ሕዝቡ የሚቀበሉት።

*115፥1-8!* ለሕዝቡ ስላሳየው ፍቅርና ለሕዝቡም ስላለው ታማኝነት እግዚአብሔርን የሚያወድስ ክፍል ሲሆን የአሕዛብን ሽሙጥ ጸጥ ያሰኘ ፍቅርና ታማኝነት ነው።

115፥1 *ለእኛ ሳይሆን ... ለእኛ ሳይሆን!* የእስራኤል ሕልውና ደግሞም በዓመታት መካከል ጸንታ መኖሯ በራሷ ጥረትና ኀይል የተገኘ አይደለም። *ለስምህ!* የ5፥11 ማብ ይመ። ... *ምሕ ረትህና ... እውነትህ!* የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ከሚያስገኛ ቸው በረከቶች ውስጥ እነዚህ ሁለቱ በብሉይ ኪዳን የተለመዱ አባባሎች ናቸው (የ26፥3 ማብ ይመ)። *ምሕረትህ!* የ6፥4 ማብ ይመ።

115፥2 *አምላካቸው የት አለ?* እስራኤል በተፈጥሮ አደጋ እንዳልነበረ በሆነች ጊዜ (ኢዮ2፥17 ይመ) ወይም ጠላት ባደቀቃት በተለይም የይሁዳ ሕዝብ በጠፋና የእግዚአብሔርም ቤተ መቅደስ በፈረሰ ጊዜ (79፥10፤ ሚክ7፥10 ይመ) አሕዛብ የተናገሩት ሽሙጥ ነው።

115፥3 *በሰማይ ነው!* በዙፋኑ ተቀምጦአል (113፥5 ይመ)፤ ይህም "ከሰማያት ሁሉ በላይ ባለው ሰማይ" (ቍ16) ማለት ነው። *ደስ የሚለውን!* እስራኤል እንዳልነበረች ብትሆን ወይም ብትጠፋ ይህን ያደረገ እግዚአብሔር እንጂ ሌላ አይደለም፤ እንዲህ ሊሆን የቻለው እርሱ ማዳን አቅቶት ወይም ዐቅም አጥቶ አይደለም፤ ወይም ይህን ያመጡት አሕዛብ የሚያመልኩአቸው ጣዖታት አይደሉም። እስራኤል እንደ ገና ብትታደስ ወይም ብትለመልም ይህንንም የሚያደርግ ራሱ እግዚአብሔር ነው፤ ምክንያቱም እርሱን ለመቃወም የሚችል አንድም አምላክ የለም።

*115፥4-7!* የሐሰት አማልክት ምንም ያህል ክብርና ኀይል

በጕሮሮአቸውም ድምፅ አይፈጥሩም::
8እነዚህን የሚያበጁ፣
የሚታመኑባቸውም ሁሉ እንደ እነርሱ
ይሁኑ::
9የእስራኤል ቤት ሆይ፤ በእግዚአብሔር
ታመኑ፤
ረዳታቸውና ጋሻቸው እርሱ ነው::
10የአሮን ቤት ሆይ፤ በእግዚአብሔር
ታመኑ፤
ረዳታቸውና ጋሻቸው እርሱ ነው::
11እናንተ እግዚአብሔርን የምትፈሩ ሆይ፤
በእግዚአብሔር ታመኑ፤
ረዳታቸውና ጋሻቸው እርሱ ነው::
12እግዚአብሔር ያስበናል፤ ይባርከናልም፤
እርሱ የእስራኤልን ቤት ይባርካል፤
የአሮንንም ቤት ይባርካል::
13እግዚአብሔርን የሚፈሩትን ሁሉ፣
ትልቁንም ትንሹንም ይባርካል::
14እግዚአብሔር እናንተንና ልጆቻችሁን፣
በባርኮቱ ያብዛችሁ::
15ሰማይንና ምድርን በፈጠረ፣
በእግዚአብሔር የተባረካችሁ ሁኑ::
16ሰማየ ሰማያት የእግዚአብሔር ናቸው፤
ምድርን ግን ለሰው ልጆች ሰጣት::
17እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑት
የሞቱት አይደሉም፤
ወደ ዝምታው ዓለም የሚወርዱም

115፥9 መዝ37፥3፤ 62፥8
115፥10 ዘፀ30፥30፤ መዝ118፥3
115፥11 መዝ22፥23፤103፥11፤118፥4
115፥12 ዘፍ12፥2፤ 1ዜና16፥15
115፥13 መዝ112፥1
115፥14 ዘዳ1፥11
115፥15 ዘፍ1፥11 ሐሥ14፥15፤ራእ10፥6
115፥16 ዘፍ1፥28፤ መዝ8፥6-8፤89፥11
115፥17 መዝ88፥ 10-12
115፥18 መዝ28፥6፤33፥2፤103፥1፤ 111፥1፤113፥2
116፥1 መዝ6፥9፤ 18፥1፤28፥2፤31፥22፤ 40፥1
116፥2 መዝ5፥1
116፥3 2ሳሙ22፥6፤መዝ18፥4-5
116፥4 መዝ80፥2፤ 18፤118፥5
116፥5 ዘፀ9፥27፤ 22፥27፤2ዜና12፥6፤ ዕዝ9፥15፤መዝ86፥15
116፥6 መዝ18፥3፤ 22፥5፤79፥8፤107፥13
116፥7 መዝ13፥6፤ 46፥10፤62፥1፤106፥1፤131፥2፤142፥7፤ ማቴ11፥29
116፥8 መዝ86፥13

አይደሉም::
18ከአሁን ጀምሮ እስከ ዘላለም፣
እግዚአብሔርን የምንባርክ እኛ ነን::
እግዚአብሔር ይመስገን::[ሀ]

## መዝሙር 116

### ምስጋና

1የልመናዬን ድምፅ ሰምቶአልና፣
እግዚአብሔርን ወደድሁት::
2ጆሮውን ወደ እኔ አዘንብሎአልና፣
በሕይወት ዘመኔ ሁሉ ወደ እርሱ እጣራለሁ::
3የሞት ወጥመድ ያዘኝ፤
የሲኦልም[ለ] ጣር አገኘኝ፤
ጭንቅና ሐዘን አሸነፈኝ::
4እኔም የእግዚአብሔርን ስም ጠራሁ፤
"እግዚአብሔር ሆይ፤ ነፍሴን ታድናት
ዘንድ እለምንሃለሁ" አልሁ::
5እግዚአብሔር ቸርና ጻድቅ ነው፤
አምላካችን መሓሪ ነው::
6እግዚአብሔር ገሮችን ይጠብቃል፤
እጅግ ተቸግሬ ሳለሁ አዳነኝ::
7ነፍሴ ሆይ፤ ወደ ዕረፍትሽ ተመለሺ፤
እግዚአብሔር መልካም አድርጎልሻልና፤
8አንተ ነፍሴን ከሞት፣
ዐይኔን ከእንባ፣
እግሮቼን ከመሰናከል አድነሃልና::

[ሀ]18 ዕብራይስጡ ሃሌ ሉያ ይላል::
[ለ]3 ዕብራይስጡ ሲኦል ይላል::

አላቸው ተብሎ ቢታሰብም (እነርሱን እንዲወክሉ በተቀረጹት ምስሎች ላይ እንደሚታየው) እነርሱ ግን ሰው እንዳሉ ከገዛ ጉልበተው አንቅቶ የፈጠራቸውና ያበጃቸው በመሆናቸው ምንም የማይጠቅሙ ከንቱ ናቸው (135፥15-18፤ ኢሳ46፥1-7 ይመ)::

115፥8 *የሚያበጁ፤* አሽሟጣጭ አሕዛብን ማለት ነው (ከቍ2 ጋር ያስተያዩ):: *እንደ እነርሱ፤* ዐቅመቢስና ደካሞች ናቸው:: ስለዚህ ጉዳይ በዝርዝር ለማወቅ ኢሳ44፥9-20 ይመ::

*115፥9-11፤* በጣዖታት ሳይሆን በእግዚአብሔር መታመን እንደሚገባ የተደረገ ጥሪ ነው (ቍ8 ይመ):: በመቀባበል ሦስት ጊዜ የሚባል ስለመሆኑ የ96፥1-3 ማብ ይመ:: ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ስለ ሆኑት ደግሞ 118፥2-4 ይመ፤ እንዲሁም 135፥19-20 ይመ::

115፥11 *እናንተ ... የምትፈሩት፤* ይህ ምናልባት ከአምልኮ ጣዖት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር ወይም ወደ ይሁዲነት የተመለሱትን የሚያመለክት ጥሪ ነው (1ነገ8፥41-43፤ ዕዝ 6፥21፤ ነህ10፥28 ይመ)::

*115፥12-13፤* ሕዝቡ በእግዚአብሔር የሚታመን መሆኑን የሚገልጽ ንስሓ ነው::

*115፥14-15፤* የካህናት ቡራኬ ነው::

115፥14 *በባርኮቱ ያብዛችሁ፤* በቍጥር፣ በሀብትና በብርታት ማለት ነው (መክ2፥9 ላይ "ይበልጥ የከበርሁ ታላቅ ..." ከሚለው ጋር ያነጻጽሩ፤ ይህም ቃል በቃል ሲተረጐም፣ "ከሚገባው በላይ የበዛ ወይም የተትረፈረፈ" ማለት ነው)::

*115፥16-18፤* ሕዝቡ በመደምደሚያ ላይ ያቀረቡት ምስጋና ነው::

115፥16 *ሰማየ ሰማያት ... ምድርን፤* አንዱ እጅግ ከፍ ከፍ ያለው የልዑል እግዚአብሔር ዙፋን ያለበት ሲሆን፣ ሌላው ግን ሰው በእግዚአብሔር ሕግ ጸንቶ በእግዚአብሔር ጥበቃ እየታዘዘና ታላቅ በረከቱን እያገኘ እንዲኖርበት የተወሰነለት ቦታ ነው (ቍ12-13)፤ ሰው ለእግዚአብሔር የሚገባውንም ምስጋና የሚያቀርበው ከዚሁ ሆኖ ነው (ቍ18)::

115፥17 *ወደ ዝምታው ዓለም የሚወርዱም፤* ሙታን አንድ ጊዜ ካለፉ በኋላ በሕይወት ሥጋ "በዚች ምድር ላይ" (ቍ6) መኖር አይችሉም፤ ነገር ግን ጸጥ ዕረጭ ወዳለው ወደ ዝምታው ዓለም ይወርዳሉ፤ በዚያ በረከት እንዲሁም ማመስገን አይኖርም (የ6፥5፤ 30፥1 ማብ ይመ)::

*መዝ116፤* እግዚአብሔር ከሞት ስለታደገው ለእርሱ የቀረበ ምስጋና ነው:: መዝሙሩ የተጻፈው በአንድ ንጉሥ ሳይሆን አይቀርም (ቍ16 እና ማብ ይመ፤ እንዲሁም ሕዝቅያስ ካቀረበው ምስጋና ጋር ያነጻጽሩ፤ ኢሳ38፥10-20) የመዝሙሩ ቋንቋ በአብዛኛው የዳዊትን መዝሙሮች ያስተጋባል:: በአይሁድ የዝማሬ ተሰጥዎ እንደተለመደው (የመዝ113 መግቢያን ይመ) እኔ በሚለው ነጠላ የተጸውዖ ስም ግራና ቀኝ እየተቀበሉ (የመዝ30 ርእስ ይመ) ሳይጠቀሙበት አልቀረም:: እንዲሁም "ሞት" የሚለው ቃል የገባው የግብፁን ባርነት እና/ወይም የባቢሎንን ምርኮ ለማመልከት ሳይሆን አይቀርም:: ይህ ሰባት አንጓ ያለው የምስጋና ዝማሬ (ቍ7ን ከሚቀጥሉት ቍጥሮች ጋር አገናዝበው ሲያነቡት፤ የቍ7ን ማብ ይመ) በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች የሚከፈል ቍ1-6፡ 7-14፡ 15-19) ሲሆን እያንዳንዱን ክፍል የሚያስተሳስር አንድ ዐቢይ ሐሳብ ጐልቶ ይታያል::

*116፥1-6፤* እግዚአብሔርን እወደዋለሁ፤ ምክንያቱም ልመናዬን ሰምቶኛል፤ ከሞትም አድኖኛል::

116፥2 *ወደ እርሱ እጣራለሁ፤* በእርሱ እታመናለሁ፤ ምንጊዜም ቢሆን ጸሎቴን የማቀርበው ለእርሱ ነው፤ ይህም በእያንዳንዱ ዋና ክፍል ተደጋግሞ የተገለጠ ቃል ነው (ቍ13፡17 ይመ)::

*116፥3-4፤* 18፥4-6 ይመ::

116፥3 *የሞት ወጥመድ፤* የ18፥5 ማብ ይመ::

116፥5 *አምላካችን፤* ጸሐፊው እግዚአብሔር አምላኩ እንደሆነ ተረድቶአል፤ ስለዚህ እግዚአብሔርን "በሕዝቡ ሁሉ ፊት" ያመሰግነዋል (ቍ14፡18)::

116፥6 *ገሮችን፤* እግዚአብሔርን አለኝታውና መታመኛው በማድረግ እንደ ሕፃን ልጅ የሆነውን ሰው የሚያመለክት ነው (የ19፥7 ማብ ይመ)::

*116፥7-14፤* እግዚአብሔር ለእኔ ያሳየውን በጎነት እንዴት አድርጌ እከፍለዋለሁ!

116፥7 *ነፍሴ ሆይ፤* የ103፥1-2፡22 ማብ ይመ:: *ወደ ዕረፍትሽ፤* ሥጋት የሌለበትን ሕይወት የሚያሳይ ነው (ከኤር6፥16 ጋር ያነጻጽሩ፤ 1ነገ5፥4 ይመ፤ "ሰላም" እንዲሁም የ23፥2 ማብ ይመ፤ "የረጋ ወይም ጸጥ ያለ ውሃ" ማለትም ይሆናል):: *መልካም አድርጎልሻል፤* የዕብራይስጡ ቃል በውስጡ የያዘው ትርጕም በቍ12 ላይ "በጎነት" ከሚለው ቃል ጋር አንድ ነው (ማብ ይመ)::

116፥8 *ነፍሴ፤* እኔን ራሴን ማለት ነው የ6፥3 ማብ ይመ::

[9]እኔም በሕያዋን ምድር፣
በእግዚአብሔር ፊት እመላለሳለሁ።
[10]“እጅግ ተጨንቄአለሁ” ባልሁበት ጊዜ
እንኳ፣[ፈ]
እምነቴን ጠብቄአለሁ።
[11]ግራ በተጋባሁ ጊዜ፣
“ሰው ሁሉ ሐሰተኛ ነው” አልሁ።
[12]ስለ ዋለልኝ ውለታ ሁሉ፣
ለእግዚአብሔር ምን ልክፈለው?
[13]የመዳንን ጽዋ አነሣለሁ፤
የእግዚአብሔርንም ስም እጠራለሁ።
[14]በሕዝቡ ሁሉ ፊት፣
ስእለቴን ለእግዚአብሔር እፈጽማለሁ።
[15]የቅዱሳኑ ሞት፣
በእግዚአብሔር ፊት የተከበረ ነው።
[16]እግዚአብሔር ሆይ፤ እኔ በእውነት
ባሪያህ ነኝ፤
እኔ የሴት ባሪያህ[ፐ] ልጅ፣ ባሪያህ ነኝ፣
ከእስራቴም ፈታኸኝ።
[17]ለአንተ የምስጋና መሥዋዕት አቀርባለሁ፤
የእግዚአብሔርንም ስም እጠራለሁ።
[18]በሕዝቡ ሁሉ ፊት፣
ስእለቴን ለእግዚአብሔር እፈጽማለሁ፤
[19]ኢየሩሳሌም ሆይ፤ ይህን በመካከልሽ፣
በእግዚአብሔር ቤት አደባባይ አደርጋለሁ።
ሃሌ ሉያ።[ገ]

## መዝሙር 117

### የምስጋና ጥሪ

[1]አሕዛብ ሁላችሁ፤ እግዚአብሔርን
አመስግኑት፤
ሕዝቦችም ሁሉ፤ በምስጋና ከፍ ከፍ
አድርጉት፤
[2]እርሱ ለእኛ ያሳየው ምሕረት ታላቅ ነውና፤
የእግዚአብሔርም ታማኝነት ጸንቶ
ይኖራል።
ሃሌ ሉያ።[ጠ]

116፥9 ዘፍ5፥22፤ኢዮ28፥13፤መዝ27፥13፤56፥13፤89፥15፤ኢሳ38፥11፤ኤር11፥19 116፥10 መዝ9፥18፤72፥2፤107፥17፤119፥67፡71፡75፤2ቆሮ4፥13 116፥11 ኤር9፥3-5፤ሆሴ7፥13፤ሚክ6፥12፤ሮሜ3፥4 116፥12 መዝ103፥2፤106፥1 116፥13 መዝ105፥1 116፥14 ዘኍ30፥2፤መዝ66፥13 116፥15 ዘኍ23፥10፤መዝ72፥14 116፥16 ኢዮ12፥18፤መዝ86፥16፤119፥125፤143፥12 116፥17 ዘሌ7፥12፤ዕዝ1፥4 116፥18 ቍ14፤ዘሌ22፥18 116፥19 መዝ92፥13፤96፥8፤100፥4፤102፥21፤135፥2 117፥1 መዝ22፥23፤103፥2፤ሮሜ15፥11 117፥2 መዝ17፥7፤103፥11፤119፥90፤146፥6

[ፈ]10 ወይም ያኔ እንኳን [ፐ]16 ታማኝ አገልጋይህ ወይም ታማኝ ልጅህ [ገ]19 አንዳንዶች እግዚአብሔር ይመስገን ይላሉ። [ጠ]2 አንዳንዶች እግዚአብሔር ይመስገን ይላሉ።

116፥10 *እጅግ ተጨንቄአለሁ፤* ይህ ቍጥርና በቍ11 ላይ ያለው ጥቅስ ምናልባት በቍ4 ላይ ካለው ጥቅስ ጋር አብረው የሚሄዱ ሲሆን መዝሙረ ኛው በታላቅ ሥቃይ ውስጥ በነበረበት ጊዜ ያቀረበውን ጸሎት ባጭሩ የሚያሳስቡ ናቸው። በመዝ109 እንደ ተጻፈው ሁሉ (የ5፥9፤ የ10፥7 ማብ ይመ) በዚያም ቦታ መዝሙረኛው ከሞት ቢተርፍም ጠላቶቹ ግን በሐሰት መክሰሳቸውን አልተውም (በዚህ ቍጥር ላይ የተሰጠውን ለየት ያለ ትርጕም ለማየት ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ማብ ይመ)። *አመንሁ፤* ጸሐፊው በፈራና በሠጋ ጊዜ እግዚአብሔርን ለመጥራት ስለገፋፋው እምነቱ ይናገራል።

116፥11 *ሰው ሁሉ ሐሰተኛ ነው፤* መዝሙረኛው በሐሰት የከሰሱትን ሰዎች ማንነት በተመለከተ የተናገረው ነገር ነው (ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ክሶችን ለማየት 5፥9-10፤ 35፥11፡15፤ 109፥2-4 ይመ)። አንዳንድ ሰዎች ይህን ቍጥር የሚተረጕሙት ሰዎች የሚሰጡት ተስፋ እንዲሁም ሰዎችን መተማመን ከንቱ እንደ ሆነ አድርገው ነው (60፥11፤ 118፥8-9) ስለዚህ መዝሙረ ኛው ታማኝ የሆነውን እግዚአብሔርን ይጠራል።

116፥12 *ምን ልክፈለው?* መዝሙረኛው እንደዚህ ያሉትን የጸሎትና የልመና፣ የውዳሴና የምስጋና ኀይለ-ቃላት ለእግዚአ ብሔር የማቅረብ ፍላጎት ያለው መሆኑን ይገልጻል (ቍ13-14፤ 17-18ን ከ50፥14-15፡23 ጋር ያነጻጽሩ)፣ *በጎ ነገር፤* በዕብራይስጡ የብሉይ ኪዳን ቅጅ ላይ ይህ ቃል የሚገኘው በዚህ ቦታ ብቻ ነው፤ ነገር ግን በቍ7 ላይ “መልካም ሆኖልሻልና” ለሚለው ቃል ሥሩ ይኸው ቃል ነው።

116፥13 *የመድኀኒትን ጽዋ፤* በማቴ26፥27 እና በሌሎችም ተጓዳኝ ክፍሎች ላይ እንደ ተመለከተው ይህ ጽዋ በፋሲካ ማእድ ላይ ከሚቀርበው ጽዋ ጋር ዝምድና አለው ተብሎ ይታሰባል፤ ይበልጥ ግን የምስጋና መሥዋዕት ማለትም “የድነት ጽዋ” ተብሎ በሚጠራው ሥርዐት ላይ የሚጠጣ የወይን ጽዋ ነው ቢባል ትክክል ይመስላል (22፥26፤ ዘሌ7፥11-21 ይመ)፤ “የድነት ጽዋ” መባሉም የምስጋና መሥዋዕቱና ማዕዱ በጌታ የተደረገውን ትድግና ለማክበር የሚውል በመሆኑ ነው።

116፥14 *ስእለቴን፤* እግዚአብሔርን ለማመስገን የተሳለው ስእለት ነው (የ7፥17 ማብ ይመ)።

*116፥15-19፤* እግዚአብሔር ሕይወቴን ስላከበረ ሁለንተናዬን ለእርሱ እሰጣለሁ።

116፥15 *የቅዱሳኑ ሞት ... የተከበረ፤* በዋጋ ተመን ሳይሆን፣ ከፍ ያለ ጥበቃ የሚደረግለት በመሆኑ ነው “ደማቸው በፊቱ የከበረች ናት” (72፥14) ከሚለው ተመሳሳይ ሐረግ ጋር ያነጻጽሩ። *የቅዱሳኑ፤* የ4፥3 ማብ ይመ።

116፥16 *ባሪያህ፤* ይህ ቃል መዝሙረኛው በእግዚአብሔር የተቀባ መሆኑን ያሳያል (78፥70 ይመ)፤ መዝሙረኛው የተቀባው ግን በማንኛውም ጊዜ መላ ሕይወቱን ለእግዚአብሔር እንዲያውል ነው (19፥11፡13 ይመ)። *የሴት ባሪያህ ልጅ፤* 86፥16 አግራጭ ትርጕሙን ይመ።

116፥19 *አደባባይ፤* የቤተ መቅደሱን ቅጥር ግቢ ነው (84፥2፡10፤ 2ነገ21፥5፤ 23፥11-12 ይመ)።

*መዝ117፤* በመጽሐፈ መዝሙር ውስጥ ከሚገኙት መዝሙ ራት ሁሉ እጅግ አጭሯ መዝሙር ይህች ናት፤ እንዲሁም በመ ጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አጭሯ ምዕራፍ ይህች ናት፤ መዝ117 ሃሌ ሉያ የሚለው ሐሳብ ሰፋ ባለ መልኩ የተገለጸባት ነች (አንዳንድ ጊዜም ከመዝሙር 118 ጋር ተያይዛ ትገኛለች)። በመጀመሪያ ግን ሃሌ ሉያ ለሚሉት መዝሙሮች ሃሌ ሉያ፣ ሃሌ ሉያ (መዝ 111-116) ሰባተኛዋ ሆና እንደ ማሳረጊያ ሳታገለግል አትቀርም። በዚህ መዝሙር ላይ ለምድር ሕዝቦች ሁሉ ጥሪ ቀርቦአል፤ ጥሪውም እግዚአብሔር ለእስራኤል ያሳየውን ታላቅ ፍቅርና ታማኝነት (ኢሳ 12፥4-6 ይመ) ተመልክተው እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ ነው (ይህም በ47፥1፤ 67፥3-5፤ 96፥7፤ 98፥4፤ 100፥1 ላይ እንደ ተጻፈው ማለት ነው፤ የ9፥1 ማብ ይመ)። በመሆኑም በመጽሐፈ መዝሙር ውስጥ የሚገኙት ሃሌ ሉያዎች አንድ በአንድ ሲተነተኑ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ አጽንዖት የተሰጠውን እንደ ታላቅ ቁም ነገር ቍልጭ አድርገው ያሳያሉ፤ ይኸውም የምድር ሕዝቦች ዕጣ ፈንታ የተመሠረተው እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ በሚያ ደርገው በጎነት ላይ መሆኑን ነው (ለምሳሌ 2፥8-12፤ 47፥9፤ 67፥2፤ 72፥17፤ 102፥15፤ 110፤ ዘፍ12፥3፤ ዘዳ32፥43፤ 1ነገ8፥41-43፤ ኢሳ 2፥2-4፤ 11፥10፤ 14፥2፤ 25፥6-7፤ 52፥15፤ 56፥7፤ 60፥3፤ 66፥18-24፤ ኤር3፥17፤ 16፥19-21፤ 33፥9፤ አሞ9፥11-12፤ ሚክ5፥7-9፤ ሶፎ3፥8-9፤ ሐጌ2፥7፤ ዘካ2፥10-11፤ 8፥20-23፤ 9፥9-10፤ 14፥2-3፤ ሚል3፥12 ይመ)። እንዲሁም የመዝ113 መግቢያ ይመ።

*117፥1፤* በሮሜ 15፥11 ላይ ተጠቅሶአል፤ የተጠቀሰበትም ምክንያት አሕዛብ ድነትን ለማግኘትና እግዚአብሔርንም ለማ መስገን የበቁት ባጋጣሚ አለመሆኑን ለማረጋገጥ ነው።

*117፥2፤* ለምስጋናው ምክንያት የሆነውን ነገር ይጠቅሳል። *ምሕረት ... ታማኝነትም፤* ለእኛ ያለው ፍቅርና ታማኝነት ማለት ነው (36፥5 እና ማብ ይመ፤ እንዲሁም የ3፥7 ማብ ይመ)። *ምሕ ረት፤* የ6፥4 ማብ ይመ።

*መዝ118፤* ከጠላት እጅ ለታደገ አምላክ የቀረበ የምስጋና ዝማሬ ነው። በዚህ መዝሙር ላይ ከተሰጡት በርካታ አስተያየ ቶች ውስጥ (በዝርዝር ነገሩ ላይ ሰፋ የለ ልዩነት ቢኖረም) ሦስቱ በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት አላቸው፤ እነዚህም (1) አንድ ከዳዊት ቤት የወጣ ንጉሥ ተባብረው ከገጠሙት መንግሥታት ጋር የሞት የሽረት ጦርነት ካካሄደ በኋላ (ከ2ዜና 20፥27-28 ጋር ያነጻጽሩ፤ እንዲሁም የቍ19 ማብ ይመ) ስለ ትድግናውና ስለ ተቀዳጀው ድል እግዚአብሔርን በዜማ ተሰጠው በማመስገን ሕዝ ቡን ይመራል፤ (2) እስራኤል ከግብፅ ባርነት ነጻ የወጣችበትንና በከነዓናውያንም ላይ ድል የተጐናጸፈችበትን ሁኔታ በዳስ ክብረ-በዓል ላይ ስታከብር የተዘመረ ነው የሚሉ አሉ፤ (3) ከባቢሎን ምርኮ የተመለሱ አይሁድ ከጠላታቸው እጅ ነጻ የወጡበትን ቀን ሁለተኛው ቤተ-መቅደስ ተሠርቶ በተመረቀበት ዕለት (ዕዝ6፥16 ይመ) ወይም የኢየሩሳሌም ቅጥር እንደ ገና ተሠርቶ በተመረቀ

## መዝሙር 118

### ለጸስ በዓል የቀረበ የጉዞ መዝሙር

1 *እግዚአብሔር* ቸር ነውና አመስግኑት፤
ምሕረቱም ለዘላለም ጸንታ ትኖራለች።

2 የእስራኤል ሕዝብ፣
"ምሕረቱ ለዘላለም ነው" ይበል።
3 የአሮን ቤት፣
"ምሕረቱ ለዘላለም ነው" ይበል።
4 *እግዚአብሔርን* የሚፈሩ ሁሉ፣
"ምሕረቱ ለዘላለም ነው" ይበሉ።

5 በተጨነቅሁ ጊዜ *እግዚአብሔርን* ጠራሁት፤
*እግዚአብሔርም* መለሰልኝ፤ ከመጠበብም
አወጣኝ።
6 *እግዚአብሔር* ከእኔ ጋር ነው፤ አልፈራም፤
ሰው ምን ሊያደርገኝ ይችላል?
7 ይረዳኝ ዘንድ *እግዚአብሔር* ከእኔ ጋር
ነው፤
የጠላቶቼንም ውድቀት አያለሁ።

8 ሰውን መከታ ከማድረግ ይልቅ፣
በ*እግዚአብሔር* መታመን ይሻላል።
9 በገገዦች ተስፋ ከማድረግ ይልቅ፣
በ*እግዚአብሔር* መታመን ይሻላል።

10 ሕዝቦች ሁሉ ከበቡኝ፤
ነገር ግን በ*እግዚአብሔር* ስም
አስወግዳቸዋለሁ።
11 መክበቡንስ በየአቅጣጫው ከበቡኝ፤
ነገር ግን በ*እግዚአብሔር* ስም
አስወግዳቸዋለሁ።
12 እንደ ንብ መንጋ ከበቡኝ፤
ነገር ግን እንደሚነድ እሾኽ ከሰሙ፤
በእርግጥም በ*እግዚአብሔር* ስም
አስወግዳቸዋለሁ።

13 ተገፍትሬ ልወድቅ ተንገደገድሁ፤
*እግዚአብሔር* ግን ረዳኝ።
14 *እግዚአብሔር* ብርታቴና ዝማሬዬ ነው፤
አዳኝ ሆነልኝ።

15 በጻድቃን ድንኳን የእልልታና የሆታ
ድምፅ፣
እንዲህ እያለ ያስተጋባል፤
"የ*እግዚአብሔር* ቀኝ እጅ ብርቱ ሥራ
ሠራች፤
16 የ*እግዚአብሔር* ቀኝ እጅ ከፍ ከፍ አለች፤
የ*እግዚአብሔር* ቀኝ እጅ ብርቱ ሥራ
ሠራች።

17 ተርፌ በሕይወት እኖራለሁ እንጂ
አልሞትም፤
የ*እግዚአብሔርን*ም ሥራ ገና እናገራለሁ።
18 መገሠጹን *እግዚአብሔር* እጅግ
ገሥጾኛል፤
ነገር ግን ለሞት አሳልፎ አልሰጠኝም።

19 የጽድቅን ደጆች ክፈቱልኝ፤
በዚያ ገብቼ *እግዚአብሔርን*
አመሰግናለሁ።

118፥1 1ዜና16፥8፤ 2ዜና5፥13፤7፥3፤ዕዝ 3፥11
118፥2 መዝ106፥1 ፤115፥9፤136፥1-26
118፥3 ዘፀ30፥30፤ መዝ115፥10
118፥4 መዝ115፥11
118፥5 ቍ21፤መዝ 18፥6፤31፥7፤34፥4፤7 7፥2፤86፥7፤116፥1፤ 120፥1፤138፥3
118፥6 ዘዳ31፥6፤ መዝ56፥4፤ዕብ13፥5
118፥7 ዘዳ33፥29፤ መዝ54፥7፤ዕብ13፥6
118፥8 2ዜና32፥7-8፤መዝ2፥12፤5፥11፤ 9፥9፤37፥3፤40፥4፤ 108፥12፤ኢሳ2፥22፤ 25፥4፤57፥13
118፥9 መዝ146፥3
118፥10 መዝ37፥9
118፥11 መዝ3፥6፤ 88፥17
118፥12 ዘዳ1፥44፤ መዝ37፥9፤58፥9
118፥13 ቍ7፤2ዜና 18፥31፤መዝ86፥17
118፥14 ዘፀ15፥2፤ መዝ62፥2
118፥15 ዘፀ15፥6፤ ኢዮ8፥21፤መዝ 89፥13፤106፥5፤ 108፥6፤ሉቃ1፥51
118፥17 ዘዳ32፥3፤ መዝ64፥9፤71፥16፤73 ፥28፤ዕን1፥12
118፥18 መዝ86፥13 1ኤር31፥18፤1ቆሮ11፥32፤ዕብ12፥5
118፥19 መዝ24፥7፤100፥4

በት ዕለት (ነህ 12፥37-43 ይመ) የተዘመረ ነው ያሉም አሉ። እንደ መጀመሪያው ትርጓሜ ከሆነ፣ በቍ5-21 ላይ መሪው ንጉሡ ነው፤ እንደ ሁለተኛውና እንደ ሦስተኛው ትርጓሜ ከሆን ደግሞ፣ ሕዝቡን ወክሎ የሚመራው ሌዋዊ ወይም ካህን ነው። ቀጥሎ ያሉት ማስታወሻዎች የመጀመሪያውን ትርጓሜ የሚከተሉ ናቸው። ከምርኮ በኋላ ተሻሽለው ከተዘጋጁት መዝሙሮች ውስጥ (የመዝ113ን መግቢያ ይመ)። ይህ መዝሙር ሕዝቡ ከባርነት ነጻ የወጣበትን ቀን ለማስታወስ የሚዘመር ነው። የተሰጥዎው ምስጋና የመጨረሻ ዝማሬ በመሆኑ በመጀመሪያዪቱ "የጌታ ራት" ምሽት (ማቴ26፥30 ይመ) ጌታ ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ በሥርዐቱ ማሳረጊያ (መደምደሚያ) ላይ የዘመሩት ይህንን መዝሙር ሳይሆን አይቀርም። ከተሰጥዎ የምስጋና ጥሪ ቀጥሎ (ቍ1-4) ንጉሡ ከባርነት ነጻ የወጡበትንና ድልም የተጐናጸፉበትን ቀን በማስ ታወስ የምስጋና ዝማሬ ያቀርባል። በቍ22-27 ላይ ሕዝቡ እግዚ አብሔር ስላደረገው ድንቅ ነገር ደስታውን ይገልጻል። ከዚህ በኋላ ንጉሡ የምስጋ ናውን የመጨረሻ ቃል (ቍ28) እና የተሰጥዎውን ማሳረጊያ (ቍ29) ይናገራል፤ ይህም በመዝሙሩ መግቢያ ላይ የቀረበውን የምስጋና ጥሪ እንደ ገና ያሚያውሣ ሲሆን ሥርዐተ-ውዳሴው የተቀነበበው በእነዚህ የምስጋና ጥሪዎች ነው።

*118፥1-4፤* በተሰጥዎ ላይ የቀረበ የምስጋና ጥሪ ነው።

*118፥1፤* ለምስጋና በሚደረግ ጥሪ ላይ የተለመደ ቋንቋ ነው (ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ከመዝ105-107፤ 136፤ 1ዜና16፥8፡34፤ 2ዜና20፥21 ጋር የሚጋራው ቁም ነገር አለው) *አመስግኑት፤* የመዝ100 ርእስ ማብ ይመ። ይህ ቍጥር እና ቍ2-4 እንዲሁም ቍ29 በቍ5-21 ላይ ከተናገረው ሰው ድምጽ (ቃል) ጋር አንድ ዐይነት ሳይሆኑ አይቀርም። *ምሕረቱም፤* ቍ2-4፡29 ይመ፤ እንዲሁም የ6፥4 ማብ ይመ።

118፥2-4 *የእስራኤል ... የአሮን ቤት ... እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሁሉ፤* 115፥9-11 እና ማብ ይመ። አንድን ነገር ሦስት ጊዜ እየደጋገሙ መናገር በዚህ መዝሙር ውስጥ የተለመደ የአነ ጋገር ስልት ነው (የ96፥1-3 ማብ ይመ)።

*118፥5-21፤* ከባርነት ነጻ የወጡበትንና ድልም የተጐና ጸፉበትን ሁኔታ አስታውሶ ንጉሡ ያዜመው ዝማሬ ነው።

118፥5 *አወጣኝ፤* ቃል በቃል ሲተረጐም "ሰፊ በሆነ ቦታ/ ስፍራ" ማለት ነው፤ 18፥19 እና ማብ ይመ።

118፥7 *አያለሁ፤* ወይም "እያቸዋለሁ" ማለት ነው።

*118፥8-9፤* 33፥16-19 ይመ፤ እንዲሁም መዝ62፤146 ይመ።

118፥10 *በእግዚአብሔር ስም፤* 1ሳሙ17፥45 ይመ። *ስም፤* ቍ11-12፡26 ይመ፤ እንዲሁም የ5፥11 ማብ ይመ።

118፥12 *እንደሚነድ እሾኽ፤* 58፥9 እና ማብ ይመ።

118፥13 *ልወድቅ፤* ልገደል ማለት ነው (ቍ17-18 ይመ፤ እንዲሁም የ13፥4 ማብ ይመ)።

*118፥14፤* ምናልባት በዘፀ15 ላይ ያለውን የድል ዝማሬ የሚያሳስብ ሳይሆን አይቀርም። ይሁን እንጂ ይህ ቍጥር ስለ ምስጋና በሰፊው የሚመሰክር ዝማሬ ተደርጎ ቢወሰድ የተሻለ ነው (ኢሳ12፥2 ይመ)።

118፥15 *በጻድቃን፤* እስራኤላውያን እንደ ሕዝብነታቸው በልባቸውም፣ በሕይወታቸውም ለእግዚአብሔር የተለዩ ወገኖች ለመሆናቸው ቃል መግባታቸውን ያረጋግጣል (ቍ20 ይመ፤ እንዲሁም 68፥3 እና ማብ ይመ)። "የክፉዎች ድንኳን" (84፥10) ከሚለውም ጋር ያነጻጽሩ። *ድንኳን፤* መኖሪያ ማለት ነው።

118፥17 *እኖራለሁ ... እናገራለሁ፤* 115፥17-18 ይመ፤ የ6፥5 ማብ ይመ።

118፥18 *ገሥጾኛል፤* እግዚአብሔር ንጉሡ በሕይወቱ ያሳለፈውን ከባድ መከራ በመጠቀም ሥርዐት ያለው ሰው እንዲሆንና ትሕትናንም የተላበሰ መንፈሳዊነት እንዲማር ያደረገው መሆኑን በሚገባ ተረድቶአል (6፥1፤ 38፥1፤ 94፥12፤ ዘዳ4፥36፤ 8፥5 ይመ)።

118፥19 *ክፈቱልኝ፤* ይህ መዝሙር (ስንኙ) (ቍ27) ንጉሡ ደስታ በፈነቀለው ሕዝብ ፊት ቀድሞ ወደ ቤተ መቅደሱ ቅጥር ግቢ በመቅረብ ላይ ሳለ (መዝ24፥68 ይመ) የተከናወነው ሥርዐት ምን ይመስል እንደ ነበር ያሳያል። *ደጆች፤* ወደ ውስጠኛው የቤተ መቅደሱ አደባባይ የሚያመሩትን መንገዶች ማለት ነው። *የጽድቅን፤* የአንድ በተለይ በዚህ ስም የሚጠራ በር ስም ነው ተብሎ ይታሰባል፤ ይሁን እንጂ "ጻድቃን ብቻ በውስጡ ዐልፈው የሚሄዱበት" (ቍ20) መሆኑን ለማመልከት የተነገረ ሳይሆን አይቀርም የሚል አስተያየት አለ። በዓሉን ሊያከብር የወጣው ሕዝብ ወግና ሥርዐቱን ተከትሎ መንቀሳቀስ የጀመረው ከከተ ማዪቱ ቅጥር ውጭ ሲሆን፣ "የጽድቅ በሮች" የተባሉትም የእግዚ አብሔር ከተማ የሆነችው የኢየሩሳሌም ቅጥር በሮች ናቸው (የ24፥7 ማብ ይመ፤ እንዲሁም ኢሳ26፥2 ይመ)።

[20]ይህች *የእግዚአብሔር* ደጅ ናት፤
ጻድቃን በእርሱ በኩል ይገባሉ።
[21]ስምተህ መልሰህልኛልና፣
አዳኝም ሆነህልኛልና አመሰግንሃለሁ።
[22]ግንበኞች የናቁት ድንጋይ፣
እርሱ የማእዘን ራስ ሆነ።
[23]*እግዚአብሔር* ይህን አደረገ፤
ለዐይናችንም ድንቅ ናት።
[24]*እግዚአብሔር* የሠራት ቀን ይህች ናት፤
በእርሷ ሐሤት እናድርግ፤ ደስም
ይበለን።
[25]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ እባክህ አድነን፤
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ እባክህ አሳካልን።
[26]*በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ
ነው።*
*ከእግዚአብሔር* ቤት ባረክናችሁ።
[27]*እግዚአብሔር* ስምሳክ ነው፤
ብርሃኑንም በላያችን አበራ፤
እስከ መሠዊያውⁿ ቀንዶች ድረስ
በመውጣት፣
ዝንጣፊ ይዛችሁ በዓሉን ከሚያከብሩት
ጋር ተቀላቀሉ።
[28]አንተ ስምላኬ ነህ፤ አመሰግንሃለሁ፤
አንተ ስምላኬ ነህ፤ ከፍ ከፍ አደርግሃለሁ።
[29]ቸር ነውና፣ *እግዚአብሔርን* አመስግኑ፤
ምሕረቱም ለዘላለም ጸንታ ትኖራለች።

## መዝሙር 119[a]

## ውዳሴ ለሕገ እግዚአብሔር

### ℵ አሌፍ

[1]*መንገዳቸው ነቀፋ የሌለበት፣*

118፥20 መዝ15፥1-2፤24፥3-4፤122፥1-2፤ራእ22፥14
118፥21 ቍ5፤መዝ27፥1
118፥22 ኢሳ8፥14፤17፥10፤19፥13፤28፥16፤ዘካ4፥7፤10፥4፤ማቴ21፥42፤ማር12፥10፤ሉቃ20፥17፤ሐሥ4፥11፤1ጴጥ2፥7
118፥23 ማቴ21፥42፤ማር12፥11
118፥24 መዝ70፥4
118፥25 መዝ28፥9፤116፥4
118፥26 መዝ129፥8፤ማቴ11፥3፤21፥9፤23፥39፤ማር11፥9፤ሉቃ 13፥35፤19፥38፤ዮሐ12፥13
118፥27 ዘፀ27፥2፤ዘሌ23፥40፤1ነገ18፥21፤መዝ27፥1፤ኢሳ58፥10፤60፥1፡19፡20፤ሚል4፥2፤1ጴጥ2፥9
118፥28 ዘፍ28፥21 ፤ዘፀ15፥2፤መዝ16፥2 ፤63፥1፤ኢሳ25፥1
119፥1 ዘፍ17፥1፤ ዘዳ18፥13፤መዝ1፥2፤128፥1፤ምሳ11፥20

ⁿ27 ወይም የክብረ በዓልን መሥዋዕት በገመድ ማሰር ወይም መውሰድ

[a]119 የዚህ መዝሙር የግጥም ስንኞች መነሻ ወይም መነሻና መድረሻ ሆሄያት ቍልቍል ሲነበቡ ትርጕም አዘል ናቸው። እያንዳንዱ ስንኝ ተመሳሳይ በሆነ በዕብራይስጥ ፊደል ይጀምራል።

*118፥21፤* ይህ የምስጋናው ዝማሬ መደምደሚያ የሆነው ቍጥር፣ በቍጥር 1 ላይ "አመስግኑት" የሚለውን፣ በቍ5 ላይ "መለሰልኝ" የሚለው እንዲሁም በቍ14 ላይ የተሰጠውን ምስክርነት የሚያስተጋባ ነው።

*118፥22-27፤* የሕዝቡን ታላቅ ደስታ የሚገልጽ ክፍል ነው።

118፥22 *ግንበኞች የናቁት ድንጋይ፤* ይህ ቃል የሚያመለክተው ራሱ ንጉሡን ሲሆን፣ የሚያስተዳድረውን ግዛት የወረሩት ነገሥታት ማለትም የዚህ ዓለም ሥልጣን ወይም ምስፍና ግንበኞች እንደ ምናምንቴና ከንቱ ነገር ተመልክተውታል። አንዳንድ ሰዎች ይህ ቃል የሚያመለክተው እስራኤልን ነው ይላሉ። *የማእዘን ራስ፤* ቃል በቃል ሲተረጐም "የማእዘን ዐናት" ማለት ነው፤ ይህም ከበር በላይ ያለ ባለ ማእዘን ወይም አንድ የሕንፃ ግድግዳ እንዳይዛነፍ ግጥም አድርጎ የሚይዘው ትልቅ ድንጋይ ወይም የአንድ ቅስት መደምደሚያ ድንጋይ ማለት ነው (ዘካ4፥7፤ 10፥4 ይመ)። የመዝሙሩ ደራሲ ተመሳሳይ ድምፀት ያላቸውን ቃላት በመጠቀም በዕብራይስጡ "ኙን" የሚለው ቃል "ዋና ወይም ጠቅ ላይ ገዥ/አዛዥ" የሚል ፍቺ እንዲሰጥ አድርጓል ("ማእዘን" ለሚለው የዕብራይስጡ ቃል "መሪ ወይም ገዥ" የሚል ተለዋጭ ዘይቤ አዘል ፍቺ አለው ኢሳ19፥13 ይመ፤ እንዲሁም መሳ20፥2፤ 1ሳሙ 14፥38 ይመ)። ይህ በዓለም ኀያላን ገዦች የተናቀና እንደ ምናምንቴም ነገር የተቈጠረው ድንጋይ እግዚአብሔር በእስራኤል በኩል በሚያመጣው በአዲሱ የዓለም ሥርዐት ውስጥ እጅግ የተከበረ ድንጋይ ሆኖአል። ኢየሱስ ይህንን (እንዲሁም ቍ23ን) ወስዶ ለራሱ ተጠቅሞበታል (ማቴ21፥42፤ ማር12፥10-11፤ ሉቃ20፥17 ይመ፤ እንዲሁም የሐሥ4፥11፤ ኤፌ2፥20፤ 1ጴጥ2፥7 ይመ)።

118፥24 *እግዚአብሔር የሠራት ቀን ... ሐሤት እናድርግ፤* ይህች የደስታ ቀን የተገኘችው በእግዚአብሔር ትድግና በሚከበረው የድል ነጻነት ምክንያት ነው፤ ሌሎች ግን ይህን ጥቅስ ከፋሲካ ወይም ከዳስ በዓል ጋር ያዛምዱታል። *የሠራት ... ናት፤* ወይም አድርጎታል ማለት ሲሆን (ቍ15-17፡23 ይመ) "የማእዘኑን ድንጋይ ዋና የማእዘን ድንጋይ" ማድረጉን ያመለክታል።

*118፥25፤* ሕዝቡን መታደግና ዐቅፎ-ደግፎም መያዙን እንዲያቋርጥ ለእግዚአብሔር የቀረበ ጸሎትና ልመና ነው።

118፥26 *በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ፤* ጠላትን በእግዚአብሔር ርዳታ "በእግዚአብሔር ስም" (ቍ10-12 ይመ) ያሸነፈን ሰው የሚያመለክት ነው። ከእግዚአብሔር ቤት ከእዚያው ከእግዚአብሔር ፊት ማለት ነው (134፥3 ይመ)። *ባረክናችሁ፤* አማራጭ ትርጕሙን ይመ። ቃሉ በብዙ ቍጥር መነገሩ እግዚአብሔር ከሁሉ ነጥሎ የባረከውን የ1ነገ9፥6 አማራጭ ትርጕሙን ይመ። ንጉሥ ከፍ ከፍ አድርጎ ለማሳየት ነው። ወይም ደግሞ ከጦርነቱ ድል በኋላ ከንጉሡ ጋር የተመለሰውን ዘማች ለማመልከት የገባ ቃል ሊሆን ይችላል። ጌታ ኢየሱስ በአህያ ተቀምጦ በድል አድራጊነት ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ ደስታ ፈንቅሎት የተቀበለው ሕዝብ ከቍ25-26 ያለውን፣ቃል ዘምሮታል (ዮሐ12፥13 ይመ)።

118፥27 *ብርሃኑንም በላያችን አበራ፤* ይህ ቃል ካህናት ይሰጡን የነበረውን ቡራኬ የሚያንጸባርቅ ነው (ዘኍ6፥25 ይመ)። *ዝንጣፊ ... እስከ፤* ለምስጋናው ተሰጥዎ ቍንጮ የሆነውን ሐሳብ ለመቋጨት የቀረበ ጥሪ ነው (ዘሌ7፥11-21 ይመ)። ሌሎች ግን ይህን የዳስ በዓል ምስጋና ተሰጥዎ ነው ይሉታል።

*118፥28-29፤* የዚህን መዝሙር መግቢያ ይመ።

*መዝ119፤* በእግዚአብሔር ቃል ምንነት ላይ የተደረገ አስተንትኖ ነው። የመዝሙሩ ጸሐፊ እስራኤላዊ ሲሆን መንፈሳዊነቱም ለሌሎች ምሳሌ የሚሆን ነው፤ ምናልባትም ከባቢሎን ምርኮ በኋላ የነበረ ሰው ሳይሆን እንዳልቀረ ይገመታል፤ ጸሐፊው:- 1) የእግዚአብሔር ቃል የሕይወት ቃል መሆኑን አምኖ ሕይወቱን ለዚሁ ያዋለ ሰው ነው፤ (2) ልቡና ሕይወቱ ከትክክለኛው መንገድ እየሳቱ ወይም እየወጡ እንዴት እንደሚያስቸግሩት ራሱን ሳይደብቅ የተናገረ ሰው ነው፤ (3) ከእግዚአብሔር የመጣበት የእርምትና ተግሣጹ የሚያም ቢሆንም ጣፋጭ መሆኑንም የተረዳ ሰው ነው፤ (4) እንዲሁም የእግዚአብሔርን ቃል በናቁና ባቃለሉ ሰዎች እጅ መከራን የተቀበለና የጥላቻቸው፣ የንቀታቸውና የሁሜታቸው ዒላማም የሆነ ሰው ነው። ይህ ሰው ምናልባት ካህን ሳይሆን አይቀርም (የቍ23፡57 ማብ ይመ)፤ መዝሙሩም የተጻፈው እንደ እግዚአብሔር ሰው እንዴት መኖር እንደሚገባ ክህነታዊ መመሪያ ለመስጠት ነው። ጸሐፊው የ19፥7-13 ፍሬ ሐሳብ በሚገባ ያብራራ ሲሆን ይህን ፍሬ ሐሳብ የእግዚአብሔርን ማዳን ከሚማጸኑ ጸሎቶች ጋር አዛምዶአል፤ ስፊ ትዕግሥትን የሚጠይቁና በጥሞናም ሊውጠነጡኑ የሚገባቸውን ሐሳቦች የዕብራይስጡን የፊደል ገበታ መሠረት በማድረግ አዘጋጅቶአል። ይህ መዝሙር በርዝማኔው፣ በቅርጹና በአጻጻፉ (በአቀራረቡ) በዚህ የመዝሙራት መጽሐፍ ውስጥ ከሚገኙ መዝሙሮች ሁሉ ለብቻው የሚቆም ነው። ከሌሎቹ መዝሙሮች ሁሉ ይልቅ ይህ መዝሙር በጽሑፍ መልክ ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን በመጀመሪያ ሲጻፍ ለዜማና ለቃል ጥናት ሳይሆን ለንባብ ብቻ የተዘጋጀ መዝሙር ነው። መዝሙሩ ከያዛቸው ስንኞች (መስመሮች) ብዙዎቹ ወደ እግዚአብሔር የሚጣሩ ሲሆን ጸሎትና ለእግዚአብሔር ሕግ መገዛት የሚገባ መሆኑን ከሚገልጹ ሐሳቦች ጋር እያዛመዱ አቅርበዋል። ይህም ብቻ አይደለም፤ የእያንዳንዱ ክፍል የመጀመሪያ ቍጥር በግልጽ እንደሚያሳየው መዝሙሩ የተዘጋጀው መንፈሳዊ ወይም የእግዚአብሔር ሰው መሆን የተገባ መሆኑን ለማስተማር ነው (ልክ እንደ መዝ1 ማለት ነው፤ ቍ9 እና ማብ ይመ)። ይህ መዝሙር በዚህ መዝሙራት መጽሐፍ ውስጥ የገባውም መንፈሳዊነትን በአርአያነት ለማሳየት ስለ መሆኑ ምንም አያጠራጥርም። በዚህ የመዝሙራት መጽሐፍ ውስጥ በሚገኙት ሌሎች መዝሙሮች ላይ ትልቅ አጽንዖት የተሰጠው ፍሬ ሐሳብ እግዚአብሔር በፍጥረት ላይ ስላሳየው ታላቅ ሥራው፣ ስለ ማዳኑና በዓለምም ላይ ስላሰፈነው አገዛዙ ሲሆን በዚህ ቦታ ግን አጽንዖት የተሰጠው ፍሬ ሐሳብ ለእግዚአብሔር ቃል (እንዲሁም ለቃሉ አምላክ) ራስን ስለመስጠት ነው። የመዝሙሩ ጸሐፊ የእግዚአብሔር ቃል ሁለት ገጽታዎች እንዳሉት ይናገራል፤ (1) እግዚአብሔር ለሕይወት መመሪያ ይሆን ዘንድ የሰጠው ቃል ነው፤ (2) እግዚአብሔር ለሕይወት ተስፋ ይሆን ዘንድ የሰጠው ቃል ነው፤ የመጀመሪያው ለእግዚአብሔር ቃል መታዘዝ አስፈላጊ መሆኑን ጥሪ የሚያቀርብ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የእምነትን አስፈላጊነት አስመልክቶ ጥሪ ያቀርባል፤ (እነዚህ ሁለት ነገሮች የእውነተኛ መንፈሳዊ ሰው መለያዎች ናቸው 34፥8-14

በእግዚአብሔርም ሕግ የሚሄዱ የተባረኩ
ናቸው::
2 ምስክርነቱን የሚጠብቁ፣
በፍጹምም ልብ የሚሹት የተባረኩ
ናቸው፤
3 ዐመፅን አያደርጉም፤
ነገር ግን በመንገዱ ይሄዳሉ::
4 ጠንቅቀን እንጠብቃት ዘንድ፣
አንተ ሥርዐትን አዘሃል::
5 ሥርዐትህን እጠብቅ ዘንድ፣
ምነው መንገዴ ጽኑ በሆነልኝ ኖሮ!
6 ወደ ትእዛዛትህ ስመለከት፣
በዚያን ጊዜ አላፍርም::
7 የጽድቅ ፍርድህን ስማር፣
በቅን ልብ ምስጋና አቀርብልሃለሁ::
8 ሥርዐትህን እጠብቃለሁ፤
ፈጽመህ አትተወኝ::

ጋ ቤት

9 ጕልማሳ መንገዱን እንዴት ያነጻል?
በቃልህ መሠረት በመኖር ነው::
10 በሙሉ ልቤ ፈለግሁህ፤
ከትእዛዛትህ ፈቀቅ እንዳልል አድርገኝ::
11 አንተን እንዳልበድል፣
ቃልህን በልቤ ሰወርሁ::
12 እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ቡሩክ ነህ፤
ሥርዐትህን አስተምረኝ::
13 ከአንደበትህ የሚወጣውን ደንብ ሁሉ፣
በከንፈሬ እናገራለሁ::

119፥2 ቍ146፤ ዘዳ10፥12፤መዝ40፥16፤99፥7፤112፥1፤ 1ዜና16፥11፤መዝ40፥16፤99፥7፤112፥1፤ኢሳ 56፥2
119፥3 መዝ59፥41 128፥1፤ኤር6፥16፤7፥23፤1ዮሐ3፥9፤5፥18
119፥4 ቍ56፤ዘዳ 6፥17፤መዝ103፥18
119፥5 ዘሌ19፥37
119፥6 ቍ46:80: 117
119፥7 ዘዳ4፥8
119፥8 መዝ38፥21
119፥9 ቍ65:169 ፤መዝ39፥1
119፥10ቍ21:118 ፤መዝ9፥1
119፥11 ቍ133: 165፤ዘዳ6፥6፤ኢዮ 22፥22፤መዝ18፥22-23፤19፥13፤ምሳ3፥23፤ኢሳ 63፥13 119፥12 ዘፀ18፥20፤መዝ28፥6፤143፥8:10
119፥13 ቍ72

እና ማብ ይመ):: እነዚህንም በተመለከተ ከብሉይ ኪዳን ትውፊት ያገኛቸውን ስምንት የዕብራይስጥ ቃላት (መጠሪያ ስሞች) በመጠቀም ገልጾአቸዋል፤ እነዚህም:- "ቶራ"፣ ሕግ፤ "ኤዱት"፣ ሥርዐት፤ "ፒቁዲም"፣ ድንጋጌ፤ "ሚስዎት"፣ ትእዛዝ (ትእዛዛት)፤ "ሚሽፓቲም"፣ ሕግጋት (እነዚህ ሁሉ የመዝ19፥7-9 ይዘት የሚጋሩ ናቸው:: ሚሽፓቲም "ሕጎች" ተብሉ በ19፥9 ላይ ተተርጕሞአል)፤ ሁቂም፣ "ውሣኔዎች" (ዐዋጆች)፤ ዳባር፣ "ቃል" (ዐልፎ ዐልፎ "ሕግ" በሚል፣ አንዳንድ ጊዜም ተስፋ በሚል ትርጕም ገብቶአል)፤ ኢምራህ፣ "ቃል" ብዙ ጊዜ ግን "ተስፋ" የሚል ትርጕም ይዞ ገብቶአል:: እነዚህንም ቃሎች (መጠሪያ ስሞች) በ22 አንጓዎች ወይም ክፍሎች ዘርዝሮ አቸዋል (በሄ፤ በዋው፤ በሔት፤ በዮድ፤ በካፍ፤ በፔ ስምንት ቍጥሮች እንዲኖራቸው ሲያደርግ ሌሎች ግን ከስድስት ያላነሱ ቍጥሮች እንዲኖራቸው አድርጓል):: መዝሙሩ የዕብራይስጡን የፊደል ገበታ ተከትሎ የተዋቀረ መሆኑን በግልፅ ከማስተዋል በቀር ስለ መዝሙሩ ምንም ነገር መናገር አይቻልም:: የሆነ ሆኖ ግን አንድ ነገር መታወቅ አለበት፤ ይኸውም የመጀመሪያዎቹ ሦስት ቍጥሮችና የመጨረሻዎቹ ሦስት ቍጥሮች ለሁሉም እንደ መቅድምና እንደ መደምደሚያ ሆነው የተዘጋጁ መሆናቸው ነው:: የመግቢያዎቹ ቍጥሮች እግዚአብሔርን በመፍራት (በፈሪሀ እግዚአብሔር) ጥበብ መታነጹን የሚያስተጋቡ መመሪያዎች ሲሆኑ፣ የመጨረሻዎቹ ቍጥሮች ግን የመዝሙሩን ፍሬ ሐሳብ ባጭሩ ቍልጭ አድርገው ያሳያሉ:: እንዲሁም የዚህ መዝሙር አማካይ ሁለተኛው ክፍል በዚሁ ተመሳሳይ በሆነ መንገድ ሦስት ቍጥር ባለው መግቢያ የሚጀምር መሆኑን ማስተዋል ይገባል (የቍ89-91 ማብ ይመ)::

*119፥1-31* ጠቅላላ መግቢያ ነው::

119፥1-2 *የተባረኩ፤* የ1፥1 ማብ ይመ::

119፥1 *መንገዳቸው ነቀፋ የሌለበት፤* ይህ ጠቅላላ የመግቢያ ገለጻ ወደፊት እንደምናገኘው በሌሎቹም መግቢያዎች እንደ ዚሁ "በመንገዱ ይሄዳሉ" በሚል አጠቃላይ ገለጻ ይደመድማል (ቍ3)፤ እንዲሁም ዘፍ17፥1 ይመ:: ከዘፍ26፥5 ጋር ያነጻጽሩ:: *ሕግ፤* በዕብራይስጡ አገባብ ቶራ ማለት ነው፤ ይህም ሕዝቡ እንዲመራበት፣ እንዲተዳደርበት ከእግዚአብሔር የተሰጠው ቃል ኪዳን መጠሪያ ነው (ዘዳ4፥44 ይመ):: "ሕግ" የሚለው ቃል አብዛኛውን ጊዜ በተለይ ደግሞ፣ በኋለኞች ዘመናት አምስቱ ብሔረ አሪት (አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት) የሚጠሩበት ስም ነው (ሉቃ 24፥44 ይመ) እንዲያውም የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ባጠቃላይ ቶራ ተብለው የተጠሩበትም ጊዜ አለ (ዮሐ15፥25፤ 1ቆሮ 14፥21 ይመ)፤ በዚህ ቦታ ግን ከሌሎች ቃላት ጋር ተመሳሳይ ፍቺ በመያዝ የተወሰነ አጠቃቀም ብቻ እንዲኖረው ተደርጓአል::

119፥2 *ምሥክርነቱን፤* በዕብራይስጡ ኤዱት የተባለው ሲሆን ከቃል ኪዳን ጋር የተያያዘ ቃል ነው፤ ይህ ቃል የቃል ኪዳኑ አምላክ የሰጠውን መመሪያ የሚያመለክት ነው ("ግዳጅ" 25፥10 ይመ፤ "ድንጋጌዎች" ዘዳ4፥45):: *ልባቸው፤* ቍ7 ይመ፣ እንዲሁም 94፥7 ማብ ይመ::

119፥3 *በመንገዱ፤* ይህ ቃል በዚህ በመጽሐፍ መዝሙራት ውስጥ ተጽፎ የሚገኘው በጥቂት ቦታዎች ላይ ብቻ ሲሆን በዘዳግምና በሌሎች ቦታዎች ግን የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን የሚጠይቀውን ግዴታ የሚያሳይ ቃል ነው (የ25፥4 ማብ ይመ)፤ ቃሉ እዚህ ላይ የገባው በቍ1 ላይ የተጠቀሰውን ቃል ሚዛን ለመጠበቅ ነው::

119፥4-8 የእግዚአብሔርን ሕግ (ቃል) የሚታዘዙ (ቍ4-5:8 ይመ)የእግዚአብሔርን ርዳታ ተስፋ ማድረግ ይችላሉ (ቍ6-8 ይመ)::

119፥4 *ሥርዐትን፤* በዕብራይስጡ ፒቁዲም ማለት ሲሆን፣ በእግዚአብሔር የተሰጠ የቃል ኪዳን ሕግ ማለት ነው (19፥8፤ 111፥7 ይመ)::

119፥5 *ሥርዐትህን፤* በዕብራይስጡ ሁቂም ማለት ሲሆን፣ በቃል ኪዳኑ መሠረት የተሰጠ ማለት ነው (ዘዳ6፥2፤ 28፥15:45፤ 30፥10:16፤ 1ነገ11፥11 ይመ)::

119፥6 *አላፍርም፤* መዝሙረኛው በጠላቶቹ ምክንያት ድኽነት፣ ሕመም፣ ወይም ውርደት ደርሶበታል፤ ከዚህም የተነሣ ማላገጫ ሆኖአል (ቍ31:46:80፤ 25፥2-3:20 ይመ)፤ እግዚአብሔርን ለማመስገን ግን በቂ ምክንያት አለው፤ (ቍ7 ይመ) ይኸውም እግዚአብሔር በጠላቶቹ እጅ አበሳውን እንዲያይ አልተወውም፤ ይልቁንም ባረከው፣ ከጠላቶቹም ታደገው (ቍ8 ይመ):: *ስመለከት፤* ከፍተኛ ግምት ወይም/ዋጋ መስጠት ማለት ነው (ቍ15፤ 74፥20 ይመ):: *ትእዛዛትህ፤* በዕብራይስጡ "ሚስዎት" ማለት ሲሆን፣ በቃል ኪዳኑ መሠረት የተሰጠ መመሪያ ማለት ነው (ዘፀ20፥6፤ 24፥12፤ ዘዳ4፥2 ይመ)፤ ይህም እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት በትክክል መፈጸም ያለበት ትእዛዝ ነው::

119፥7 *የጽድቅ፤* መዝሙረኛው የእግዚአብሔርን ሕግ ባሕርይ የሚገልጽበት በጣም የሚወደው ቃል ነው (ቍ62:75:106: 123:138:144:160:164:172 ይመ:: እንዲሁም 19፥9 ይመ):: *ሕጎች፤* በዕብራይስጥ "ሚሽፓቲም" ማለት ሲሆን፣ በቃል ኪዳኑ መሠረት የተሰጠ መመሪያ ማለት ነው (ዘፀ21፥1፤ 24፥3፤ ዘፀ4፥1 ይመ)፤ ይህም በአንድ ገዥ (ወይም በአንድ ንጉሥ) እንደ ተሰጠ መመሪያ ዐይነት ነው::

119፥8 *አትተወኝ፤* ለድኽነት ወይም ለሕመም ወይም ለጠላቶቼ አሳልፈህ አትስጠኝ ማለቱ ነው::

119፥9 *ጕልማሳ፤* አንዳንድ ሰዎች ይህ ቃል የሚያመለክተው ጸሐፊውን ራሱን ነው የሚል አስተያየት አላቸው፤ ይበልጥ የሚመስለው ግን ጕልማሳ፣ ጥበብን የሚያስተምሩ መምህራን የሚኖሩትን ዐይነት ሕይወት እንዲኖር የሚያሳስብ መመሪያ ነው (34፥11፤ ምሳ1፥4፤ መክ11፥9፤ 12፥1 ይመ):: *ያነጻል?* ከምግባቸውም የሥነ ምግባር ጕድለት የጸዳ ማለት ነው (73፥13 ይመ):: *በቃልህ፤* በዕብራይስጡ ዳባር ሲሆን፣ ይህም ባጠቃላይ የእግዚአብሔርን (ቃል) መገለጥ የሚያሳይ ቃል ነው፤ በዚህ ቦታ ግን በተለየ መንገድ ሕጉን (አንዳንድ ጊዜም ተስፋዎቹን) የሚያመለክት ቃል ነው::

119፥10 *ፈለግሁህ፤* ጸሐፊው ሕይወቱን ሙሉ በሙሉ የሰጠው የሕግና የተስፋ አምላክ ለሆነው ጌታ ነው፤ ለእርሱ የተለየ ትርጕም የሚሰጡት እነዚህ ብቻ ናቸው፤ ምክንያቱም ሕጉና ተስፋው የእግዚአብሔር የሕይወት ቃሎች ናቸውና:: *ልቤ፤* ቍ11 ይመ፤ እንዲሁም የ4፥7 ማብ ይመ::

119፥11 *ቃልህን፤* በዕብራይስጡ ኢምራህ ሲሆን ይህም ከዳባር ጋር ተመሳሳይ ቃል ነው ("ቃል" የቍ9 ማብ ይመ፤ እንዲሁም ዘዳ33፥9፤ ምሳ30፥5 ይመ):: በሌላ ቦታ በግልጽ ካልተጠቀሰ በቀር በዚህም ቦታ ሆነ በዚህ በመዝሙራት መጽሐፍ ውስጥ "ቃል" ሲገባ ዳባር ማለት ነው፤ ኢምራህ አብዛኛውን ጊዜ "ተስፋ" ተብሉ ተመስሉአል (ተተርጕሞአል)::

119፥13 *እናገራለሁ፤* በአስተንትኖ ወይም በተሰጥዖ መልክ ራሴን ለቃል ኪዳኑ እያስገዛሁ ለእግዚአብሔር በተገባ ብፅዐት መሠረት ዐውጃለሁ ማለት ነው (50፥16 ይመ)::

14ሰው በሀብቱ ብዛት ደስ እንደሚለው፣
ምስክርነትህን በመከተል ደስ ይለኛል።
15ድንጋጌህን አሰላስላለሁ፤
ልቤን በመንገድህ ላይ ጥያለሁ።
16በሥርዐትህ ደስ ይለኛል፤
ቃልህንም አልዘነጋም።

ገ ጋሜል

17ሕያው እንድሆን፣ ቃልህንም እንድጠብቅ፣
ለአገልጋይህ መልካም አድርግ።
18ከሕግህ ድንቅ ነገርን እንዳይ፣
ዐይኖቼን ክፈት።
19እኔ በምድር ላይ መጻተኛ ነኝ፤
ትእዛዛትህን ከእኔ አትሰውር።
20ዘወትር ደንብህን በመናፈቅ፣
ነፍሴ እጅግ ዛለች።
21ከትእዛዛትህ የሳቱትን፣
እብሪተኞችንና ርጉሞችን ትገሥጻለህ።
22ምስክርነትህን ጠብቄአለሁና፣
ስድብንና ንቀትን ከእኔ አርቅ።
23ገዦች ተቀምጠው ቢዶልቱብኝ እንኳ፣
አገልጋይህ ሥርዐትህን ያሰላስላል።
24ምስክርነትህ ለእኔ ደስታዬ ነው፤
መካሪዬም ነው።

ደ ዳሌጥ

25ነፍሴ ከዐፈር ጋር ተጣበቀች፤
እንደ ቃልህ መልሰህ ሕያው አድርገኝ።

26ስለ መንገዴ ገልጬ ነገርሁህ፤ አንተም
መለስህልኝ፤
ሥርዐትህን አስተምረኝ።
27የድንጋጌህን መንገድ እንዳስተውል
አድርገኝ፤
እኔም ድንቅ ሥራህን አሰላስላለሁ።
28ነፍሴ በሐዘን ተዝለፈለፈች፤
እንደ ቃልህ አበርታኝ።
29የሽንገላን መንገድ ከእኔ አርቅ፤
ሕግህን በጸጋህ ስጠኝ።
30የእውነትን መንገድ መርጫለሁ፤
ሕግህንም ፊት ለፊቴ አድርጌአለሁ።
31እግዚአብሔር ሆይ፤ ከምስክርነትህ ጋር
ተጣብቄአለሁ፤
አሳልፈህ ለውርደት አትስጠኝ።
32ልቤን አስፍተህልኛልና፣
በትእዛዛትህ መንገድ እሮጣለሁ።

ሀ ሄ

33እግዚአብሔር ሆይ፤ የሥርዐትህን መንገድ
አስተምረኝ፤
እኔም እስከ መጨረሻው እጠብቀዋለሁ።
34ሕግህን እንድጠብቅ፣ በፍጹም ልቤም
እንድታዘዘው፣
ማስተዋልን ስጠኝ።
35በእርሷ ደስ ይለኛልና፣

119፥14 ቍ111 119፥15 ቍ97፡ 148፤መዝ1፥2 119፥16 መዝ112፥1 119፥17 ቍ67፤መዝ 13፥6፤103፥20፤ 116፥7 119፥19 ዘፍ23፥4፤ ዕብ11፥13 119፥20 ቍ131፤ መዝ42፥2፤63፥1፤ 84፥2፤ኢሳ26፥9 119፥21 ቍ10፡51 ፤ዘዳ27፥26፤ኢዮ30፥1 ፤መዝ5፥5፤ኤር20፥7 ፤50፥32፤ዳን4፥37፤ ሚል3፥15 119፥22 ቍ2፤መዝ 39፥8 119፥25 ቍ9፡50፡ 107፤መዝ44፥25፤ 143፥11 119፥26 መዝ25፥4 ፤27፥11፤86፥11 119፥27 መዝ105፥2 ፤145፥5 119፥28 ቍ9፤መዝ 6፥7፤18፥1፤116፥3፤ ኢሳ40፥29፤41፥10፤ 51፥11፤ኤር45፥3 119፥29 ዘኍ6፥25፤ መዝ26፥4 119፥30 ኢሱ24፥22 ፤መዝ26፥3፤108፥1 119፥31 ዘዳ10፥20 119፥33 ቍ12

119፥34 ቍ27፡69፡73፡144፡169፤ዘዳ6፥25፤ኢዮ32፥8፤ምሳ2፥6፤ ዳን2፥21፤ያዕ1፥5 119፥35 ቍ32፤መዝ1፥2፤25፥4-5

119፥14 *ሰው በሀብቱ ... ደስ እንደሚለው፤* ቍ72፡ 111፡162 ይመ።

119፥15 *በመንገድህ፤* ይህ ቃል በዕብራይስጡ ቍ3 ላይ መንገዶችህ ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው (እነዚህ ሁለት የዕብራይስጥ ቃላት በ25፥4 ላይ፣ ፊት ለፊት ወይም ጐን ለጐን ተነጻጽረው ቀርበዋል)።

*119፥17-24፤* ለእግዚአብሔር ሕግ የሚታዘዙ የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆናቸውን ያሳያል፤ ይህም ከዓለም እብሪተኞች ጋር አንድነት የሌላቸው መሆኑን ያረጋግጣል (ቍ21)።

119፥17 *ቃልህንም እንድጠብቅ፤* ከእግዚአብሔር ጥበቃና በረከት የተነሣ፣ የእርሱን ቃል እታዘዛለሁ ማለቱ ነው።

119፥18 *ድንቅ ነገርን፤* ይህ ሐረግ አብዛኛውን ጊዜ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ ነው (9፥1 እና ማብ ይመ)፤ ይሁን እንጂ የእግዚአብሔርም ሕግ ራሱ ድንቅ ነገሮችን በውስጡ ይዞአል (ቍ27 ይመ)።

119፥19 *እኔ በምድር ላይ መጻተኛ ነኝ፤* የእግዚአብሔር አገልጋይ ማለትም የመንግሥቱ ወራሽ በመሆኑ፣ የትኛውም ምድራዊ መንግሥት ዜጋ አይደለም (39፥12እና ማብ ይመ፤ እንዲሁም የቍ54 ማብ ይመ)።

119፥20 *ነፍሴ ...፤* እኔ ራሴ ማለት ነው (ቍ28፡81 ይመ። እንዲሁም የ6፥3 ማብ ይመ)።

119፥21 *እብሪተኞችንና፤* የራሳቸው ሕግ እነርሱ ራሳቸው መሆናቸውን የሚናገሩ ሲሆን እንዲሁም በ10፥2-11 ላይ በዝርዝር ተነግሮአል (ቍ51፡69፡78፡85፡122 ይመ፤ እንዲሁም የ31፥23 ማብ ይመ)። የሚቀጥሉት ሁለት ቍጥሮችና ሌሎችም በርካታ ቍጥሮች እንደሚያሳዩት መዝሙረኛው ለእግዚአብሔርና ለሕጉም ካለው ቅናት የተነሣ በጠላቶቹ እጅ አያሌ መከራን ተቀብሎአል። *ርጉሞችን፤* የእግዚአብሔር ፍርድ በላያቸው ሊገለጥ የተቃረቡ ማለት ነው።

119፥22 *ስድብንና ንቀትን፤* በእብሪተኞች ማለት ነው።

119፥23 *ገዦች፤* መዝሙረኛው "በነገሥታት ፊት" (ቍ46) የሚል ነገር በመናገሩና "ገዦች" የሚያሳድዱት (ቍ161) መሆኑን በመግለጹ የኀላፊነት ቦታ የተሰጠው ካህን ሳይሆን አይቀርም (ከካህንም ተግባሮች አንዱ የእግዚአብሔርን ሕግ ማስተማር እንደ ነበር ይታወቃል፤ ዘሌ10፥11፤ ዕዝ7፥6፤ ነህ8፥2-8፤ ኤር 2፥8፤ 18፥18፤ ሚል2፥7 ይመ። እንዲሁም የቍ57 ማብ ይመ)። (እነዚህ ነገሥታትና ገዦች ምናልባት ከነገሥታቱ ዘመን ጀምሮ የነበሩ የእስራኤል ነገሥታት ወይም ከምርኮ በኋላ የነበሩ የፋርስ ነገሥታት ሳይሆኑ አይቀሩም)። *ተቀምጠው፤* በዚህች ዓለም ተደላድለው እንደ ተቀመጡ ማለት ነው፤ ይህ ግን መጻተኞችን አይመለከትም (ከቍ19 ጋር ያነጻጽሩ)። *ቢዶልቱብኝም፤* ዓለማዊ አስተሳሰባቸ ውን በጋራ በሚመካከሩበት ሰዓት ከእነርሱ ጋር በሐሳብ የማይተባበረውን ያንቋሽሹታል፤ ያናንቁታልም፤ ይህም የሚሆንበት ምክንያት እርሱ በእግዚአብሔር ሥርዐቶች ደስ ስለ ሚሰኝና እነዚህንም ሥርዐቶች መካሮቹ ስላደረጋቸው ነው (ቍ24)።

*119፥25-32፤* "ዝቅ ዝቅ ብል" (ቍ25) ወይም "ነጻ ብወጣ" (ቍ32) የእግዚአብሔርን ቃል የሙጥኝ ለማለት ወስኖ አል (ቍ31)።

119፥25 *ወድቄአለሁ፤* መዝሙረኛው ስለደረሰበት ሐዘን፣ መከራና ሥቃይ ብዙ ይናገራል (ቍ28፡50፡67፡71፡75፡83፡92፡107፡ 143፡153፡ ይመ) የእግዚአብሔርን ቃል (ሕጉንና ተስፋውን ማለት ነው) የሕይወቱ ተስፋ በማድረጉ ጠላቶቹ ሲያንቋሽሹት፣ ሲያሙትና ሲያሳድዱት ይታያል (42፡51፡65፡69፡78፡85፡95፡110፡134፡ 141፡150፡154፡157፡161 ይመ። እንዲሁም የቍ6፤ 5፥9፤ 31፥11-12 ማብ ይመ)። *ከዐፈር፤* 44፥25 እና ማብ ይመ። *ቃልህ፤* በተለይ ተስፋውን ማለት ነው፤ ይህም በቍ28፡37፡42፡49፡65፡74፡81፡ 107፡114፡147፡ እንደ ተጻፈው ማለት ነው።

119፥27 *ድንቅ ሥራዎችህን፤* የቍ18 ማብ ይመ።

119፥29 *የሽንገላን መንገድ፤* ትክክልና ቀና መስሎ የሚታይ፣ ነገር ግን ወደ ሞት የሚመራ መንገድ ነው (ምሳ14፥12 ይመ)፤ ይህም መንገድ ታማኝ ከሆነውና (ቍ86፡138 ይመ) እውነትም ከሆነው (ቍ142፡151፡160 ይመ) ከእግዚአብሔር ሕግ ጋር ተቃራኒ ነው። *ሕግህን፤* ለትእዛዝህ ራሴን በታማኝነት ያስገዛሁ በመሆኔ በረከትህን እንዳገኝ ርዳኝ።

119፥30 *የእውነትን መንገድ፤* የቍ29 ማብ ይመ።

119፥31 *አሳልፈህ ... አትስጠኝ፤* የቍ6 ማብ ይመ።

119፥32 *ልቤን አስፍተህልኛልና፤* ቃል በቃል ሲተረጐም "ልቤን ነጻ አድርገኸዋልና" ማለት ነው፤ ይህም በደስታ አሰፋኸው ማለት ነው (ኢሳ60፥5 "በደስታ ያብጣል" ይመ)። ሌሎች ደግሞ "ማስተዋልን ጨመርኸልኝ" በማለት ተርጕመውታል (1ነገ 4፥29፣ "የማስተዋል ብዛት/ስፋት")። *ልቤን፤* የ4፥7 ማብ ይመ።

*119፥33-40፤* ሥርዐቱን በሚናፍቅበት ጊዜ እግዚአብሔር ፈቃዱን እንዲያስታውቀው ያቀረበው ጸሎት ነው።

119፥34 ... *ልቤም፤* ቍ36 ይመ፤ እንዲሁም የ4፥7 ማብ ይመ።

በትእዛዝህ መንገድ ምራኝ።
36ከራስ ጥቅም ይልቅ፥
ልቤን ወደ ምስክርነትህ አዘንብል።
37ከንቱ ነገር ከማየት ዐይኖቼን መልስ፤
በራስህ መንገድ[*] እንደ ገና ሕያው
አድርገኝ።
38ትፈራ ዘንድ፥
ለአገልጋይህ የገባኸውን ቃል ፈጽም።
39የምፈራውን መዋረድ ከእኔ አርቅ፤
ደንብህ መልካም ነውና።
40እነሆ፤ ድንጋጌህን ናፈቅሁ፤
በጽድቅህ ሕያው አድርገኝ።

*ו ዋው*

41*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ምሕረትህ ወደ እኔ
ይምጣ፤
ማዳንህም እንደ ቃልህ ይላክልኝ።
42በቃልህ ታምኛለሁና፥
ለሚሰድቡኝ መልስ እሰጣለሁ።
43ሕግህን ተስፋ አድርጌአለሁና፥
የእውነትን ቃል ከአፌ ፈጽመህ አታርቅ።
44ከዘላለም እስከ ዘላለም፥
ሕግህን ዘወትር እጠብቃለሁ።
45ሥርዐትህን እሻለሁና፥
እንደ ልቤ ወዲያ ወዲህ እመላለሳለሁ።
46ምስክርነትህን በነገሥታት ፊት እናገራለሁ፤
ይህን በማድረግም ዕፍረት አይሰማኝም።
47እኔ እወድዋለሁና፥
በትእዛዝህ ደስ ይለኛል።
48እጆቼን ወደምወዳቸው[°] ትእዛዛትህ
አነሣለሁ፤
ሥርዐትህንም አሰላስላለሁ።

*ז ዛይ*

49ለአገልጋይህ የገባኸውን ቃል አስብ፤
በዚያ ተስፋ ሰጥተኸኛልና።
50ቃልህ ሕያው ያደርገኛልና፥
ይህች በመከራዬ መጽናኛዬ ናት።
51እብሪተኞች እጅግ ተሣለቁብኝ፤
እኔ ግን ከሕግህ ንቅንቅ አላልሁም።
52*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ከጥንት የነበረውን
ድንጋጌህን አሰብሁ፤
በዚህም ተጽናናሁ።
53ሕግህን ከተዉ ክፉዎች የተነሣ፥
ቍጣ ወረረኝ።
54በእንግድነቴ አገር፥
ሥርዐትህ መዝሙሬ ናት።
55*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ስምህን በሌሊት
አስባለሁ፤
ሕግህንም እጠብቃለሁ።
56ሥርዐትህን እከተላለሁ፤
ይህችም ተግባሬ ሆነች።

*ח ሔት*

57*እግዚአብሔር* ዕድል ፈንታዬ ነው፤
ቃልህን ለመታዘዝ ቈርጫለሁ።
58በፍጹም ልቤ ፊትህን ፈለግሁ፤
እንደ ቃልህ ቸርነትህን አሳየኝ።
59መንገዴን ቃኘሁ፤
አካሄዴንም ወደ ምስክርህ አቀናሁ።
60ትእዛዝህን ለመጠበቅ፥
ቸኰልሁ፤ አልዘገየሁም።
61የክፉዎች ገመድ ተተበተበብኝ፤
እኔ ግን ሕግህን አልረሳሁም።

119፥36 ኢሱ24፥23፤ሕዝ33፥31
119፥37 ቍ9:25፤ መዝ71፥20
119፥38 ዘኍ23፥19
119፥39 ቍ22፤መዝ 69፥9፤89፥51፤ኢሳ 25፥8፤51፥7፤54፥4
119፥40 ቍ20:25: 149:154
119፥41 ቍ76:116 :154:170፤መዝ6፥4
119፥42 መዝ42፥10 ፤ምሳ27፥11
119፥43 ቍ74:81 :114:147፤ኑኀ17፥24
119፥44 ቍ33:34 :55፤ዘዳ6፥25
115፥45 ቍ94:155
119፥46 ቍ6፤ማቴ 10፥18፤ሐሥ26፥1-2
119፥47 ቍ77:97: 127:143:159:163:1 65፤መዝ112፥1
119፥48 ዘፍ24፥63
119፥49 ቍ9:43
119፥50 ቍ25
119፥51 ቍ21፤ ኢዮ 16፥10፤17፥2፤ 23፥11
119፥52 መዝ103፥ 18
119፥53 ዘፀ32፥19፤ 33፥4፤መዝ89፥30
119፥54 ቍ172፤ መዝ101፥1፤138፥5
119፥55 ቍ44:62: 72፤መዝ1፥2፤42፥8፤ 63፥6፤77፥2፤ኢሳ 26፥9፤ሐሥ16፥25
119፥56 ቍ4:100: 134:168፤ዘኍ15፥40
119፥57 ቍ17:67: 101፤ዘዳ32፥9፤ኤር 51፥19፤ሰቆ3፥24
119፥58 ቍ41፤ዘፍ 43፥29፤ዘዳ4፥29፤1ዜና16፥11፤ዕዝ9፥8፤ መዝ34፥4 119፥59 ኢሱ24፥14-15፤መዝ39፥1 119፥60 ቍ115
119፥61 ቍ83: 109:153:176

*37 አንዳንድ ትርጕሞች *እንደ ቃልህ* ይላሉ።
°48 ወይም *ለምወዳቸው*

119፥36-37 *ልቤን ... ዐይኖቼ፤* 101፥2ለ-3ሀ እና ማብ ይመ።

119፥38 *ትፈራ ዘንድ፤* በሰጠው ተስፋ መሠረት የማዳን ሥራውን በመፈጸሙ እርሱ እውነተኛ አምላክ መሆኑን አረጋግጦ አል (130፥4፤ 2ሳሙ 7፥25-26፤ 1ነገ 8፥39-40፤ ኤር 33፥8-9 ይመ)።

119፥39 *የምፈራውን መዋረድ፤* የቍ6:25 ማብ ይመ።

119፥40 *በጽድቅህ፤* የ4፥1 ማብ ይመ።

*119፥41-48፤* እግዚአብሔር ይታደገኝ እውነቱንም ከአንደበቴ አይውሰድብኝ፤ እኔም ሕጉን በሕይወቴ ዘመን ሁሉ አከብራለሁ፤ በነገሥታት ፊት ሕጉን እናገራለሁ፤ ምክንያቱም ትእዛዛቱን አፈቅራለሁና።

119፥41 *ምሕረትህ፤* ቍ64:76:88:124:149:159 ይመ። እንዲሁም የ6፥4 ማብ ይመ።

119፥42 *ለሚሰድቡኝ፤* የቍ25 ማብ ይመ ("ወድቄ አለሁ")። *በቃልህ፤* የቍ25 ማብ ይመ።

119፥43 *የእውነትን ቃል ከአፌ፤* ቍ13 እና ማብ ይመ። እንዲሁም ቍ46 ይመ።

119፥45 *እንደ ልቤ፤* ቃል በቃል ሲተረጐም "ሰፊ ቦታ" ማለት ነው፤ ይህም ማለት በጭንቅና በመከራ ያልተከበበ ማለት ነው (18፥19 እና ማብ ይመ)።

119፥46 *በነገሥታት ፊት፤* እንግዲህ የባለመዝሙሩ ድፍረት እስከዚህ ድረስ ነው (የቍ23 ማብ ይመ)።

119፥48 *እጆቼን ወደ ... አነሣለሁ፤* ምስጋናን የሚያጅብ ድርጊት ነው (በ63፥4፤ በ134፥2 ላይ እንደ ተመለከተው ማለት ነው)፤ ስለዚህ ድርጊቱ "አመሰግንሃለሁ" ማለት ነው።

*119፥49-56፤* በምንም ዐይነት ሁኔታ ውስጥ ብሆን የእግዚአብሔር ቃል መጽናኛዬና መመሪያዬ ነው።

*119፥49፤* ቃል የቍ25 ማብ ይመ።

119፥50-51 *ከመከራዬ ... እብሪተኞች ... ተሳለቁብኝ፤* የቍ25 ማብ ይመ ("ወደቅሁ")።

119፥51 *እብሪተኞች፤* የቍ21 ማብ ይመ።

119፥52 *ከጥንት፤* የእግዚአብሔር ሕግ የሚፍረከረክ አይደለም፤ ነገር ግን ከቶ በማይለወጠው ሥነ ምግባራዊ ባሕርያት ላይ ጸንቶ የተመሠረተ ነው። እንግዲህ ለመዝሙረኛው የመጽናኛና ሕጉንም ከልብ ለመውደድ ምክንያት የሆነው ይህ ነው (ቍ89:144:152: 160 ይመ)።

119፥53 *ቍጣ ወረረኝ፤* ለእግዚአብሔር ሕግ ያለው መንፈሳዊ ቅናት (ቍ136:139 ይመ) ሕጉን በሚቃወሙት ሰዎች ላይ (ቍ113:115:158 ተመ)፥ ጽድቅን የተሞላ ቍጣ ይቀሰቅስባቸዋል፤ ደግሞም ሕጉን በሚቃወሙ ሰዎች ላይ ጥላቻን ያመጣባቸዋል (ቍ104:128:163 ይመ)፤ የሚያከብሩትን ግን ወደ ራሱ ይስባቸዋል (ቍ63 ይመ)።

119፥54 *በእንግድነቴ አገር፤* ቃል በቃል ሲተረጐም "በጊዜያዊ መጠለያዬ" ማለት ነው። የዚህ ቍጥር ሐሳብ ከቍ19 ጋር ተመሳሳይነት አለው (ማብ ይመ)።

119፥55 *ስምህን፤* የ5፥11 ማብ ይመ።

*119፥57-64፤* እግዚአብሔር የመዝሙረኛው እውነተኛ ዕድል ፈንታ ነው፤ ምክንያቱም ሕይወት በምድር ላይ ዋስትና ያላትና ደስተኛም ትሆን ዘንድ የሚያደርጋት የእግዚአብሔር ሕግ ነው። ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ተስፋው ናቸው፤ እንዲሁም የእግዚአብሔር ጻድቅ ሕጎች ደስታው ናቸው።

119፥57 *ዕድል ፈንታዬ፤* መዝሙረኛው ካህን ወይም ሌዋዊ መሆኑን ይጠቍማል (73፥26 እና ማብ ይመ)።

119፥58 *ልቤ፤* የ4፥7 ማብ ይመ።

119፥61 *ገመድ ተተበተበብኝ፤* ቢጨቍኑኝ፥ ቢያሠቃዩኝ ማለት ነው።

[62]ስለ ጻድቅ ሥርዐትህ፣
በእኩለ ሌሊት ላመሰግንህ እነሣለሁ።
[63]እኔ ለሚፈሩህ ሁሉ፣
ሥርዐትህንም ለሚጠብቁ ባልንጀራ ነኝ።
[64]እግዚአብሔር ሆይ፤ ምድር በምሕረትህ
ተሞላች፤
ሥርዐትህን አስተምረኝ።

ሀ ጤት

[65]እግዚአብሔር ሆይ፤ እንደ ቃልህ፣
ለአገልጋይህ በጎ ውለሃል።
[66]በትእዛዛትህ አምናለሁና፣
በጎ ማስተዋልንና ዕውቀትን አስተምረኝ።
[67]እንዲያው ሳይቸግረኝ መንገድ ስቼ
ሄድሁ፤
አሁን ግን ቃልህን እጠብቃለሁ።
[68]አንተ መልካም ነህ፤ የምታደርገው
መልካም ነው፤
እንግዲህ ሥርዐትህን አስተምረኝ።
[69]እብሪተኞች ስሜን በሐሰት አጠፉ፤
እኔ ግን ትእዛዝህን በፍጹም ልብ
እጠብቃለሁ።
[70]ልባቸው የሰባና የደነደነ ነው፤
እኔ ግን በሕግህ ደስ ይለኛል።
[71]ሥርዐትህን እማር ዘንድ፣
በመከራ ውስጥ ማለፌ መልካም ሆነልኝ።
[72]ከአእላፋት ብርና ወርቅ ይልቅ፣
ከአፍህ የሚወጣው ሕግ ይሻለኛል።

' ዮድ

[73]እጆችህ ሠሩኝ፤ አበጃጁኝም፤
ትእዛዛትህን እንድማር ማስተዋልን
ስጠኝ።
[74]ቃልህን ተስፋ አድርጌአለሁና፣
የሚፈሩህ እኔን አይተው ደስ
ይበላቸው።
[75]እግዚአብሔር ሆይ፤ ፍርድህ የጽድቅ
ፍርድ፣
ያስጨነቅኸኝም በታማኝነት እንደ ሆነ
ዐወቅሁ።
[76]ለአገልጋይህ በገባኸው ቃል መሠረት፣
ምሕረትህ ለመጽናናት ትሁነኝ።
[77]ሕግህ ደስታዬ ነውና፣
በሕይወት እኖር ዘንድ ቸርነትህ
ትምጣልኝ።
[78]እብሪተኞች ያለ ምክንያት በደል
አድርሰውብኛልና ይፈሩ፤
እኔ ግን ትእዛዛትህን አሰላስላለሁ።
[79]አንተን የሚፈሩህ፣
ምስክርነትህንም የሚያውቁ ወደ
እኔ ይመለሱ።
[80]እኔ እንዳላፍር፤
ልቤ በሥርዐትህ ፍጹም ይሁን።

ጋ ካፍ

[81]ነፍሴ ማዳንህን እጅግ ናፈቀች፤
ቃልህንም ተስፋ አደርጋለሁ።
[82]"መቼ ታጽናናኛለህ?" እያልሁ፣
ዐይኖቼ ቃልህን በመጠባበቅ ደከሙ።
[83]ጢስ የጠጣ የወይን አቍማዳ ብመስልም፣
ሥርዐትህን አልረሳሁም።
[84]የባሪያህ ዕድሜ ስንት ቢሆን ነው?
ታዲያ፣ በሚያሳድዱኝ ላይ
የምትፈርደው መቼ ይሆን?

119፥62 ቍ7፡55 ፤ሐሥ16፥25
119፥63 ቍ56፤ መዝ15፥4፤101፥6-7 ፤103፥11፤111፥10
119፥64 ቍ12፡108፤መዝ33፥5
119፥65 ቍ9፡17፤ መዝ125፥4፤50፥2፤ 59፥1፤ሚክ2፥7
119፥66 መዝ51፥6
119፥67 ቍ17፤ መዝ95፥10፤116፥10፤ ኤር8፥4
119፥68 ዘፀ18፥20፤ መዝ100፥5፤106፥1፤ 107፥1፤135፥3
119፥69 ኢዮ13፥4፤ መዝ109፥2
119፥70 መዝ17፥10 ኢሳ29፥13፤ሐሥ 28፥27
119፥71 ቍ67፡75
119፥72 ኢዮ28፥17 ፤መዝ19፥10
119፥73 ዘፍ1፥27፤ ኢዮ4፥17፤10፥8፤መዝ 138፥8፤139፥13-16
119፥74 ቍ9፤መዝ 34፥2፤130፥5
119፥75 ቍ7፡138፡ 172፤ዕብ12፥5-11
119፥76 ቍ41፤ መዝ6፥4
119፥77 ቍ47፤ መዝ90፥13፤103፥13
119፥78 ቍ51፡86 ፡161፤መዝ35፥19፤ ኤር50፥32
119፥79 ቍ27፡125
119፥80 ቍ1፡6፤ ዘፍ26፥5፤1ነገ8፥61
119፥81 ቍ20፡43፡ 123፤መዝ84፥2
119፥82 ቍ41፡123፤መዝ6፥7፤69፥3፤ሰቆ2፥11 119፥83 ቍ61
119፥84 ቍ51፤ መዝ6፥3፤ኤር12፥3፤15፥15፤20፥11፤ራእ6፥10

119፥62 *ላመሰግንህ፤* የመዝ100 ርእስ ማብ ይመ። *ጻድቅ፤* የቍ7 ማብ ይመ።

119፥63 *ባልንጀራቸው፤* የቍ53 ማብ ይመ።

119፥65 *በጎ ውለሃል፤* ከቍ68 ጋር ያነጻጽሩ። 31፥19፤ 86፥17 እና ማብ ይመ። *ቃልህ፤* የቍ25 ማብ ይመ።

119፥66 *አምናለሁና፤* ስለምመካ ማለት ነው፤ የእግዚአብሔር ትእዛዞች የሚያታልሉ፣ የሚሸነግሉ አይደሉም (የቍ29 ማብ ይመ)፤ ወይም የሚለዋወጡ አይደሉም (የቍ52 ማብ ይመ)።

119፥67 *ሳይቸግረኝ፤* በእግዚአብሔር እጅ ማለት ነው (ቍ71 ይመ፤ እንዲሁም የቍ25 ማብ ይመ)። *ለቃልህ፤* የቍ11 ማብ ይመ።

119፥69 *እብሪተኞች፤* የቍ21 ማብ ይመ።

119፥70 *የሰባና የደነደነ፤* ቃል በቃል ሲተረ ጐም ድድር ያለ ማለት ነው። ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ የሆነ አገላለጽ በኢሳ 6፥10፤ በኤር5፥28 ላይ ይገኛል (እንዲሁም 17፥10 ይመ)።

119፥72 *ከአእላፋት ብርና ወርቅ ይልቅ፤* ቍ14፡57፡111፡ 162 ይመ።

*119፥73-80፤* እብሪተኞች ያፍሩና አንተን የሚፈሩ ከእኔ ጋር ሐሤት ያደርጉ ዘንድ ጽድቅ የሆኑትን ሕጎችህን እንድጠብቅ ፍጹም አድርገህ ሥራኝ (አበጃጀኝ)፤ የስንኞቹ ማእከላዊ አወቃቀር ተመሳሳይ ነው፤ ከቍ73 እና 80፤74 እና79፤ 75 እና78፤ 76 እና 77 ጋር ያነጻጽሩ።

119፥73 *ማስተዋልን፤* እኔን በሠራህ ጊዜ የጀመርኸውን ሥራ ከፍጻሜ ለማድረስ የሚያስፈልገኝ ይህ ማስተዋል ነው ማለቱ ነው።

119፥74 *የሚፈሩህ፤* ቍ79 ይመ። እንዲሁም የ34፥8-14 ማብ ይመ። *እኔን አይተው፤* ፍጹም ሆኜ በተሠራሁ ጊዜና አንተን ለሚፈሩት የምትሰጠውን በረከት አግኝቼ ደስ በተሰኘሁ ጊዜ ማለት ነው። *ቃልህን፤* የቍ25 ማብ ይመ።

119፥75 *ፍርድህ፤* ቃሉ በዕብራይስጥ ሚሽፓቲም ነው፤ ከዚህ በታች ያሉት ቍጥሮች እንደሚያመለክቱት እግዚአብሔር ከአገልጋዮቹ ጋር ካለው ግንኙነት አንጻር የሚሰጠውን ትክክለኛ ውሳኔ የሚያሳይ ነው (ቍ84 እና ማብ ይመ)። *ያስጨነቅኸኝም፤* ቍ67፡71 ይመ።

119፥76 *ምሕረትህ፤* የ6፥4 ማብ ይመ። *ለመጽናናት፤* በተጨነቅሁ ጊዜ።

119፥77 *በሕይወት እኖር ዘንድ፤* በጭንቅ ውስጥ ሳለሁ እንዳልጠፋ ማለት ነው።

119፥78 *እብሪተኞች፤* የቍ21 ማብ ይመ። *ይፈሩ፤* እኔን ለኀፍረት እንደዳረጉኝ እነርሱም እንዲሁ ይድረስባቸው ማለቱ ነው (የ5፥10 ማብ ይመ)። *በደል አድርሰውብኛልና፤* የቍ25፥10 ማብ ይመ።

119፥79 *ወደ እኔ ይመለሱ፤* ቍ63 እና የቍ53 ማብ ይመ።

119፥80 *ልቤ፤* የ4፥7 ማብ ይመ። *እንዳላፍር፤* የቍ6 ማብ ይመ።

*119፥81-88፤* በሰጠኸኝ ተስፋ መሠረት ከጭንቀቴና ከአሳዳጆቼ አድነኝ፤ እኔም ለሥርዐቶችህ እታዘዛለሁ። የመዝሙሩ የመጀመሪያው አጋማሽ የሆነው ይህ የመጨረሻው አንጓ እንደ መዝሙሩ መደምደሚያ አንጓ ሁሉ የእግዚአብሔርን ርዳታ በሚጠይቅ ጸሎት የተሞላ ነው (የቍ25 ማብ ይመ)።

119፥81 *ነፍሴ፤* የ6፥3 ማብ ይመ።

119፥82 *ዐይኖቼ ደከሙ፤* የ6፥7 ማብ ይመ።

119፥83 *ጢስ የጠጣ የወይን አቍማዳ፤* እሳት ከሚነድበት ምድጃ በላይ ተሰቅሉ ጢስ የጠገበ አቍማዳ ጥቀርሻ እንደሚያደራበት ሁሉ መዝሙረኛውም ይህንኑ የመሰለ አስከፊ ነገር ደርሶበታል።

119፥84 *ዕድሜ ስንት ቢሆን ነው?* ቃል በቃል ሲተረጐም "የባርያህ ዘመኑ ስንት ነው?" የሕይወት ዘመኔ አጭር ስለ ሆነች የአሳዳጆቼን ቅጣት አታዘግይ። *የምትፈርደው፤* ቃል በቃል ሲተረጐም "የፍትህ ውጤት" ማለት ነው ("ፍትህ" ለሚለው ቃል የዕብራይስጡ "ሚሽፋት" ነው፤ በቍ7 ላይ "ሕጎች" ተብሎአል። እንዲሁም የ5፥10 ማብ ይመ)።

85በሕግህ መሠረት የማይሄዱ፣
እብሪተኞች ጕድጓድ ቈፈሩልኝ።
86ትእዛዛትህ ሁሉ አስተማማኝ ናቸው፤
ሰዎች ያለ ምክንያት አሳደውኛልና
ርዳኝ።
87ከምድር ላይ ሊያስወግዱኝ ጥቂት
ቀራቸው፤
እኔ ግን ትእዛዛትህን አልተውሁም።
88እንደ ምሕረትህ መልስህ ሕያው
አድርገኝ፤
እኔም የአፍህን ምስክርነት እጠብቃለሁ።

ኀ ላሜድ

89*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ቃልህ በሰማይ፣
ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።
90ታማኝነትህ ከትውልድ እስከ ትውልድ
ሁሉ ይኖራል፤
ምድርን መሠረትሃት፤ እርሷም ጸንታ
ትኖራለች።
91ሁሉም አገልጋይህ ነውና፣
በሕግህ መሠረት እስከ ዛሬ ድረስ
ጸንተው ይኖራሉ።
92ሕግህ ደስታዬ ባይሆን ኖሮ፣
በመከራዬ ወቅት በጠፋሁ ነበር።
93በእርሱ ሕያው አድርገኸኛልና፣
ትእዛዝህን ከቶ አልረሳም።
94እኔ የአንተ ነኝ፤ እባክህ አድነኝ፤
ሕግህንም ፈልጌአለሁና።
95ክፉዎች ሊያጠፉኝ አድብተዋል፤
እኔ ግን ምስክርነትህን አሰላስላለሁ።
96ለፍጹምነት ሁሉ ዳርቻ እንዳለው አየሁ፤
ትእዛዝህ ግን እጅግ ሰፊ ነው።

ሸ ሜም

97አቤቱ፤ ሕግህን ምንኛ ወደድሁ!
ቀኑን ሙሉ አሰላስለዋለሁ።
98ትእዛዛትህ ምን ጊዜም ስለማይለዩኝ፣
ከጠላቶቼ ይልቅ አስተዋይ አደረጉኝ።
99ምስክርነትህን አሰላስላለሁና፣
ከአስተማሪዎቼ ሁሉ የላቀ አስተዋይ
ልብ አገኘሁ።
100መመሪያህን ተከትዬ እሄዳለሁና፣
ከሽማግሌዎች ይልቅ አስተዋይ ሆንሁ።
101ቃልህን እጠብቅ ዘንድ፣
እግሬን ከክፉ መንገድ ሁሉ ከለከልሁ።
102አንተው ራስህ አስተምረኸኛልና፣
ከድንጋጌህ ዘወር አላልሁም።
103ቃልህ ለምላሴ ምንኛ ጣፋጭ ነው!
ለአፌም ከማር ወለላ ይልቅ ጣዕም
አለው።
104ከመመሪያህ ማስተዋልን አገኘሁ፤
ስለዚህ የሐሰትን መንገድ ሁሉ ጠላሁ።

ነ ኖን

105ሕግህ ለእግሬ መብራት፣
ለመንገዴም ብርሃን ነው።
106የጽድቅ ሕግህን ለመጠበቅ፤
ምያለሁ፤ ይህንኑ አጸናለሁ።
107እጅግ ተቸግሬአለሁ፤
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ እንደ ቃልህ
መልስህ ሕያው አድርገኝ።
108*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ፈቅጄ ያቀረብሁትን
የአፌን የምስጋና መሥዋዕት
ተቀበል፤
ሕግህንም አስተምረኝ።

119፥85 ቍ51፤ መዝ35፥7፤57፥6፤ኤር 18፥20፡22
119፥86 ቍ78፡138 ፤መዝ7፥1፤109፥26
119፥87 ቍ150፤ ኢሳ1፥4፡28፤58፥2፤ 59፥13
119፥88 ቍ2፡100፡ 124፡129፡134፡168፤ መዝ41፥2፤51፥1፤ 109፥26
119፥89 ቍ111፡ 144፤መዝ111፥8፤ኢሳ 51፥6፤ማቴ5፥18፤ 1ጴጥ1፥25
119፥90 ኢዮ8፥19፤ መዝ36፥5፤45፥17፤ 148፥6
119፥91 መዝ104፥ 2-4፤ኤር31፥35፤ 33፥25
119፥92 ቍ50፡67፤ መዝ37፥4፤112፥1
119፥93 ቍ83፤ መዝ103፥5
119፥94 ቍ45፡ 146፤መዝ54፥1፤116፥ 4፤ኤር17፥14፤31፥18 ፤42፥11
119፥95 ቍ99፤ መዝ69፥4
119፥96 መዝ19፥7
119፥97 ቍ15፡47
119፥98 ቍ130፤ ዘዳ4፥6፤መዝ19፥7፤ 2ጢሞ3፥15
119፥99 ቍ15
119፥100 ቍ56፤ ዘዳ6፥17
119፥101 ቍ57፤ ምሳ1፥15
119፥102 ዘዳ4፥5፤ 17፥20
119፥103 መዝ19፥ 10፤ምሳ24፥13-14
119፥104 ቍ128፤ መዝ111፥10
119፥105 ቍ130፤ ምሳ6፥23፤20፥27፤2ጴጥ1፥19
119፥106 ቍ7፤ ነህ10፥29
119፥107 ቍ25
119፥108 ቍ64፤ መዝ51፥15፤63፥5፤71፥8፤109፥30

119፥85 *እብሪተኞች፤* የቍ21 ማብ ይመ። *የማጥመጃ ጕድጓድ ቈፈሩልኝ፤* ምናልባት የደረሰበትን ሐሜት ሳያሳይ አይቀርም፤ መዝሙረኛው ክፉ ኀጢአት ባይሠራ ኖሮ እንዲህ ባለው መከራ ውስጥ አይገባም ነበር በማለት ስሙን በአደባባይ ያጠፉት መሆኑን ሊያመለክት ይችላል። *በሕግህ መሠረት፤* ዘፀ 20፥16 ይመ።

119፥86 *አስተማማኝ፤* በቍ29 ማብ ላይ "በማታለል መንገድ" የሚለውን ይመ።

119፥88 *ምሕረትህ፤* የ6፥4 ማብ ይመ።

*119፥89-91፤* የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት የማይሻረው ቃል ዓለምን ይገዛል፤ በሥርዐትም ይመራዋልም። (እነዚህ የመዝሙሩ ሁለተኛ ክፍል የመጀመሪያው ሦስት ቍጥሮች የሚያስተምሩት ስለ ጠቅላላ እውነት ነው፤ ከቍ1-3 ጋር ያነጻጽሩ)።

119፥89 *ቃልህ፤* በዚህ ቦታ የሚያመለክተው ሁሉን ነገር የፈጠረበትን፣ በሥርዐት የሚመራበትንና የሚያስተዳድርበትን ቃል ነው (33፥4፡6፤ 107፥20፤ 147፥15፡18 ይመ)። በሰማያት ጸንቶ ይኖራል፤ ጸንቶ የሚኖረው የሰማያትና የምድር ሥርዐት (ቍ90)፣ የእግዚአብሔርን ቃል (ማለትም "ሕግጋቱ" ቍ91)፣ እርግጠኛነት ያውጃል (19፥1-4)፤ ይህም ሥነ-ፍጥረቱን ሁሉ ደግፎ የያዘበትና የሚገዛበት ሥልጣኑ ሲሆን ጸንቶ የሚኖርና (ዘላለማዊና) ታማኝ ቃል ነው ("ታማኝነትህ" ቍ90)። እንግዲህ የእግዚአብሔር ሰው ልዩ መገለጥና ታማኝ በሆነው በእግዚአብሔር ቃል ላይ ያለውን ጽኑ እምነት (ሕጎቹንና ተስፋዎቹን) የሚያረጋግጥለት ታላቁ እውነታ ይህ ነው (የ93፥5፤ የ96፥10 ማብ ይመ። እንዲሁም በቍ29 ማብ ላይ "በማታለል መንገድ" የሚለውን ሐረግ ይመ)።

119፥90 *ታማኝነትህ፤* በተዘዋዋሪ የእግዚአብሔር ቃል የሚያመለክት ነው (ቍ89 እና ማብ ይመ)።

119፥92 *በመከራዬ ወቅት በጠፋሁ ነበር፤* ከሕግህ (ቍ67፡71፤ እንዲሁም የ65-72 ማብ ይመ)፣ የሕይወትን መንገድ መማር ባልቻልሁ ነበር (ቍ93 ይመ)።

119፥95 *ክፉዎች፤* የቍ21 ማብ ይመ ("እብሪተኞች") እኔን ለማጥፋት አድብተዋል፤ የቍ25 ማብ ይመ ("ወድቀዋል")።

119፥96 *ለፍጹምነት፤* ምናልባት በሙሉነት ደረጃ ፍጹምነትን የሚያመለክት አነጋገር ነው። *ትእዛዝህ ... ሰፊ ነው፤* ቃል በቃል ሲተረጐም ወሰን የሌላቸው ማለት ነው። እነዚህም ተዝቀው የማያልቁ፣ ለሕይወት ጠቃሚ የሆነ የዕውቀት ምክር የሚገኝባቸው ናቸው (ቍ97-100 ይመ)።

*119፥97-104፤* የእግዚአብሔርን ሕግ ማሰላሰል ከፍተኛ ጥበብን ያስገኛል።

119፥98 *ከጠላቶቼ፤* እነዚያ እብሪተኞች ማለት ነው (የቍ21 ማብ ይመ)፤ እነርሱም በዚህ ዓለም ጥበብ የሚታመኑ፣ የሚመኩ ናቸው።

119፥99 *ከአስተማሪዎቼ፤* ሰዎችን ያመለክታል።

119፥100 *ከሽማግሌዎች፤* በልምድ ብዙ ዕውቀት ያካበቱ አረጋውያን (የዘፀ3፥16 ማብ ይመ)።

119፥102 *አንተው ራስህ አስተምረኸኛልና፤* በሕጎችህ አማካይነት።

119፥103 *ቃልህ፤* እዚህ ላይ ሕጎችህ ቢባል የተገባ ሳይሆን አይቀርም (ቍ67፡133፡158፡172 እና የቍ11 ማብ ይመ)።

119፥104 *የሐሰትን መንገድ ሁሉ ጠላሁ፤* የቍ53 ማብ ይመ።

119፥105 *መብራት ...ብርሃን፤* ያለ እነዚህ መኖር፣ በጨለማ ውስጥ በዳበሳ ብቻ መንከላወስ ማለት ነው።

119፥106 *ምያለሁ ይህንኑ አጸናለሁ፤* ቃል ኪዳን መግባት ማለት ነው (ነህ10፥29 ይመ)።

*119፥107፤* ቍ25 እና ማብ ይመ።

109 ነፍሴ ዘወትር አደጋ ላይ ናት፤
ሕግህን ግን አልረሳሁም።
110 ክፉዎች ወጥመድ ዘረጉብኝ፤
እኔ ግን መመሪያህን አልተላለፍሁም።
111 ምስክርነትህ የዘላለም ውርሴ ናት፤
ልቤ በዚህ ሐሤት ያደርጋልና።
112 ትእዛዝህን ለዘላለም፣ እስከ ወዲያኛው
ለመፈጸም፣
ልቤን ወደዚያው አዘንበልሁ።

*ዐ ሳምኬት*

113 መንታ ልብ ያላቸውን ጠላሁ፤
ሕግህን ግን ወደድሁ።
114 አንተ መጠጊያዬና ጋሻዬ ነህ፤
ቃልህን በተስፋ እጠብቃለሁ።
115 የስምባኬን ትእዛዛት እጠብቅ ዘንድ፣
እናንት ክፉ አድራጊዎች፣ ከእኔ ራቁ።
116 እንደ ቃልህ ደግፈኝ፤ እኔም ሕያው
እሆናለሁ፤
ተስፋዬም መና ቀርቶ አልፈር።
117 ያለ ሥጋት እቀመጥ ዘንድ ደግፈህ
ያዘኝ፤
ሥርዐትህንም ዘወትር እመለከታለሁ።
118 መሰሪነታቸው በከንቱ ነውና፣
ከሥርዐትህ ውጭ የሚሄዱትን ሁሉ
ወዲያ አስወገድሃቸው።
119 የምድርን ክፉዎች ሁሉ እንደ ጥራጊ
አስወገድሃቸው፤
ስለዚህ ምስክርህን ወደድሁ።
120 ሥጋዬ አንተን በመፍራት
ይንቀጠቀጣል፤
ፍርድህንም እፈራለሁ።

*ሀ ዔ*

121 ፍትሕና ጽድቅ ያለበትን ሠርቻለሁ፤
ለሚጨቍኑኝ አሳልፈህ አትስጠኝ።
122 ለባሪያህ በጎነት ዋስትና ሁን፤
እብሪተኛ እንዲጨቍኑኝ አትፍቀድላቸው።
123 ዐይኖቼ ማዳንህን፣
የጽድቅ ቃልህን በመጠባበቅ ደከሙ።
124 ለባሪያህ እንደ ምሕረትህ መጠን
አድርግ፤
ሥርዐትህንም አስተምረኝ።
125 እኔ ባሪያህ ነኝ፤
ምስክርነትህን ዐውቅ ዘንድ ማስተዋልን
ስጠኝ።
126 *እግዚአብሔር* ሆይ፤
ሕግህ እየተጣሰ ነውና፣
ጊዜው አንተ የምትሠራበት ነው።
127 ስለዚህ ከወርቅ፣ ከንጹሕ ወርቅ ይልቅ፣
ትእዛዛትህን ወደድሁ።
128 መመሪያህ ሙሉ በሙሉ ልክ ነው
አልሁ፤
ስለዚህ የሐሰትን መንገድ ሁሉ ጠላሁ።

*ፀ ፌ*

129 ምስክርነትህ ሁሉ ድንቅ ነው፤
ስለዚህ ነፍሴ ትጠብቀዋለች።
130 የቃልህ ትርጓሜ ያበራል፤
አላዋቂዎችንም አስተዋዮች ያደርጋል።
131 ትእዛዝህን ናፍቄአለሁና፣
አፌን ከፈትሁ አለከለክሁም።
132 ስምህን ለሚወዱ ማድረግ ልማድህ እንደ
ሆነ ሁሉ፣
ወደ እኔ ተመልሰህ፣ ምሕረት
አድርግልኝ።
133 አካሄዴን እንደ ቃልህ ቀና አድርግልኝ፤
ኀጢአትም በላዬ እንዲሠለጥን
አትፍቀድ።

119፥109 ቍ61፤ መሳ12፥3
119፥110 ቍ10፤ መዝ25፥15፤64፥5፤ ኢሳ8፥14፤አሞ3፥5
119፥111 ቍ14፡ 162
119፥112 ቍ33፤ መዝ108፥1
119፥113 ቍ47፤ 1ነገ18፥21፤ያዕ1፥8፤ 4፥8
119፥114 ቍ43፤ ዘፍ15፥1፤መዝ18፥2
119፥115 መዝ6፥8
119፥116 ቍ41፤ መዝ18፥35፤41፥3፤ 55፥22፤ኢሳ46፥4፤ ሮሜ5፥5
119፥117 ቍ6፤ መዝ34፥4፤ኢሳ 41፥10፤46፥4
119፥118 ቍ10
119፥119 ቍ47፤ ኢሳ1፥22፡25፤ሕዝ 2፥18፡19
119፥120 ኢሱ 24፥14፤ኢዮ4፥14፤ ኢሳ64፥2፤ኤር10፥7 ፤ዕን3፥2
119፥121 2ሳሙ 8፥15፤ኢዮ27፥6
119፥122 ቍ21፡ 121፡134፤ኢዮ17፥3፤ መዝ106፥42
119፥123 ቍ81፡82 ፤ኢሳ38፥14
119፥124 ቍ12፡88 ፤መዝ25፥7
119፥125 ቍ79፤ መዝ116፥16
119፥126 ዘኍ15፥ 31
119፥127 ቍ47፤ ኢዮ3፥21፤መዝ19፥10
119፥128 ቍ104፡ 163፤መዝ19፥8፤31፥6 ፤ምሳ13፥5
119፥129 ቍ18፡ 22፡88 119፥130 ቍ105፤ መዝ19፥7
119፥131 ቍ20፤መዝ42፥1 119፥132 2ሳሙ24፥14፤መዝ 5፥11 ፤6፥4፤9፥13፤2ሳሙ24፥14 119፥133 ቍ9፡11፤ሮሜ6፥16

119፥109 *ነፍሴ ... አደጋ ላይ ናት፤* ማስፈራራትና ጥላቻ ቢኖርበትም እንኳ (በተለይ ቍ23፡46፡161 ይመ)፣ የእግዚአብሔርን ሕግ በይፋ ያከብራል።

119፥110 *ወጥመድ ዘረጉብኝ፤* ቍ85 እና ማብ ይመ።

119፥111-112 *ልቤን ... ልቤ፤* የ4፥7 ማብ ይመ።

119፥111 *ውርሴ፤* ሕይወቴ የሚያስፈልጋትን ነገር የምታገኘው ርስቷ ከሆነው ከእግዚአብሔር ከተሰጣት ሀብትና ንብረት ነው (ቍ57-64 ይመ)።

119፥113 *መንታ ልብ ያላቸውን ጠላሁ፤* ቍ115 ይመ፤ እንዲሁም የቍ53 ማብ ይመ። ሐሳቡ የተከፈለ ሰው በሚያደርገው ነገር ሁሉ ወላዋይ ነው፤ ቍርጠ አንድ ነገር መወሰን አይችልም (ያዕ1፥8)።

119፥114 *ቃልህን፤* የቍ25 ማብ ይመ።

119፥118 *አስወገድሃቸው፤* ወይም "ታርገፈግፋቸዋለህ" (ትነቀንቃቸዋለህ) ወይም "ታቃልላቸዋለህ" ማለት ነው። *መሠሪነታ ቸው፤* ምናልባት የማታለል (የቍ29 ማብ ይመ) መንገዳቸውን ወይም የሚያታልሉበትን መንገድ ሳያመለክት አይቀርም።

119፥119 *ጥራጊ፤* ከቀለጠ ብረት የሚወጣ ቈሻሻ ነገር ነው። በዕብራይስጡ ይህ ቃል በቍ118 ላይ "ስተው የሚወጡትን" የሚለው ቃል ከሚሰጠው ትርጕም ጋር ተመሳሳይ ነው። በአማርኛ ቅኔ አንዱ ቃል ሰምና ወርቅ ሆኖ ሁለት ዐይነት ትርጕም እንደሚሰጥ ማለት ነው። የሳቱ ሰዎች እንደ ጥራጊ ይቈጠራሉ፤ እንደ ቈሻሻና ጕድፍ ይወገዳሉ።

119፥120 *ሥጋዬ ... ይንቀጠቀጣል፤* ለእግዚአብሔር ካለው ጥልቅ አክብሮት የተነሣ ይንቀጠቀጣል።

*119፥121-128፤* ታማኝ ባሪያህ እንደ መሆኔ ከሚያሳድዱኝና ከሚጨቍኑኝ ሰዎች እንድትታደገኝ ወደ አንተ እጸልያለሁ፤ የእግዚአብሔርን ማዳን ወይም ትድግና በጽኑ የሚሻ ሌላ ጸሎት ነው (ቍ81-88 እና ማብ ይመ፤ እንዲሁም የቍ25 ማብ ይመ)።

119፥121 *ፍትሕና ጽድቅ ያለበትን፤* የእግዚአብሔርን ሕግ ማለት ነው።

*119፥122፤* በዚህ መዝሙር ውስጥ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ጨርሶ የማይገናኝ ቍጥር ነው (በቍ 90፡121፡132 ላይ እንዳለው ዐይነት ማለት ነው፤ እንዲሁም የቍ75 ማብ ይመ)። *እብሪተኞች፤* የቍ21 ማብ ይመ።

119፥123 *ዐይኖቼ ... ደከሙ፤* የ6፥7 ማብ ይመ።

119፥124 *ምሕረትህ፤* የ6፥4 ማብ ይመ።

119፥126 *የምትሠራበት፤* ባሪያውን ለመታደግ ወይም በሕግ አፍራሾች ላይ ለመፍረድ ወይም ደግሞ ሁለቱንም ለማድረግ ሊሆን ይችላል።

119፥127 *ከወርቅ ... ይልቅ፤* ቍ14፡57፡72፡111 ይመ።

119፥129 *ድንቅ፤* ቍ18 እና ማብ ይመ።

119፥130 *ትርጓሜ፤* ቃል በቃል ሲተረጐም "መከፈት" ማለት ሲሆን በዚህ ቦታ የያዘው ፍቺ (1) የቃልህ መገለጥ (2) የቃልህ ትርጓሜ (በ49፥4 ላይ "እገልጣለሁ" የሚለውን ይመ) (3) የቃልህን ወደ ልቤ ጠልቆ መግባት የሚሉ ናቸው። *ገሮችንም፤* 19፥7 እና ማብ ይመ።

119፥132 *ማድረግ ልማድህ እንደ ሆነ ሁሉ፤* ቃሉ በዕብራይስጥ "ሚሽፓት" ማለት ነው፤ "እደራረግህ" (ወይም "አሠራርህ") ማለት ሲሆን በተዘዋዋሪ የእግዚአብሔርን ሕግ ያመለክታል (የቍ122 ማብ ይመ፤ እንዲሁም የቍ7 ማብ ይመ)።

119፥134፡154 *ታደገኝ፤* ተቤዠኝ ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው።

134 ትእዛዝህን መጠበቅ እንድችል፣
ከሰዎች ጥቃት ታደገኝ።
135 በባሪያህ ላይ ፊትህን አብራ፤
ሥርዐትህንም አስተምረኝ።
136 ሕግህ ባለመከበሩ፤
እንባዬ እንደ ውሃ ይፈሳል።

ሧ ጻዴ

137 እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ጻድቅ ነህ፤
ፍርድህም ትክክል ነው።
138 ምስክርነትህን በጽድቅ አዘዝህ፤
እጅግ አስተማማኝም ነው።
139 ጠላቶቼ ቃልህን ዘንግተዋልና፣
ቅናት አሳረረኝ።
140 ቃልህ እጅግ የነጠረ ነው፤
ባሪያህም ወደደው።
141 እኔ ታናሽና የተናቅሁ ነኝ፤
ነገር ግን መመሪያህን አልዘነጋሁም።
142 ጽድቅህ ዘላለማዊ ጽድቅ ነው፤
ሕግህም እውነት ነው።
143 መከራና ሥቃይ ደርሶብኛል፤
ነገር ግን ትእዛዝህ ደስታዬ ነው።
144 ምስክርነትህ ለዘላለም የጽድቅ ምስክርነት ነው፤
በሕይወት እኖር ዘንድ ማስተዋልን ስጠኝ።

ፇ ቆፍ

145 እግዚአብሔር ሆይ፤ በፍጹም ልቤ እጮኻለሁና መልስልኝ፤
ሥርዐትህንም እጠብቃለሁ።
146 ወደ አንተ እጣራለሁና አድነኝ፤
ምስክርነትህንም እጠብቃለሁ።
147 ትረዳኝ ዘንድ ጎሕ ሳይቀድ ተነሥቼ እጮኻለሁ፤
ቃልህንም ተስፋ አደርጋለሁ።
148 ቃልህን አሰላስል ዘንድ፣
ዐይኔ ሌሊቱን ሙሉ ሳይከደን ያድራል።
149 እንደ ቸርነትህ መጠን ድምፄን ስማ፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ እንደ ሕግህ መልስህ ሕያው አድርገኝ።
150 ደባ የሚያውጠነጥኑ ወደ እኔ ቀርበዋል፤
ከሕግህ ግን የራቁ ናቸው።
151 እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ግን ቅርብ ነህ፤
ትእዛዛትህም ሁሉ እውነት ናቸው።
152 ለዘላለም እንደ መሠረትሃቸው፣
ከጥንት ምስክርነትህ ተረድቻለሁ።

ገ ሬስ

153 ሕግህን አልረሳሁምና፣
ሥቃዬን ተመልከት፤ ታደገኝም።
154 ተሟገትልኝ፤ አድነኝም፤
እንደ ቃልህም ሕያው አድርገኝ።
155 ሥርዐትህን ስለማይሹ፣
ድነት ከክፉዎች የራቀ ነው።
156 እግዚአብሔር ሆይ፤ ርኅራኄህ ታላቅ ነው፤
እንደ ሕግህ ሕያው አድርገኝ።
157 የሚያሳድዱኝ ጠላቶቼ ብዙዎች ናቸው፤
እኔ ግን ከምስክርህ ዘወር አላልሁም።
158 ቃልህን አይጠብቁምና፣
ከዳተኞችን አይቼ አርቃቸዋለሁ።
159 መመሪያህን እንዴት እንደምወድ ተመልከት፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ እንደ ምሕረትህ ሕያው አድርገኝ።
160 ቃልህ በሙሉ እውነት ነው፤
ጻድቅ የሆነው ሕግህም ዘላለማዊ ነው።

ሸ ሳን

161 ገዦች ያለ ምክንያት አሳደዱኝ፤
ልቤ ግን ከቃልህ የተነሣ እጅግ ፈራ።
162 ትልቅ ምርኮ እንዳገኘ ሰው፤

119፥134 ቍ56:88:122
119፥135 ቍ12፤ዘኍ6፥25፤መዝ4፥6፤67፥1፤80፥3
119፥136 ቍ158፤መዝ6፥6፤106፥25፤ኤሳ22፥4፤42፥24፤ኤር9፥1:18፤13፥17፤14፥17፤ሰቆ1፥16፤34፥8፤ሕዝ9፥4
119፥137 ዘፀ9፥27፤ዕዝ9፥15፤ነህ9፥13
119፥138 ቍ75:86፤መዝ19፥7
119፥139 መዝ69፥9፤ዮሐ2፥17
119፥140 ቍ47፤ኢሱ23፥14፤መዝ12፥6
119፥141 ቍ61:134፤መዝ22፥6
119፥142 ቍ151:160፤መዝ19፥7
119፥143 ቍ24:47
119፥144 ቍ34
119፥145 ቍ10:22:55
119፥146 ቍ94
119፥147 መዝ5፥3፤57፥8፤108፥2
119፥148 መዝ63፥6
119፥149 ቍ40:124፤መዝ27፥7
119፥150 መዝ37፥7
119፥151 ቍ142፤መዝ34፥18፤ፊል4፥5
119፥152 ቍ7:73:89፤መዝ111፥8፤ሉቃ21፥33
119፥153 መዝ3፥7፤13፥3፤44፥17
119፥154 ቍ25:41፤1ሳሙ24፥15፤መዝ35፥1፤ኤር50፥34፤ሚክ7፥9
119፥155 ቍ94:118
119፥156 ቍ25:149፤ነህ9፥27፤ያዕ5፥11
119፥157 መዝ7፥1፤44፥18 119፥158 ቍ104:136፤ዘዐ32፥19
119፥159 ቍ25፤መዝ41፥2 119፥160 ቍ89፤መዝ111፥8
119፥161 ቍ23:120:122:157፤1ሳሙ24፥14-15
119፥162 ቍ111፤1ሳሙ30፥16፤ኢሳ 9፥3፤53፥12

119፥134 *ጥቃት፤* የቍ ጥር 25 ማብ ይመ ("ወድቄአለሁ")።

119፥135 *ፊትህን አብራ፤* የ13፥1 ማብ ይመ ("ፊትህን ለውር")።

*119፥136፤* ቍ53 እና ማብ ይመ።

*119፥137-144፤* እግዚአብሔርና ሕጉ ጻድቅ ናቸው።

119፥137 *ጻድቅ፤* የ4፥1 ማብ ይመ።

119፥138 *አስተማማኝም፤* ቍ142 ይመ። በቍ29 ማብ ይመ ("ከሽንገላ መንገድ")።

119፥139 *ቅናት፤* የቍ53 ማብ ይመ።

119፥140 *ቃልህ፤* ዕብራይስጡ ኢምራህ ይለዋል፤ ምናልባትም እዚህ ላይ ቃል ተብሎ ቢተረጐም የተሻለ ሳይሆን አይቀርም (የቍ11 ማብ ይመ)። *የነጠረ ነው፤* ቃል በቃል ሲተረጐም "የተፈተነ" ማለት ሲሆን፣ የእግዚአብሔር ቃል ጥቅም የሌለውና አንድም ነገር አለመያዙን ወይም እጅግ ከፍ ያለ ዋጋና ጥቅም ያለው መሆኑን ያመለክታል።

119፥141 *ታናሽና የተናቅሁ፤* ከቍ143 ጋር ያነጻጽሩ። እንዲሁም የቍ25 ማብ ይመ።

119፥145-152 *ጌታ ሆይ፤ አድነኝ፤ እኔም ሕግህን እጠብቃለሁ፤* መዝሙሩ ሊፈጸም ሲቃረብ የእግዚአብሔርን ማዳን ወይም ትድግና ለማግኘት የሚደረገው ጸሎት ይበልጥ እየበረታና እያየለ ሲሄድ ይታያል (በቍ25 ማብ ላይ "ወድቄአለሁ" የሚለውን ይመ)።

119፥148 *ሌሊቱን ሙሉ፤* የመሳ7፥19 ማብ ይመ፤ እንዲሁም ሰቆ2፥19 ይመ።

119፥149 *ቸርነትህ፤* የ6፥4 ማብ ይመ። *ሕግህ፤* ወይም "ፍርድህ" ማለት ነው (ይህም "ፍቅርህ" ለሚለው ቃል እንደ ማሟያ የሚያገለግል ነው)፤ በዕብራይስጡ ሚሽፓት ይባላል (የቍ75 ማብ ይመ)።

119፥150 *ከሕግህ ... የራቁ፤* ቍ21:53:85:118:126:139:155:158 ይመ።

119፥151 *እውነት ናቸው፤* የቍ29 ማብ ይመ ("ከማታለል መንገድ")።

119፥152 *ለዘላለም ... ከጥንት፤* የቍ52 ማብ ይመ።

*119፥153-160፤* የቍ145-152 ማብ ይመ።

119፥155 *ከክፉዎች፤* የቍ21 ማብ ይመ ("እብሪተኞች")።

119፥156 *እንደ ሕግህ፤* ቍ149 እና ማብ ይመ።

119፥158 *ቃልህን፤* ዕብራይስጡ ኢምራ ይለዋል (የቍ11 ማብ ይመ)።

119፥160 *በሙሉ፤* ቃል በቃል ሲተረጐም "ድምሩ" ማለት ነው (በመዝ137፥17 እንደ ተጻፈው ማለት ነው)። *እውነት፤* የቍ29 ማብ ይመ ("ከማታለል መንገድ")። *ዘላለማዊ፤* የቍ52 ማብ ይመ።

*119፥161-168፤* የቍ145-152 ማብ ይመ።

119፥161 *ገዦች፤* የቍ23 ማብ ይመ። *ልቤ፤* የ4፥7 ማብ ይመ።

119፥162 *ትልቅ ምርኮ፤* ቍ14:72:111 ይመ።